ድል አድራጊ ሁን!

እርግጠኛና ክቡር ከሆነው የክርስቶስ ምጽአት የተነሣ፥ ክርስቲያን አሸናፊ ነው!

ጸሐፊ፡- ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

ትርጉም፡- ግርማዊ

እርማት፡- ዓቢይ ደምሴ።

Copyright © 1995 by S.I.M. Addis Ababa, Ethiopia. Originaly published in English under the title of BE VICTORIOUS. Copyright © 1985 by SP Publications, Inc., Wheatou, Illinois, USA. All rights reserved.

ማውጫ

መግቢያ ....
1. እጅግ የተለየ መጽሐፍ (ራእይ 1)..................1
2. ክርስቶስና አብያተ ክርስቲያናት - ክፍል 1 (ራእይ 2) ...17
3. ክርስቶስና አብያተ ክርስቲያናት - ክፍል 2 (ራእይ 3) ...31
4. ኑ - እርሱን እናወድሰው ! (ራእይ 4-5) 46
5. ማኅተሞቹና የታተሙ ሰዎች (ራእይ 6-7) 61
6. መለከቶቹን ንፉ! (ራእይ 8-9) 75
7. የምስክርነት ጊዜ (ራእይ 10-11)...................89
8. ሦስቱ አስከፊ ባሕርያት (ራእይ 12-13) 103
9. የድል ድምፆች (ራእይ 14-16).....................118
10. ጥፋትና ውድመት (ራእይ 17-18) 131
11. ንጉሡና መንግሥቱ (ራእይ 19-20)..............145
12. ሁሉም ነገር ሲታደስ! (ራእይ 21-22)............159

መግቢያ

የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ መጽሐፍ ለዘመናት የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችን ሲፈታተንና አትኩሮታቸውንም ሲስብ ኖሯል። በእራሴ ቤተ መጽሐፍ ውስጥ በዚህ መጽሐፍ ላይ የተጻፉ በደርዘን የሚቆጠሩ ማብራሪያዎች የሚገኙ ሲሆኑ፥ ማናቸውም ሁለት ጸሐፍት በሁሉም ነጥቦች ላይ ሙሉ ለሙሉ አይስማሙም።

ይሁንና ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ አይደለም። ዋናውና አስፈላጊው ቁም ነገር የራእይን መጽሐፍ ዓቢይ መልእክት አለመዘንጋታችን ነው - ኢየሱስ ክርስቶስ በጠላቶቹ ሁሉ ላይ የሚቀዳጀውን የከበረ ድል! ይሁን እንጂ፥ የሚያሳዝነው ጉዳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪው ይህን የላቀና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውን እውነት በመረዳት ምትክ፥ እጅግ በረቀቀ የትንቢት ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሰጥሞ መዋከቡ ነው። ከሁሉም በላይ የሆነውና የላቀው እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ አሸናፊዎች ነን የሚለው ብቻ ነው።

ዮሐንስ ይህንን መጽሐፍ የጻፈው በታላቅ መከራ ውስጥ የነበሩትን የአንደኛ ክፍለ-ዘመን ክርስቲያኖች ለማበረታታት ነው። በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ዘመን፥ የራእይ መጽሐፍ ለክርስቲያኖች የልብ መጽናናትንና ተስፋን አስገኝቷል። ለምን? ምክንያቱም የመጽሐፉ ተምሳሌቶች በጊዜ የማይገደቡና በየትኛውም የታሪክ ወቅት ለሚኖሩ አማኞች ለመረዳት የማይከብዱ በመሆናቸው ነው፤ ይህም የሆነው የመጽሐፉ የተስፋ ቃሎች ዘላለማዊና በቅዱሳን ሁሉ ሊታመኑ ስለሚችሉ ነው።

ዮሐንስ ስለ ግልጽ ክስተቶችና ስለክስተቶቹም ትክክለኛ ቅደም-ተከተል እንደተነበየ አምናለሁ። ይሁንና ይህ የግል የትንቢት ትርጓሜዬ አንባቢዬን ከመጽሐፉ ዓቢይ መልእክት ላይ ከመድረስ እንዲያዘገየው አልሻም፤ ዓቢዩም መልእክት ኢየሱስ ክርስቶስ አሸናፊ በመሆኑ፥ አማኞች ሁሉ የዚህ የታላቅ ድል ተካፋዮች ይሆናሉ የሚል ነው።

የራእይን ዝርዝር ጥናት የሚፈልግ ሰው የሚከተሉትን ማብራሪያዎች እንዲያነብ አበረታታለሁ:- ሌህማን ስትራውስ (ልዋዞ ብራዘርስ)፥ ጆን ኤፍ ዋልቨርድ (ሙዲ ፕሬስ)፥ ደብልዩ ኤ ክሪስዌል (ዘንደርቫን)፥ ዊሊያም አር. ኒዌል (ሙዲ ፕሬስ) እና ሌዎን ሞሪስ (ደብልዩ ኤም ኤርድማንስ)።

ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ

«ድል ለነሣው፥

ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ» (ራእይ 3፡21)።

የራእይ መጽሐፍ የዙፋን መጽሐፍ ነው። መልእክቱም በጉ ድል እንደነሣና በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ አሸናፊዎች እንደሆኑ የሚያስረዳ ነው። ቀኑ የቱንም ያህል ቢጨልም፥ ተቃውሞውም የቱንም ያህል ቢበረታ፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ድል-ነሺዎች ይሆናሉ!

በዚህ የራእይ ትንታኔያቸው፥ ዋረን ዌርዝቢ የትንቢትን ተግባራዊነት በግልጽ ያብራራሉ። ሐዋርያው ዮሐንስ ይህንን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የጻፈው፥ በዘመኑ በመከራ ማዕበል የሚንገላቱትን ቅዱሳን ለማበረታታት ብቻ አልነበረም፤ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ የሚያልፉ ቅዱሳንም ለዓይነ ሕሊናው እየታዩት ነበር!

በክርስቶስ ምጽዓት ብርሃን ለመኖርና

ድል ለመንሣት

ጊዜው አሁን ነው።

ዶክተር ዋረን ደብልዩ ዌርዝቢ በደራሲነት፥ በመጋቢነትና በሬድዮ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህርነት እጅግ የታወቁ አገልጋይ ናቸው። ለብዙ ዓመታት በሺካጎ የሙዲ መታሰቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ በመሆን ያገለገሉ ሲሆን፥ በቅርቡ ደግሞ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ ለተባለው አገልግሎት ዋና ዳይሬክተርና የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር በመሆን ሠርተዋል። በ«ቪክተር ቡክስ» አሳታሚ ድርጅት የሚሰራጩትን የአዲስ ኪዳን የማብራሪያ መጻሕፍት ጨምሮ ከ100 መጻሕፍት በላይ ለንባብ አብቅተዋል።

_ 1 _

እጅግ የተለየ መጽሐፍ

ራእይ 1

አሜሪካዊ ተረበኛ ጆሽ ቢልንግስ፥ «የተሳሳተ ትንቢት ብትናገር፥ ማንም አይረሳውም፤ ትክክለኛ ትንቢት ብትናገር ደግሞ፥ ማንም ሰው አያስታውሰውም - ስለዚህ፥ ከቶውንም ትንቢት አትናገር» ብሎ ነበር።

በዘመናት ሁሉ ትንቢቶች ተፈራርቀዋል፤ ይሁን እንጂ በመጀመሪያው ክፍለ-ዘመን ማብቂያ አካባቢ በሐዋርያው ዮሐንስ የተጻፈው የትንቢት መጽሐፍ ግን ዛሬም ቢሆን አብሮን አለ። ይህን መጽሐፍ በልጅነቴ እንዳነበብሁትና ስለምንነቱም በማሰብ እንደተገረምሁ ትዝ ይለኛል። ከዚያም በኋላ ለበርካታ ዓመታት ተመስጬ ባጠናውም ቅሉ፥ ዳሩ ግን ዛሬም ቢሆን የዚህ መጽሐፍ መልእክትና ምሥጢሮች ትኩረቴን ይስቡታል።

በራእይ 1፥ ዮሐንስ መጽሐፉን ያስተዋውቅና፥ ትንቢቱን ያለማወላወል ለመቀበልና ለመረዳት የሚቻልበትን አስፈላጊ መረጃ ይሰጣል።

ርእሱ (ራእይ 1፡1)

«ራእይ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «መግለጥ» ማለት ነው። ዛሬ ግን ይህ ቃል (በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ) በአሳዛኝ መልኩ ሥርዓት አልበኝነትንና እጅግ የከፋን ገጠመኝ ለመግለጽ ከሚያገለግለው «ውድመት» ከተሰኘው ቃል ጋር የሚዛመድ ሆኗል። የአንቀጹ ቀጥተኛ ትርጉም «ሽፋኑን ማንሣት፥ መግለጥ፥ ማሳየት» የሚል ነው። በዚህ መጽሐፍ፥ መንፈስ ቅዱስ መጋረጃውን በማንሣት፥ በሰማይ የከበረውን ክርስቶስን እንድናየውና፥ በዓለምም ውስጥ የሉዓላዊ ዓላማዎቹን ፍጻሜ የማሳየት ዕድል ይከፍትልናል።

በሌላ አባባል፥ ራእይ እግዚአብሔር ዕቅዶቹንና ዓላማዎቹን ለቤተ ክርስቲያኑ የሚገልጥበት መጽሐፍ ነው። ዳንኤል ትንቢቱን ጽፎ በጨረሰ ጊዜ፥ «ቃሉን ዝጋ፥ መጽሐፉንም አትም» የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶት ነበር (ዳን. 12፡4)፤ ለዮሐንስ የተሰጠው ትእዛዝ ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ነበር -

«የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው» (ራእይ 22፥10)። ለምን? ከኅልነታ፥ ከትንሣኤና ከመንፈስ ቅዱስ መምጣት ጀምሮ፥ እግዚአብሔር «የመጨረሻውን ዘመን» (ዕብ. 1፥1-2) ለማምጣት በዓለም ውስጥ ስውር ዓላማዎቹን በመፈጸም ላይ በመገኘቱ ነው። «ዘመኑ ቀርቦአልና» (ራእይ 1፥3፤ 22፥10)።

የዮሐንስ ትንቢት ትኩረት በመጀመሪያ ደረጃ በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ እንጂ፥ ወደፊት በሚፈጸሙ ጉዳዮች ላይ መገለጥ አይደለም። አካሉ ሳይኖር ትንቢቱ ሊፈጸም ስለማይችል፥ አካሉን ከትንቢቱ መለየት የለብንም። ዶክተር ሜሪል ቴኒ፥ «እርሱ ለተግባሩ ማሚያ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የተግባሩ ዋና ባለቤት ነው» በማለት ጽፎዋል። ከራእይ 1-3፥ ክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያገለግል ከፍ ያለ ካህን - ንጉሥ ሆኖ ተገልጿል። ከራእይ 4-5፥ ደግሞ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ እንደሚገዛ ክቡር የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ታይቷል። እንደዚሁም በራእይ 6-18፥ ክርስቶስ የምድር ሁሉ ፈራጅ ሆኖ የተገለጸ ሲሆን፥ በራእይ 19፥ እንደ ድል አድራጊ ንጉሠ-ነገሥት ወደ ምድር ይመለሳል። መጽሐፉ የሚደመደመው፥ ወደ ከበረችው ሰማያዊት ከተማ ሙሽራውን ማለትም ቤተ ክርስቲያንን የሚወስድ ሰማያዊ ሙሽራን በማቅረብ ነው።

ይህን መጽሐፍ በምታጠናበት ጊዜ፥ ምንም ይሁን ምን፥ አዳኝህን በበለጠ ለማወቅ ትጋ።

ጸሐፊው (ራእይ 1፥1-2፤ 4፥9፤ 22፥8)

መንፈስ ቅዱስ፥ በሐዋርያው ዮሐንስ ሦስት ዓይነት በመንፈስ ምሪት የተጻፉ ሥነ-ጽሑፎችን ለማስተላለፍ ተጠቅሞበታል - የዮሐንስ ወንጌልን፥ ሦስቱን የዮሐንስ መልእክቶችንና የዮሐንስ ራእይን። ዓላማዎቹን እንደሚከተለው በአስተዋጽኦ መልክ ማቅረብ ይቻላል፡-

የዮሐንስ ወንጌል	መልእክቶች	ራእይ
እመኑ 20፥31	እርግጠኛ ሁኑ 1ኛ ዮሐ. 5፥13	ተዘጋጁ 22፥20
ሕይወት ተገኘ	ሕይወት ተገለጸ	ሕይወት ተሰጠ
ደኅንነት	ቅድስና	ሉዓላዊነት
ነቢዩ	ካህኑ	ንጉሡ

የዮሐንስ ራእይ በ95 ዓ.ም.፥ በሮማዊው ንጉሠ ነገሥት ቲቶ ፍላቪዮስ ዶሚትያን የአገዛዝ ዘመን በሐዋርያው ዮሐንስ ተጻፈ። ንጉሡ፥

እራሱን እንደ «ጌታ አምላክ» እንዲያመልኩት ጠይቆ ነበርና፥ የአይሁዶችና የክርስቲያኖች ለድንጋጌው አለመታዘዝ የከፋ ስደት አስከተለ። በአፈ-ታሪክ ዘገባ መሠረት፥ ዮሐንስን የሮም እስረኞች ወደሚታሰሩባት በትንሹ እስያ ዳርቻ ወደምትገኘው የፍጥሞ ደሴት የላከው ዶሚትያን ነው። ይህ የዮሐንስ የምርኮኝነት መኖሪያ በመሆኑ፥ «ባሕር» የሚለው ቃል በመጽሐፉ ውስጥ ሃያ ስድስት ጊዜ ተጠቅሶ መገኘቱ አያስደንቀንም።

ኢየሱስ በምድር ላይ በሚያገለግልበት ወቅት፥ ዮሐንስና ወንድሙ ያዕቆብ፥ ኢየሱስን ከዙፋኑ አጠገብ የተለየ ሥፍራ በመስጠት ያከብራቸው ዘንድ ጠይቀውት ነበር። ጌታም የመከራው ተካፋዮች በመሆን፥ ዙፋኖቻቸውን እንዲያገኙ ነግሯቸው ነበር። በመሆኑም፥ ያዕቆብ የመጀመሪያው ሰማዕት ሐዋርያ ሲሆን (የሐዋ. 12፡1-2)፥ ዮሐንስ ደግሞ ከሁሉም ሐዋርያት በኋላ ነበር የሞተው፤ ይሁንና ከመሞቱ በፊት በፍጥሞ ደሴት ብዙ ተሠቃይቷል (ማቴ. 20፡20-23 ተመልከት)።

ጌታ የዚህን መጽሐፍ ይዘት ለባሪያው ያስተላለፈው እንዴት ነበር? በራእይ 1፡1-2 ዘገባ መሠረት፥ አብ ራእዩን ለወልድ ሲሰጥ፥ ወልድ ደግሞ «መልአኩን» መካከለኛ በማድረግ፥ ለሐዋርያው አስተላለፈለት። አንዳንድ ጊዜ መረጃውን ለዮሐንስ ያስተላለፈው ራሱ ክርስቶስ ሲሆን (1፡ ከቁጥር 10 ጀምሮ)፥ አንዳንድ ጊዜም ከሽማግሌዎቹ አንደኛው (7፡13)፥ ለብዙ ጊዜ ግን መልአኩ ነበር (17፡1፤ 19፡9-10)። አልፎ አልፎም «ከሰማይ የሚመጣው ድምፅ» ዮሐንስ ምን እንደሚናገር ወይም እንደሚያደርግ ይነግረው ነበር (10፡4)። የመገናኛ መንገዱ የተለያየ ቢሆንም፥ መጽሐፉ ግን ከእግዚአብሔር ወደ ዮሐንስ የተላከና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈ መጽሐፍ ነበር።

«አመለከተ» (1፡1) የሚለውን ቃል መረዳት አስፈላጊ ሲሆን፥ «በምልክት ማሳየት» የሚል ትርጉም አለው። በራእይ ውስጥ ስያሜው «ምልክት» (15፡1)፥ «ድንቅ» (12፡1-3)፥ እና «ተአምር» (19፡20) ተደርጎ ተተርጉሟል። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስን ተአምራት ለማመልከት ያገለገለው ይኸው ቃል ነበር፤ ይህም የሆነው ተአምራቱ እንዲያው ኃይልን ለመግለጽ ሳይሆን፥ የጠለቀ መንፈሳዊ መልእክት የነበራቸውን ክስተቶች ያቀፉ በመሆናቸው ነው።

የራእይን መጽሐፍ ስታጠና፥ በአብዛኛው ከብሉይ ኪዳን ጋር የሚዛመዱ በርካታ ተምሳሌቶች እንደሚያጋጥሙህ ተገንዘብ።

ዮሐንስ ተምሳሌታዊ አቀራረብን የተጠቀመው ለምንድን ነው? በአንድ በኩል፥ የዚህ ዓይነቱን «መንፈሳዊ ምሥጢር (ኮድ)» የሚረዱት ክርስቶስን በቅርብ በግል የሚያውቁት ናቸው። ማናቸውም የሮም ባለሥልጣኖች ራእይን ክርስቲያኖችን የመቃወሚያ መረጃ አድርገው ሊጠቀሙበት ሞክረው ቢሆን ኖሮ፥ መጽሐፉ ለመረዳት ግራ የሚያጋባና እንቆቅልሽ በሆነባቸውም ነበር። ይሁንና ከዚህ የሚበልጠውም ምክንያት የተምሳሌቱ መልእክት በጊዜ ርዝመት እንኳን አለመዳከሙ ነው። ዮሐንስ በእግዚአብሔር ራእይ ውስጥ የሚገኙትን ታላላቅ «ምስሎች»፥ ለዘመናት ስደትና መከራ የተፈራረቀባቸውን ቅዱሳን ካበረታታው አስደናቂ ትዕይንት ጋር በማመሳሰል ለማቅረብ ችሎ ነበር። ይህም ሆኖ፥ የዮሐንስ የተምሳሌት አጠቃቀም እንደሚያመለክተው፥ የተገለጹት ነገሮች እውነተኞች እንዳልሆኑ አድርገህ መደምደም የለብህም። የተጠቀሱት ነገሮች እውነተኞች ናቸው።

ዮሐንስ ለምን ተምሳሌትን እንደተጠቀመ የሚያስረዳ ሦስተኛም ምክንያት አለ - ተምሳሌቶች መልእክቱን ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እሴቶችን የማስገንዘብና ስሜቶችን የመቀስቀስ ብቃታቸው ከፍ ያለ ነው። ዮሐንስ «አንድ አምባገነን መሪ ዓለምን ይገዛል» ብሎ ሊጽፍ ሲችል፥ ዳሩ ግን «አውሬ» በማለት ገልጾታል። እንዲያው የ«አምባገነኑን» ስም ከመጥቀስ ይልቅ፥ ተምሳሌቱ እጅግ የበለጠ መልእክት ያስተላልፋል። የዓለምን አሠራር በመግለጽ ምትክ፥ ዮሐንስ «ታላቋን ባቢሎን» በማስተዋወቅ፥ «ጋለሞታይቱን» ከ«ሙሽራይቱ» ጋር አነጻጽሯል። «ባቢሎን» የሚለው ስም ራሱ፥ ብሉይ ኪዳንን ለሚያውቁ አንባቢዎች የጠለቀ መንፈሳዊ እውነት ያስተላልፋል።

ይሁንና፥ የዮሐንስን ተምሳሌት በመረዳቱ በኩል አስተሳሰባችን ከመሥመር እንዳይወጣ መጠንቀቅ አለብን። የመጽሐፍ ቅዱስ ተምሳሌቶች ከጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው። አንዳንድ ተምሳሌቶች ተገልጸዋል (1፡20፤ 4፡5፤ 5፡8)፤ ሌሎቹ ደግሞ ከብሉይ ኪዳን ግንዛቤ በመነሣት የምንረዳቸው ናቸው (2፡7፥ 17፤ 4፡7)፤ የተቀሩት ደግሞ (ለምሳሌ በ2፡17 «ነጭ ድንጋይ») ጥራሽም ያልተገለጹ ናቸው። በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ወደ

300 የሚጠጉ የብሉይ ኪዳን ማጣቀሻዎች ይገኛሉ። በመሆኑም፥ የዚህ መጽሐፍ አተረጓጎማችን እግዚአብሔር ቀደም ብሎ በገለጸው እውነት ላይ መልሕቁን መጣል አለበት ማለት ነው፤ ይህም ይህንን አስፈላጊ የትንቢት መጽሐፍ አዛብተን እንዳንተረጉመው ይረዳናል።

ተደራሲያኑ (ራእይ 1፡3-4)

መጽሐፉ በመጀመሪያ የተላከው በትንሹ እስያ ለሚገኙ ሰባቱ ነባር አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆን፥ ዮሐንስ ማንኛውም አማኝ ሊያነብና ሊጠቀምበት እንደሚችል በግልጽ አስፍሯል (1፡3)። እንዲያውም፥ እግዚአብሔር መጽሐፉን ለሚያነብና እንደ መልእክቱም ለሚታዘዘው ሰው ልዩ በረከት እንደሚሰጥ የተስፋ ቃል ሰጥቷል። («ማንበብ» ማለት «ድምፅን ከፍ አድርጎ ለሌሎች ማሰማት» ማለት ነው። ራእይ በመጀመሪያዎቹ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ስብሰባዎች ላይ ይነበብ ነበር።) ሐዋርያው ጳውሎስ ለሰባት አብያተ ክርስቲያናት - ሮም፥ ቆሮንቶስ፥ ገላትያ፥ ኤፌሶን፥ ፊልጵስዩስ፥ ቈላስይስና ተሰሎንቄ - ደብዳቤዎችን ልኮ ነበር፤ አሁን ደግሞ ዮሐንስ አንዱን መጽሐፍ ለሰባት አብያተ ክርስቲያናት ልኳል። በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ፥ ከክርስቶስ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የተላለፈ መልእክት ይገኛል።

ዮሐንስ ይህንን የትንቢት መጽሐፍ ለማኅበረ ምዕመናን የላከው፥ ወደፊት ስለሚፈጸሙ ነገሮች ለማወቅ ያላቸውን ጉጉት ለማርካት አልነበረም። ይልቁኑ የእግዚአብሔር ሰዎች በከፉ ስደት ውስጥ የሚያልፉበት ወቅት ነበርና፥ ማበረታቻ ያስፈልጋቸው ነበር። በመሆኑም ስለዚህ መጽሐፍ ሲሰሙ፥ መልእክቱ ብርታትንና ተስፋን ይሰጣቸው ነበር። ከዚህም በላይ ደግሞ፥ የግል ሕይወታቸውን (እና የእያንዳንዱን አጥቢያ ጉባኤ) እንዲመረምሩና መስተካከል የሚገባቸውን ደካማ ጎኖች እንዲያውቁ ይረዳቸው ነበር። መስማትም ብቻ ሳይሆን፥ በቃሉም መጠቀም ነበረባቸው - ይህም ማለት መጽሐፉን እንደከበረ መዝገብ በመጠበቅ ብቻ ሳይሆን፥ ቃሉ የሚለውን መለማመድ ነበረባቸው። በረከቱ የሚመጣው በመስማት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ይበልጥ በማድረግ ነው (ያዕ. 1፡22-25)።

በራእይ ውስጥ ሰባት «ብፅዕናዎች» መኖራቸውን መመልከቱ ተገቢ ነው - 1፡3፤ 14፡13፤ 16፡15፤ 19፡9፤ 20፡6፤ 22፡7፥14። ቁጥር ሰባት ፍጹምነትንና ሙላትን ስለሚያመለክት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ

ተቀዳሚ ሥፍራ አለው። በራእይ፥ እግዚአብሔር ታላቅ ሥራውን እንዴት እንደሚፈጽምና ዘላለማዊ መንግሥቱን እንዴት እንደሚመሠርት ይነግረናል። በራእይ፥ ሰባት ማኅተሞች (5፡1)፥ ሰባት መለከቶች (8፡6)፥ ሰባት ጽዋዎች (16፡1)፥ ሰባት ከዋክብት (1፡16)፥ እና ሰባት መቅረዞች (1፡12፥ 20) ያጋጥሙናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተጨማሪ የሚያጋጥሙንን ሌሎች «ሰባቶች»፥ መጽሐፉን በምናጠናበት ጊዜ የምንወያይባቸው ይሆናሉ።

በራእይ 2-3፥ ውስጥ ለእያንዳንዳቸው ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ መልእክቶች ተሰጥተዋል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በእነዚህ ሰባት አብያተ ክርስቲያናት ተምሳሌትነት፥ ከሐዋርያት ዘመን (ኤፌሶን) እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የክህደት ወቅት (ሎዶቅያ) ድረስ ያለውን «የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መነሻና መድረሻን» ለመመልከት ስለመቻላቸው ይናገራሉ። እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎችን ሊገልጹ ቢችሉም፥ ዳሩ ግን የተወሰኑ ጉባኤዎች የመመረጣቸው ዋንኛው ምክንያት ምናልባትም ለዚህ ዓላማ ብቻ ሲባል ላይሆን ይችላል። ይልቁንም፥ እነዚህ ደብዳቤዎች ከፍ ከፍ የተደረገው የቤተ ክርስቲያን ራስ በእያንዳንዱ ጉባኤ የሚካሄደውን ነገር እንደሚያውቅና ከእርሱና ከቃሉ ጋር ያለን ግንኙነት የአጥቢያ ጉባኤን አገልግሎትና ሕይወት እንደሚወስን ያስታውሱናል።

እዚህ ላይ ከልብ ልታጤነው የሚገባው ነጥብ፥ በትንሹ እስያ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት በስደት ውስጥ እንደነበሩና ከጌታና እርስ በርሳቸውም ትክክለኛ ግንኙነት ማድረጋቸው አስፈላጊ መሆኑን ነው። አብያተ ክርስቲያናቱ እያንዳንዳቸው በጨለማው ዓለም ውስጥ ብርሃን የሚረጩ (ፊልጵ. 2፡15፤ ማቴ. 5፡14-16)፥ ሰባት የተለያዩ መቅረዞች ሆነው ተገልጸዋል። ቀኑ ይበልጥ እየጨለመ ሲሄድ፥ ብርሃኑም ይበልጥ እየደመቀ መሄድ አለበት፤ የሚያሳዝነው ግን ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ቢያንስ የአምስቱ ብርሃናቸው ደብዛዛ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ደግመኛ ደምቆ እንዲያበራ ለማስቻል የነበሩት ሁኔታዎች መስተካከል ነበረባቸው። ራእይ 2-3ን ስታነብ፥ ጌታ ሁልጊዜም የራሱን ማንነት እንደሚያስገነዝባቸውና «ድል-ነሺዎች» ይሆኑ ዘንድ እንደሚያበረታታቸው ልብ በል።

ከሁሉ ልቆ ሊታይ የሚገባው፥ የኢየሱስ ክርስቶስ የምጽአቱ ተስፋ፥ ለሁሉም ክርስቲያኖች በሁሉም ጊዜ ለመታዘዝና ለቅድስና አነሣሽ ምክንያት መሆኑ ነው (1፡3፥7፤ 2፡5፥25፤ 3፡3፥ 11፤ 22፡7፤ 12፥20፤ እንዲሁም 1ኛ ዮሐ. 1፡1-3 ተመልከት)። ማንኛውም አማኝ ወደፊት የሚፈጸሙትን ነገሮች ለማወቅ ባለው ጉጉት ምክንያት ብቻ ትንቢትን ማጥናት የለበትም። ዳንኤልና ዮሐንስ ወደፊት የሚፈጸመውን የእግዚአብሔርን መገለጥ በተቀበሉ ጊዜ፥ ሁለቱም እንደሞተ ሰው ሆነው ወደቁ (ራእይ 1፡17፤ ዳን. 10፡7-10)፤ ባዩት ነገር እጅግ ተመስጠው ነበር። እኛም ይህን መጽሐፍ ማጥናት ያለብን እንደ ቀለም ተማሪዎች ሳይሆን እንደ አድናቂዎችና አምላኪዎች መሆን አለበት።

መታሰቢያነቱ (ራእይ 1፡4-6)

አንድ ወዳጄ፥ «መጻሕፍት መጻፍ ካላቆምህ፤ መጽሐፍህን በመታሰቢያነት የምትሰጠውን ሰው ታጣለህ» ብሎኝ ነበር። ይሁንና ይህንን አድናቆቱን አመስግኜ ብቀበልም፥ ዳሩ ግን ከአሳቡ ጋር አልተስማማሁም። ዮሐንስ መጽሐፉን ለማን በመታሰቢያነት እንደሚሰጥ የማወቅ ችግር አልነበረበትም። ሆኖም የመታሰቢያ ዓረፍተ ነገሮቹን ከመጻሕፍቱ መግቢያ ላይ ከመጻፉ በፊት፥ አንባቢዎቹን አበክሮ ያሳሰባቸው፥ ያዳናቸውና የከፋውን የመከራ ሕይወት በሚገፉበት ጊዜ የሚጠብቃቸው ራሱን በሦስትነት የገለጸው አንዱ አምላክ (ሥላሴ) መሆኑን ነው።

እግዚአብሔር አብ እንደ ዘላለማዊ አካል ተገልጿል (1፡8፤ 4፡8 ተመልከት)። መላው ዓለም በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርሰውን ስደት ጨምሮ፥ ታሪክ ሁሉ የዘላለማዊ ዕቅዱ አካል ነው። ቀጥሎም አንድ እንጂ ሰባት መናፍስት ስለሌሉ፥ መንፈስ ቅዱስ በምልዓቱ ተገልጿል። ምናልባት ይህ ክፍል የሚያመለክተው፥ ኢሳይያስ 11፡2ን ይሆናል።

በመጨረሻም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በሦስቱ ሥልጣናት፥ ማለትም በነቢይነት (ታማኝ ምስክር)፥ በካህንነት (ከሙታን በመነሣት በኩር) እና በንጉሥነት (የምድር ነገሥታት ገዥ) ተገልጿል። ከሙታንም በኩር የሚለው፥ «በመጀመሪያ ከሙታን የተነሣ» ማለት ሳይሆን፥ «ከሙታን ከተነሡት ሁሉ በላይ» ማለት ነው። «በኩር» የአክብሮት ማዕረግ ነው (ሮሜ 8፡29፤ ቈላ. 1፡15፥ 18)።

ይህም ሆኖ ይህ መጽሐፍ ከሥላሴ ሦስት አካላት ውስጥ በመታሰቢያነት የተሰጠው ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ለምን? ለሕዝቡ ካደረጋቸው ነገሮች የተነሣ። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ይወደናል (በአብዛኛዎቹ መዛግብት ውስጥ ቃሉ በአሁን ጊዜ ተገልጿል)። ይህም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኘው አትኩሮት ጋር ይዛመዳል። እንዲሁም ደግሞ፥ ኃጢአታችንን አጥቦልናል፤ ወይም እንደ አንዳንድ ምንባቦች አባባል፥ ከኃጢአታችን አንጽቶናል። ይህም ከዮሐንስ መልእክቶች ጋር ይዛመዳል (1 ኛ ዮሐ. 1፡ ከቁጥር 5 ጀምሮ አንብብ)። እንደ ማዕዘን ራስ፥ ክርስቶስ የካህናት መንግሥት ያደረገን ሲሆን፥ ራእይ መጽሐፍ የሚያተኩረው በዚህ አሳብ ላይ ነው። ዛሬ ክርስቶስ እንደመልከ ጼዴቅ ካህን - ንጉሥ ሲሆን (ዕብ. 7)፥ እኛም ከእርሱ ጋር በዙፋኑ ላይ ተቀምጠናል (ኤፌ. 2፡ 1-10)።

እግዚአብሔር በፍቅሩ፥ እስራኤልን የካህናት መንግሥት እንድትሆን በጠራትም ነበር (ዘጸ. 19፡ 1-6)፤ ዳሩ ግን አይሁዶች ከእግዚአብሔር ጋር ለመንገዝ ባለመቻላቸው መንግሥታቸው ተወሰደባቸው (ማቴ. 21፡ 43)። ዛሬ የእግዚአብሔር ሕዝቦች (ቤተ ክርስቲያን) መንፈሳዊ ሥልጣን እየተለማመዱ፥ በዚህች ዓለም ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ነገሥታቱና ካህናቱ ናቸው (1ኛ ጴጥ. 2፡ 1-10)።

የመጽሐፉ ዓቢይ አሳብ (ራእይ 1፡ 7-8)

የራእይ መጽሐፍ የሚያስተላልፍልን ዋና አሳብ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ክፉውን ለማሸነፍና መንግሥቱን ለመመሥረት፥ ስለመመለሱ ነው። በመሆኑም፥ መጽሐፉ በትክክል የድል መጽሐፍ ሲሆን፥ ሕዝቡም እንደ «አሸናፊዎች» ተቆጥረዋል (2፡ 7፥ 11፥ 17፥ 26፤ 3፡ 5፤ 12፥ 21፤ 11፡ 7፤ 12፡ 11፤ 15፡ 2፤ 21፡ 7 ተመልከት)። በመጀመሪያው መልእክቱም፥ ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ «አሸናፊዎች» በማለት ጠርቷቸዋል (2፡ 13-14፤ 4፡ 4፤ 5፡ 4-5)። በማያምኑ ሰዎች ዓይኖች ፊት፥ ኢየሱስ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ በዚህ ዓለም ውስጥ የተሸነፉ ሲሆኑ፥ በአማኒያን ዓይኖች ፊት ግን፥ እርሱና ቤተ ክርስቲያኑ እውነተኛ ድል አድራጊዎች ናቸው። አንድ ጊዜ ፒተር ማርሻል እንደተናገሩት ሁሉ፥ «በመጨረሻው ላይ ለሸንፈት በሚዳርግ ጉዳይ ላይ ድል ከመንሣት ይልቅ፥ በመጨረሻው ላይ አሸናፊ በሚሆን ጉዳይ መረታቱ ይመረጣል።»

በቁጥር 7 ላይ፥ «እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል» የሚለው ዓረፍተ ነገር ጌታችን ወደ ምድር የሚመለስበትን ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን፡ በራእይ 19 ከቁጥር 11 ጀምሮ በአጽንኦት ቀርቧል። ይህ ሕዝቡን ለመንጠቅ በአየር ላይ ከሚገለጽበት ሁኔታ የተለየ ነው (1ኛ ተሰ. 4፤13-18፤ 1ኛ ቆሮ. 15 ከቁጥር 51 ጀምሮ)። ቤተ ክርስቲያኑን ለመንጠቅ በሚመጣበት ጊዜ፥ እንደ «ሌባ» ሆኖ የሚገለጽ ከመሆኑም (ራእይ 3፡3፤ 16፡15)፥ የሚመለከቱትም ደግሞ ዳግም የተወለዱት ብቻ ናቸው (1ኛ ዮሐ. 3፡1-3)። በራእይ 1፡7 ላይ የተገለጸው ክስተት ግን በዓለሙ በተለይም ንስሐ በሚገባው የእስራኤል ሕዝብ ፊት በይፋ የሚታይ ይሆናል (ዳን. 7፡13፤ ዘካ. 12፡10-12 ተመልከት)። ይህም በስውር ሳይሆን በይፋ የሚገለጽና ከራእይ 6-19 ውስጥ የተጠቀሰውን የታላቁን መከራ ጊዜ ከፍጻሜ የሚያደርስ ይሆናል (ማቴ. 24፡30-31)።

ፈሪሃ-እግዚአብሔር ያለባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት እስኪመሠረት ድረስ በሚፈጸሙ ክስተቶች ቅደም ተከተል ላይ ሁልጊዜም አይስማሙም (ራእይ 21-22)። በግሌ እንደማምነው በእግዚአብሔር የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ቀጣዩ ክስተት፥ ክርስቶስ በአየር ላይ ተገልጾ ቤተ ክርስቲያኑን ወደ ክብር የሚወስድበት ንጥቀት ነው። ቤተ ክርስቲያን በታላቁ መከራ ውስጥ እንደማታልፍ ክርስቶስ በራእይ 3፡10-11 የሰጠው የተስፋ ቃል ከማመልከቱም በላይ፥ ጳውሎስም በ1ኛ ተሰሎንቄ 1፡10፤5፡9-10 ይህንኑ አሳብ ደግፏል። በበኩሌ በራእይ 3፡22 እና 22፡16 መካከል «ቤተ ክርስቲያን» የሚል ቃል አለመጠቀሱ ከፍተኛ ግምት የምሰጠው ነው።

ቤተክርስቲያን ከተነጠቀች ወዲያ፥ በራእይ 6-19 ውስጥ የተጠቀሱት ክስተቶች ይፈጸማሉ - «የዓመፅ ሰው መነሣት»፥ ታላቁ መከራ (የእግዚአብሔር ቁጣ) እና የሰው ሠራሽ ዓለም መንግሥት ውድመት፥ ከዚያም የክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት መመለስ። ዳንኤል ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ መከራ የሚጸናበት ጊዜ ለሰባት ዓመታት እንደሚቆይ አመልክቷል (ዳን. 9፡25-27)። በራእይ መጽሐፍ ሁሉ ከዚህ የሰባት ዓመታት የጊዜ ገደብ ጋር የሚዛመዱ የጊዜ መለኪያዎችን እናገኛለን (11፡2-3፤ 12፡6፥14፤ 13፡5)።

ለእግዚአብሔር በቁጥር 8 ላይ የተሰጡት ማዕረጎች ያለምንም ጥርጥር የሚያሳዩት፥ መለኮታዊ ዓላማዎቹን በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ

በግልጽ ሊፈጽም እንደሚችል ነው። አልፋና ዖሜጋ በግሪክ የፊደል ገበታ ውስጥ የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደላት ሲሆኑ፥ እግዚአብሔር በነገሮች መጀመሪያና መጨረሻ ላይም ሕልውናውን እንደጠበቀ እንደሚኖር ያመለክታሉ። እርሱ በጊዜ ያልተገደበ ዘላለማዊ አምላክ ነው (ቁ. 4 ተመልከት)። እንዲሁም ማንኛውንም ነገር ለማድረግ የሚችል ሁሉን ቻይ ጌታ ነው። «ሁሉን ቻይ» የሚለው በራእይ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ቁልፍ ቃል ነው (1፡8፤ 4፡8፤ 11፡17፤ 15፡3፤ 16፡7፥14፤ 19፡6፥15፤ 21፡22)።

በራእይ 1፡8 እና 21፡6 ላይ እግዚአብሔር «አልፋና ዖሜጋ» ተብሎ የተጠራ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ይኸው ስያሜ ለልጁም ተሰጥቷል (1፡11፤22፡13)። ይህም የክርስቶስን አምላክነት በማያወላውል ሁኔታ ያረጋግጣል። እንደዚሁም «የመጀመሪያውና የመጨረሻው» የሚለው ወደ ኋላ ተጉዞ በኢሳይያስ ውስጥ የተጠቀሰውን ሲያመለክት (41፡4፤ 44፡6፤ 48፡12-13)፥ ለኢየሱስ አምላክነት ሌላው ማረጋገጫ ነው።

ወቅቱ (ራእይ 1፡9-18)

ይህ መጽሐፍ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በምርኮኛነት ከነበረበት ጥብቅ መንፈሳዊ ልምምድ የተወለደ ነው።

በዚያን የጌታ ዕለት ዮሐንስ የሰማው ነገር ከበስተኋላው የሚያስተጋባ የመለከት ዓይነት ድምፅ ነበር (1፡9-11)። ይህም ከኢየሱስ ክርስቶስ አፍ የሚወጣው ቃል ነበር። እስከምናውቀው ድረስ፥ ሐዋርያው ከስድሳ ዓመታት ከሚልቅ ጊዜ በፊት ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ከሰማው የጌታው የመጨረሻ ድምፅ በስተቀር ሌላ የሰማበት ጊዜ አልነበረም። ጌታ ይህን መጽሐፍ እንዲጽፍና ወደመረጣቸው ሰባት አብያተ ክርስቲያናት እንዲልክ ዮሐንስን መርጦት ነበር። ወደ በኋላ ላይ፥ ዮሐንስን ሌላ መለከት መሳይ ድምፅ ወደ ሰማይ እንዲወጣ ሲጋብዘው ይሰማል (4፡1)። (አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህንን ከ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-18 ጋር በማዛመድ፥ የዮሐንስን «ንጥቀት» የቤተ ክርስቲያን ንጥቀት መግለጫ አድርገው ያቀርባሉ።)

ዮሐንስ የተመለከተው (1፡12-16) የከበረውን የክርስቶስን ራእይ ነበር። ራእይ 1፡20 በግልጽ የሚያመለክተን ራእዩን ቃል በቃል መተርጎም እንደሌለብን ነው - በተምሳሌቶች የተሞላ ነውና። ሰባቱ

መቅረዞች መጽሐፉ የሚላክላቸውን ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት ይወክላሉ። እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በዚህ በጨለማ ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ብርሃን የምታበራ ነች። ይህንን ራእይ ከዳንኤል ራእይ ጋር አስተያይ (ዳን. 7፡9-14)።

የክርስቶስ አልባሳት ክብርንና ሥልጣንን የተጎናጸፉ የፈራጅ - ንጉሥ ልብሶች ናቸው። ነጩ ጸጉር ዘላለማዊነቱን ያሳያል - «ለዘመናት የሸመገለው» (ዳን. 7፡9፥ 13፥ 22)፥ ዓይኖቹ ሁሉንም በመመልከት (ራእይ 19፡12፤ ዕብ. 4፡12) በጽድቅ እንዲፈርድ ያስችሉታል። እሳቱ የኃጢአት መሥዋዕት የሚቃጠልበት የነሐሱ መሠዊያ እንደመሆኑ በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉት እግሮቹም የፍርድን አሳብ ያንጸባርቃሉ። ጌታ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ለመፍረድ መጥቶ ነበርና በክፉው የዓለም ዘይቤ ላይም ይፈርዳል።

«የብዙ ውኆች ድምፅ» (ቁ. 15) የሚለው አገላለጽ ስለ ታላቁ የኒያጋራ ፏፏቴ እንዳስብ ያደርገኛል። ምናልባትም ይህ የሚያመለክተው ሁለት አሳቦችን ይሆናል። 1. ክርስቶስ «የመገለጦችን ምንጮች» ሁሉ የሚያሰባስብና እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው «የመጨረሻው ቃል» መሆኑን (ዕብ. 1፡1-3)፤ 2. የሚናገረው በሥልጣንና ኃይል እንደመሆኑ ሊደመጥ እንደሚገባው። የአፉ ሠይፍ በትክክል የእግዚአብሔርን ሕያው ቃል ስለሚያመለክት (ዕብ. 4፤12፤ ኤፌ. 6፡17)፥ በቃሉ በመጠቀም ጠላቶቹን ይዋጋል (ራእይ 2፡16፤ 19፡19-21)።

በቁጥር 20 ላይ የተጠቀሱት በእጁ ውስጥ የሚገኙ ሰባቱ ከዋክብት የሚያመለክቱት መላእክትን (የግሪኩ ቃል መልእክተኞች ተብሎ የተተረጎመበትን ሉቃስ 7፡24 ተመልከት)፥ ወይም ምናልባት የሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎች ነው። እግዚአብሔር ባሪያዎቹን በመምራት «እንዲያበሩለት» በሚፈልገው ሥፍራ ያስቀምጣቸዋል። በዳንኤል 12፡3 ጥበበኛ መስካሪዎች ከሚያበሩ ከዋክብት ጋር ተዛምደዋል።

ይህም የጌታችን ፊት በማብራት በተራራ ላይ ስለመለወጡ (ማቴ. 17፡2) እና ስለሚልክያስ 4፡2 ትንቢት እንድናስብ ያደርገናል - («የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች»)። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፀሐይ የተለመደች የእግዚአብሔር አምሳል መግለጫ ስትሆን (መዝ.

(84)፡ 11)፥ በረከትን ብቻ ሳይሆን ፍርድንም ታስታውሰናለች። ፀሐይ ሊ ተሞቅም ልታቃጥልም ትችላለች!

ይህ የክርስቶስ ራእይ ጌታ በምድር ላይ «በሥጋ» ሆኖ በሚያገለግልበት ጊዜ ዮሐንስ ከሚያውቀው አዳኝ ሙሉ በሙሉ የተለየ ነበር። ስሚታውያን ሊቀኙለት የሚፈልጉት «ገር ይሁዳዊ አናጢ» አልነበረም። ይልቁንም፥ ከራሱ ሕዝብ ጀምሮ በሰዎች ሁሉ ላይ የመፍረድ ሥልጣን ያለው ካህን - ንጉሥ (1ኛ ጴጥ. 4፤ 17)፥ ከሞት የተነሣ፥ የከበረና ከፍ ከፍ የተደረገ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ዮሐንስ ያደረገው (1፡ 17-18) አግባብነት ያለው ነገር - እንደሞተ ሰው ሆኖ ከጌታ እግር ሥር ወደቀ! ሆኖም ግን የአሁኑ ዮሐንስ እንደቀድሞው ወደ ኢየሱስ ደረት ለመጠጋት ድፍረት የነበረው ሐዋርያው አልነበረም (ዮሐ. 13፡ 23)። ከፍ ከፍ የተደረገው የክርስቶስ ራእይ የሚያስከትለው እንዲህ ዓይነቱን ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ነው (ዳን. 10፡ 7-9)። ዛሬ እጅግ ብዙ አማኞች፥ ለእግዚአብሔር በማይገባ ዓይነት አቀራረብ በሚናገሩበትና በሚከውኑበት ጊዜ፥ እኛ ግን የዚህ ዓይነቱን የአክብሮት ዝንባሌ ልናዳብር ይገባል። ዮሐንስ የሰጠው ምላሽ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5፡ 16 ላይ የጻፈውን ያብራራዋል - «ክርስቶስንም በሥጋ እንደሆነ ያወቅነው ... ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።» ዮሐንስ ከዚያ በፊት ካደረገው ጋር በማዛመድ ወደ ጌታ ደረት አልተጠጋም።

ጌታ ግን ሰውነቱን በመንካትና በማነጋገር ለዮሐንስ ዳግም ማረጋገጫ ሰጥቶታል (ዳን. 8፡ 18፤ 9፡ 21፤ 10፡ 10፥ 16፥ 18 ተመልከት)። «አትፍራ!» የሚለው ቃል ለማንኛውም የእግዚአብሔር ልጅ ታላቅ ማበረታቻ ነው። እርሱ «ሕያው» ነውና ሕይወትን ልንፈራት አይገባም። እርሱ ሞትን ድል ነሥቶ አሁን በሕይወት ስላለ ሞትንም መፍራት አያስፈልገንም። እንዲሁም እርሱ የሲኦል (የሙታንን ዓለም) እና የሞትን መክፈቻዎች በእጁ ስለያዘ፥ ዘላለማዊነትንም መፍራት አያሻንም። መክፈቻውን የሚይዘው ባለሥልጣኑ ነው።

ገና ከመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ፥ ኢየሱስ ራሱን ለሕዝቡ በከበረ ግርማ ሞገስ አቅርቦታል። ለአሁኗም ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ይህንን የክርስቶስን ማንነትና ክብር ለይቶ ማወቅ ነው። ጌታን «በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ» ልናየው ይገባል (ኢሳ. 6፡ 1)። ዛሬ

በጉባኤያችን ውስጥ አደገኛ የሆነ የፍርሃትና የአምልኮ መታጣት ይታያል። ከእግሩ ሥር በመውደቅ ፈንታ፥ በእግራችን በመቆማችን እንመካለን። ኢቫን ሮበርትስ የተባሉት የሃይማኖት መሪ «የኩራት መንፈሴን ስበረው!» እያሉ ለዓመታት ይጸልዩ ነበርና፥ እግዚአብሔር ጸሎታቸውን በመለሰበት ጊዜ ታላቅ መንፈሳዊ መነቃቃት በአገራቸው በዌልስ ተካሄደ።

አስተዋጽኦ (ራእይ 1፡ 19)

እኔ እስከማውቀው ድረስ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመንፈስ ምሪት ያረፈበትን የማውጫ ርእሶች የያዘው የዮሐንስ ራእይ ብቻ ነው። «ያየኸውን» የሚለው በምዕራፍ 1 ውስጥ የሚገኘውን ራእይ የሚያመለክት ሲሆን፥ «አሁንም ያለውን» የሚለው በምዕራፍ 2-3 ውስጥ የሠፈረው ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላለፉትን ልዩ መልእክቶች ያሳያል። «ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለው» የሚለው ከምዕራፍ 4-22 ውስጥ የተገለጹትን ክስተቶች ያካትታል። ዮሐንስ በ4፡ 1 ላይ የሰማው ድምፅ ይህንኑ ትርጓሜ ያጠናክራል።

በመሆኑም፥ በዚህ በቁጥር 19 አተረጓጎም ላይ የተመሠረተ አስተዋጽኦ እነሆ፡-

1. ያየኻቸው ነገሮች - ምዕ. 1

   ዮሐንስ ከፍ ከፍ ስለተደረገው ክርስቶስ የተመለከተው ራእይ

2. አሁን ያሉት ነገሮች - ምዕ. 2-3

   ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ መልእክቶች

3. ከዚህ በኋላ የሚሆኑ ነገሮች - ምዕ. 4-22

   ሀ. በሰማይ የታየው ዙፋን ፥ 4-5

   ለ. በምድር ላይ የሚደርሰው መከራ ፥ 6-19

      1. የመጀመሪያው አጋማሽ ፥ 6-9

      2. መካከለኛው ጊዜ ፥ 10-14

      3. የመጨረሻው አጋማሽ ፥ 15-19

   ሐ. የክርስቶስ መንግሥት፥ 20

   መ. አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፥ 21-22

በክለሳ መልክ፥ የዚህን አስደናቂ መጽሐፍ መሠረታዊ ባሕርያት እንደሚከተለው ልናጠቃልል እንችላለን፡-

1. ይህ መጽሐፍ ክርስቶስን ማዕከላዊ ያደረገ መጽሐፍ ነው። በመሠረቱ፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ስለአዳኙ ይናገራሉ፤ ይህም ሆኖ የራእይ መጽሐፍ በተለይ የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነትና ክብር አጉልቶ ያሳያል። መጽሐፉም ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ራእይ እንጂ፥ የወደፊት ክስተቶች ራእይ አይደለም።

2. «የተከፈተ» መጽሐፍ ነው። የመጽሐፉ እያንዳንዱ መልእክት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ዮሐንስ ይህንን መጽሐፍ እንዳያትም ተነግሮታል (22፡10)። ምንም እንኳ መጽሐፉ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እስክንሰባሰብ ድረስ ለመረዳት የማንችላቸውን ምሥጢራት ቢይዝም፥ ጠቅላላ መንፈሱን ልንገነዘብ እንችላለን። ዮሐንስ ይህንን መጽሐፍ በትንሹ እስያ ይኖሩ ለነበሩት ሰባት አብያተ ክርስቲያናት መላኩ፥ መልእክተኞቹ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲያነቡዋቸው፥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለነበሩት ቅዱሳን በከፍተኛ ደረጃ ሊያበረታቷቸው የሚችሏቸውን ያህል እውነቶች እንደሚረዱ በመተማመን ነበር።

3. በተምሳሌቶች የተሞላ መጽሐፍ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ተምሳሌቶች በመልእክታቸው በጊዜ ያልተገደቡ ከመሆናቸውም፥ በይዘታቸውም ገደብ የሌላቸው ናቸው። ለምሳሌ፥ የ«ባቢሎን» ተምሳሌት ከዘፍጥረት 10-11 ይመነጭና በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ውስጥ ትርጉሙ እያደገና እየሰፋ በመሄድ በራእይ 17-18 ይደመደማል። የ«በጉ» እና የ«ሙሽራው» ተምሳሌቶችም እንዲሁ ናቸው። በእነዚህ ተምሳሌቶች የተላለፉትን የበለጸጉ ትርጉሞች ተመራምሮ ማግኘቱ አስደሳች ነው።

4. የትንቢት መጽሐፍ ነው። ይህ በግልጽ በራእይ 1፡3፤ 22፡7፥10፥ 18-19 ውስጥ በትክክል ተገልጿል። 10፡11ንም እንደዚሁ ልብ ብለህ ተመልከት። በትንሹ እስያ ለሚገኙ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩት ደብዳቤዎች በእነዚያ ማኅበረ-ምዕምናን ውስጥ ለሚገኙ አንገብጋቢ ችግሮች መፍትሔ የሚያስገኙ ነበሩ - ዛሬም በእኛ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የምንጋፈጣቸው ችግሮች ተመሳሳይ ናቸው። የቀረው የመጽሐፉ ክፍል ግን ሙሉ ለሙሉ ለማለት ይቻላል ትንቢታዊ መገለጦችን ያካትታል። ስደት የተፈራረቀባቸው ክርስቲያኖች

ለአስቸጋሪው የምስክርነት ሥራቸው ብርታት ያገኙት፥ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረበውን ድል-ነሺውን ክርስቶስን በመመልከት ነበር። ለወደፊቱ ጉዳይ ዋስትና ሲኖርህ፥ ለአሁኑ ሕይወትህ ጽናትን ታገኛለህ። ዮሐንስ እራሱ በሮም እጅ መከራ ይቀበል ነበርና (1፡9)፥ መጽሐፉ የተወለደው ከመከራ ነበር።

5. በረከት ያለበት መጽሐፍ ነው። በራእይ 1፡3 ላይ የተጠቀሰውን የተስፋ ቃል ቀደም ብለን የተመለከትን ሲሆን፥ በመጽሐፉ ውስጥ ተሰበጣጥረው የሚገኙትንም ሌሎች ስድስት «ብፅዕናዎች» አይተናል። መጽሐፉ ሲነበብ መስማት (ወይም ማንበብ) ብቻ በቂ አይደለም - ከልባችን ለመልእክቱ ልንታዘዝ ይገባል። በግላችን ቃሉን ከሕይወታችን ጋር በማገናዘብ፥ ለመልእክቱ እምነት የታከለበትን የ«አሜን» ምላሽ ልንሰጥ ይገባል። (በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን በርካታ «አሜን» የሚሉትን ቃላት ተመልከት፡- 1፡6፥7፥18፤ 3፡14፤5፡14፥ 7፡12፤ 19፡4፥ 22፡20-21)።

6. ከዘመኑ ጋር የሚዛመድ መጽሐፍ ነው። «ዘመኑ ስለቀረበ፥» ዮሐንስ የጻፈው ነገር «በቶሎ የሚፈጸም» ነበር (1፡1)፤ ምክንያቱም «ጊዜው ስለደረሰ» ነው (1፡3)። (በተጨማሪም 22፡7፥10፥12፥20 ተመልከት)። «ቶሎ» የሚለው ቃል «አሁኑኑ» ወይም «ወዲያውኑ» ማለት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን «በፍጥነት» ማለት ነው። እግዚአብሔር ጊዜን የሚለካው እኛ እንደምንለካው አይደለም (2ኛ ጴጥ. 3፡1-10)። ማንም ጌታችን መቼ እንደሚመለስ አያውቅም፤ ይሁንና የመጽሐፉን ጥቅልል ማኅተሞች መክፈት ከጀመረ (6፡ ከቁጥር 1 ጀምሮ) ክስተቶች ያለማቋረጥ በፍጥነት ይፈጸማሉ።

7. ግርማ-ሞገስ ያለው መጽሐፍ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ «ዙፋን» የሚለው ቃል አርባ ስድስት ጊዜ ተጠቅሶ ስለሚገኝ ራእይ «የዙፋን» መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት የሚያጎላ ሲሆን፥ ክርስቶስን በክብሩና በአገዛዙ ቀርቦ እናየዋለን።

8. አጽናፍ-አቀፍ መጽሐፍ ነው። ዮሐንስ የተለያዩ ብሔሮችንና ሕዝቦችን እንደ እግዚአብሔር መርሐ-ግብር አካላት ተመልክቷል (10፡11፤ 11፡9፤ 17፡15)። በተጨማሪም የሰማዩን የዙፋን መቀመጫ የተመለከተ ሲሆን፥ ድምፆችን ከአጽናፍ-ዓለም ዳርቻዎች ሰምቷል።

9. የፍጻሜ መጽሐፍ ነው። ራእይ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ከመጨረሻው የላቀ ደረጃ የሚደርስበት የፍጻሜ መጽሐፍ ነው። በዘፍጥረት የተጀመረው ሁሉ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድ አኳያ ከፍጻሜ ይደርሳል። እርሱ «አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያና መጨረሻ» ነው (1፡8)። እግዚአብሔር የሚጀምረውን ነገር ከፍጻሜ ያደርሰዋል።

ይሁንና የሰማዩን የዙፋን መቀመጫ ከመጎብኘታችን በፊት፥ «በመቅረዞች መካከል የሚመላለሰው ሰው» በየአብያተ ክርስቲያናቶቻችንና በየራሳችን ልብ ውስጥ በግል የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሲገልጥ ለማዳመጥ ለአንድ አፍታ ቆም እንበል። «መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ!»

- 2 -

ክርስቶስና አብያተ ክርስቲያናት -

ክፍል 1

ራእይ 2

ወደ አዲስ ማኅበረሰብ በመሄድ፥ አዲስ የማምለኪያ ቤተ ክርስቲያን የመምረጥ ኃላፊነት አጋጥሞህ ከሆነ፥ የአንድን ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መመርመርና መገምገም ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ታውቃለህ። ማራኪ ሕንፃዎች በማጣጣር ላይ ያሉ ወይም የሞቱ ማኅበረ ምዕምናንን የሚያስተናግዱትን ያህል፥ በሌላ በኩል ደግሞ ዝቅተኛና ተራ ቤቶች ለጌታ ሥራ የበረቱ ጉባኤተኞችን ሊይዙ ይችላሉ። «ባለጸጋ» እንደሆነች የምናስባት ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ጎስቋላ ልትሆን ስትችል (ራእይ 3፡17)፥ «ድሀይቱ» ሀብታም ልትሆን ትችላለች! (2፡9)።

የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እያንዳንዷን ቤተ ክርስቲያን በትክክል ሊመረምርና እውነተኛ ሁኔታዋን ሊረዳ ይችላል፤ ምክንያቱም እርሱ ውጫዊውን ሳይሆን ውስጣዊውን ገጽታ ስለሚመለከት ነው (2፡23)። በትንሹ እስያ ለሚገኙ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በተላኩት በእነዚህ ልዩ መልእክቶች፥ ጌታ ለእያንዳንዱ ጉባኤ የነበረበትን ሁኔታ የሚያመለክት የምርመራ ወይም የ«ኤክስ-ሬይ» ውጤት ሰጥቷል። ይሁንና ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን መልእክቶች እንዲያነቧቸው ብቻ ሳይሆን እንዲጠቀሙባቸውም ይፈልጋል። (በ2፡7፥11፥17፥29፤ 3፡6፥13፥22 «አብያተ ክርስቲያናት» የሚለውን የብዙ ቁጥር ተመልከት)።

ይህም ሆኖ ጌታ ለግለሰቦችም እየተናገረ ነበር - እኔና አንተንም በቀጥታ የሚመለከተው ይህ ክፍል ነው። «ጆሮ ያለው ይስማ»። አብያተ ክርስቲያናት የግለሰቦች ጥርቅም ሲሆኑ፥ የማኅበረ ምዕምናኑን መንፈሳዊ ሕይወት የሚወስኑትም እነዚሁ ግለሰቦች ናቸው። በመሆኑም፥ እነዚህን መልእክቶች በምናነብበት ጊዜ፥ ልባችንን በመመርመር ከግል ሕይወታችን ጋር ማዛመድ አለብን።

በመጨረሻም፥ ዮሐንስ እነዚህን አብያተ ክርስቲያናት በአስቸጋሪው ወደት ጊዜ ለማበረታታት የሚፈልግ እውነተኛ መጋቢ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል። ክርስቶስ በዓለም ላይ ከመፍረዱ በፊት፥ በራሱ ሕዝቦች ላይ መፍረድ አለበት (1ኛ ጴጥ. 4፡17፤ ሕዝ. 9፡6)። የንጹች ቤተ ክርስቲያን የሰይጣንንም ሆነ የሰዎችን ጥቃቶች መፍራት አይኖርባትም። ጂ. ካምቤል ሞርጋን፥ «ስደት የደረሰባት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ንጽሕት ስትሆን፥ መልካም መስተንግዶ የሚደረግላት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ግን፥ ግድፈት የሚታይባት መሆኑ በጣም አስገራሚ ነው» በማለት ጽፈዋል።

ኤፌሶን - ግድየለሿ ቤተ ክርስቲያን (ራእይ 2፡ 1-7)

ሰባቱ መልእክቶች እያንዳንዳቸው የሚጀምሩት በራእይ 1 ውስጥ ከተጠቀሰው የክርስቶስ ራእይ በተወሰደ የኢየሱስ ክርስቶስ የግል መግለጫ ወይም ማዕረግ ነው (ኤፌሶንን በተመለከተ 1፡12፥16፥20ን ተመልከት)። በኤፌሶን ማኅበረ ምዕመናን ዘንድ እንደ ጳውሎስ፥ ጢሞቴዎስ እና ራሱንም ሐዋርያውን ዮሐንስ የመሳሰሉ «ኮከብ» መሪዎች አገልግለው ነበር - ይሁንና ጌታ «ኮከቦቹን» ደስ ባሰኘው ሥፍራ እያስቀመጠ አገልግሎቱን የሚቆጣጠረው ራሱ እንደሆነ ያስታውሳቸዋል። ሆኖም ግን አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት መጋቢዎችና አስተማሪዎች የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውንና በማንኛውም ጊዜ ሊወሰዱ የሚችሉ መሆናቸውን በቀላሉ በመኩራራት ይዘነጉታል (ኤፌ. 4፡11)። በተጨማሪም ለሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት ቢሆን ጌታን እንጂ መጋቢያቸውን ማምለክ እንደማይገባቸው ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ሙገሳ (2፡2-3፥ 6) - ጌታ በሙገሳ ቃላት መጀመሩ እንዴት ቸር እንደሆነ ያሳያል። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ይህች ቤተ ክርስቲያን የጌታን ሥራ በመሥራት የምትጣደፍ አገልጋይ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ሳምንታዊ የጊዜ ሰሌዳቸው በተለያዩ ተግባራት የተሞላ ለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። «ድካምህን» የሚለው «በድካም እስኪዝሉ ድረስ መሥራት» ማለት ስለሆነ፥ ራስዋን በመሠዋት የምታገለግልም ቤተ ክርስቲያን ነበረች። የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ጌታን ለማገልገል ዋጋ ከፍላለች። «ትዕግሥት» የሚለው ቃል «በመከራ መጽናት» የሚል ትርጉም ስላለው፥ ጽኑ ማኅበረ ምዕመናን ነበራት። ጉዞው ከባድ

በሚሆንበት ጊዜም ሳይቀር፥ ምዕመናኗ መንፈሳዊ ጉዞአቸውን እንደቀጠሉ ነበር።

የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የጎብኚ አገልጋዮችን እውነተኛነት እስከምትረዳ ብርቱ ጥንቃቄ ታደርግ የነበረ በመሆኑም (2ኛ ዮሐ. 7-11)፥ የተለየች ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎች ከውጭ እንደሚመጡና ከውስጥም እንኳ እንደሚነሡ በመግለጽ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ያስጠነቀቀ ሲሆን (የሐዋ. 20፡28-31)፥ ዮሐንስም «መናፍስትን እንዲለዩ» አስተምሯቸዋል (1ኛ ዮሐ. 4፡1-6)። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ሰይጣን የራሱ የሐሰት አስተማሪዎች ስላሉት፥ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሰዎች ለመለየትና ለማስወገድ ሁልጊዜም ልትነቃ ይገባል (2ኛ ቆሮ. 11፡1-4፥ 12-15)።

የኤፌሶን ክርስቲያኖች ከሐሰት ትምህርት ብቻ ሳይሆን፥ ከሐሰተኛ ተግባራትም ራሳቸውን ለይተው ነበር (ራእይ 2፡6)። «ኒቆላውያን» የሚለው ቃል «ሕዝብን ማሸነፍ» ማለት ሲሆን፥ እንደ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እምነት፥ ይህ በቤተ ክርስቲያን ላይ «ሸክም የሚጭን» እና ሕዝቡም በክርስቶስ ያገኘውን ነፃነት የሚገፍ ኑፋቄ ነበር (3ኛ ዮሐ. 9-11 ተመልከት)። እነዚህ ወገኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትኛውም ሥፍራ ያልተጠቀሰውን የ«ካህናት» እና የ«ተራ ምዕምናን» ቡድን በማበጀት ክፍፍል ፈጥረው ነበር። ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉም «ነገሥታትና ካህናት» ሲሆኑ (ራእይ 1፡6፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡9)፥ በክርስቶስ ደም በኩል ሁላቸውም ወደ አብ የመግባት እኩል እድል አላቸው (ዕብ. 10፡ ከቁጥር 19 ጀምሮ)። ይህንን አደገኛ ኑፋቄ ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን የተጻፈውን መልእክት በምናጠናበት ጊዜ ደግሞ እናገኘዋለን።

በኤፌሶን የነበሩት አማኞች የሚደርስባቸውን ማናቸውንም ፈተና በትዕግሥት የሚቋቋሙና ባለመታከት ተግተው የሚሠሩ መከራ ተቀባዮች ነበሩ። ይህንንም ሁሉ ያደረጉት ለጌታ ስም ሲሉ ነበር። እነዚህን ማኅበረ ምዕምናን በየትኛውም መልክ ብትገመግማቸው «ወደ ፍጹምነት ተቃርበዋል» ብለህ መደምደምህ የማይቀር ነው። ይህም ሆኖ፥ በመቅረዞቹ መካከል የሚመላለሰው እርሱ የልባቸውን ተመልክቶ ኖሮ ከእኛ የተለየ የምርመራ ውጤት አስተላለፈ።

ነቀፋ (2፡4) - ይህች ትጉ፥ የተለየች፥ በመሥዋዕትነት የምታገለግል ቤተ ክርስቲያን «በልብ ሕመም» ትታወክ ነበር። ምዕመናኗ የመጀመሪያውን ፍቅራቸውን ትተው ነበር! «ሥራ፣ ድካም፣ ትዕግሥት» ቢኖራቸውም (ራእይ 2፡2)፥ እነዚህ ብቃቶች ለክርስቶስ ካላቸው ፍቅር የመነጩ አልነበሩም። (በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡3 ላይ ከተጠቀሰው «የእምነት ሥራ፥ የፍቅር ድካም፥ የተስፋ መጽናት» ጋር አወዳድር።) ለጌታ የምናደርገው ነገር አስፈላጊ የመሆኑን ያህል፥ የምናደርገውን የምናደርግበት ምክንያትም እንዲሁ አስፈላጊ ነው!

«የመጀመሪያ ፍቅር» ማለት ምንድነው? ብዙውን ጊዜ የአዲስ ክርስቲያን መለያ የሆነው የጋለ፥ ግላዊ፥ የማይታቀብ፥ አስደሳችና በግልጽ የሚታይ ለክርስቶስ የመሰጠት ሕይወት ነው። ይህም የባልና ሚስትን «የጫጉላ ቤት ፍቅር» የሚመስል ነው (ኤር. 2፡1-2)። የበሰለ የጋብቻ ፍቅር እየጠለቀና እየበለጸገ እንደሚሄድ ቢታወቅም፥ የእነዚያን «የጫጉላ ቤት - ቀናት» ደስታና አድናቆትም ማጣት እንደሌለበት እውነት ነው። ባልና ሚስት እርስ - በርሳቸው እንደዋዛ ሲተያዩና ሕይወትም አሰልቺ ተግባር ሲሆን፥ ጋብቻው በአደጋ ላይ ይወድቃል።

እስኪ አስበው፦ በእውነተኛ ልብ ኢየሱስ ክርስቶስን ባላፈቅረውም፥ ዳሩ ግን ላገለግል፥ ልሠዋና «ለራሴ ስል» መከራ ልቀበል እችላለሁ። የኤፌሶን አማኞች አምልኮን እስኪዘነጉ ድረስ መለየታቸውን በማጥበቁ ተግባር ላይ ይጣደፉ ነበር። ሥራ ለፍቅር መተኪያ ሊሆን አይችልም - ንጽሕናም መሻትን አይተካም። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን እንድታስደስት ከተፈለገ፥ ሁለቱንም አሟልታ ልትገኝ ይገባል።

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈውን መልእክት በማንበብ፥ ስለፍቅር የሚገልጹ ቢያንስ ሃያ ማጣቀሻዎችን ታገኛለህ። እንዲሁም ጳውሎስ አማኞች «በክርስቶስ . . . በሰማያዊ ስፍራ» ከፍ ብለው ለመቀመጣቸው የሰጠውንም አጽንኦት ትመለከታለህ። ይሁንና የኤፌሶኗ ቤተ ክርስቲያን ወደዚህ መመዘኛ ለመድረስ ያልበቃችና በክርስቶስ ካላት ሰማያዊ ሥፍራ አንጻር የማትመላለስ ነበረች (ራእይ 2፡5)። ክርስቶስን በታማኝነት ልናገለግል የምንችለው ከልባችን ስንወደው ብቻ ነው። በመሆኑም ለእርሱ የሚኖረን ፍቅር ንጹሕ ሊሆን ይገባል (ኤፌ. 6፡24)።

ምክር (2፡5-7) - ክርስቶስ የሰጣቸውን ሦስቱን ትእዛዛት እስከተከተልን «የመጀመሪያው ፍቅር» ሊታደስ ይችላል። በመጀመሪያ፥ ያጣነውን ነገር ልናስታውስና ያንኑ የቀረበ ኅብረት ደግሞ ለመጎናጸፍ ፍላጎት ሊኖረን ይገባል። ከዚያም ንስሐ ልንገባ - አእምሮአችንን ልንቀይር - እና ኃጢአታችንን ለጌታ ልንናዘዝ ይገባል (1ኛ ዮሐ. 1፡9)። ሦስተኛ፥ ከኃጢአታችንና ከቸልተኛነታችን የተነሣ የፈራረሰውን የመጀመሪያውን ኅብረት ደግሞ ለመጠገን የሚያስችሉትን የመጀመሪያ ተግባራት ልንፈጽም ይገባል። ይህም ማለት ለአንድ ክርስቲያን ጸሎት ማድረስ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብና ማሰላሰል፥ ታዛዥነት የሚታይበትን አገልግሎት መፈጸምና አምልኮን ማካሄድ ማለት ነው።

ደስ ከተሰኘችባቸው መልካም ዕድሎች ባሻገር፥ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ብርሃንዋን የማጣት አደጋም አንዣብቦባት ነበር። አንዲት ቤተ ክርስቲያን በእምነት ትምህርቷ የቱንም ያህል ጤነኛ ብትሆንም፥ ፍቅሯን ያጣች ከሆነ ግን ብዙም ሳይቆይ ብርሃንዋን ታጣለች፤ «አለዚያ እመጣብሃለሁ» (2፡5) የሚለው፥ በፍጥነት ሊወርድባቸው የነበረውን ፍርድ እንጂ፥ የጌታን ምጽአት አያመለክትም። ድሮ የከበረችው የኤፌሶን ከተማ ዛሬ ከድንጋይ ቁልል ባሻገር ደምቆ የሚታይ ብርሃን የላትም።

ቁጥር 7 እንደሚያለመክተው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙት ምዕመናን ብዙዎቹ እንዳሻቸው የሚያደርጉ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ለጌታ ታማኞች የሆኑ የተወሰኑ ግለሰቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ እንመለከታለን። በእነዚህ ሰባት መልእክቶች እንደምንመለከተው «ድል-ነሺዎች» «መንፈሳዊ ምርጦች» ሳይሆኑ፥ በእምነታቸው ድልን የተቀዳጁ እውነተኛ አማኞች ናቸው (1ኛ ዮሐ. 5፡4-5)። ኃጢአተኛው ሰው ወደ ሕይወት ዛፍ እንዳይደርስ ማዕቀብ የተጣለበት ሲሆን (ዘፍጥ. 3፡22-24)፥ ዳሩ ግን በክርስቶስ ዘላለማዊና የተትረፈረፈ ሕይወት አለን (ዮሐ. 3፡16፤ 10፡10)። አሁንም በዚህ በረከት ደስ የምንሰኝ ሲሆን፥ በዘላለማዊው መንግሥት በበለጠ እንረካበታለን (ራእይ 22፡1-5)።

የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ የነበራቸውን ፍቅር ችላ ያሉ ግድየለሽ አማኞች የሚገኙባት «ግድየለሽ ቤተ ክርስቲያን» ነበረች። እኛስ በዚሁ ዓይነት የቸልተኝነት ኃጢአት በድለን ይሆን?

ሰምርኔስ - የተሸለመችው ቤተ ክርስቲያን (ራእይ 2፡8-11)

«ሰምርኔስ» የሚለው ቃል «መራራ» ማለት ሲሆን፥ «ማራ» ከሚለው ቃል ጋር ዝምድና አለው። ከተማይቱ ዛሬ «ኢዝሚር» በሚል ስያሜ ትታወቃለች። በሰምርኔስ የነበሩ ማኅበረ-ምዕምናን ስለእምነታቸው ስደት ደርሶባቸው ነበር፤ ይህም ጌታ መልእክቱን በሚጀምርበት ጊዜ በሞቱና በትንሣኤው ላይ ያተኮረበትን ምክንያት ይገልጻል። የእግዚአብሔር ሰዎች በምንም ዓይነት ልምምድ ውስጥ ቢሆኑ፥ ጌታቸው ከጎናቸው ይቆማል።

ሙገሳ (2፡9) - በሰምርኔስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ቀላል ጊዜ አልነበራትም! ምዕመናን ምናልባትም ከሌሎች ጋር ተስማምተው፥ «ቄሳር ጌታ ነው!» ለማለት ባለመፍቀዳቸው ስደት ይደርስባቸው ነበር። ሰምርኔስ የሮም ንጉሣዊ ኑፋቄ ዓይነተኛ ማዕከል ስትሆን፥ የቄሳርን ጌትነት የማይቀበል ማንም ቢሆን ከሙያ ማኅበራት ይባረር ነበር። ይህም ሥራ አጥነትንና ጉስቁልናን ያስከትል ነበር። በዚህ ሥፍራ ለ«ድህነት» የተሰጠው ቃል «አሳፋሪ ጉስቁልና፥ ምንም ነገር ማጣት» ማለት ነው።

በርካታ አባላት የሚገኙበት የአይሁድ ማኅበረሰብ በሰምርኔስ በጥሩ ሁኔታ ይኖር ነበር። በእርግጥ አይሁዶች ሃይማኖታቸው በሮም ተቀባይነት ስላገኘ፥ ከንጉሣዊ ኑፋቄ ጋር መወዳጀት አያስፈልጋቸውም ነበር፤ ይህም ሆኖ አለጥርጥር ከክርስትና እምነት ጋር አይተባበሩም ነበር። በመሆኑም በሰምርኔስ የነበሩ ክርስቲያኖች ከሁለቱም ወገን ማለትም ከአይሁዶችና ከአሕዛቦች የስም ማጥፋት ዘመቻና የተለያየ በደል ይደርስባቸው ነበር።

ይህም ሆኖ ሀብታሞች ነበሩ! ከቶውንም ለማይለወጡ ለዘላለማዊ እሴቶች ይኖሩ ነበር - ምንም ኃይል የማይገፉቸው ብልጽግናዎች! «ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለጠጎች እናደርጋለን» (2ኛ ቆሮ. 6፡10፤ 8፡9)። እንዲያውም፥ ለክርስቶስ መከራ መቀበላቸው ብልጽግናቸውን ከማሳደግ በቀር ያደረሰው ጉዳት አልነበረም።

ትግላችን ሰዎችን የዓላማው መፈጸሚያ አድርጎ ከሚጠቀም ከጠላታችን ሰይጣን ጋር እንጂ፥ ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለም። የአይሁድ ምኩራብ በእርግጥም የሰይጣን ምኩራብ ነበር። እውነተኛው አይሁዳዊ በሥጋዊ ሁኔታ ወይም በዘር ሐረግ ቆጠራ አይሁዳዊ የሆነው ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ከመንፈሳዊ መለኪያ አንጻር አይሁዳዊ የሆነው ነው

(ሮሜ 2፡17-29)። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የማይቀበል ማንኛውም ሃይማኖታዊ ቡድን - አይሁዳዊም ይሁን አሕዛብ - የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚጻረር የተረጋገጠ እውነት ነው።

ምክር (2፡10-11) - በሰምርኔስ ለነበሩት ማኅበረ-ምዕምናን ምንም ዓይነት የወቀሳ ቃላት አልተሰነዘሩም። የሰዎችን ሙገሳ ላያገኙ ቢችሉም፥ የእግዚአብሔርን ምስጋና ተቀብለዋል። ይህም ሆኖ፥ እያደገ በሚሄድ መከራ ውስጥ ስለነበሩ፥ ጌታ ጠንካራ የምክር ቃል ሰጥቷቸዋል - «አትፍራ!» የሚል።

ጌታ የዲያብሎስን ዕቅዶች እንደሚያውቅና ሁኔታውንም ሙሉ ለሙሉ በመቆጣጠር ላይ እንዳለ አረጋገጠላቸው። ከአማኞቹ አንዳንዶቹ ይታሰሩና ሮምን እንደካዱ ሰዎች በመቆጠር በጥብቅ ይመረመሩ ነበር። ይሁንና በመጽሐፍ ቅዱስ፥ «አሥር ቀን»፥ «አጭር የጊዜ ገደብ»ን ስለሚያመለክት - (ዘፍ. 24፡55፤ የሐዋ. 25፡6)፥ የመከራ ጊዜያቸው አይረዝምም ነበር። አስፈላጊው ነገር ታማኝነት ነበር - መንግሥት የፈለገውን ዓይነት ዛቻ ቢሰነዝርም፥ ለክርስቶስ እውነተኛ ሆኖ መቆምን!

«የሕይወት አክሊል» በዓመታዊ የአትሌቲክስ ውድድር ላይ ለአሸናፊው የሚሰጥ ሽልማት ነው። ሰምርኔስ በውድድሮች ውስጥ ቁልፍ የተሳትፎ ሚና ስለነበራት፥ ይህ የተስፋ ቃል በተለይ በዚያ ለነበሩት አማኞች ትርጉም የሚሰጥ ነበር። ጌታ በያዕቆብ የተሰጠውን የተስፋ ቃል በማጽናት (ያዕ. 1፡12)፥ ምንም የሚፈሩት ነገር እንደሌለ ለሕዝቡ አረጋግጦላቸዋል። እርሱን ስለተማመኑት ድል ነሺዎች ነበሩ - የእምነት ውድድር አሸናፊዎች (ዕብ. 12፡1-3)። እንዲሁም፥ ድል-ነሺዎች እንደመሆናቸው የሚፈሩት ነገር አልነበረም። በሰማዕትነት ቢያልፉ እንኳ፥ ሽልማቶችንም ተጎናጽፈው ወደ ክብር ስፍራ ይገባሉ። የእሳት ባሕር ለሆነው ለሁለተኛው ሞት አስፈሪ ፍርድ አይዳረጉም (ራእይ 20፡14፤ 21፡8)።

የተሰጠ ክርስቲያን ሆኖ፥ በተለይም በአንዳንድ ሥፍራዎች መገኘት ከሌሎችም የበለጠ ዋጋ ያስከፍላል። የመጨረሻው ዘመን ውጥረቶች ሲጨምሩ፥ ስደቱም በዚያ ልክ ስለሚጨምር፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊዘጋጅ ይገባዋል (1ኛ ጴጥ. 4 ከቁጥር 12 ጀምሮ)። ዓለም «ድሀ ክርስቲያኖች»ልትለን ብትችልም፥ ጻሩ ግን በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ባለጸጋዎች ነን!

ጴርጋሞን - ከዓለም ጋር የምትስማማ ቤተ ክርስቲያን (ራእይ 2፥12-17)

«በትንሹ እስያ ታላቋ ከተማ» የተባለችው ጴርጋሞን ለቄሳር መታሰቢያነት የተሠራው የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ የሚገኝባት ስትሆን፥ ንጉሣዊ ኑፋቄ በማስፋፋቱ በኩል የአክራሪነት ሚና ትጫወት ነበር። በቁጥር 13 ላይ «የሰይጣን ዙፋን» የተባለው ይኸው ሳይሆን አይቀርም። በተጨማሪም ከተማዪቱ የፈውስ አምላክ እንደሆነ ለሚታመነው «ኤስኩላፕዩስ» ለተባለ ጣዖት የተሰጠ ቤተ መቅደስ ነበራት። የዚህም ጣዖት መለያ፤ በበትር ላይ የተጠመጠመ እባብ ነበር። (ዛሬም ቢሆን በሕክምና ምልክት ሆኖ የምንገለገልበት ነው።) በእርግጥ ሰይጣንም እንደዚሁ በእባብ ተምሳሌትነት ተገልጿል (2ኛ ቆሮ. 11፥3፤ ራእይ 12፥9፤ 20፥2)።

ሙገሳ (2፥13)- በሰሞርኔስ እንደሚገኙ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው፥ በጴርጋሞን የነበሩ አማኞችም የስደት መከራ የደረሰባቸው ሲሆን፥ ከመካከላችውም አንዱ ለእምነቱ ሲል ሞቶ ነበር። ከጠበቀ መከራ ባሻገር፥ ይህች ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር እውነተኛ ሆና ቆይታለች። ምዕመናኗ ዕጣን ወደ መሠዊያው በመወርወር፥ «ቄሳር ጌታ ነው!» ለማለት አልፈለጉም ነበር። እንደዚሁም ሰይፍ የሮም ባለሥልጣን ምልክት ስለነበር፥ ጌታ «በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው» (ቁ. 12) በማለት ስለራሱ የሰጠው መግለጫ ያለጥርጥር አማኞቹን አበረታቷቸው ነበር። ቤተ ክርስቲያን ከሮም ሰይፍ ይልቅ የክርስቶስን ሰይፍ መፍራቷ የበለጠ አስፈላጊ ነበር (ቁ. 16)።

ወቀሳ (2፥14-15) - ስደትን ተቋቁመው ከመጽናታቸው ባሻገር፥ በጴርጋሞን የነበሩ አማኞች በጌታ ፊት ያለነቀፋ አልነበሩም። ሰይጣን እንደሚያገሳ አንበሳ በመምጣት ሊያጠፋቸው ባይችልም (1ኛ ጴጥ. 5፥8)፤ ዳሩ ግን እንደ ተንኮለኛ እባብ ተጽእኖውን ከማስፋፋት አልቦዘነም ነበር። ከዓለም ጋር የሚወዳጁ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ኅብረት ሰርገው ገብተው ነበርና፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምህሮዎቻቸውንና ልምምዶቻቸውን ጠላው።

እነዚህ ሰርጎ-ገቦች «ኒቆላውያን» ተብለው የሚጠሩ ሲሆን፥ ቀደም ብለን በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ጥናታችን አግኝተናቸዋል (2፥6)። የስሙ ትርጉም «ሕዝብን መግዛት» ማለት ሲሆን፥ ትምህርታቸውም «የበለዓም

ትምህርት» ይባላል (2፡14)። በለዓም የሚለውም የዕብራይስጥ ስያሜ ምናልባት ከኒቆላውያን ጋር ተመሳሳይ ነው። ትርጒሙም «የሕዝብ ጌታ» የሚል ነው። የሚያሳዝነው፥ ይህን ዓይነት ትምህርት የሚከተሉ ክርስቲያን ነን ባዮች ሸክሙን በሕዝቡ ላይ «በመጫን» ወደ ጥፋት መርተዋቸው ነበር።

የበለዓምን ታሪክ መረዳት ስለዚህ እየከፋና እየተስፋፋ የሚሄድ ቡድን በበለጠ በትክክል ለመተርጐም ያስችለናል (ዘኍል. 22-25)። በለዓም የእስራኤልን ሕዝብ እንዲረግም ከቀጠረው ባላቅ ገንዘብ ለመቀበል ሲል ስጦታዎቹን ለገንዘብ የሸጠ፥ የለወጠ፥ ነቢይ ነበር። ሆኖም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዳይረግም ከለከለው፥ እንዲያውም እርግማኑን ወደ በረከት ለወጠው! ይህም ሆኖ ባላቅ ለበለዓም ለከፈለው ገንዘብ በቂ ብድራት አግኝቷል። እንዴት? የበለዓምን ምክር በመከተልና ከእስራኤላውያን ጋር በመወዳጀት፥ አይሁዶች በአረማዊ መሠዊያ ዙሪያ አምልኮት እንዲፈጽሙ በማድረግ። «ሊታጠቃቸው ካልቻልህ፥ ከእነርሱ ጋር ግንባር ፍጠር» እንደሚለው የእንግሊዝኛ አባባል መሆኑ ነው።

አይሁዶች በወጥመዱ ውስጥ ወደቁና ብዙዎቹ ለባላቅ «ጥሩ ወዳጆች» ሆኑት። ለጣዖት ከተሠዋው ሥጋ ከመብላታቸውም በላይ፥ እንደ አረማዊ የሃይማኖት ሥርዓቶች የወሲብ ተግባርም ፈጸሙ። እግዚአብሔርን ከማያምኑ ሰዎች ጋር ለመስማማት ባደረጉት ያለመታዘዝ ተግባር ሃያ አራት ሺህ ሰዎች ሞቱ (ዘኍል. 25፡1-9)።

ይህ የጥንታዊ ታሪክ ክፍል ከጴርጋሞን አማኞች ሕይወት ጋር የተዛመደው እንዴት ነበር? የተዛመደበት ምክንያቱ ከዚያ ቤት ክርስቲያን ውስጥ አንዱ ቡድን፥ «ከሮም ጋር መወዳጀቱ ምንም ስሕተት አይደለም። አንዲት እፍኝ ዕጣን ወደ መሠውያው በመጨመር፥ ለቄሳር ያለንን ታማኝነት ብናረጋግጥ ምን ይጎዳናል?» ይል ነበር። አንቲጳስ ከሮም ጋር ለመወገን ባለመፈለጉ በመስዋዕትነት ሲያልፍ፥ ሌሎች ግን «ቀላሉን መንገድ» በመምረጥ ከሮም ጋር ተባበሩ።

«ለጣዖት የታረደው» የሚለው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 8 እና 10 ከጠቀሰው አሳብ ጋር አንድ ዓይነት አይመስልም። በዚህ ሥፍራ ወቀሳው እንደ ጳውሎስ ዕድል የሚሰጥ ሳይሆን ምንም የከፈተው በር አልነበረም። ጌታ በጴርጋሞን የነበሩትን ክርስቲያኖች የወቀሰው «ቄሳር ጌታ ነው!» በማለት ስለፈጸሙት የ«መንፈሳዊ አመንዝራነት» ኃጢአት ነው። እርግጥ

ይህ ከሮም ጋር የመወዳጀቱ ተግባር በሙያ ማኅበራት ውስጥ ተቀባይነት ከማስገኘቱም፥ ከሮም የስደት አበሳም ቢያሳርፋቸውም፥ ዳሩ ግን ምስክርነታቸውንና አክሊላቸውን አሳጥቷቸዋል።

ዛሬም አማኞች መንፈሳዊነት ከጎደለው ዓለም ጋር በመስማማት፥ የግል ጥቅም ለማግኘት በተግባር ይፈተናሉ። «ጴርጋሞን» የሚለው ስም «ያገባ» ማለት ሲሆን፥ እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን «የክርስቶስ እጮኛ» እንደሆነችና በንጽሕናም ልትኖር እንደሚገባ ያስታውሰናል (2ኛ ቆሮ. 11፡1-4)። በራእይ ውስጥ ወደ በኋላ እንደምንመለከተው፥ የአሁኑ የዓለም ዘይቤ እንደረከሰች ጋለሞታ ተደርጎ የተገለጸ ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያን እንደንጽሕት ሙሽራ ሆና ቀርባለች። ከመከራ ለማምለጥ ወይም አንድን ነገር ለማግኘት ብቻ ከዓለም ጋር የሚስማማ ጉባኤ ወይም ክርስቲያን ግለሰብ «መንፈሳዊ አመንዝራነትን» በመፈጸም ለጌታ ታማኝ አለመሆኑን ያሳያል።

ምክር (2፡16-17) - ምንም እንኳ አንቲጳስ በሮም ሰይፍ የተሰየፈ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን በጴርጋሞን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ንስሐ ካልገባች የክርስቶስ ሰይፍ - ቃሉ (ዕብ. 4፡12) ይጠብቃት ነበር። ይህም የሚያመለክተው የጌታን ምጽአት ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል በምትተላለፍበት ጊዜ የሚመጣባትን ወቅታዊ ፍርድ ነው። ጌታ ራሱን እንደ «ስለታም ሰይፍ» አድርጎ ስላቀረበ (ራእይ 2፡12)፥ ቤተ ክርስቲያን የዚህን ነገር አደገኛነት መገንዘብ አይከብዳትም ነበር።

እንደ ቀደሙት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ፥ ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን በተላለፈው ማሳሰቢያ መዝጊያ ላይ የቀረበው ልመና ግለሰብን የሚመለከት ነው - «ጆሮ ያለው ... ድል የሚነሣ» (ቁ. 17)። እግዚአብሔር እስራኤላውያን በምድረ በዳ ውስጥ በሚጓዙበት ጊዜ መና በማውረድ የመገባቸው ሲሆን፥ አንድ ማድጋ መና በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ ተቀምጦ ነበር (ዘጸ. 16፡32-36፤ ዕብ. 9፡4)። «ለጣዖት የተሠዋውን» በመመገብ ፈንታ (ራእይ 2፡14)፥ የጴርጋሞን አማኞች በቃሉ አማካኝነት በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን የሕይወትን እንጀራ መረጡ (ዮሐ. 6 ከቁጥር 32 ጀምሮ፤ ማቴ. 4፡4)። በጴርጋሞን ሥልጣን ከነበረው የሰይጣን ዙፋን በተቃራኒ (ራእይ 2፡13)፥ የቃል

ኪዳኑ ታቦት የእግዚአብሔር ዙፋን ነበር [2ኛ ሳሙ. 6:2፤ ኢሳ. 37:16፤ መዝ. (80):1]።

በዚያን ዘመን፥ በችሎት ፊት የቀረበው ሰው በነፃ መለቀቁን ለማሳወቅ ዳኛው ነጭ ድንጋይ በዕቃ ውስጥ ይጨምር ነበር። እንዲሁም ደግሞ ነጭ ድንጋይ ወደ ግብዣ ቤት ለመግባት እንደ «ቲኬት» ሆኖ ያገለግል ነበር። በመንፈሳዊ ሁኔታ ሁለቱም ከአማኙ ሕይወት ጋር ይዛመዳሉ። በክርስቶስ በማመን ጻድቅ መሆኑ የታወጀለት ሲሆን፥ ዛሬ ከክርስቶስ ጋር ይበላል (3:20) - በክብርም አብሮት ይመገባል (19:6-9)።

ትያጥሮን - ብልሹ ቤተ ክርስቲያን (2:18-29)

ከመልእክቶቹ ሁሉ እጅግ ረዥሙ መልእክት የተላከው ከሁሉም አነስተኛ በሆነች ከተማ ለነበረችው ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ነበር። ትያጥሮን የወታደር ጦር ሠፈር የሚገኝባት ከተማ ከመሆኗም፥ በርካታ የሙያ ማኅበራት የሚገኙባት የንግድ ማዕከልም ነበረች። ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል፥ የሙያ ማኅበራት በሚገኙበት ጊዜ ሁሉ፥ የቀድሞዋ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱ አስከፊ ጠላቶች - ማለትም የጣዖት አምልኮና የወሲብ ኃጢአት አብረው ይገኙ ነበር።

ከተማይቱ «አፖሎ» በተባለው የ«ፀሐይ አምላክ» ልዩ መቅደስ ትታበይ ነበርና፥ ጌታም ራሱን «የእግዚአብሔር ልጅ» በማለት ያስተዋወቀው በዚህ ምክንያት ነው (ይህ ማዕረግ በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ያገለገለው በዚህ ሥፍራ ብቻ ነው)። ዮሐንስ ለዚህ ማኅበረ-ምዕመናን የጠነከረ ማስጠንቀቂያና ፍርድ ያለበትን መልእክት ማስተላለፍ ነበረበት። ይህም የጌታን ዓይኖችና እግሮች ገለጻን ያመለክታል።

ሙገሳ (2:19) - የትያጥሮን አማኞች አገልግሎት ይበዛባቸው ነበር። ለሌሎች ሲሉ ራሳቸውን ሠውተው ያገለግሉ ነበር። በተጨማሪም ሥራቸው እያደገ ከመሄዱም፥ በግልጽ ይታይ እንደነበረው በፍቅር፥ በእምነትና በትዕግሥት በመረጋገጡ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ «ሃይማኖታዊ ተግባር» ብቻ እንደምታከናውን ተቆጥራ አልተወቀሰችም።

ወቀሳ (2:20-23) - ዳሩ ግን ጌታ በትያጥሮን ጉባኤ ውስጥ ሌሎች የሚጋለጡና የሚኮነኑ ተግባራት ማግኘቱ አሳዛኝ ነው። የቱን ያህል የፍቅርና የመሥዋዕትነት ተግባር ቢፈጸምም፥ ለክፉት መሸፋፈኛ ወይንም

መካከሻ ሆኖ መቅረብ አይችልም። ቤተ ክርስቲያኒቱም በሕዝቡ ላይ ተጽዕኖ በማድረግ ከዓለም ጋር እንዲስማሙ ታደርግ ዘንድ የውሸተኛ ነቢያትን አገልግሎት ተቀብላ ነበር። መቼም «ኤልዛቤል» እንደሚለው የጎደፈ ስም ዓይነት ወላጅ ለልጇ ስለማያወጣ፥ ይህች ሴት በእርግጥ በዚህ ስም የምትጠራ አይመስልም። ስለዚህ ይህ ስም ተምሳሌታዊ ነው - ኤልዛቤል እስራኤላውያን በሃይማኖታዊ ሥርዓቶቻቸው ላይ የበአልን አምልኮ እንዲጨምሩ ያደረገች ጣዖት አምላኪ የንጉሥ ሚስት ነበረች (1ኛ ነገሥት 16-19)። ማራኪው የኤልዛቤል ትምህርት ጌታ በጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ከኮነነው «የበለዓም ትምህርት» ጋር ተመሳሳይ ነበር (ራእይ 2፡14)። ክርስቲያኖች ሥራቸውን ወይም ሕይወታቸውን ላለማጣት፥ እንዴት ከሮም ሃይማኖትና የሙያ ማኅበራት ልምምዶች ጋር ተስማምተው መኖር እንደሚችሉ ታስተምር ነበር።

በኤፌሶንና በትያጥሮን የነበሩትን አብያተ ክርስቲያናት ማነጻጸሩ መልካም ነው። የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በፍቅሯ ቀዝቅዛ ሳለ፥ በሐሰተኛ አስተማሪዎች ላይ ለመፍረድ ታማኝ ነበረች፤ ዳሩ ግን በትያጥሮን ጉባኤ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በፍቅራቸው የበረቱ ቢሆንም፥ ሆኖም፥ ሐሰተኛ ትምህርትን በቸልታ ያልፉና ይታገሡ ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለቱንም አክራሪ አቋሞች ማስወገዱ ተገቢ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ሚዛን «እውነትን በፍቅር መናገር» ሲሆን (ኤፌ. 4፡15)፥ እውነተኛ ትምህርትን አለመውደድና ከዓለም ጋር መስማማትን መምረጥ ግን፥ ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊዎች ናቸው።

የትያጥሮን ቤተ ክርስቲያን ከፉን መታገሥ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ትዕቢተኛና ንስሐ ለመግባት የማትፈልግ ነበረች። ጌታ ለሐሰተኛይቱ ነቢይት ንስሐ የምትገባበትን ጊዜ ቢሰጣትም፥ ፈቃደኛ አልሆነችም። አሁን ለተከታዮችዋ ንስሐ የሚገቡበትን ዕድል እየሰጣቸው ነበር። እሳትማ ዓይኖቹ ልባቸውንና ኩላሊታቸውን መርምሮ ነበርና፥ ከተናገረው ምንም ዓይነት ስሕተት ሊገኝበት አይችልም ነበር።

እንዲያውም ጌታ፥ «አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ» ክፉን እንዳይታገሡ ይህንኑ ጉባኤ ምሳሌ እንደሚያደርግ ዝቷል። በኤልዛቤልና በልጆችዋ (በተከታዮችዋ) ላይ የመከራና የሞት ፍርድ ይሰጥ ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ጣዖትን ማምለክና ከዓለም ጋር መስማማት ለጋብቻ ቃል ኪዳን እንደ አለመታመንና ዝሙትን እንደመፈጸም ያህል የሚቆጠር

ነው (ኤር. 3 ከቁጥር 6 ጀምሮ፤ ሆሴዕ 9፡ ከቁጥር 1 ጀምሮ)። የኤልዛቤል የኃጢአት አልጋ የመቅሠፍት አልጋ መሆኑ የማይቀር ነበር! «በሞት እገድላቸዋለሁ» የሚለው «በመቅሰፍት እገድላቸዋለሁ» ማለት ነው። እግዚአብሔር በሐሰተኛዋ ነቢይትና በተከታዮችዋ ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፍርድን ይገልጽ ነበር።

ምክር (2፡24-29) - በጉባኤው ውስጥ ለጌታ ያልታመነው ሁሉም አማኝ ስላልነበር፥ ለእነዚህ ለታማኞቹ ጌታ የተለየ ቃል ነበረው። እነዚህ ታማኞቹ፥ ክርስቶስ «የሰይጣን ጥልቅ ነገር» ከሚለው ከኤልዛቤልና ከተከታዮችዋ ሐሰተኛ ትምህርትና ከዓለም ጋር የመስማማት ልምምድ ራሳቸውን ለይተው ነበር። (የጥልቅ ነገር ተነጻጻሪን ከ1ኛ ቆሮ. 2፡10 ተመልከት)። ጌታ የሚጠይቀው የተለየ ነገር አልነበረውም፤ ከፉውን በመቃወም ተግባራቸው ብቻ እንዲጸኑ ይፈልግ ነበር። «እስከመጣ ድረስ» የሚለው ክርስቶስ ለሕዝቡ የሚመለስበትን ጊዜ የሚያመለክት ሲሆን፥ በዚያን ጊዜም ለታማኝነታቸው ይሸልማቸዋል (3፡3፤ 16፡15፤ 22፡7፥17፥20 ተመልከት)። በራእይ ውስጥ ጌታ ለቤተ ክርስቲያኑ ስለ መምጣቱ ማለትም ስለ ንጥቀት ሲጠቅስ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነው (1ኛ ተሰ. 4፡13-18 ተመልከት)። በአንጻሩ፥ በራእይ 1፡7 ላይ የተጠቀሰው፥ ክርስቶስ ጠላቶቹን ለማሸነፍና መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር በፍርድ መመለሱን ያመለክታል (ራእይ 19፡ ከቁጥር 11 ጀምሮ)።

በትያጥሮን የነበሩ አማኞች በአሕዛብ ላይ ሥልጣን እንደሚሰጣቸው የተስፋ ቃል ተገብቶላቸዋል፤ ይህም ምናልባት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከክርስቶስ ጋር የመኖራቸውንና የመግዛታቸውን እውነት የሚያመለክት ይሆናል (20፡4 ተመልከት)። ጌታ መንግሥቱን በዓለም ላይ በሚመሠርትበት ጊዜ፥ ፍጹም ፍትሕ የሰፈነበት የጽድቅ መንግሥት ይሆናል። በብረት በትር ይገዛቸዋል! (መዝ. 2፡8-9)። በመሆኑም ዓመፀኞች እንደሸክላ ዕቃ በቀላሉ ይሰበራሉ!

ኢየሱስ ክርስቶስ «የሚያበራ የንጋት ኮከብ» ነው (ራእይ 22፡16)። በቁጥር 28 ላይ የሚገኘው የተስፋ ቃል እንደሚያመለክተው፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እጅግ በቀረበ ሁኔታ ከክርስቶስ ጋር አንድነት ይፈጥሩና እርሱም «የእነርሱ ወገን» ይሆናል። ይህም ሆኖ፥ በዚሁ አጋጣሚ፥ ለራሱ መንግሥት ለፈለገውና አንድ ጊዜ ወድቆ ከሰገደለት

የዓለምን መንግሥታት ለክርስቶስ እንደሚሰጥ ስለተናገረው ሰይጣን፥ በእጅ አዙር መንገድ የተጠቀሰ ነገር ሳይኖር አይቀርም (ማቴ. 4:8-11)። በኢሳይያስ 14:12 ሰይጣን ማለትም «ሉሲፈር» በዕብራይስጥ ትርጉሙ «የንጋት ልጅ፥ አጥቢያ ኮከብ» ተብሎ ተገልጿል። በትያጥሮን ከዓለም ጋር የሚስማሙ ሰዎች ወደ ጽልመትና ሞት የሚጠራውን «የሰይጣንን ጥልቅ ነገር» ይከተሉ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የእግዚአብሔር አሸናፊዎች በንጋት ኮከብ ብርሃን ይመላለሳሉ።

ለአብያተ ክርስቲያናት የተላለፉትን እነዚህን አራት መልእክቶች በምታጤንበት ጊዜ፥ ዛሬም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚያንዣብቡትን አደጋዎች ልትመለከት ትችላለህ። እንደ ኤፌሶን ቀናዒና ንጹሕ ትምህርት ያለን ልንሆንና ዳሩ ግን ለክርስቶስ የነበረንን መሰጠት ልናጣ እንችላለን። ወይም፥ እንደ ትያጥሮን ፍቅራችን እያደገ የሚሄድ ሆኖ፥ ዳሩ ግን የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና ለማስጠብቅ አስፈላጊ የሆነውን የመለየት ተግባር እናጣ ይሆናል (ፊልጵ. 1:9-11 ተመልከት)። ደግሞም እንደ ጴርጋሞንና ትያጥሮን ክፉውን አብዝተን በመታገሥ፥ ጌታን ልናሳዝንና ፍርዱን ልንጋብዝ እንችላለን።

ምናልባት ሰምርኔስን ከአራቱ የበለጠች መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያን አድርገን እንመርጥ ይሆን? ላይሆን ይችላል፤ ጌታ ግን መርጧታል! ልብን የመመርመር ብቃት ያለው ጌታ ብቻ ስለሆነ (1ኛ ቆሮ. 4:5)፥ እኛም በተሳሳቱ መመዘኛዎች በመመራት፥ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ላለመፍረድ መጠንቀቅ አለብን።

ጌታ (ከሰምርኔስ በቀር) ለእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የሰጠው ምክር፥ «ንስሐ ግባ! አእምሮህን አስተካክል ወይንም አስተሳሰብህን ቀይር!» የሚል ነበር። ንስሐ መግባት የሚኖርባቸው ከደኅንነት ርቀው የጠፉ ኃጢአተኞች ብቻ ሳይሆኑ፥ የማይታዘዙ አማኞችም ጭምር ናቸው። ንስሐ ካልገባንና ከሕይወታችንና ከጉባኤያችን ኃጢአትን ካላስወገድን፥ ጌታ ሊፈርድብንና መቅረዛችንን ሊወስደው ይችላል (ራእይ 2:5)። አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቀስ በቀስ እምነቷን ስትተውና ለክርስቶስ የነበራትን ምስክርነት ስታጣ ማየት ምንኛ ያሳዝናል!

«መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ!»

- 3 -

ክርስቶስና አብያተ ክርስቲያናት - ክፍል 2

ራእይ 3

እነዚህ ከክርስቶስ የተላለፉ መልእክቶች እንደ መጀመሪያው ምዕተ-ዓመት ትውልድ ሁሉ፥ የእኛንም ዘመን ስለሚመለከቱ፥ መንፈስ ቅዱስ ቀደም ሲል ለአብያተ ክርስቲያናት የተናገረውን፥ እኛም በዛሬው ጊዜ በመስማት ላይ እንገኛለን። አብያተ ክርስቲያናት ሰዎች ስለሆኑና የሰዎችም ባሕርይ ስላልተለወጠ፥ ጥናታችንን በምናካሂድበት ጊዜ፥ እነዚህን ደብዳቤዎች እንደ ጥንታዊ ቅርሶች ልንመለከታቸው አይገባም። በአንጻሩ፥ እነዚህ መልእክቶች ራሳችንን የምንመለከትባቸው መስተዋቶች ናቸው።

ሰርዴስ - ደካማይቱ ቤተ ክርስቲያን (ራእይ 3፡ 1-6)

የሊድያ ርእሰ ከተማ የነበረችው ጥንታዊት ሰርዴስ በጣም የታወቀች ከተማ ነበረች። ከኤፌሶን በስተምሥራቅ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከመገኘቷም፥ የአምስት ዐበይት ጎዳናዎች መገናኛ በመሆኗ ታላቅ የንግድ ማዕከል ለመሆን በቅታ ነበር። እንደዚሁም በቀላሉ ከሞላ ጎደል ከማይበገር ኮረብታ ላይ በመመሥረቷ ወታደራዊ ማዕከልም ነበረች። የሰርዴስ ከተማ ተራራ ከዐበይት መንገዶች 1500 ጫማዎች ያህል ከፍ ብሎ ስለሚገኝ፥ ለመዝለቅ የሚያዳግት የተፈጥሮ ምሽግ ነበር። በከተማይቱ ውስጥ ዋንኛው ሃይማኖት በሞትና ዳግም ልደት አሳብ ላይ የተመሠረተ የ«አርጤምስ አምልኮ» ሲሆን፥ ይህም ከ«ተፈጥሮ ኑፋቄዎች» አንዱ ነው።

በተጨማሪም ከተማይቱ በሱፍ ልብስ አምራችነቷ የምትታወቅ ስትሆን፥ ይህም ክርስቶስ በዚያ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ባስተላለፈው መልእክት ውስጥ ተንጸባርቋል። ሆኖም በዚያን ዘመን ከተማይቱ በቀድሞ ዝናዋ ብቻ በመሞካሸት የምትኖር ከመሆኗም፥ ቤተ ክርስቲያኒቱም እንደከተማይቱ አስመሳይ መሆኗ አሳዛኝ ነገር ነው - በስም ብቻ ሕያው ነበረች።

ለሰርዴስ የተላለፈው መልእክት በቀደመው ክብራቸው ለሚኖሩ «ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት» ሁሉ ማስጠንቀቂያ ነው። ዶክተር ቫንስ ሐቨኔር ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ አገልግሎቶች በአራት ደረጃዎች ማለትም በሰው፥ በእንቅስቃሴ፥ በማሽን፥ ከዚያም በመታሰቢያ ሐውልት ደረጃ ውስጥ እንደሚያልፉ አስገንዝበውናል። ሰርዴስም በመጨረሻው በ«ሐውልት» ደረጃ ላይ የምትገኝ ብትሆንም፥ ዳሩ ግን አሁንም ተስፋ ነበራት!

ይህም የሆነው ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ስለሆነና አዲስ ሕይወት ለማምጣት ስለሚችል ነበር። ራሱንም የገለጸው በሰባት መናፍስትና በሰባት ከዋክብት እንደሚመላለስ አድርጎ ነው። ያለው አንድ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ሲሆን (ኤፌ. 4፡4)፥ ቁጥር ሰባት የሚያመለክተው ፍጹምነትንና ምልዓትን ነው። መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ሕይወትን ይሰጣል - ለሰርዴስ ሰዎችም የሚያስፈልገው ይኸው ሕይወት ነው። ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት እንደ ሰባት የእሳት መብራቶችና (ራእይ 4፡5) ሁሉን እንደሚመለከቱ ሰባት ዓይኖች ተገልጸዋል (5፡6)።

ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ሰው ሠራሽ መርሐ-ግብር ሕይወት የመስጠቱ ጉዳይ፥ አንድ የ«ሰርከስ» ትዕይንት አቅራቢ የሞተን ሰው ለማስነሣት ከሚያደርገው ከንቱ ሙከራ ዓይነት የተሻለ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው በዕለተ-በዓለ ኀምሳ መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ በመሆኑ (የሐዋ. 2)፥ ሕይወቷ የሚመጣው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ በሚያዝንበት ጊዜ፥ ቤተ ክርስቲያን ሕይወትና ኃይል ታጣለች። የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ኃጢአታቸውን ተናዝዘው፥ ከእግዚአብሔር እና እርስ በርሳቸው ስምምነትን ሲፈጥሩ፥ መንፈስ ቅዱስ አዲስ ሕይወትን ያመጣል - መነቃቃትም ይሆናል!

እንዲሁም ክርስቶስ የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች የሆኑትን ሰባቱንም ከዋክብት ይቆጣጠራቸዋል (ራእይ 1፡20)፤ ምናልባት ይህ መጋቢዎችን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም። አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የምትሞተው በመጋቢዋ ጥፋት በመሆኑ፥ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ያንን ኮከብ በማስወገድ በቦታው ሌላ መተካት ያስፈልጋል።

ለሰርዴስ አማኞች የቀረበ ምንም ዓይነት የሙገሳ ቃል የለም። እንዲሁም መታረም የሚገባው ምንም ዓይነት የእምነት ጉዳይ አልተጠቀሰም። ስለ ተቃውሞ ወይም ስደትም የተገለጸ ነገር የለም። ቤተ

ክርስቲያኒቱ በቀድሞው ዝናዋ ብቻ ተመቻችታና ረክታ እንደመኖር፥ ምናልባትም በስደት ብትፈተን ኖሮ የተሻለ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴም ባሳየች ነበር። በምትኩ ግን ከእውነት የራቀ ዝና፥ ከኃይል የራቀ ቅርፅ ነበራት። እንደ ከተማይቱ ሁሉ፥ የሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን በቀድሞ ዝናዋ እየተመካች፥ በወቅቱ የደረሰባትን ውድቀት ዘንግታ ነበር።

እንዲያውም፥ ያው የተዳከመው የእድገት ደረጃቸው እንኳን ለሞት ተቃርቦ ነበር። ለምን? ምክንያቱም አማኞቹ አንቀላፍተው ነበርና ነው። በረዥም ታሪኳ ውስጥ፥ የሰርዴስ ቅጥር ሁለት ጊዜ የተወረረ ሲሆን፥ በሁለቱም ጊዜ ወረራው የተፈጸመው ወታደሮቹ የጥበቃ ሥራቸውን በታማኝነት ባለመፈጸማቸው ነበር። በተመሳሳይ ሁኔታ ጠላት ወደ ቤተ ክርስቲያን የመግቢያ ቀዳዳ የሚያገኘው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምዕመናን ባገኙዋቸው በረከቶች ሲደላደሉና ስለ አገልግሎታቸው «ጥጋብ» ሲሰማቸው ነው።

በሰርዴስ የነበረው ጉባኤ ለከተማይቱ ጠንካራ ምስክርነት አላቀረበም ነበር። የጠላትን ግዛት ስላልወረሩ፥ ስደትም አልደረሰባቸውም ነበር። ብዙውን ጊዜ ግጭት ከሌለ፥ እንቅስቃሴም የለም። በሰርዴስ ከደኅንነት ርቀው የነበሩ ሰዎች፥ ቤተ ክርስቲያኒቷን አደገኛነትም ሆነ ማራኪነት የሌላቸው የተከበሩ ሰዎች ቡድን አድርገው ይመለከቷት ነበር። ምዕመናኗ የሚሞት ምስክርነትና የሚፈራርስ አገልግሎት ይዘው በጭምትነት የሚኖሩ ነበር።

ጌታችን ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠው ምክር የጀመረው፥ «የነቃህ ሁን!» በሚል ቃል ነው (ሮሜ 13፡ ከቁጥር 11 ጀምሮ ተመልከት)። ቅጥር ጠባቂዎቹ «ወታደሮች» አንቀላፍተው ነበር። ወደ ሞት የተቃረበችን ቤተ ክርስቲያን ለማዳን የመጀመሪያው እርምጃ አንድ ነገር እንደተበላሸ በትክክል መረዳቱ ነው። አካሉ ደህና ከሆነ፥ ዕድገት፥ ጥገና፥ መራባትና ኃይል አለ፤ እነዚህ ነገሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከታጡ፥ ያች ቤተ ክርስቲያን አንድም እየሞተች ነው ካልሆነም ቀደም ብላ ሞታለች።

ጌታ ንስሐ ካልገቡ መጥቶ መቅረዛቸውን እንደሚወስድ በመግለጽ፥ ለኤፌሶን ቅዱሳን ማስጠንቀቂያ ሰጥቷል (ራእይ 2፡5)። ለጴርጋሞን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ መጥቶ በመንፈስ ሰይፍ እንደሚወጋቸው አስጠንቅቋል (2፡16)። የሰርዴስ አማኞች ትእዛዛቱን የማይከተሉ ከሆነ፥ በተዘናጉበት

ጊዜ እንደ ሌባ እንደሚመጣባቸው አስጠንቅቋቸው ነበር - ይህም ፍርድ መሆኑ ነው።

ይሁንና፥ በሞት ላይ በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳን ሳይቀር ራሳቸውን ለጌታ የሰጡ ጥቂት ሰዎች ይኖራሉ። የሰርዴስ ክርስቲያኖች ደካማም ቢሆኑ፥ ሕይወት ነበራቸው። ሥራዎቻቸውም መሆን እንደሚገባችው ባይሆኑም፥ እንደነገሩ ይሠሩ ነበር። ጌታም በበለጠ ተንቀሳቅሰው እንዲጠናከሩ እንጂ፥ ቤተ ክርስቲያኒቱ ደካማ በመሆኗ ሥራቸውን እርግፍ አድርገው እንዳይተው መከሯቸዋል። ሕይወት ባለበት ስፍራ ተስፋ አለ!

እነዚህ ራሳቸውን ለጌታ የሰጡ የክርስቲያን ቅሪቶች ከሌሎቹ የሚለዩት እንዴት ነበር? ልብሳቸውን አላረከሱም ነበር (ቁ. 4)። የመቅደስ አምላኪዎች የቆሸሸ ልብስ ለብሰው ወደ አማልክቶቻቸው እንደማይቀርቡ አንዳንድ ጥንታዊ መረጃዎች ያስረዳሉ። በሰርዴስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩትም ቅሪቶች በአካባቢያቸው ከነበረው የአረማውያን ማኅበረሰብ ጋር ካለመስማማታቸውም በላይ፥ በራስ የመርካት ዝንባሌም አላደረባቸውም ነበር። የወደፊቱን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የያዙት እነዚሁ ራሳቸውን ለጌታ የሰጡ ጥቂቶቹ መንፈሳዊ ቅሪቶች ነበሩ።

«ንቃ! እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደሰማህ አስብ! ጠብቀውም! ንስሐም ግባ!» ይህ የመነቃቃት መመሪያ (ፎርሙላ) ነው። መንፈሳዊ ቅርሳችንን ከጥቃት መከላከል ቢኖርብንም፥ ዳሩ ግን በኖራ ልንለስነው አይገባም። ለእምነት እውነተኛ መሆንና ትልቅ ታሪክ መሥራቱ ብቻ አይበቃም - ያ እምነት ሕይወትንና ሥራዎችን ማፍራት አለበት።

በቁጥር 5 ላይ «በነጭ ልብስ ይጎናጸፋል» የሚለው የተስፋ ቃል፥ በተለይ የሱፍ ልብሶች በሚሠሩባት ከተማ ለሚኖሩ ሰዎች የጎላ ትርጉም ይሰጥ ነበር። እንዲሁም ዜግነት ከፍተኛ ግምት በሚሰጥበት በሮም መንግሥት ለሚኖሩ ሰዎች (የሐዋ. 22፡24-30 ተመልከት)፥ ስለ ስም መደምሰስ የሚናገረውም ዐረፍተ ነገር ክብደት ይኖረዋል።

በዚህ አጋጣሚ እውነተኛ አማኝ ደኅንነቱን ሊያጣ እንደሚችል የሚያስጠነቅቅ ነገር ተጠቅሶ ይሆን? አይመስለኝም። የእግዚአብሔር የሕይወት መጽሐፍ፥ ኃጥአንንና ጻድቃንን ጨምሮ፥ የሕያዋንን ሁሉ ስሞች ይይዛል [መዝ. (69)፡28]። ራእይ 13፡8 እና 17፡8

እንደሚያመለክቱት፥ የዳኑት ሰዎች ስሞች በዚያው መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉት ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ - ማለትም ምንም ዓይነት ክፉም ሆነ በጎ ምግባር ሳይከውኑ በፊት ነው። በእግዚአብሔር ጸጋ፥ ከዘመን ጅማሬ በፊት በክርስቶስ ተመርጠዋል (ኤፌ. 1፡4፤ ማቴ. 25፡34 ተመልከት)።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ስሞቻቸው «በሰማያት ስለተጻፉ» ደስ እንዲሰኙ ነግሯቸዋል (ሉቃ. 10፡20)። የግሪኩ ግሥ፥ «ስሞቻችሁ በሰማያት ስለተጻፉና በዚያውም ለዘለቄታው ተመዝግበው ስለሚኖሩ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ኢየሱስ በዚህ ወሳኝ ጉዳይ ላይ ከራሱ ጋር ይጻረራርል ለማለት አይቻልም።

የአማኞች (የምርጦች) ስሞች ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የተመዘገቡ ከሆነና እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የሚያውቅ ከሆነ፥ እንግዲህ አንድ ቀን በስሕተተኛነቱ ወድቆ ከመጽሐፉ የሚፋቀውን ሰው ለምን ይመዘግበዋል? በሰማይ መዝገብ ውስጥ የተመዘገብነው ዳግም ስለተወለድን ነው (ዕብ. 12፡23)፤ እንዲሁም አንድ ልጅ ምንም ያህል ዓመፀኛ ቢሆን፥ ዳግም «የመወለድ» ምንም ዕድል ሊኖረው አይችልም።

የማያምኑት ሰዎች ሲሞቱ፥ ስማቸው ከመጽሐፍ ይፋቅና በመጨረሻው የፍርድ ዕለት በመጽሐፉ ውስጥ የአማኞች ስም ብቻ ይቀራል (ራእይ 20፡12-15)። በመሆኑም ከዚያን ወዲያ መጽሐፉ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የዳኑት ሰዎች ስም ብቻ ስለሚገኝበት፥ «የበጉ ሕይወት መጽሐፍ» ይሆናል። ሌሎች ስሞች ሁሉ ይደመሰሳሉ፤ ይህም እግዚአብሔር በማንኛውም እውነተኛ ልጁ ላይ የማይፈጽመው ነው (ዘጸ. 32፡32፤ ሮሜ 9፡3 ተመልከት)። መጽሐፉ የሕይወት መጽሐፍ ስለሆነ፥ ከደኅንነት ርቀው የጠፉ ኃጢአተኞች «ሙታን» ናቸው (ኤፌ. 2፡1)።

በዚህ ስፍራ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ በአብያተ ክርስቲያናታችን ምቾት እንዳይጫነን፥ አለዚያ ግን ቀስ በቀስ እየሞትን እንደምንሄድ ነው። ማበረታቻው የቀሩትን ነገሮች ለማጠናከር የሚፈቅዱ ራሳቸውን የሰጡ ቅሬታዎች እስካሉባት ድረስ፥ የትኛዋም ቤተ ክርስቲያን ተስፋዋ እንዳልተሟጠጠ ነው።

ፊልድልፍያ- ታማኝዋ ቤተ ክርስቲያን (ራእይ 3፡7-13)

ብዙ ሰዎች እንደሚያውቁት፥ «ፊልድልፍያ» ማለት «የወንድማማች ፍቅር» ማለት ነው። በመሠረቱ፥ የወንድማማች መዋደድ በጣም አስፈላጊ የሆነ የክርስቲያን መለያ ነው። እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እግዚአብሔር አስተምሮናል (1ኛ ተሰ. 4፡9) - እግዚአብሔር አብ (1ኛ ዮሐ. 4፡19)፥ እግዚአብሔር ወልድ (ዮሐ. 13፡34)፥ እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (ሮሜ 5፡5)። ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔርንና አማኞችን መውደዱ ብቻ በቂ አይደለም - ከደኅንነት ርቆ የጠፋውን ዓለም ልንወድና የማያምኑትን ሰዎች በመስቀሉ መልካም የምስራች ልንደርሳቸው ይገባል። ይህች ቤተ ክርስቲያን ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን በወንጌል የመድረስ ራእይ ነበራትና፥ እግዚአብሔርም በፊታቸው የተከፈተ በር አስቀመጠላቸው።

ፊልድልፍያ ለሮማ መንግሥት ወደ ምሥራቅ ክፍለ ግዛት ደብዳቤዎችን ለመላክ በሚያስችል አማካይ መንገድ ላይ በመገኘቷ ወሳኝ ስፍራ ነበራት - በዚህም ምክንያት «የምሥራቅ በር» ተብላ ትታወቅ ነበር። እንዲሁም በከተማይቱ ውስጥ ከሚገኙ በርካታ መቅደሶች የተነሣ «ትንሿ አቴንስ» ትባል ነበር። ቤተ ክርስቲያኒቱ ያለጥርጥር ከፍተኛ ጠቀሜታ ባለው ስፍራ ተመሥርታ ነበር።

በአካባቢው የነበረው ብቸኛው ዓቢይ ችግር ስፍራው ለመሬት መንቀጥቀጥ መጋለጡ ነበር። ፊልድልፍያ የመልከዓ ምድር ችግር ነበረባትና በ17 ዓ.ዓ. ሰርዴስንና ሌሎች አሥር ከተሞችን ባወደመው ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ተመታ ነበር። ከዚያም ወዲህ፥ ከዜጎችዋ መካከል አንዳንዶቹ ወደ ከተማይቱ ለመመለስ ባለመፈለጋቸው፥ በአካባቢው ገጠርማ ስፍራ ተቀምጠዋል፤ ይህንንም አካባቢ «የተቃጠለ ምድር» በማለት ይጠሩት ነበር። በመሆኑም፥ በወንድማማች ከተማ ውስጥ እምብዛም የተረጋጋ ሕይወት የነበረ አይመስልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለፊልድልፍያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን «ቅዱስ . . . የሆነው» በማለት አቅርቧል። ይህም ከእግዚአብሔር ጋር በቅድስና መተካከሉን የሚገልጽ አባባል ነው - በእርግጥም እርሱ እግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርይ፥ በቃሉ፥ በተግባሩና በዓላማዎቹ ሁሉ ቅዱስ ነው። ቅዱስ እንደመሆኑ፥ ከማንኛውም ነገር የተለየ ነውና ከእርሱ ጋር የሚወዳደር አንዳችም ነገር የለም።

እንዲሁም፥ እርሱ እውነተኛ - ማለትም ቃሉ የማይታበል ፍቱን ነው። እርሱ ምንጭ እንጂ ቅጂ አይደለም - መሠረት እንጂ የሰው ፈጠራ ሥራ ውጤት አይደለም። በዚያን ዘመን በመቶ የሚቆጠሩ ወንድና ሴት አማልክት ቢኖሩም፥ (1ኛ ቆሮ. 8፡5-6)፥ ዳሩ ግን በትክክል እውነተኛ እግዚአብሔር መሆኑን ሊናገር የሚችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነበር።

ሰማዕታት በሰማይ ጌታን ሲጠሩ፥ «ቅዱስና እውነተኛ» ማለታቸውን ልብ ማለቱ ተገቢ ነው (ራእይ 6፡10)። ሙግታቸውም ቅዱስ ስለሆነ በኃጢአት ላይ መፍረድ እንደሚያስፈልገውና እውነተኛም በመሆኑ፥ በግፍ ለታረዱት ሕዝቦች ፍትሕን ሊሰጥ እንደሚገባ ነበር።

እውነተኛና ቅዱስ ከመሆኑም በተጨማሪ በሮችን የመክፈትና የመዝጋትም ሥልጣን አለው። የዚህ መግለጫ ሥረ መሠረት የሚገኘው በኢሳይያስ 22፡15-25 ውስጥ ነው። (ኢሳይያስ እንዳስጠነቀቀው፥) አሦር ይሁዳን ወርራ ሳለ፥ የአይሁድ መሪዎች ሕዝቡን ለመታደግ በእግዚአብሔር ሳይሆን በግብፅ ላይ ይደገፉ ነበር። በዚህም ጊዜ ከነበሩት ከሃዲ መሪዎች አንዱ ሥልጣኑን ለሕዝቡ በጎነት ሳይሆን፥ ለግል ጥቅሙ ያዋለው ሳምናስ ነበር። እግዚአብሔርም ይህንኑ ጉዳይ በመመልከቱ፥ ሳምናስ ከሥልጣን ተወግዶ፥ ታማኙ ኤልያቄም በሥልጣን ቦታው ተተካ። ኤልያቄም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጉዳዮች በሚያስተማምን ሁኔታ የሚያስተዳድር የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስም የሲኦልና የሞት መክፈቻ አለው (ራእይ 1፡18)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ «የተከፈተ በር» የአገልግሎትን ዕድል ያሳያል (የሐዋ. 14፡27፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡9፤ 2ኛ ቆሮ. 2፡12፤ ቈላ. 4፡3)። ክርስቶስ የመከሩ ጌታና የቤተ ክርስቲያኑ ራስ በመሆኑ፥ ሕዝቡ የሚያገለግልበትን ጊዜና ስፍራ የሚወስነው እርሱ ነው (የሐዋ. 16፡6-10)። ክርስቶስ ፊልድልፍያ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰፊ በር ከፍቶላታል።

ይሁንና ምዕመናኗ በዚህ ታላቅ ዕድል ተጠቅመውበት ይሆን? በማሸነፍ ሊያልፏቸው የሚገባ ቢያንስ ሁለት መሰናክሎች ሲኖሩ፥ የመጀመሪያው የራሳቸው ብርታት ማጣት ነው (ራእይ 3፡8)። ይህች ቤተ ክርስቲያን ሰፊ ወይም ጠንካራ ሳትሆን፥ ዳሩ ግን ታማኝ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ለእግዚአብሔር ቃል ታማኞች ሲሆኑ፥ ስሙን ለመሸከም

አልፈሩም ነበር። ቁጥር 10 እንደሚያመለክተው፥ አንዳንድ የተለዩ ፈተናዎችን ታግሠው ታማኝነታቸውን አስመስክረዋል።

የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የሚወስነው፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ ስፋት ወይም ጥንካሬ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በጌታ ጥሪና ትእዛዝ ላይ እምነት መጣሉ ነው። «የእግዚአብሔር ትእዛዛት የእግዚአብሔር የብቃት መንገዶች ናቸው።» ኢየሱስ ክርስቶስ የተከፈተ በር ከሰጣቸው፥ በዚያ ውስጥ ለማለፍ መቻላቸውን ይመለከት ነበር። ይህንንም እውነታ ማርቲን ሉተር በታወቀው መዝሙሩ ውስጥ እንደሚከተለው በግሩም ሁኔታ አስቀምጦታል፡-

ትክክለኛው እውነተኛው

እግዚአብሔር ራሱ የመረጠው

እርሱ ከጎናችን ባይቆም ኖሮ

ጥረታችን መቼ ሰምሮ?

ይልቅ ባጠቃን ነበር ሮሮ!

ሁለተኛው መሰናክል በከተማይቱ የነበሩ አይሁዶች ተቃውሞ ነበር (ቁ. 9)። እኛ ከሥጋና ከደም ጋር ስለማንዋጋ (ኤፌ. 6፡12)፥ በእርግጥም ይህ የሰይጣን ተቃውሞ ነበር። እነዚህ ሰዎች በሥጋ አይሁዶች ሊሆኑ ቢችሉም፥ ዳሩ ግን በአዲስ ኪዳን ግንዛቤ «እውነተኛ እስራኤላውያን» አልነበሩም (ሮሜ 2፡17-29)። የአይሁድ ሕዝብ ያለጥርጥር ትልቅ ውርስ ቢኖራቸውም፥ ዳሩ ግን ይህ ለደኅንነት ዋስትና አይሰጣቸውም (ማቴ. 3፡7-12፤ ዮሐ. 8 ከቁጥር 33 ጀምሮ)።

እነዚህ አይሁዶች የፊልድልፍያን ቤተ ክርስቲያን ይቃወሙ የነበሩት እንዴት ነበር? አንደኛው ነገር፥ የአይሁድ አማኞችን ከምኩራብ በማግለል ነበር። ሌላው መግሪያ ምናልባትም የውሸት ክስ ማቅረብ ይሆናል፤ የማያምኑ አይሁዶች ብዙውን ጊዜ ጳውሎስን ያጠቁት በዚህ መንገድ ነበርና። ሰይጣን ከሳሽ በመሆኑ፥ ሃይማኖታዊ ሰዎች እንኳ በሥራው እንዲረዱትና እንዲተባበሩት በማድረግ ይጠቀማል (ራእይ 12፡10)። በማኅበረሰቡ ውስጥ የመሪነት ሚና ያላቸው ሰዎች ስለአንተ ውሸትን በሚያስፋፉበት ጊዜ፥ ስለ ክርስቶስ መመስከር ቀላል አይሆንም።

የሰምርኔስም ቤተ ክርስቲያን የዚህ ዓይነት ተቃውሞ ደርሶባት ነበር (2፡9)።

የፊልድልፍያ አማኞች ልክ ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡9ን በሚጽፍበት ጊዜ በነበረበት ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ነበሩ - መልካም ዕድሎችና መሰናክሎችም አጋጥመዋቸው ነበር። በእንደዚህ ዓይነቱ ወቅት አለማመን በመሰናክሎቹ ላይ ሲያተኩር፥ እምነት ግን ብሩህ በሆኑት መልካም ዕድሎች ላይ ያነጣጥራል። ጌታ መክፈቻዎችን ስለሚይዝ፥ የሚመጣውንም ውጤት ይቆጣጠራል። እንግዲህ ምንን እንፈራለን? ጌታ እስከከፈተው ድረስ፥ በሮቹን ሊዘጋ የሚችል የለም። ፍርሃት፥ አለማመንና መዘግየት፥ ቤተ ክርስቲያንን እግዚአብሔር የሰጣትን በርካታና መልካም ዕድሎች እንድታጣ አድርገዋት ነበር።

አዳኛችን ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ሦስት አስደናቂና አበረታች የተስፋ ቃሎችን ሰጥቶአታል። በመጀመሪያ የጠላቶቻቸውን ጥቃት ያስወግድላቸው ነበር (ራእይ 3፡9)። ውሎ ይደር እንጂ፥ ሆኖም አንድ ቀን፥ እነዚህ ሰዎች ክርስቲያኖች ትክክል መሆናቸውን መመስከራቸው የማይቀር ነበር! (ኢሳ. 60፡14፤ ፊልጵ. 2፡10-11) እኛ ለእግዚአብሔር ሥራ ስንጠነቀቅ፥ እርሱ የእኛን ጦርነት ይዋጋል።

ሁለተኛ፥ ከመከራ ይጠብቃቸው ነበር (ራእይ 3፤10)። ይህ በእርግጥ ዮሐንስ ከምዕራፍ 6-19 ለገለጸው «የያዕቆብ የመከራ ጊዜ» ማጣቀሻ ነው። «በምድር የሚኖሩትን» ስለሚል፥ ይህ በአንድ የተወሰነ ክልል ውስጥ ስለሚደርስ መከራ የሚናገር አይደለም (6፡10፤ 8፡13፤ 11፡10፤ 12፡12፤ 13፡8፥12፥14፤ 14፡6፤ 17፡2፥8 ተመልከት)። በቅርብ የሚያመለክተው ሊመጣ የነበረውን ይፋዊ የሮም ስደት ሲሆን፥ ዳሩ ግን ከሁሉም በላይ የሚያተኩረው ክርስቶስ መንግሥቱን ለመመሥረት ከመመለሱ በፊት ምድርን በሚያጥለቀልቀው ታላቁ መከራ ላይ ነው። እንደ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች መረዳት፥ ቁጥር 10 ቤተ ክርስቲያን ታላቁን መከራ እንደማትጋፈጥና ዳሩ ግን ይኸው መከራ ከመጀመሩ በፊት ወደ ሰማይ እንደምትወሰድ የሚያረጋግጥ የተስፋ ቃል ነው (1ኛ ተሰ. 4፡13 - 5፡11 ተመልከት)። «እነሆ፥ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ» የሚለው ማበረታቻ ይህንኑ አመለካከት ያጠናክራል።

ለፊልድልፍያ አማኞች የተሰጠው ሦስተኛው የተስፋ ቃል እግዚአብሔር እንደሚያከብራቸው ነው (ራእይ 3፡12)። የዚህ ጥቅስ ተምሳሌት፥ በተለይ በማያቋርጥ የምድር መናድ አደጋዎች ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ትርጉም ነበረው - የዓምዱ ጽናት፥ የሚያመለክተው ምንም ነገር የማያወድማትን ሰማያዊት ከተማ ሲሆን፥ ከእርሷም ውስጥ በፍርሃት መሸሽና መውጣት አስፈላጊ አልነበረም። ብዙውን ጊዜ የጥንት ከተሞች የታላላቅ መሪዎቻቸው ስሞች የተቀረጹባቸውን ዓምዶች በማቆም አክብሮታቸውን ይገልጹ ነበር። በሰማያዊቷ ከተማ ግን ምንም መቅደስ ስለሌለ (ራእይ 21፡22)፥ የእግዚአብሔር ዓምዶች ከድንጋይ የተሠሩ አይደሉም። ዓምዶቹ ስሙን ለክብሩ የሚሸከሙ ታማኝ ሰዎች ናቸው (ገላ. 2፡9)።

በጣም ግልጽ ባለ ሁኔታ ለመናገር፥ የዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ከፊልድልፍያዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተመሳሳይ ነች - እግዚአብሔር በፊታችን በርካታ ክፍት በሮችን አስቀምጦአልና። በሮቹን ከከፈተልን መሥራት፥ በሮቹን ከዘጋብን ደግሞ መጠበቅ አለብን። ከሁሉም በላይ፥ ለእርሱ ታማኞች በመሆን መልካም ዕድሎችን መመልከት እንጂ፥ በመሰናከሎች ላይ ማተኮር የለብንም። መልካም ዕድሎቻችንን ካጣን፥ ሽልማቶቻችንን (አክሊሎቻችንን) እናጣለን - ይህም እርሱ በሚገለጽበት ጊዜ ማፈር ማለት ነው (1ኛ ዮሐ. 2፡28)።

ሎዶቅያ - ሞኟ ቤተ ክርስቲያን (ራእይ 3፡14-22)

እንደቀደሙት አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ፥ አሁንም ጌታ ቃሎቹን ማኅበረ-ምዕምናኑ ከሚገኙባት ከተማ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ማዛመዱን እናያለን። በዚህም መሠረት፥ ሎዶቅያ በሀብቷ፥ በልዩ የዓይን ኩል ምርቷና ማራኪ ጥቁር ሱፍ በማቅረብ ትታወቅ ነበር። እንዲሁም ደግሞ ዝነኛ የፍል ውኃ (ጠበል) ምንጮችና የታወቁ ንጹሕና ቀዝቃዛ የቈላስይስ ፈሳሾች በሚገኙባት በሂራፖሊስ አቅራቢያ የተቆረቆረች ነበረች።

ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ጌታ ራሱን ያቀረበው «አሜን የሆነው» በማለት ሲሆን፥ ይህም ለእግዚአብሔር የተሰጠ የብሉይ ኪዳን ስያሜ ነው («እውነት» የሚለው ቃል በዕብራይስጥ «አሜን» የሚል ትርጉም ያለበትን ኢሳይያስ 65፡16 ተመልከት)። እርሱ «ታማኝና እውነተኛ ምስክር» ስለሆነ (ራእይ 3፡14)፥ እውነተኛና፥ እውነትንም ተናጋሪ

ነው። ጌታ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ስለነበረችበት መንፈሳዊ ሁኔታ እውነቱን ሊነግራት ቢሞክርም የሚያሳዝነው ግን ምዕመናኑ የእርሱን ግምገማ አልተቀበሉም ነበር።

አንድ ጊዜ አንድ ወጣት መጋቢ፥ «አዳዲስ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮችን የሚፈጥሩት ለምንድነው?» በማለት ጠየቀኝ። እኔም፥ «እነርሱ ችግሮችን ይገልጣሉ እንጂ አይፈጥሩም። እኛ ስለለመድናቸው እንጂ፥ ችግሮቹ ሁልጊዜም እዚያው ነበሩ። አዳዲስ ክርስቲያኖች እንደ ትናንሽ ሕፃናት እውነቱን ሳይደብቁ ይናገራሉ» ብዬ መለስኩለት።

የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ጉድለቶችዋን ለማየት እስከማትችልበት ደረጃ ድረስ የታወረች በመሆኗ እውነቱን ለመጋፈጥ አትፈልግም ነበር። ይሁንና የራሳችንን ደካማነት በማመን፥ ኃጢአታችንን በመናዘዝ፥ የሚያስፈልገንን ሁሉ ከእግዚአብሔር እጅ በመጠየቅና ታማኝነታችንን በማረጋገጥ፥ እውነተኛውን የበረከት ሕይወት ለመኖር ልንጀምር እንችላለን። እግዚአብሔር ከሁሉም የተሻለውን ነገር በሕይወታችንና በቤተ ክርስቲያናችን እንዲያደርግ የምንፈልግ ከሆነ፥ ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ነገር እውነተኞች ልንሆንና እርሱም በእውነተኛነት እንዲሠራ መፍቀድ አለብን።

«በእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ» የሚለው ሐረግ (ቁ. 14) ኢየሱስ እንደተፈጠረና በዚህም ምክንያት ዘላለማዊ አምላክ እንዳልሆነ የሚያመለክት አይደለም። «መጀመሪያ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «ምንጭ፥ መገኛ» ማለት ነው (ዮሐ. 1፡3፤ ቈላ. 1፡15፥18 ተመልከት)።

ጌታ በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን አራት የጉድለት አቅጣጫዎችን አመልክቷል፡-

ብርታት አጥተው ነበር (3፡16-17)። በክርስትና ሕይወት፥ ሦስት «መንፈሳዊ የሙቀት ደረጃዎች» አሉ - በእግዚአብሔር ቃል የሚቃጠል ልብ (ሉቃ. 24፡32)፥ ቀዝቃዛ ልብ (ማቴ. 24፡12)፥ እና ለብ ያለ ልብ (ራእይ 3፡16)። ለብ ያለው ክርስቲያን ምድራዊው ሕይወት የተስማማው፥ ባለው የረካና ጉድለቱን የማያውቅ ነው! ቀዝቃዛ ቢሆን ኖሮ፥ ቢያንስ የቅዝቃዜ ስሜት ይሰማው ነበር። ከቈላስይስ የሚመጣው

ቀዝቃዛ ውኃና ከሂራፖሊስ የሚመጣው ሙቅ ውኃ፥ ሎዶቅያ ደርሶ በሚደባለቅበት ጊዜ ለብ ይላል።

እኛ ግን በኢየሱስ ክርስቶስ የምናምን ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ «በመንፈስ ለመቃጠል» የሚያበቁን በቂ ምክንያቶች አሉ (ሮሜ 12፡11)። በዚህ ዓይነት በተነቃቃ መንፈስ የሚደረግም ጸሎት ዋንኛ አስፈላጊ ነው (ቈላ. 4፡12)። የኤማሁስ መንገድ ደቀ መዛሙርት ልብ የተቃጠለው ቃሉን በሰሙ ጊዜ ነበር። ጳውሎስ ለቈላስይስ የጻፈውን ደብዳቤ አሳቡን በመቀየር ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን እንዲላክለት ማዘዙ አስገራሚ አይሆንም (ቈላ. 4፡16)።

የድካም ማስወገጃዎች (ሻይ፥ ቡና፥ ለስላሳ) ሞቃት ወይም ቀዝቃዛ ሆነው ሲቀርቡልን ደስ ይለናል። ለብ ያለ ከሆነ ግን አይጥመንም። ለዚህም ነው በስኒዎችና ብርጭቆዎች ላይ ትኩስ ቡና ወይም በረዶ የሚጨመረው። ሁለተኛው የሙቀት ሕግ እንደሚደነግገው፥ «ሙቀትን የማያስገባና የማያስወጣ ነገር» በመጨረሻ ራሱን ስለሚያስተካክል ተጨማሪ ኃይል ለማመንጨት አይችልም። ከውጭ ሌላ ነገር እስካልተጨመረ ድረስ፥ የሙቀት አቅሙ ወደ ሞት ያመራል። እሳቱ እንዳይጠፋ ነዳጅ ካልተጨመረ በስተቀር በማሞቂያው ውስጥ የተጨመረው ሙቅ ውኃ ይቀዘቅዛል። የኤሌክትሪክ ኃይል ከሌለ፥ በማቀዝቀዣ «ፍሪጅ» ውስጥ የተቀመጠው ነገር ወደ ሞቃትነት ይለወጣል።

ቤተ ክርስቲያን «ዝግ አሠራር» ሊኖራት አይችልም። ኢየሱስ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም!» ብሏል (ዮሐ. 15፡5)። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን እራሷን የቻለች፥ በእራሷ የረካችና በአስተማማኝ ሁኔታዎችዋ የተኩራራች ነበረች። ምዕመኖችዋ «እኛም ምንም ችግር የለብንም!» ባዮች ነበሩ። ይህም ሆኖ ግን፥ መንፈሳዊ ኃይላቸው እየተሟጠጠ ነበር። የእነርሱ ቁሳዊ ሀብታቸውና የከበርቴነታቸው መጠን በመፈረካከስ ላይ የሚገኙትን አስከሬኖቻቸውን የሚደብቁ ከፈኖች ነበሩ። ጌታቸው ግን በውጭ ቆሞ ለመግባት ይሞክር ነበር (ራእይ 3፡20)።

እሴቶቻቸውን አጥተው ነበር (3፡17-18) - በሰምርኔስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ራሷን እንደ ድሀ አድርጋ ብትቆጥርም፥ ሀብታም ነበረች (2፡9)። ባንጻሩ የሎዶቅያ አማኞች ድሀዎች ሳሉ ስለ ሀብታቸው ብዙ በመናገር ይታበዩ ነበር። ምናልባት በዚህ ስፍራ ይህች ቤተ ክርስቲያን

ለምን በመንፈሳዊ ሕይወቷ እንደወደቀች የሚያመለክት ፍንጭ እናገኛለን - በአገልግሎታቸው መታበይ ጀምረው ነበርና፥ ነገሮችን በመንፈሳዊ እሴቶቻቸው ሳይሆን በሰብአዊ መመዘኛዎች ይለኩ ነበር። ይሁንና በጌታ ፊት፥ «ጎስቋላና ምስኪንም፥ ድሀም፥ ዕውርም» ነበሩ።

ሎዶቅያ ሀብታምና የገንዘብ ልውውጥ ገበያ የደራባትም ነበረች። ታዲያ ከገበያው ስፍራ መናፍስት አንዳንዶቹ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሰርገው ገብተው እንደሆነም እንጃ እሴቶቻቸው የተገላቢጦሽ ሆኑ። በአሁኑስ ጊዜ በበርካታ የቤተ ክርስቲያን የዜና መግለጫዎችና በደብዳቤ ርእሶች ላይ የሚቀረጹት ሥዕሎች የሕንፃዎች መሆኑ ለምን ይሆን? ከሁሉም በላይ የሚያስፈልጉን ነገሮች ሕንፃዎቹ ይሆኑ? የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ቦርድ ዓመታዊውን ዘገባ ከማራኪ የሂሳብ መግለጫ አኃዞች ጋር ሊያቀርብ ይችል ነበር፤ ይህም ሆኖ ግን ኢየሱስ ከአፉ ሊተፋቸው እንደተቃረበ ይናገራል።

መፍትሔው ምንድን ነው? «በእሳት የነጠረ ወርቅ» ለማግኘት ውድ ዋጋ ሊከፈልበት ይገባል። ማለትም ምዕመናኑ ከገደብ በላይ ተመቻችተው ስለነበር ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንዳንድ ስደቶችን ልትጋፈጥ በግድ ያስፈልጋት ነበር (1ኛ ጴጥ. 1፡7)። ለእግዚአብሔር ሰዎች፥ እንደፈታኝ መከራ በአስቸኳይ ወደ አምላካቸው እንዲመለሱ የሚያደርጋቸው ነገር የለም።

ራእያችውን አጥተው ነበር (3፡18) - የሎዶቅያ አማኞች ዕውር ስለነበሩ፥ እውነተኛውን ነገር ለማየት አይችሉም ነበር። ተቀባይነት በምታጣው ቤተ ክርስቲያናቸው እየተመኩ፥ በሞኞች ገነት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ሐዋርያው ጴጥሮስ አንድ አማኝ በጌታ ሳያድግ ሲቀር፥ መንፈሳዊ ራእዩ የተሟላ እንደማይሆን ያስተምራል (2ኛ ጴጥ. 1፡5-9)። «ምግብ» በአንድ ሰው ዓይን ላይ በመንፈሳዊም ሆነ ሥጋዊ መልኩ ለውጥ ያስከትላል።

እነዚህ ሰዎች እውነተኛ ማንነታቸውን ሊመለከቱ አልቻሉም ነበር። እንዲሁም ከቤተ ክርስቲያኒቱ በር ውጭ በመቆም ለመግባት ይጠባበቅ የነበረውን ጌታቸውን ሊመለከቱ አልቻሉም ነበር - የተከፈቱ የአገልግሎት በሮችንም እንዲሁ። የራሳቸውን መንግሥት በመገንባት ሂደት ስላተኮሩ፥ ከደኅንነት ርቆ ለጠፋው ዓለም የሚኖራቸው ሸክም ለብ አለ።

ለዚህ መፍትሔው ምንድን ነው? መፍትሔው ሰማያዊ ኩል መኳል ይሆናል። የሎዶቅያ ከተማ በዓይን ኩሏ የታወቀች ብትሆንም፥ ዳሩ ግን ለቅዱሳን የሚያስፈልገው የሕክምና አገልግሎት በባለ መድኃኒቶች ሱቅ ውስጥ አይገኝም ነበር። ዓይን ከሰውነት ክፍሎች በቀላሉ ተጠቂ ከሆኑት አካላት አንዱ ሲሆን፥ ጉዳቱን «ለማስተካከልና» መሆን እንደሚገባው ለመንከባከብ የሚችለው፥ አንድ ታላቁ ሐኪም ብቻ ነው። ምናልባትም በዮሐንስ 9 ውስጥ ታሪኩ ለተመዘገበለት ሰው እንዳደረገው ሁሉ፥ አንድን ዓይን ከማብራቱ በፊት ጭቃ ቀብቶ እንዲያሳክክ ሊያደርግም ይችላል። ይሁንና የእርሱን ሕክምና ልንቀበልና፥ ብሎም ዕይታችን እየጨመረ ይሄድ ዘንድ መልካም የመንፈሳዊ «ጤንነት ልማዶችን» ልናዳብር ይገባል።

አልባሳታቸውን አጥተዋል (3፡17-18)-በሀንስ ክርስቲያን አንደርሰን ታሪክ ውስጥ እንደነበረው ንጉሥ፥ እነዚህ ክርስቲያኖች ራቁታቸውን ሆነው በሚማርክ ልብስ እንደተጎናጸፉ ያስቡ ነበር። መራቆት ማለት መረታትና መዋረድ ማለት ነው (2ኛ ሳሙ. 10፡4፤ ኢሳ. 20፡1-4)። የሎዶቅያ አማኞች ወደ ገበያ ወጥተው ምርጥ የሱፍ ልብሶችን ሊገዙ ቢችሉም፥ ዳሩ ግን ያ እውነተኛ ጉድለታቸውን ሊሞላ አይችልም ነበር። የእግዚአብሔር ጽድቅና ጸጋ ስጦታዎች የሆኑት ነጭ አልባሳት ያስፈልጓቸው ነበር። በራእይ 19፡8 ዘገባ መሠረት፥ «ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ» መልበስ ሲኖርብን፥ ይህም «የቅዱሳን የጽድቅ ሥራ»ነው። ደኅንነት ማለት የክርስቶስ ጽድቅ ለእኛ ተቆጥሯል ማለት ሲሆን፥ ቅድስና ግን ጽድቁ የባሕርያችንና የፀባያችን አካል ሆኖአል ማለት ነው።

ለዚህች ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ መለኮታዊ ሙገሳ የለም። በእርግጥ፥ የሎዶቅያ አማኞች ራሳቸውን ለማሞጋገስ ይጣደፉ ነበር። ራቁታቸውን እንደሚሄዱ ሁሉ ስሙን እያሰደቡ ሳለ፥ እግዚአብሔርን የሚያስከብሩ ይመስላቸው ነበር።

ጌታ ይህንን ደብዳቤ በሦስት ልዩ ዐረፍተ ነገሮች ይደመድመዋል። መጀመሪያ፥ መግለጫ- «እኔ የምወዳቸውን እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ» (ቁ. 19)። የእነርሱ ፍቅር ለርሱ ቢቀዘቅዝም ቅሉ፥ እርሱ አሁንም እነዚህን ለብ ያሉ አማኞች ይወድ ነበር። በመሆኑም፥ እንደ ፍቅሩ መግለጫ ሊቀጣቸው ዐቀደ (ምሳሌ 3፡11-12፤ ዕብ. 12፡5-6)። እርሱ የሚፈልገውን ይሆኑ ዘንድ፥ እግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት በመከራ ውስጥ እንዲያልፉ ይፈቅዳል።

ሁለተኛ፥ ምክር - «እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ» (ራእይ 3፡19)። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ስለ ትዕቢቷ ንስሐ ልትገባና ምዕመናኗም በጌታ ፊት ራሳቸውን ሊያዋርዱ ያስፈልግ ነበር። ስለሆነም፥ ያንኑ ውስጣዊ እሳት በማቀጣጠል (2ኛ ጢሞ. 1፤6)፥ የሚቃጠል ልብ ማግኘት ያስፈልጋቸው ነበር።

በመጨረሻም፥ ግብዣ- (ራእይ 3፡20-22) ብዙውን ጊዜ ይህን ጥቅስ የምንጠቀመው ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ሰዎች ወደ ክርስቶስ ለመምራት ሲሆን፥ ዳሩ ግን መሠረታዊ ተዛምዶው ለአማኝ ነው። ጌታ ከሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ቆሞ ነበር። እርሱም «ማንም» በማለት ለሰዎች በግለሰብ ደረጃ ተናገራቸው እንጂ፥ ለማኅበረ-ምእመናኑ ሁሉ አይደለም። ከዚህ በፊት በሰርዴስ አነስተኛ ቁጥር ላላቸው ቅሪቶች ጥሪ ያቀረበ ሲሆን (3፡4-5)፥ አሁን ደግሞ ግለሰቦችን ይጠራል። በአንድ ራሱን ለጌታ አሳልፎ በሰጠ ግለሰብ በመጠቀም እንኳ፥ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላላቅ ነገሮችን ሊያደርግ ይችላል።

ክርስቶስ ትዕግሥቱን አላጣም ነበር። የግሡ ትርጉም «ቆሜአለሁ» የሚል ነው። በሁኔታዎች አማካኝነት ደጁን «ከማንኳኳቱም» በቃሉም አማካኝነት ይጣራል። የሚለምናቸው ለምንድን ነው? ለኅብረትና ለአንድነት፥ የሕዝቡ ልብ በሙሉ መሻት ወደ እርሱ እንዲሆን። የሎዶቅያ አማኞች ምንም ያልጎደለባችውና ራሳቸውን ችለው የሚኖሩ ሲሆን፥ ዳሩ ግን በክርስቶስ የመኖርና ከእርሱም ኃይል የመቀበል ልምምድ አልነበራቸውም። «የተሳካ መርሐ-ግብር» ቢኖራቸውም፥ ይህ ግን በክርስቶስ ከመኖር የተገኘ ፍሬ አልነበረም (ዮሐ. 15፡1-8)።

እርሱን ወደ ውስጥ በምናስገባበት ጊዜ፥ የምግብ አዳራሹ የዙፋን መቀመጫ እንደሚሆን ልብ በል። ድልን የምናገኘውና አሸናፊዎች የምንሆነው ከክርስቶስ ጋር በሚኖረን ኅብረት አማካኝነት ነው።

ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩት ደብዳቤዎች፥ የራሳችንን ሕይወትና አገልግሎት እንመረምር ዘንድ የተሰጡን የእግዚአብሔር የመመርመሪያ መሣሪያዎች (ኤክስ-ሬይ) ናቸው። ፍርድ ወደዚህ ዓለም የሚመጣ ሲሆን፥ ዳሩ ግን የሚጀምረው ከእግዚአብሔር ቤት ነው (1ኛ ጴጥ. 4፡17)። ከእነዚህ ደብዳቤዎች ማበረታቻና ተግሣጽም እናገኛለን።

እስኪ መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያንና በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች በዛሬው ጊዜ እየተናገረ ያለውን ነገር እንሰማ ዘንድ ጌታ ይርዳን!

- 4 -

ኑ - እርሱን እናወድሰው!

ራእይ 4-5

በሕይወታችንም ሆነ በአብያተ ክርስቲያናታችን ውስጥ ከማንኛውም ነገር አብልጦ ሊኖረን የሚገባው እውነተኛ መንፈሳዊ አምልኮ ነው። ዛሬ ለክርስቶስ ስለመመስከርና ስለማገልገል የማያቋርጥ ትኩረት ቢደረግም፥ ዳሩ ግን እርሱን ስለማምለክ የሚነገረው ያንንም ያህል በቂ አይደለም። «ማምለክ» ማለት «የሚገባውን ለእርሱ መስጠት» ማለት ነው (ራእይ 4:11፤ 5:12 ተመልከት)። ይህም እግዚአብሔርን ስለ እርሱነቱና ስላደረጋቸው ነገሮች ለማመስገን ባለን ኃይልና ባለን ነገር ሁሉ መጠቀም ማለት ነው።

መንግሥተ ሰማይ የአምልኮ ሥፍራ ስለሆነ፥ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለዘለዓለም እርሱን ማምለክ አለባቸው። በመሆኑም፥ ዛሬ መለማመዱን ብንያያዘው ሳይሻል አይቀርም! የራእይ 4-5 ጥናት እግዚአብሔርን እንዴት እንደምናመልክና የሚገባውንም ክብር እንዴት እንደምንሰጠው በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ያስችለናል።

ራእይ 1:19 እግዚአብሔር በመንፈሱ ምሪት ለዚህ መጽሐፍ የሰጠው አስተዋጽኦ ከሆነ፥ ምዕራፍ 4 ደግሞ ወደ ሦስተኛው ክፍል ያሸጋግረናል - «ከዚህ በኋላ ይሆን ዘንድ ያለው።» እንዲያውም፥ እግዚአብሔር ዮሐንስን ወደ ሰማይ ሲጠራው ይህንኑ ነበር የነገረው። ዮሐንስ በዚህ ልምምዱ፥ የቤተ ክርስቲያን ዘመን በሚፈጸምበት ጊዜ በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ምን እንደሚደርስ የሚያስረዳ ይመስላል - ሰማይ ይከፈታል፤ ድምፅና የመለከት ማስተጋባት ይከተላል፤ ቅዱሳንም ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ (1ኛ ተሰ. 4:13-18፤ 1ኛ ቆሮ. 15:52)። ከዚያ ወዲያ፥ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚያፈሰው ፍርድ ሊጀምር ይችላል።

ይሁንና እግዚአብሔር ቁጣውን ከማፍሰሱ በፊት፥ የክብሩን ጨረፍታ እንድናይና፥ በሰማይ እግዚአብሔርን የሚያመልኩ ፍጥረታት ምስጋናቸውን ሲያቀርቡ እንድንሰማ ያደርጋል። የአምልኮዎቻቸውንም

ሁለት ገጽታዎች እንድንማራቸውና እንድንከተላቸው በመቀጠል ቀርበዋል:-

ፈጣሪን ያመልኩታል (ራእይ 4)

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ቁልፉ ቃል «ዙፋን»የሚለው ሲሆን፥ 14 ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። በእርግጥ ይኼ ቁልፍ ቃል በዚህ በራእይ መጽሐፍ በጠቅላላው አርባ ስድስት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል። በምድር ላይ ምንም ቢደርስ፥ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ሁሉንም በመቆጣጠር ላይ ይገኛል። የተለያዩ መምህራን ራእይን በተለያዩ መንገዶች ቢተረጉሙትም፥ ዳሩ ግን ሁላቸውም ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ክብርና ሉዓላዊነት በማጉላቱ አሳብ ላይ ይስማማሉ። ይህ በዮሐንስ ዘመን በመከራ ውስጥ ለነበሩ ቅዱሳንና በታሪክ ውስጥ ለሚገኘው ዘመን ሁሉ ምንኛ ማበረታቻ ነው!

ዙፋኑን ማዕከላዊ ሥፍራ አድርገን በመውሰድ፥ የዚህን አስደሳች ምዕራፍ አቀማመጥ በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን።

በዙፋኑ ላይ - ሁሉን ቻይ አምላክ (4:2-3):- ወልድ ወደዙፋኑ የሚቀርበው በ5:6 ላይ ስለሆነና መንፈስ ቅዱስም በ4:5 ላይ በዙፋኑ ፊት ስለተጠቀሰ፥ በዚህ ሥፍራ የሚገኘው እግዚአብሔር አብ ነው። እግዚአብሔር በመለኮታዊ ባሕርዩ ምን እንደሚመስል በሰብአዊ ቋንቋ ለመግለጽ የሚቻልበት መንገድ የለም። ስለሆነም ዮሐንስ ማድረግ የሚችለው በሚታወቁ ነገሮች አወዳድሮ መግለጽ ብቻ ነበር። ኢያስጲድ የከበረ ድንጋይ ሲሆን (21:11 ተመልከት)፥ ሰርድዮን ቀይ ነው። መዝሙር (104):2 እና 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:16 እንደሚገልጹት፥ ጌታ ብርሃንን የለበሰ ነው። ሁለቱም ኢያስጲድና ሰርድዮን በሊቀ ካህኑ የደረት መታጠቂያ ላይ ይደረጉ ነበር (ዘጸ. 28:17-21)።

በዙፋኑ ዙሪያ - ቀስተ ደመና (4:3):- በሰማይ ላይ ነገሮች ሁሉ ሙሉ በመሆናቸው፥ ይህ ቀስተ ደመና ሙሉ እንጂ ግማሽ ክብ አልነበረም። ቀስተ ደመናው እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን የሚያስታውሰን ሲሆን (ዘፍጥ. 9:11-17)፥ ዳግመኛ ምድርን በውኃ እንደማያጠፋት የሚያመለክት ነው። ቀጥለን እንደምንመለከተው፥ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ከኖኅ ጋር ብቻ ሳይሆን፥ ከፍጥረቱ ሁሉ ጋር ነበር።

ፍርድ ሊገለጽ የቀረበ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ቀስተ ደመናው በሚፈርድበት ጊዜም ሳይቀር እግዚአብሔር መሐሪ እንደሆነ ያስታውሰናል (ዕንባ. 3፡2)። ብዙውን ጊዜ ቀስተ ደመና የሚታየው ከማዕበል በኋላ ሲሆን፥ በዚህ ሥፍራ ላይ ግን ከማዕበሉ በፊት እናየዋለን።

በዙፋኑ ዙሪያ - ሽማግሌዎችና እንስሳት (4፡3-4፤ 6-7)፡- እነዚህ ሰማያዊ ፍጥረታት በዙፋኑ ዙርያ የተቀመጡት የጎን መሥመር ይዘው ሲሆን፥ ቀስተ ደመናው የላይ መሥመር ተከትሎ እንደነበር አያጠራጥርም። እነዚህ የሰማይ ፍጥረታት በንጉሡ ችሎት ፊት የሚገኙ ነበሩ።

በዙፋን ላይ የተቀመጡት ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች እነማናቸው? መላእክት ስላልተቆጠሩ (ዕብ. 12፡22)፥ አክሊልን ስላላደረጉ፥ ወይም በዙፋን ላይ ስላልተቀመጡ እነዚህ ሽማግሌዎች መላእክት ናቸው ለማለት አያስደፍርም። በተጨማሪም፥ በራእይ 7፡11 ላይ ሽማግሌዎቹ ከመላእክት ተለይተው ተጠቅሰዋል (5፡8-11 ተመልከት)። ደግሞም ያደረጓቸው አክሊሎች «የድል አክሊሎች» (በግሪኩ እስጢፋኖስ - 2፡10 ተመልከት) ሲሆኑ፥ ለመላእክት ግን ሽልማት እንደሚሰጥ የሚያመለክት መረጃ የለም።

እነዚህ ሽማግሌዎች ምናልባት በሰማይ ዙፋንና ሽልማት ተሰጥቷቸው የሚኖሩትን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች የሚያመለክቱ ይሆናሉ። በብሉይ ኪዳን መቅደስ ውስጥ ሃያ አራት የክህነት አገልግሎት ሥርዓቶች ነበሩ (1ኛ ዜና 24፡3-5፥18፤ ሉቃ. 1፡5-9 ተመልከት)። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከክርስቶስ ጋር የሚገዙና የሚያገለግሉ «ነገሥታትና ካህናት» ናቸው (ራእይ 1፡6)። በተለይ ምስጋናቸውን ልብ በል (5፡9-10)። ዳንኤል ዙፋናት ተዘርግተው ሲመለከት (ዳን. 7፡9)፥ ተቀማጭ አልነበረባቸውም። ዳሩ ግን ዮሐንስ ሲመለከታቸው በተቀማጭ ተሞልተው ነበር። እንደሚታወሰው አሥራ ሁለት የእስራኤል ነገዶችና አሥራ ሁለት ሐዋርያት ስለነበሩ፥ ምናልባትም ቁጥር ሃያ አራት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ምልዓት ያመለክት ይሆናል።

ነጫጭ ልብሶችና የዘንባባ ዝንጣፊዎች ድልን ያሳያሉ (7፡9 ተመልከት)። እነዚህ በክርስቶስ ላይ በነበራቸው እምነት ምክንያት ድል የነሡ «አሸናፊዎች» ናቸው (1ኛ ዮሐ. 5፡4-5)።

እንዲሁም በዙፋኑ ዙሪያ ዮሐንስ ከመላእክትና ከሽማግሌዎች በላይ ወደ እግዚአብሔር የቀረቡትን «አራት እንስሳት» ተመልክቷል። እነዚህም ነቢዩ ሕዝቅኤል የተመለከታቸውን ኪሩቤል የሚመስሉ ሲሆን (ሕዝ. 1፡4-14፤ 10፡20-22)፥ ዳሩ ግን ምስጋናቸው (ራእይ 4፡8) በኢሳይያስ 6 ላይ የተጠቀሱትን ሱራፌሎች ያስታውሰናል። እነዚህ ልዩ እንስሳት የእግዚአብሔርን ፍጥረታት ሁሉ እንደሚያመለክቱና እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር ካደረገው ቃል ኪዳን ጋር እንደሚዛመዱ አምናለሁ (ዘፍጥ. 9፡8-17)። የእንስሳቱ ፊቶች እግዚአብሔር በዘፍጥረት 9፡10 ከተናገረው ጋር ይመሳሰላሉ - ቃል ኪዳኑ ከኖኅ ጋር ነው (የሰው ፊት)፥ ወፎች (የንስር ፊት)፥ እንስሳት (የጥጃ ፊት)፥ እንዲሁም የምድር አራዊት ሁሉ (የአንበሳ ፊት)።

እነዚህ ፍጥረታት የእግዚአብሔርን ጥበብ («ዓይኖች የሞሉአቸው») ከማመልከታቸውም በላይ፥ የእግዚአብሔርን ቅድስና ያውጃሉ። እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር ቃል ኪዳን እንዳለውና በዙፋኑ ላይ ሆኖ ፍጥረታቱን እንደሚገዛ የሚያስታውሱን ሰማያዊ አካላት ናቸው። ቀስተ ደመና በፍቅር ለተገባው ቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ ስለተሰጠ፥ የጠራው ቀስተ ደመና መኖሩ ይህንኑ መግለጫ ያጠናክረዋል። በእግዚአብሔር ምድር ላይ ምንም ዓይነት አስጨናቂ ፍርዶች ቢወርዱም፥ እርሱ ግን ቃሉን ለመጠበቅ በታማኝነቱ ይጸናል። በፍርድ ወራት ሰዎች ሊረግሙት ቢችሉም (ራእይ 16፡9፥ 11፥ 21)፥ ዳሩ ግን ተፈጥሮ ያመሰግነዋል - ቅድስናውንም ያውጃል።

በሕዝቅኤል 1 ውስጥ የተጠቀሱት ኪሩቤል፥ «በመንኰራኩር ውስጥ እንዳለ መንኰራኩር» ተብሎ በተገለጸው ዓለም ውስጥ እግዚአብሔር በሚያከናውናቸው መለኮታዊ ተግባራት፥ ውሱን ሚና ያላቸው ይመስላል። እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም በተፈጥሮ ኃይላት ይጠቀማል (መዝ. (148))፤ በዚህም ፍጥረት ሁሉ ያመሰግነዋል።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች እነዚህ የእንስሳት ፊቶች መግለጫ (ራእይ 4፡7)፤ በወንጌላት ዘገባ ለተሰጠው የክርስቶስ ባለ

አራት ገጽታ ምስል ማብራሪያ እንደሚሆኑ ይስማማሉ። ማቴዎስ በአንበሳ የተገለጸ የንጉሥ ወንጌል ነው። ማርቆስ በጌታ አገልግሎት አስመልክቶ በባርነት ገጽታ ላይ ሲያተኩር (ጥጃ)፥ ሉቃስ ክርስቶስን እንደሩኅሩኅ የሰው ልጅ አድርጎ ያቀርበዋል። ዮሐንስ የክርስቶስን አምላክነት የሚያጎላ አቀራረብ አለው (ንስር)።

በመጨረሻም፥ እነዚህ እንስሳት «ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ» በሚለው የሙገሣ ስም መጠቀማቸው የእግዚአብሔርን ኃይል ያጎላዋል። በምዕራፍ 1 ውስጥ እንደተጠቀሰው፥ «ሁሉን የሚገዛ» የሚለው ቃል በራእይ ውስጥ 9 ጊዜ ተጠቅሷል። በአዲስ ኪዳን እንዲህ ዓይነት አጠቃቀም የሚገኘው በ2ኛ ቆሮንቶስ 6፡18 ላይ ብቻ ሲሆን፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን የፈጣሪነት ኃይል በሚያንጸባርቀው በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ቢያንስ 31 ጊዜ ያህል ተጠቅሷል።

ከዙፋኑ ውስጥ- የማዕበል ምልክቶች (4፡5)፡- «ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ፥ ነጎድጓድም ይወጣል።» እነዚህ የሚመጣውን የመከራ ማዕበል የሚያመለክቱና የእግዚአብሔርን አስፈሪ ኃይል የሚያስታውሱን ናቸው (ዘጸ. 19፡16፤ 9፡23፥ 28)። በፍርድ ጊዜም «ማዕበል ምልክቶቹ» ከእግዚአብሔር ዙፋንና መቅደስ በመደጋገም ይወጣሉ (ራእይ 8፡5፤ 11፡19፤ 16፡18)። በእርግጥ እግዚአብሔር ዙፋኑን ለፍርድ አዘጋጅቷል (መዝ. 9፡7፤ እንዲሁም (77)፡18ን ተመልከት)።

ይህቺ ዓለማችን ግን እግዚአብሔርን የፍርድ አምላክ አድርጋ ለማሰብ ስለማትፈልግ፥ ከዙፋኑ የሚወጣውን መብረቅና ነጎድጓድ በመመልከት ምትክ፥ ከዙፋኑ ዙሪያ የሚገኘውን ቀስተ ደመና ለማየት ትመርጣለች። በመሠረቱ እግዚአብሔር የጸጋ አምላክ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ጸጋው «የሚገዛው በጽድቅ» ነው (ሮሜ 5፡21)። ይህም እግዚአብሔር ለኃጢአተኞች ያለውን ፍቅርና በኃጢአት ላይ ያለውን ቁጣ በገለጸበት መስቀል ላይ ታይቷል።

ከዙፋኑ ፊት - መብራቶችና ባሕር (4፡5-6)፡- ሰባቱ መብራቶች ምልዓትን ሲገልጹ፥ የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ ያመለክታሉ (1፡4፤ ሕዝ. 1፡13 ተመልከት)። እንዲሁም ዮሐንስ በዚህ በራእይ ገለጻው ውስጥ «ሰማያዊው መቅደስ» የምድራዊውን የመገናኛ ድንኳንና

መቅደስ መልክ እንደሚይዝ የሚያመለክት ይመስላል (ዕብ. 9፡23 ተመልከት)። ተዛምዶዎቹም እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡-

ምድራዊ መቅደስ	ሰማያዊ መቅደስ
- ቅድስተ ቅዱሳን	- የእግዚአብሔር ዙፋን
- ሰባት ቅርንጫፎች ያሉት መቅረዝ	- በዙፋኑ ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች
- የነሐስ ገበታ	- የብርጭቆ ባሕር
- በምሕረት መቀመጫ ላይ የሚደረግ ኪሩቤል	- በዙፋኑ ዙርያ የሚገኙ አራት እንስሳት
- ካህናት	- ሽማግሌዎች (ነገሥታትና ካህናት)
- የነሐስ መሠዊያ	- መሠዊያ (6፡9-11)
- የዕጣን መሠዊያ	- የዕጣን መሠዊያ (8፡3-5)
- የቃል ኪዳን ታቦት	- የቃል ኪዳን ታቦት (11፥19)

ሆኖም በሰማይ የሚገኘው መቅደስ ቁሳዊ ይዘት ይኖረዋል ብለን መገመት የለብንም። በቅዱስ ዙፋኑ ፊት ለሚያገለግሉ ሁሉ መላው ሰማይ የእግዚአብሔር መቅደስ ነው (7፡15)። ይሁንና፥ ዮሐንስ በራእይ 15፡5-8 ልዩ የእግዚአብሔር «መቅደስ» እንዳለ ያመለክታል (11፡19ንም ተመልከት)። በዘላለማዊው መንግሥት ግን መቅደስ አይኖርም (21፡22)።

ጥሩ የብርጭቆ ባሕር የእግዚአብሔርን ቅድስና ሲያመለክት፥ እሳቱ ቅዱስ ፍርዱን ያሳያል። ይህም በሕዝቅኤል ሕልም ውስጥ የነበረውን «የጠፈር አምሳያ» ያስታውሰናል (ሕዝ. 1፡22)፤ ይህም የእግዚአብሔር ዙፋን መሠረት መሆኑ ነው። በተጨማሪም ይህንን የ«ብርጭቆ ባሕር» እስራኤል በግብፅ ላይ ካገኘችው ድል ጋር በተያያዘ መልኩ በራእይ 15 ላይ በድጋሚ እናገኘዋለን።

ለዙፋኑ የቀረበ ምስጋና (4፡9-11)፡- እንስሳቱም እግዚአብሔርን በሚያከብሩበት ጊዜ ሁሉ፥ ሽማግሌዎቹም በፊናቸው ከዙፋኑ ፊት ወድቀው ይሰግዱለት ነበር። የራእይ መጽሐፍ የተሞላው በምስጋና

መዝሙር ነው (4፡8፥11፤ 5፡9-13፤ 7፡12-17፤ 11፡15-18፤ 12፡10-12፤ 15፡3-4፤ 16፡5-7፤ 18፡2-8፤ 19፡2-6)። ዮሐንስ ይህን መጽሐፍ የጻፈው በመከራና በስደት ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች ለማበረታታት እንደሆነ በምታስታውስበት ጊዜ ለምስጋና የተሰጠውን አጽንኦት ልብ ልትለው ይገባል።

በራእይ 5 ሽማግሌዎች ለ«አዳኙ አምላክ» ምስጋና ቢያቀርቡም፥ የዚህ መዝሙር ዋና አሳብ «ፈጣሪ አምላክ» የሚል ነው። በምዕራፍ 4 ውስጥ ምስጋና የቀረበው በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለእግዚአብሔር አብ ሲሆን፥ በምዕራፍ 5 በዙፋኑ ፊት ለሚገኘው ለእግዚአብሔር ወልድ (ለበጉ) ነው። የመደምደሚያ መዝሙሩ ለሁለቱም የቀረበ ሲሆን (5፡13)፥ ይህም ለወልድ አምላክነት ሌላው ማረጋገጫ ነው።

ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በሰማይ የሚኖሩትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚያመለክቱ ከሆነ፥ «የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ለምን ያመሰግኑታል?» ብለን መጠየቅ አለብን። ይህን ካነሣንና በተጨማሪም ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር የሚናገሩ ከሆነ፥ ሰማያዊው የእግዚአብሔር ሕዝብስ ለምን የምስጋናውን አዝማች አብረው አይዘምሩም የሚለውን ሌላም ጥያቄ አብረን ማየት ይኖርብናል [መዝ. (19)]። ፍጥረት ለእግዚአብሔር ኃይል፥ ጥበብና ክብር የማያቋርጥ ምስክርነት ይሰጣል። የፈጣሪውን ህልውና ተቀብሎ አዳኙን ማመንና ማመስገን የማንኛውም ፍጡር የመጀመሪያ እርምጃ ነው (የሐዋ. 14፡8-18፤ 17፡22-31)። «ሁሉ በእርሱ (በክርስቶስ)ና ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል» (ቈላ. 1፡16-17)።

ይሁንና ኃጢአተኛ ሰው በፈጣሪው ፈንታ የተፈጠረውን ያመልካል - ያገለግላልም፤ ይህም ጣዖትን ማምለክ ነው (ሮሜ 1፡25)። በተጨማሪም፥ ኃጢአተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ግሩም ፍጥረት በመበከልና በማውደም ከፍተኛ ጥፋት የፈጸመ እንደመሆኑ፥ ለዚሁም ዋጋ ይከፍላል (ራእይ 11፡18 ተመልከት)። ፍጥረት ለእግዚአብሔር ምስጋናና ደስታ የተዘጋጀ ሲሆን፥ ሰው የእግዚአብሔር የሆነውን ነገር ለመቀናቀን መብት የለውም። ሰው ፍጥረትን ለኃጢአት ስለዳረገው፥ መልካሙ የእግዚአብሔር ፍጥረት (ዘፍጥ. 1፡31) ዛሬ የሚቃትት ፍጥረት ሆኗል (ሮሜ 8፡22)። ይህም ሆኖ፥ ክርስቶስ በመስቀል ላይ

ከፈጸመው ሥራ የተነሣ፥ አንድ ቀን ነጻ ይወጣና የከበረ ፍጥረት ይሆናል (8፡18-24)።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የፍጥረትን አምላክ ወደ ዳር የመግፋቷ ጉዳይ በእጅጉ አሳዛኝ ነው። ለአካባቢ ብክለት እውነተኛው ምላሽ የመዋዕለ-ንዋይ መፍሰስ ወይም የሕጎች መደንገግ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን መንፈሳዊ ተጋድሎ ነው። ችግሩም እልባት የሚያገኘው ሰው ፈጣሪውን ሲያመሰግንና በፍጥረታትም በአግባቡ መጠቀም ሲጀምር ብቻ ነው።

አዳኙን ያመልኩታል (ራእይ 5)

የአሁኑ ትኩረታችን ደግሞ በእግዚአብሔር እጅ ወደሚገኘውና በሰባት ማኅተሞች ወደታተመው የመጽሐፉ ጥቅልል ይመለሳል። የመጽሐፉ ጥቅልል ስለታሸገና በ7 ማኅተሞች ስለታተመ፥ ሊነበብ አይችልም ነበር። በተጨማሪም በመጽሐፉ ገጾች በፊትና በጀርባቸው ተጽፎባቸው ስለነበር፥ ዮሐንስ ምንም ነገር መጨመር አይችልም ነበር። የተጻፈው ነገር የተፈጸመና የተደመደመ ነበር።

የመጽሐፉ ጥቅልል ክርስቶስ በመስቀል ላይ ላቀረበው መሥዋዕትነት እግዚአብሔር ተስፋ የገባለትን «የውርስ ሀብት» ያመለክታል። «ለምነኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ፥ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ» (መዝ. 2፡8)። ኢየሱስ ክርስቶስ «የሁሉም ወራሽ» ነው (ዕብ. 1፡2)። እኛን ከእስራት ነጻ ለማውጣትና የጠፋውን ወራሽነታችንን ደግሞ ለመመለስ የፈቀደ ውድ «አዳኛችን» ነው (ዘሌ. 25፡23-46፤ ኤር. 32፡6-15፤ መጽሐፈ ሩት ተመልከት)።

ክርስቶስ ማኅተሙን በሚፈታበት ጊዜ፥ የተለያዩ አስደናቂና አስደንጋጭ ነገሮች ይፈጸሙ ጀመር። ሰባተኛውም ማኅተም የሰባቱን መለከቶች ፍርድ ያስከትላል (ራእይ 8፡1-2)። ከዚያም፥ ሰባተኛው መለከት ሲነፋ፥ ታላቁ የእግዚአብሔር የቁጣ ቀን ይታወጃል፤ ይህም የእግዚአብሔርን ቁጣ ወደ ፍጻሜ የሚያደርሱትን «የጽዋ ፍርዶች» ያስከትላል (11፡ ከቁጥር 15 ጀምሮ፤ 15፡1)። በመጽሐፉ አንደኛው ወገን የመለከት ፍርዶች ሲጻፉ፥ በሌላው ወገን ላይ ደግሞ የጽዋ ፍርዶች ሳይሰፍሩ አይቀሩም።

የውርስን ሀብት የሚያመለክተው መዝገብ ሊከፈት የሚችለው በወራሹ እጅ ሲሆን፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በአጽናፈ-ዓለሙ

ሁሉ ማጎተሞቹን ሊፈታ የሚገባው ማንም ሰው ሊገኝ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ያዘጋጀው የከበረ የማዳን ዕቅድ መጽሐፉ እስካልተከፈተ ድረስ ሊፈጸም እንደማይችል ዮሐንስ በመረዳቱ ማልቀሱ አያስደንቅም። ነፃ አውጪው የቅርብ ዘመድ ሊሆን፥ ነፃም ለማውጣት ፈቃደኛና ይህንኑም ተግባር ለማከናወን የሚችል ሰው መሆን ነበረበት። ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ሁሉ ብቃቶች ያሟላል። አምላክ ሥጋ በመልበሱ፥ ነፃ አውጪአችን ሆነ። እኛን ስለሚወደንና ነፃም ሊያወጣን ስለሚፈቅድ፥ ዋጋ ከፍሎልናል - በመሆኑም፥ ነጻ ሊያወጣን ቻለ።

አሁን በተቀረው የራእይ 5 ክፍል ውስጥ ወደተገለጸው የአምልኮ ልምምድ ለመግባት እንችላለን። በዚህም፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማምለክ የሚያስገድዱንን አራት ምክንያቶች እንመለከታለን።

በማንነቱ ምክንያት (5፡5-7) - ማንነቱን ለመግለጽ፥ ሦስት ልዩ ስሞች ተሰጥተውታል። በመጀመሪያ፥ የይሁዳ ነገድ አንበሳ ነው። የዚህ ክፍል ማጣቀሻ የሚገኘው ያዕቆብ በትንቢታዊ ገለጻ በትረ-መንግሥቱን ለይሁዳ በመስጠት የነገሥታት ነገድ ባደረገበት በዘፍጥረት 49፡8-10 ነው። (ሳዖል ከብንያም ነገድ ስለሆነ፥ እግዚአብሔር ንጉሣዊ አገዛዝን እንዲመሠርት አልፈለገም ነበር። ሕዝቡ ንጉሥ እንዲሰጣቸው ስለጠየቁ፥ እስራኤላውያንን ለመቅጣት ተጠቅሞበታል፤ ከዚያ በኋላ ግን ከአይሁድ ነገድ ዳዊትን ሰጣቸው።)

«የአንበሳ» ምስል ክብርን፥ ሉዓላዊነትን፥ ብርታትንና ድልን ያመለክታል። በዘር ሐረግ ቆጠራ ንጉሥነቱን ሊያረጋግጥ የሚችለው ብቸኛው ሕያው አይሁዳዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። «የዳዊት ልጅ» የሚለው በምድር ላይ ያገለግል በነበረበት ጊዜ በአብዛኛው የሚጠቀስ ማዕረግ ነበር (ማቴ. 1 ተመልከት)።

ይህም ሆኖ እርሱ «የዳዊት ሥር» ማለትም ዳዊትን (እና የዳዊትን ሐረግ) ወደ ህላዌ ያመጣ ነው። ሰብአዊነቱን በተመለከተ፥ የኢየሱስ ሥር የነበረው በዳዊት ውስጥ ሲሆን (ኢሳ. 11፡1፥10)፥ ዳሩ ግን አምላክነቱን በተመለከተ፥ ኢየሱስ የዳዊት ሥር ነው። በመሠረቱ ይህ የጌታችንን ዘላለማዊነት ያመለክታል። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ እርሱ «በዘመናት የሸመገለ» ነው። ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ያቀረበው ጥያቄ፥

«መሢሑ እንዴት የዳዊት ጌታና የዳዊት ልጅ ሊሆን ይችላል?» የሚል ሲሆን፥ ጥያቄውን ሊመልሱለት አልቻሉም (ማቴ. 22፡41-46)።

ዮሐንስ ግን ለመመልከት ዞር ባለበት ጊዜ ያየው አንበሳን ሳይሆን፥ በግን ነበር። በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ቢያንስ ሃያ ስምንት ጊዜ ያህል «በግ» ተብሎ የተጠራ ሲሆን (በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ የተጠቀሰው የግሪክ ቃል «ትንሽ ለማዳ በግ»)፥ ትኩረቱም ለመረዳት የሚያዳግት አይደለም። የእግዚአብሔር ቁጣ «የበጉ ቁጣ» ነው (ራእይ 6፡16)። መንጻት የሚቻለውም «በበጉ ደም» ነው (7፡14)። ቤተ ክርስቲያን «የበጉ ሙሽራ» ናት (19፡7፤ 21፡9)።

«የበጉ» ዓቢይ አሳብ የአዳኙን የኢየሱስ ክርስቶስን አካልና ተግባር ስለሚወክል በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ውስጥ ተቀዳሚ ሥፍራ የሚሰጠው ነው። «በጉ የታለ?» የሚለው የብሉይ ኪዳን ጥያቄ (ዘፍጥ. 22፡7)፥ «እነሆ፥ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» በማለት በጮኸው በመጥመቁ ዮሐንስ ቃል ምላሽ አግኝቷል (ዮሐ. 1፡29)። ሰማያውያን መዘምራን፥ «የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ... ሊቀበል ይገባዋል» በማለት ዘምረዋል (5፡12)።

የበጉ መግለጫ (ቁ. 6)፡- በአንድ የጥበብ ሰው በቀጥታ የቀረበ ቢሆን ኖሮ እጅግ በተጋነነ መልኩ በተተረጎመም ነበር። ዳሩ ግን በአሁኑ በተምሳሌት መልክ መቅረቡ መንፈሳዊ እውነትን ያስተላልፋል። ሰባት የፍጹምነት ቁጥር ስለሆነ፥ በዚህ ሥፍራ ፍጹም ኃይል (ሰባት ቀንዶች)፥ ፍጹም ጥበብ (ሰባት ዓይኖች)፥ ፍጹም ህላዌ (በምድር ሁሉ ሰባት መናፍስት) ይገኛሉ። የሥነ-መለኮት ምሑራን እነዚህን ብቃቶች ሁሉንም የመቻል፥ ሁሉንም ነገር የማወቅ እና በሁሉም ሥፍራ የመገኘት ብቃቶች ብለው ሲጠሯቸው፥ ሦስቱም የእግዚአብሔር ባሕርያት ናቸው። በጉ እግዚአብሔር ወልድ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን የምናመልከው በማንነቱ ምክንያት ነው። ደግሞም ሌላው ሁለተኛው ምክንያት እነሆ፡-

ባለበት ሥፍራ ምክንያት (5፡6) - በመጀመሪያ ደረጃ፥ ኢየሱስ ያለው በሰማይ ነው። በግርግም፥ በኢየሩሳሌም፥ በመስቀል ላይ፥ ወይም በማኅፀን ውስጥ አይደለም ያለው። ወደ ሰማይ ዐርጎ ከፍ ከፍ ብሏል። አዳኛቸው ጠላትን ሁሉ ድል አድርጎ በክብር ሥፍራ እንደተቀመጠና

ከዚያም ሆኖ ነገሮችን እንደሚቆጣጠር መረዳቱ፥ መከራን ለሚቀበሉ ክርስቲያኖች ምንኛ ማበረታቻ ነው! እርሱም ራሱ መከራ ተቀብሎ ነበር፤ ይሁንና እግዚአብሔር መከራውን ወደ ክብር ለውጦታል።

በሰማይስ የክርስቶስ ስፍራ ወዴት ነው? በመካከል። በጉ በሰማይ የሚፈጸሙ ነገሮች ሁሉ ማዕከል ነው። ፍጥረታት ሁሉ (አራቱ እንስሳት)፥ የእግዚአብሔርም ሰዎች (ሽማግሌዎች) በእርሱ ማዕከልነት ይንቀሳቀሳሉ። በዙፋኑ ዙሪያ የሚገኙ መላእክት አዳኙን ከበው ያመሰግኑታል።

እንዲሁም በጉ በዙፋን ላይ ነው። አንዳንድ ስሜታዊ የክርስቲያን ግጥሞችና መዝሙሮች አዳኛችንን ከዙፋኑ ላይ በማውረድ በምድራዊ ሕይወቱ ላይ ብቻ ያተኩራሉ። እነዚህ ግጥሞችና መዝሙሮች «ገራገሩን አናጺ» ወይም «ትሑቱን መምህር» ሲያደንቁ፥ ዳሩ ግን ከሞት የተነሣውን ክርስቶስን ከፍ ከፍ ከማድረግ ይቆጠባሉ። እኛ የምናመልከው በሰማይ ከሚገኙት ሁሉ ማዕከላዊውን ሥፍራ የያዘውን ሕያውና ገዥ የሆነውን የእግዚአብሔር በግ እንጂ፥ በግርግም የተኛ ሕፃን ወይም በመስቀል ላይ ያለ አስከሬን አይደለም።

በሚያደርገው ነገር ምክንያት (5፡8-10) - በጉ መጥቶ መጽሐፉን ሲወስድ (ዳን. 7፡13-14 ተመልከት)፥ ለቅሶው አበቃና ምስጋና ተጀመረ። የእግዚአብሔር ሰዎችና የእግዚአብሔር ፍጥረት ተወካዮች በአዲሱ የምስጋና መርዝሙር በኅብረት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አሰሙ። ዕጣን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የሚያርግ ጸሎት መግለጫ ነውና [መዝ. (141)፡2፤ ሉቃ. 1፡10]፥ ምስጋናውና ጸሎቱ አንድነት መፍጠራቸውን አስተውል። ወደ ኋላም በራእይ 6፡9-11፤ 8፡1-6 «የዕጣን ጸሎቶችን» እናገኛለን።

ምን ዓይነት መዝሙር ነበር የዘመሩት? «ምስጋና ይገባሃል!» ሲሉ ስለነበር፥ በመጀመሪያ ደረጃ፥ የአምልኮ መዝሙር ነበር። ማምለክ ማለት «ምስጋና ... ለእግዚአብሔር እንደሚገባ መግለጽ» ሲሆን፥ ይህም የሚገባው ለኢየሱስ ብቻ ነው። በመጋቢነት በማገለግልበት ጊዜ፥ በእያንዳንዱ የማለዳ አምልኮ ወቅት የጉባዔውን ልብና አእምሮ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያነሣሣ መዝሙር ለመክፈት እሞክር ነበር። ብዙዎቹ ዘመናዊ መዝሙሮች «በክርስቶስ» ላይ የሚያተኩሩ ሳይሆኑ፥ በ«እኔነት»

ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። በመሆኑም፥ የአማኙን ልምምድ ከመጠን በላይ ስለሚያጎሉ፥ የጌታን ክብር ወደ መዘንጋቱ ይደርሳሉ። ለእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ቦታ ቢኖረውም፥ ዳሩ ግን በመንፈሳዊ አምልኮ ክርስቶስን ከሚያወድሱ ጋር የሚወዳደር ሊሆን አይገባውም።

በተጨማሪም፥ ይህ መዝሙር የ«ወንጌል መዝሙር» ነበር። «ታርደሃልና ... በደምህም ... ሰዎች ዋጅተህ ...» «ታርደሃል» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «በጭካኔ መታረድ» ማለት ነው (ቁ. 6 ተመልከት)። ሰማይ ስለመስቀሉና ስለደሙ ይዘምራል። ስለክርስቶስ ደም የሚናገሩትን ቃላት ከሁሉም መዝሙሮች ስንኞች ውስጥ ስላስወገደ አንድ የሃይማኖት ክፍል አንብቤአለሁ። ዳሩ ግን በሰማይ የሚገኙ ፍጥረታት ለዓለም ኃጢአት የታረደውን በግ ስለሚያከብሩ፥ ስለ ክርስቶስ ደም የሚናገሩት ስንኞች ሆነ ተብሎ የተፋቁበት የዚህ ዓይነት መዝሙር፥ ከቶውንም በሰማይ ሊያገለግል አይችልም።

በዘፍጥረት 22 ውስጥ በይስሐቅ ምትክ በግ ሲሠዋ እንመለከታለን፤ ይህም ክርስቶስ ሕይወቱን ለእያንዳንዱ ግለሰብ የመስጠቱ መግለጫ ነው (ገላ. 2፡20 ተመልከት)። በፋሲካ ቀን፥ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ምትክ በግ ይታረድ ነበር (ዘጸ. 12፡3)። ኢየሱስም በተመሳሳይ መንገድ፥ ለእስራኤል ሕዝብ በምትክነት እንደሞተ ኢሳይያስ ይናገራል (ኢሳ. 53፡8፤ ዮሐ. 11፡49-52 ተመልከት)። ዮሐንስም በጉ ለዓለሙ ሁሉ እንደሞተ ያረጋግጣል (ዮሐ. 1፡29)። ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ ኃይልና ደረጃ ላይ በበለጠ ባሰላሰልህ መጠን፥ ይበልጥ ትሑትና ለአምልኮ የተዘጋጀህ ትሆናለህ።

በተጨማሪም፥ ይህ መዝሙር ሚስዮናዊ መዝሙር ነበር። «ከነገድ ሁሉ፥ ከቋንቋም ሁሉ፥ ከወገንም ሁሉ፥ ከሕዝብም ሁሉ» ሰዎች ከኃጢአታቸው ነጽተው ነበር (ራእይ 5፡9)። «ነገድ» የሚለው ወደ ተመሳሳይ የኋላ የዘር ግንድ ሲያመለክት፥ «ቋንቋ» ደግሞ የጋራ መግባቢያ ነው። «ወገን» ማለት ተመሳሳይ ዘር ሲሆን፥ «ሕዝብ» ተመሳሳይ ደንብ ወይም አስተዳደርን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር ዓለሙን ሁሉ ወዷልና (ዮሐ. 3፡16)፥ መሻቱም የደኅንነት መልእክት በዓለም ሁሉ እንዲሰራጭ ነው (ማቴ. 28፡18-20)።

በውጭ አገር ለወንጌል ስርጭት የሚደረገውን የሚሲዮን እንቅስቃሴ የሚቃወም ሆኖ ሳለ፥ ዳሩ ግን ስለዚህ ጉዳይ በሚወያይ አንድ ስብሰባ ላይ ስለተገኘ አንድ ክርስቲያን ከዚህ በፊት ሰምተህ ይሆናል። የምጽዋት ሙዳዩ ከአጠገቡ ሲደርስ፥ «እኔ በሚሲዮን እንቅስቃሴ አላምንም!» አለ። አስተናጋጁም፥ «እንግዲያውስ ይህ የተሰበሰበው ለማያምኑት ነውና ለራስህ የሚሆን ጥቂት ለመውሰድ ትችላለህ» በማለት አስገርሞታል።

ከዚህ በተጨማሪም «የካህናት መንግሥት» እንደመሆናችን፥ ይህ ሰማያዊ ዝማሬ በክርስቶስ ያለንን ልዩ ስፍራ የሚያውጅ የጽሞና መዝሙር ነበር። እንደ ብሉይ ኪዳኑ መልከ ጸዴቅ፥ አማኞች ነገሥታትና ካህናት ናቸው (ዘፍጥ. 14፡ ከቁጥር 17 ጀምሮ፤ ዕብ. 7፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡5-10)። ኢየሱስ ሲሞት የቤተ መቅደሱ መጋረጃ የተቀደደ ሲሆን፥ ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውም መንገድ ተከፍቷል (ዕብ. 10፡19-25)። በመሆኑም፥ ራሳችንን ለክርስቶስ ስናስረክብና መንፈሱም በሕይወታችን እንዲሠራ ስንፈቅድ (ሮሜ 5፡17)፥ «በሕይወት እንነግሣለን» (ሮሜ 5፡17)።

በመጨረሻም፥ ይህ መዝሙር «ትንቢታዊ መዝሙር» ነው - «በምድር ላይ እንነግሣለን» (ራእይ 5፡10)። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ፥ ለ1000 ዓመታት የጽድቅ መንግሥቱን የሚመሠርት ሲሆን፥ እኛም ከእርሱ ጋር አብረን እንገዛለን (20፡1-6)። ከዚያም፥ «መንግሥትህ ትምጣ» የሚለው የቅዱሳን ጸሎት ከፍጻሜ ይደርሳል። ፍጥረትም ከኃጢአት ባርነት ይላቀቅና (ሮሜ 8፡17-23፤ ኢሳ. 11፡1-10)፥ ክርስቶስ በፍትሕና በሥልጣን ይነግሣል።

ይህ ምንኛ ድንቅ መዝሙር ነው! እርሱን በማስከበሩ ሂደት ላይ እነዚህን ሁሉ እውነቶች ለማዋሃድ ብንችል፥ አምልኮአችን የቱን ያህል በበለጸገ ነበር!

ባለው ነገር ምክንያት (ራእይ 5፡11-14) - በዚህ የመዝጊያ ምስጋና ላይ መላእክት ሁሉና በአጽናፈ-ዓለም ውስጥ የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ አዳኙን ለማምለክ ተባብረዋል። ዮሐንስ የሰማው ምን ዓይነት የውኃ ፏፏቴ የሚመስል ጣዕመ-ዜማ ነበር! በዚህ መዝሙር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለፈጸመው የመሥዋዕትነት ሞት ሊቀበላቸው የሚገባቸውን ነገሮች ዘርዝረዋል። በምድር ላይ በነበረ ጊዜ፥ በትሕትናው ምክንያት

ብዙዎቹን ነገሮች ወደ ጎን ስለተወ፥ ሰዎች እነዚህን ነገሮች ለእርሱ እንደሚገቡ አድርገው አላቀረቡለትም ነበር።

የተወለደውም የሞተውም በድካም ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ኃይል ሁሉ የእርሱ ነው። ከድሀም ድሀ ሆኖ ቢጎሳቆልም (2ኛ ቆሮ. 8፡9)፥ የሰማይና የምድር ብልጽግና ሁሉ በእጁ ነው። ሰዎች ቢስቁበትና ሞኝ ብለው ቢጠሩትም፥ እርሱ ግን የእግዚአብሔር ጥበብ ነው (1ኛ ቆሮ. 1፡24፤ ቈላ. 2፡3)።

ሲራብ፥ ሲጠማና ሲዝል፥ ኃጢአት የሌለበት የሰብአዊ ድካም ተካፋይ ሆኗል። ዛሬ በክብር ተቀምጦ፥ ብርታትን ሁሉ በእጁ ይዟል። በምድር ላይ ኃጢአተኞች ሲሳለቁበትና ሲሰድቡት፥ ውርደትንና ኃፍረትን ተቀብሏል። በንጉሥነቱ ላይ በማፌዝ፥ የመሳለቂያ ልብስ፥ አክሊልና በትረ መንግሥት አደረጉለት። ይሁንና አሁን ያ ሁሉ ተለውጦ ክብርን ሁሉ ተቀብሏል!

እንዲሁም በረከት ይገባዋል! በተላለፍነው ሕግ ምክንያት ምንም ዓይነት መርገም እንዳይደርስብን እርሱ በእኛ ምትክ፥ በመስቀል ላይ እርግማን ሆነልን (ገላ. 3፡13)። ለእርሱ ምስጋና ሁሉ ይገባዋል!

አጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ የእግዚአብሔርን በግና በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውን አብን በማመስገን፥ የአምልኮ አገልግሎት ይፈጽማል።

አራቱም እንስሳት ድምፃቸውን አሰምተው «አሜን» ይላሉ። በሰማይ «አሜን» ለማለት ተፈቅዶልናል ማለት ነው።

የዚህ ሁሉ ምስጋና ማዕከላዊው የዓለም መድኃኒት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሆኑ ልብ በል። የአምልኮአቸው ማዕከል አዳኙ ኢየሱስ እንጂ፥ መምህሩ ኢየሱስ አይደለም። ምንም እንኳን ያልተለወጠ ሰው ፈጣሪውን ሊያመሰግን ቢችልም፥ ዳሩ ግን አዳኙን በእውነተኛ ልብ ሊያመሰግን አይችልም።

የሰማያት ሁሉ ምስጋና የቀረበለት፥ በጉ መጽሐፉን ከአብ እጅ ስለወሰደ ነው። ከእንግዲህ፥ ታላቁና ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ዕቅድ ይፈጸምና ፍጥረትም ከኃጢአትና ከሞት ባርነት ነፃ ሊወጣ ይችል ነበር። አንድ ቀን በጉ ማኅተሞቹን በመፍታት፥ በመጨረሻው ወደ እርሱ

ምጽአትና ወደ መንግሥቱ ምሥረታ የሚያመሩትን ክስተቶች ያንቀሳቅስ ነበር።

አንተስ በእነዚህ ሰማያዊ የአምልኮ አገልግሎቶች በምትካፈልበት ጊዜ፥ ለዝማሬያቸው በሙሉ ልብህ «አሜን!» በማለት ትመልስ ይሆን? ክርስቶስን እንደ ፈጣሪ አድርገህ ልታምነው ብትችልም፥ ዳኑ ግን እንደ አዳኝህስ አድርገህ ተቀብለኸው ይሆን?

ይህ ካልሆነ ግን፥ አሁኑኑ ይህንን ለማድርግ ቆርጠህ ተነስተህ ይሆን?

«እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል» (ራእይ 3፡20)።

- 5 -

ማኅተሞቹና የታተሙ ሰዎች

ራእይ 6-7

ከራእይ 4-5 የተገለጸው አምልኮ ከራእይ 6-19 ለተጠቀሰው ቁጣ መዘጋጃ ነው። የአምልኮና ፍርድ ጎን ለጎን የመሄድ ጉዳይ እንግዳ ነገር ቢመስለንም፥ ዳሩ ግን ይህ ሊሆን የቻለው የእግዚአብሔርን ቅድስናም ሆነ የሰውን ኃጢአተኛነት ሙሉ ለሙሉ ባለመረዳታችን ምክንያት ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ለመፈጸም የሚፈልገውን ነገር ሙሉ ለሙሉ ካለመረዳታችንና የክፋት ኃይላትን ተቃውሞ ካለመገንዘባችንም የተነሣ ነው። እግዚአብሔር ታጋሽ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን በመጨረሻው ኃጢአትን መቅጣትና አገልጋዮቹን ከፍርድ ነፃ ማውጣት አለበት።

በዳንኤል 9፡27 መሠረት፥ በእስራኤልና በዓለም አቀፉ አምባገነኑ መሪ (ሐሳዊ-መሲሕ) መካከል ከሚደረገው የስምምነት ውል አንስቶ፥ ክርስቶስ በክፉው ላይ ለመፍረድና መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር እስከሚመለስበት ያሉት ሰባት ዓመታት በእግዚአብሔር የትንቢት የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ተወስነዋል። ከራእይ 6-19 ውስጥ የተጠቀሰውም ይኸው ጊዜ ነው። ከዮሐንስ አስተዋጽኦ በመነሣት (ራእይ 1)፥ ገለጻው በሦስት ክፍሎች እንደሚከፈል እንመለከታለን - የመጀመሪያዎቹ 3 1/2 ዓመታት (ምዕራፍ 6-9)፥ በክፍለ-ጊዜው አጋማሽ ላይ የሚፈጸሙ ነገሮች (ምዕራፍ 10-14)፥ እንዲሁም የመጨረሻዎቹ 3 1/2 ዓመታት ናቸው (ምዕራፍ 15-19)።

ለመከራው ዘመን አጋማሽ እንደተቀሩት ሁለት ክፍሎች ትኩረት የተሰጠው ለምንድን ነው? ይህ ወቅት ሐሳዊ-መሲሑ ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በማፍረስ፥ ጠባቂያቸው በመሆን ፈንታ አሳዳጃቸው የሚሆንበት ጊዜ በመሆኑ ነው (ዳን. 9፡27)።

እነዚህን አሥራ አራት በድርጊቶች የተሞሉ ምዕራፎች በምታነብበት ጊዜ፥ ልብ ልትለው የሚገባው፥ ዮሐንስ የጻፈው በየትኛውም የታሪክ ወቅት የሚገኙትን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለማበረታታት መሆኑን ነው። እንደዚሁም እርሱ የጻፈው በዘመን ፍጻሜ ላይ የሚከናወነውን ትንቢት በተመለከተ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ታላቅ የሥነ-መለኮት ትምህርት

በማስተላለፍ፥ የእግዚአብሔርን ባሕርይና የመንግሥቱን መመሪያዎች ጭምር በሥዕላዊ መልኩ በመግለጽ ነበር። ምዕራፎቹ በእግዚአብሔርና በሰይጣን፥ በአዲሷ ኢየሩሳሌምና በባቢሎን መካከል የሚደረገውን አጽናፍ-አቀፋዊ ግጭት የሚገልጹ እንደመሆናቸው፥ የዮሐንስ ራእይን ለመከፈት በየትኛውም «ቁልፍ» ብንጠቀምም፥ ከፍ ከፍ ያለው የነገሥታት ንጉሥ ሕዝቡን ከፍርድ ነፃ ሲያደርግና ለአሸናፊዎቹም ድልን ሲሰጥ ከመመልከት በቀር ሌላ የምንረዳው ነገር አይኖረንም።

ቤተ ክርስቲያን የሚመለስበትን ጊዜ ስለማታውቅ፥ እያንዳንዱ ትውልድ ምጽአቱን ነቅቶ በመጠባበቅ ሊኖር ይገባል። ስለሆነም የራእይ መጽሐፍ፥ እነዚህ ድርጊቶች በሚፈጸሙበት ወቅት ለሚኖሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆን፥ ለየትኛውም ትውልድ ሁሉ እውነቱን ማስተላለፍ መቻል አለበት። እንደ 13፡9፥ 16፡15 እና 22፡7፥ 18-20 የመሳሰሉት ጥቅሶች የዮሐንስን መልእክት በጊዜ አለመገደብ ያጠናክራሉ። እንዲሁም፥ ይህ እውነት ሐዋርያው ለምን በበርካታ ተምሳሌቶች እንደተጠቀመ ይገልጽልናል - ተምሳሌቶች ከቶውንም ትርጉማቸውን አያጡም። በታሪክ ምዕራፏ ሁሉ፥ ቤተ ክርስቲያን ከባቢሎን (ራእይ 18፡4ን ከኤር. 50-51 ጋር አወዳድር) እና ከሐሳዊ - መሢሕ ጋር መጋፈጥ ያስፈልጋት ነበር (1ኛ ዮሐ. 2፡ ከቁጥር 18 ጀምሮ ተመልከት)። እንግዲህ ራእይ 6-19 የዚህ ግጭት ከፍተኛው ደረጃ ነው።

በራእይ 6-7፥ ዮሐንስ የመከራውን የመጀመሪያ ክፍል እንደ በቀል መከፈያ፥ ብድር የመመለሻና የደኅንነት ጊዜ አድርጎ ገልጿል።

በቀል (ራእይ 6፡1-8)

በዚህ ክፍል፥ ዮሐንስ ስለ መጀመሪያዎቹ አራት ማኅተሞች መከፈት የገለጸ ሲሆን፥ እያንዳንዱ ማኅተም በሚከፈትበት ጊዜ ሁሉ ከአራቱ እንስሳት አንዱ በፈረስ ላይ የተቀመጠውን «መጥተህ እይ» እያለ ይጋብዘዋል። በሌላ አባባል፥ በምድር ላይ የሚከሰቱት ድርጊቶች ሁሉ የሚፈጸሙት እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ከሚሰጠው ሉዓላዊ መመሪያ የተነሣ ነው።

ምናልባትም የፈረሱ ምስል በዘካርያስ 1፡7-17 ከተገለጸው ራእይ ጋር ተዛማጅነት ይኖረው ይሆናል። ፈረሶች እግዚአብሔር በምድር ላይ የሚያደርጋቸውን ተግባራት ያመለክታሉ - መለኮታዊ ዓላማዎቹን

ለመፈጸም የሚጠቀምባቸውን ኃይላት። እንደዚሁም የመርሐ-ግብሩ ማዕከል እስራኤል፥ በተለይም የኢየሩሳሌም ከተማ ነች። (ኢየሩሳሌም በዘካርያስ መጽሐፍ ውስጥ 39 ጊዜ ተጠቅሳለች።) እግዚአብሔር ለእስራኤል የቃል ኪዳን ዓላማ ያለው ሲሆን፥ ያም የተስፋ ቃል እንደተናገረው ይፈጸማል።

እስኪ አሁን እነዚህን ፈረሶችና የፈረሶቹን ጋላቢዎች ለይተን እናውጣ።

ሐሳዊ-መሢሕ (6፡1-2) - ዳንኤል እስራኤልን ከጠላቶችዋ ለመጠበቅ ቃል ኪዳን የሚገባላት አለቃ እንደሚመጣ ይናገራል (ዳን. 9፡26-27)። በሌላ አነጋገር፥ ወደፊት የሚነግሠው ይህ አለቃ የዓለም ሰላም አድራጊ ሰው መስሎ ይቀርባል ማለት ነው! ከድል ወደ ድል እየተሸጋገረ ይሄድና በመጨረሻም ዓለሙን በሙሉ ይቆጣጠራል።

አንዳንዶች በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው፥ ዛሬ በዓለም ውስጥ የነገሠውን የክፋት ኃይል የሚረታው የ«አሸናፊው ክርስቶስ» ምልክት እንደሆነ ይናገራሉ። በዋቢነትም ራእይ 19፡11ን ይጠቅሳሉ፤ ይሁንና በሁለቱ መካከል የሚታየው አንድነት በነጭ ፈረስ ላይ መቀመጣቸው ብቻ ነው። ይህ በፈረስ ላይ የተቀመጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሆነ፥ በመጀመሪያው ላይ ሳይሆን በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ መጠቀሱ እንግዳ ነገር ይመስላል።

ሐሳዊ-መሢሕ፥ የሰይጣን ታላቁ የማስመሰያ መሣሪያ በመሆኑ፥ ክርስቶስን እንደሚመስል መጠበቅ አለብን። አይሁዶች እንኳን (ቅዱሳት መጻሕፍትን ያውቃሉ የሚባሉት) በእርሱ የማስመሰል ተግባር ይታለላሉ (ዮሐ. 5፡43፤ 2ኛ ተሰ. 2፡1-12)። ይህ የከፋ አሳች ሰው፥ ቀስት የሌለበትን ደጋን በመያዝ፥ ሰላማዊ መሪ መስሎ ይታያል። (የጌታችን መሣሪያ ሰይፍ ነው - ራእይ 19፡15)። ሐሳዊ መሢሑ፥ ለጊዜውም ቢሆን ለዓለም ውስብስብ ችግሮች መፍትሔ በማስገኘት፥ እንደ ታላቅ ነፃ አውጪ መሪ ተቀባይነትን ያገኛል።

በቁጥር 2 ላይ «ድል» የሚለው ቃል በግሪክ «እስጢፋኖስ» ሲሆን፥ ትርጉሙም «የድል አክሊል» ማለት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያደርገው አክሊል በግሪክ «ዲያዴማ» የሚል ሲሆን፥ ይህም «የንጉሥ አክሊል» ማለት ነው (19፡12)። ዲያዴማ የእግዚአብሔር

ልጅ ንብረት በመሆኑ፥ ሐሳዊ መሢሕ ከቶውንም ሊጠቀምበት አይችልም።

በመሠረቱ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ከኃጢአትና ከሞት ቀንበር በማላቀቁ (ቈላ. 1፡13፤ የሐዋ. 26፡18)፥ ድል የሚነሣባቸው መንገዶች አሉ። ይሁንና ይህ ድል የተጀመረው በመስቀል ላይ በተቀዳጀው ድል በመሆኑ፥ የማንተሙን መከፈት የሚጠብቅበት ምክንያት የለውም። በኋላ ላይ በግልጽ እንደምንመለከተው በራእይ 6 ውስጥ የሚገኘው የድርጊቶች አቀራረብ ቅደም - ተከተላዊ አይደለም። ጌታችን በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ለደቀመዛሙርቱ ካቀረበው ገለጻ ጋር የሚመሳሰል ነው። በዚህም መሠረት፥ በመጀመሪያ ደረጃ የተጠቀሰው የሐሰተኛ ክርስቶሶች መገለጽ ነው (ማቴ. 24፡5)።

ጦርነት (6፡3-4) - የሐሳዊ መሢሕ ድል በሰላም ይጀመርና ወዲያውኑ ቀስት የለሹ ደጋን በሰይፍ ይቀየራል። ቀይ ቀለም ብዙውን ጊዜ ከሽብርና ከሞት ጋር የተያያዘ ነው - ቀይ ዘንዶ (ራእይ 12፡3)፥ ቀይ አውሬ (17፡3)። ይህም የከፋ የደም መፋሰስ ተግባር ነው። ቃየል አቤልን ከገደለበት ጊዜ አንሥቶ ጦርነት የሰው ልጅ ልምምድ አካል ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለሰዎችና ለመንግሥታት ሕገ ወጥ ተግባራት ኃላፊነቱን ባይሸከምም፥ ሆኖም ግን ይህ ሁኔታ በበላይ ተቆጣጣሪነቱ ጸንቶ እንደሚኖር በየዘመናቱ ለሚኖሩ አማኞች ሊያስታውሳቸው ይገባል።

ረሃብ (6፡5-6) - ጥቁር ቀለም ብዙውን ጊዜ ከረሃብ ጋር የተያያዘ ነው (ኤር. 14፡1-2፤ ሰቆ. ኤር. 5፡10)። ረሃብና ጦርነት ጎን ለጎን ይሄዳሉ። የምግብ እጥረት ብዙውን ጊዜ የዋጋ ንረትን ያስከትልና መንግሥትን ያለውን እንዲያከፍል ያስገድደዋል። «እንጀራን በሚዛን ለክቶ መብላት» የምግብን እጥረት የሚያመለክት የአይሁዶች አባባል ነው (ዘሌ. 26፡26)። በዚያን ጊዜ ለቀን ሠራተኞች የሚሰጠው አንድ ዲናር ሲሆን፥ ይህም ቢሆን፥ ዛሬ ከምንጠቀምበት ሣንቲም በላይ ብዙ ነገሮችን የመግዛት አቅም ነበረው (ማቴ. 20፡2)። የስንዴው ሚዛን አንድ እርቦ ሲሆን፥ ይህም ለአንድ ሰው ዕለታዊ ቀለብ የሚበቃ ነው። ረሃብ ከመከሰቱ በፊት፥ አንድ ሰው በአንድ ዲናር ከስምንት እስከ አሥራ ሁለት መስፈሪያ ስንዴ መግዛት ሲችል፥ ረከስ የሚለውን ገብስ ደግሞ ከዚህም በተሻለ ሁኔታ መግዛት ይቻል ነበር።

ይሁንና፥ በመከራው ዘመን አንድ ሰው ዕለታዊ ምግቡን ለማግኘት ብቻ ቀኑን ሁሉ መሥራት ይኖርበታል። ለቤተሰቡ የሚተርፍ እንኳ አይኖርም! በተመሳሳይ ጊዜ፥ ሀብታሞች በተትረፈረፈ ዘይትና የወይን ጠጅ ይደሰታሉ። ሐሳዊ-መሢሕ የተራበውን ብዙሃን ለመመገብ ቃል እንደ መግባቱ፥ በመጨረሻ የምጣኔ ሀብት አውታሮችን መቆጣጠሩ አስደናቂ አይሆንም (ራእይ 13፡17)።

ሞት (6፡7-8) - ዮሐንስ ሁለት የሰው አምሳያዎችን ተመልክቷል - ሞት ሐመር ፈረስ ላይ ተቀምጦ ሲጋልብና ሲኦልም (የሙታን ስፍራ) ሲከተለው። ክርስቶስ የሞትና የሲኦል መክፈቻ ስላለው (1፡18)፥ ሁለቱም አንድ ቀን ወደ እሳት ባሕር ይጣላሉ (20፡14)። ሞት አካልን ሲፈልግ፥ ሲኦል ደግሞ የሙታንን ነፍሳት ይሻል (20፡13)። ዮሐንስ እነዚህ ጠላቶች በሰይፍ፥ በረሃብ፥ በመቅሰፍት (ሞት)፥ እና በዱር አራዊት መሣሪያነት ታጥቀው ምርኮን ለመበዝበዝ ሲወጡ ተመለከተ። በጥንት ዘመን፥ ረሃብ፥ መቅሰፍትና የዱር አራዊት ጥቃት ምንጊዜም ከጦርነት በኋላ የሚደርሱ ችግሮች ነበሩ (እንዲሁም ኤር. 15፡2፤ 24፡10፤ ሕዝ. 14፡21 ተመልከት)።

አምባ ገነንና ወራሪ መሪዎች የዓለምን ጦርነት ማስከተላቸው፥ ረሃብንና መቅሰፍትን ማስነሣታቸው አዲስ ነገር አይደለም። ከሮም መንግሥት ጀምሮ በቅርቡ እስከተካሄዱት ጦርነቶች ድረስ በመከራ ውስጥ ያለፉት ሰዎች፥ እነዚህ አራት ጨካኝ ፈረሰኞች የሚያስከትሏቸውን ጥፋቶች በቀላሉ ሊረዱ ይችላሉ። ለዚህም ነው የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ በታሪክ ሁሉ መከራ ለሚደርስባቸው ክርስቲያኖች የማበረታቻ ምንጭ የሚሆነው። በጉ ማኅተሞቹን ሲፈታ በሚመለከቱበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ነገሮችን በመቆጣጠር ላይ እንዳለና ዓላማዎቹም እንደሚፈጸሙ ይረዳሉ።

ምላሽ (ራእይ 6፡9-17)

ዮሐንስ ለማኅተሞቹ መፈታት ሁለት ምላሾችን ሰጥቷል - ከምላሾቹም አንዱ በሰማይ የተሰማ ሲሆን ሌላው ደግሞ ምድራዊ ነው።

ስማዕታት (6፡9-11) - የብሉይ ኪዳን ካህን የእንስሳት መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ፥ የእንስሳውን ደም በነሐስ መሠዊያው መሠረት ላይ ይረጭ ነበር (ዘሌ. 4፡7፥18፥25፥30)። በብሉይ ኪዳን ተምሳሌት፥ ደም ሕይወትን ይወክላል (17፡11)። ስለሆነም እነዚህ በዮሐንስ ራእይ

ውስጥ የተጠቀሱት «ከመሠዊያው በታች» የሚገኙት የሰማዕታት ነፍሳት፥ ሕይወታቸው ለእግዚአብሔር ክብር በመሥዋዕትነት መስጠቱን ያመለክታሉ። ሐዋርያው ጳውሎስም ፊልጵስዩስ 2፡17ን እና 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡6ን በሚጽፍበት ጊዜ፥ እንዲህ ዓይነት አሳብ ነበረው።

«ሰማዕት» የሚለው ቃል በግሪክ «ማርተስ» ማለት ሲሆን፥ ይኸውም «ምስክር» የሚል ፍች አለው (ራእይ 2፡13፤ 17፡6 ተመልከት)። እነዚህ ለቅዱሱ ለእግዚአብሔር እውነትና ለኢየሱስ ክርስቶስ በነበራቸው ምስክርነት ምክንያት፥ በጠላት የታረዱ ናቸው። ሰይጣን ይታለሉና ውሸቱን ይቀበሉ ዘንድ ስለሚሻ፥ እንደዚያው ሁሉ የሐሳዊ-መሲሑም ኃይላት እውነትን አይቀበሉም (19፡20፤ 20፡10፤ እንዲሁም 2ኛ ተሰ. 2፡9-12 ተመልከት)።

አሁንም ቢሆን ገዳዮቻችው ገና በሕይወት ያሉ ናቸውና እነዚህ ሰማዕታት ምናልባትም በመከራው ዘመን መጀመሪያ ላይ የሚገኙ መሆን አለባቸው። ይሁንና እነዚህ ሰማዕታት ሕይወታቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስና ለእግዚአብሔር እውነት የሰጡትን ሁሉ የሚወክሉ ሲሆን፥ ዛሬም ፈለጋቸውን ለመከተል ለሚጥሩት ሁሉ በአርአያነታቸው ማበረታቻዎች ናቸው። እነዚህም ቅዱሳን የሰማዕታት ነፍሳት በሰማያት ሆነው ትንሣኤን በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙና (ራእይ 20፡4) ሰማያዊውን ክብር ለብሰው በሰላም እንደሚኖሩ ያረጋግጡልናል።

ሆኖም ግን እነዚህ ቅዱሳን እግዚአብሔር ነፍሰ ገዳዮቻቸውን እንዲበቀል መደለያቸው ክርስቲያናዊ አመለካከት ነውን? ኢየሱስና እስጢፋኖስ በበቀል ምትክ እግዚአብሔር የሚገድሉአቸውን ሰዎች ይቅር እንዲል ጸልየዋል። እነዚህም ሰማዕታት በምድር ላይ በሚታረዱበት ጊዜ፥ ለሚገድሉአቸው ሰዎች በተመሳሳይ እንደጸለዩላቸው አልጠራጠርም - ይህም ተገቢ ነው (ማቴ. 5፡10-12፥ 43-48)።

ይሁንና ታላቁ ጥያቄ፥ ጠላቶቻቸው ላይ ፍርድ የመስጠቱ ጉዳይ ሳይሆን፥ «መቼ» እንደሚፈረድባቸው ነው። «እስከ መቼ ነው፥ ጌታ ሆይ?» የሚለው በመከራ ውስጥ የሚገኙ የእግዚአብሔር ሰዎች ለዘመናት የሚያሰሙት ጩኸት ነው [መዝ. (74)፡9-10፤(79)፡5፤ (94)፡3-4፤ ዕንባ. 1፡2 ተመልከት]። በሰማይ የሚገኙ ቅዱሳን እግዚአብሔር በመጨረሻው ጊዜ በኃጢአት ላይ በመፍረድ በምድር ላይ ጽድቅን

እንደሚመሠርት ቢያውቁም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ትክክለኛ የጊዜ ሰሌዳ አያውቁም ነበር። የፈለጉት የግል በቀልን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ቅድስና መገለጽና የፍትሑን መመሥረት ነበር። ዛሬ «መንግሥትህ ትምጣ!» በማለት ከልቡ የሚጸልይ ማንኛውም አማኝ የእነዚህን ቅዱሳን የልመና ቃል እንደ ገደል ማሚቶ እያስተጋባ ነው።

እግዚአብሔርም ለእነዚህ ሰማዕታት መሥዋዕትነታቸው በእርሱ የተወሰነ እንጂ በአጋጣሚ የተፈጸመ እንዳልሆነና ሌሎችም ፈለጋቸውን እንደሚከተሉ በግልጽ አስታወቃቸው። በሕዝቡ ሞት ውስጥ እንኳ እግዚአብሔር ከተቆጣጣሪነቱ አንዴም አይቦዝንም [መዝ. (116)፡ 15]፤ በመሆኑም፥ ምንም የሚያስፈራን ነገር የለም።

ጌታ ተመልሶ መንግሥቱን እስከሚመሠርትበት ጊዜ ድረስ በርካታ ሌሎች ቅዱሳን ይታረዳሉ (ራእይ 11፡7፤ 12፡11፤ 14፡13፤ 20፡4-5)። በዚያን ጊዜም እንደዛሬው ጠላት የሚያሸንፍ ይመስላል፤ ይሁንና እግዚአብሔር የመጨረሻ ቃል ይኖረዋል። በ«ሠለጠነው» በሃያኛው ክፍለ ዘመናችን እንኳ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ እውነተኛ አማኞች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ሠውተዋል፤ ይሁንና የሕይወት አክሊል ይጠብቃቸዋል (2፡10)።

የምድር ነዋሪዎች (6፡12 - 17) - ሰማዕታት በሰማይ ሆነው «ተበቀልልን!» ሲሉ፥ በምድር ላይ የሚኖሩና ከደኅንነት ርቀው የሚገኙ ሰዎች፥ «ሰውረን!» እያሉ ይጮኻሉ። የስድስተኛው ማኅተም መከፈት ሦስቱን የመጀመሪያ ርዕደ-ምድር እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፥ ዓለም አቀፍ መቅሰፍቶችንና አደጋዎችን ያስከትላል (6፡12፤ 11፡13፤ 16፡18-19)። ተፈጥሮ በሙሉ በጥፋት ይመታል - ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ ሰማያት፥ ተራሮችና ደሴቶች ሁሉ። ይህን ትዕይንት ከኢዩኤል 2፡30-31 እና 3፡15፥ እንዲሁም ከኢሳይያስ 13፡9-10 እና 34፡2-4 ጋር አወዳድር።

ዮሐንስ የጻፈው ተምሳሌታዊ ቋንቋ በመጠቀም ቢሆንም ቅሉ፥ እነዚህ ቁጥሮች እጅግ የበረታውን ሰው ሳይቀር የሚያስደነግጡ ትዕይንቶችን ያቀርባሉ። ሰዎች ከእግዚአብሔርና ከበጉ ፊት ለመሰወር ጥረት ያደርጋሉ። እንግዲህ ከበጉ ፊት ለመሰወር የሚደረገው መሻት ይታይህ! አንድ ጊዜ ዶክተር ቫንስ ሐቭነር፥ ቀኑ የሚመጣው እጅግ

ውድ የሆነው ርስት እንኳን በመሬት ውስጥ እንደሚገኝ ጉድጓድ በሚቆጠርበት ጊዜ ነው ብለው ነበር። ትክክል ናቸው።

በራእይ ጥናታችን ወደፊት እየገፋን ስንሄድ፥ የ«እግዚአብሔርን ቁጣ» የተለያዩ ገጽታዎች እንመለከታለን (11፡18፤ 14፡10፤ 16፡19፤ 19፡15)። እንዲሁም ደግሞ የሰይጣንን ቁጣ (12፡17) እና ሰዎችም እግዚአብሔርን በመቃወም የሚያሰሙትን የቁጣ ጩኸት እናያለን (11፡18)። ወንዶችና ሴቶች ለእግዚአብሔር ፍቅር ራሳቸውን ካልሰጡና በእግዚአብሔር ጸጋ ካልተለወጡ በስተቀር ከእግዚአብሔር ቁጣ የሚያመልጡበት ምንም መንገድ አይኖርም።

ማዕረግም ሆነ ሀብት በዚያች አስጨናቂ ዕለት ማንንም ሊታደግ አይችልም። በዮሐንስ መዘርዝር ውስጥ፥ ነገሥታት፥ የጦር አዛዦችና ባሪያዎች፥ ሀብታሞችና ድሆች ይገኛሉ። «ማን ሊቆም ይችላል?»

«የበጉ ቁጣ» የሚለው ሐረግ አደናጋሪ ይመስላል። በመሆኑም «የአንበሳ ቁጣ» የሚለው የበለጠ ተዛማጅነት ያለው ነው። በክርስቶስ ትሕትናና ገርነት ላይ ማተኮሩን ስለተላመድን (ማቴ. 11፡28-30)፥ ቅድስናውንና ፍትሕ አድራጊነቱን እንዘነጋለን። ሕፃናትን ወደ መቅደሱ የተቀበላቸው ይኸው ኢየሱስ ነጋዴዎችን ከዚያው መቅደስ ውስጥ አስወጥቷል። ይህም፥ የእግዚአብሔር ቁጣ ትክክለኛ ሕይወት ለሚመሩት ሁሉ ቅዱስ ፍቅር እንዳለውና ለክፉዎች ደግሞ የተቀደሰ ጥላቻ እንዳለው የሚያመለክት መረጃ እንጂ፥ እንደ ሕፃናት ወይም ትዕግሥት እንደሌላቸው ወላጆች ዓይነት የግንፍል ስሜት ፍንጣቂ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው። በዓለም ውስጥ በሚገኘው ክፋት ላይ በፍትሕ የማይፈርደውን አምላክ ለማምለክ የሚፈልግ ሰው ቢኖር፥ መንፈስ ደካማና ስሜታዊነት የሚያጠቃው ሰው ብቻ ነው።

በተጨማሪም፥ በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱት ሰዎች «ይቅርታ ለመጠየቅ» ፈቃደኞች ያልሆኑ ናቸው። እነርሱም ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለመስጠት ካለመፈለጋቸውም በላይ፥ ወደ እግዚአብሔር በእምነት ከመሮጥ ይልቅ ከእግዚአብሔር ፊት (እንደ አዳምና ሔዋን) መሰወርን የሚመርጡ ናቸው። በመሆኑም ይህ አድራጎታቸው ፍርድ በራሱ የሰውን ልብ እንደማይለውጥ ያረጋግጥልናል። ይህን መሰሉ ሰዎች

ከእግዚአብሔር ፊት መሰወር ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ስሙን በማርከስ ይሰድቡታልም (ራእይ 16፡9፥ 11፥ 21)።

ይሁንና በዚህ አስጨናቂ የፍርድ ሰዓት ለአማኞች አንዳች ተስፋ ይኖር ይሆንን? ደግሞስ ከሐሳዊ- መሢሕ ጋር ቃል ኪዳን የተጋቡት የእግዚአብሔር ምርጦች የሆኑት የአይሁዶችስ ጉዳይ እንዴት ይሆን? በእርግጥ ቤተ ክርስቲያን ከተነጠቀች በኋላ እንኳ ሰዎች በጌታ ማመናቸው አይቀርም፤ ዳሩ ግን መከራውን እንዴት ያልፉት ይሆን? አንዳንድ መልሶችን ለማግኘት ወደ ራእይ 7 እናልፋለን።

ይሁንና በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን የዮሐንስ ሦስተኛ ዓቢይ ነጥብ - ደኅንነት - ከማየታችን በፊት፥ በማቴዎስ 24 ውስጥ በተጠቀሱ የክርስቶስ ትንቢታዊ ቃላትና ዮሐንስ በራእይ 6 በጻፈው መካከል የሚገኙትን ተመሳሳይነቶች እንመለከታለን። የሚከተለው አጭር አስተዋጽኦ ይህንኑ ግልጽ ያደርገዋል።

ማቴዎስ 24	ራእይ 6
- ሐሰተኛ ክርስቶሶች (ቁ. 4-5)	- ነጭ ፈረስ ጋላቢ (ቁ. 1-2)
- ጦርነቶች (ቁ. 6)	- ቀይ ፈረስ - ጦርነት (ቁ. 3-4)
- ረሃብ (ቁ. 7)	- ጥቁር ፈረስ - ረሃብ (ቁ. 5-6)
- ሞት (ቁ. 7-8)	- ጉራቻ ፈረስ- ሞት (ቁ. 7-8)
- ሰማዕታት (ቁ. 9)	- ሰማዕታት ከመሠዊያው በታች (ቁ. 9-11)
- ዓለም አቀፍ - ሥርዓተ አልበኝነት (ቁ. 10-13)	- ዓለም አቀፍ ሥርዓተ- አልበኝነት (ቁ. 12-17)

ማቴዎስ (24፡14) በዓለም ሁሉ ስለመንግሥት ወንጌል መሰበክ የሚናገር ሲሆን፥ ራእይ 7ም ከዚሁ ጋር የሚስማማ ነው። ምናልባትም እግዚአብሔር በታተሙት 144,000 አይሁዶች አማካይነት ቃሉን ለዓለም በማካፈል፥ በውጤቱም እጅግ በርካታ ሕዝቦችን ያድን ይሆናል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተገለጹትን ሁለት የሰዎች ቡድኖች ማነጻጸሩ መልካም ነው።

7፡1-8	7፡9-17
- አይሁዶች	- ከነገድ ሁሉ የተውጣጡ አሕዛቦች
- በቁጥር 144, 000	- ሊቆጠሩ የማይችሉ
- በምድር ላይ የታተሙ	- በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት የቆሙ

ምንም እንኳን 144,000ዎቹ አይሁዶች የእግዚአብሔር ልዩ መልእክተኞች ስለመሆናቸውና እጅግ በርከተው የሚታዩትም አሕዛቦች በእነዚህ ምርጦች አገልግሎት መዳናቸው በግልጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባይጠቀስም፥ ትክክለኛው ድምዳሜ ግን ይኸው ይመስላል። ይህ ከሆነ ደግሞ፥ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተጣምረው የመቅረባቸው ምሥጢር ምን ይሆን? እንዲሁም በማቴዎስ 24፡14 ላይ የሚገኘው ተመሳሳይ አሳብ እንደሚጠቁመው፥ 144,000ዎቹ በታላቁ መከራ ጊዜ ለጌታ ይመሰክራሉ።

የታተሙ አይሁዶች (7፡1-8) - መላእክት ከተፈጥሮ ኃይላት ማለትም ከነፋስ (7፡1)፥ ከእሳት (14፡18)፥ እና ከውኃ ጋር ተዛምደዋል (16፡5)። ነፍሳትን ማቆም ከማዕበል በፊት የሚደረገውን ቆይታ ያመለክታል። እግዚአብሔር ተፈጥሮን ሁሉ ስለሚቆጣጠር፥ በቁጣው ቀን በሰው ልጅ ላይ ለመፍረድ በተፈጥሮ ኃይላት ይጠቀማል። «በአራቱ የምድር ማዕዘናት» የሚለው ሐረግ፥ በኢሳይያስ 11፡12 ወይም በዕለታዊ ጋዜጣ ላይ ከሚታየው ዘገባ ይልቅ ሳይንሳዊነት አይጎድለውም።

በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ማኅተም ባለቤትነትንና ጥበቃን ያሳያል። ዛሬ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የታተሙ ሲሆን (ኤፌ. 1፡13-14)፥ ይህም እንደዳንንና በአስተማማኝ ሁኔታ ላይ እንደምንገኝ፥ ብሎም ደግሞ አንድ ቀን ወደ ሰማይ እንደምንወሰድ የሚያረጋግጥልን የእግዚአብሔር ዋስትና ነው። 144,000 አይሁዶች የአብን ስም እንደማኅተም የሚቀበሉ ሲሆን (14፡1)፥ ይህም ሐሳዊ - መሲሕ

እንደማኅተም የሚቀበሉ ሲሆን (14፡1)፥ ይህም ሐሳዊ - መሲሕ ለተከታዮቹ ከሚሰጣቸው «የአውሬው ምልክት» የሚቃረን ነው (13፡17፤ 14፡11፤ 16፡2፤ 19፡20)።

ይህ ማኅተም የተመረጡትን አይሁዶች «ምድርንና ባሕርን» ከሚጎዱ ፍርዶች የሚጠብቅ ሲሆን (7፡2)፥ የመጀመሪያዎቹ አራት መላእክት መለከቶቻቸውን በሚነፉበት ጊዜ የሚፈጸም ነው (ምዕ. 8)። የከፉ አንበጣዎች ከጥልቁ በሚለቀቁበት ጊዜ ፍርዶቹ እየከበዱ ይሄዳሉ (9፡1-4)። ከእነዚህ አስፈሪ ፍርዶች ተጠብቀው፥ 144,000ዎቹ ተግባራቸውን በመፈጸም ጌታን ያስከብራሉ።

በየትኛውም ዘመን ቢሆን እግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ቅሪቶች አሉት። ኤልያስ ለእግዚአብሔር የቆመው እርሱ ብቻ እንደሆነ ቢያስብም፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ተጨማሪ 7,000 ታማኝ ሰዎች ነበሩት (1ኛ ነገሥት 19፡18)። በራእይ 7 ውስጥ የተገለጸው የማተም ተግባር፥ የእግዚአብሔር ፍርድ ከመውረዱ በፊት ታማኝ ሰዎች ከታተሙበት ከሕዝቅኤል 9፡1-7 ውስጥ ዳራውን ያገኛል። በመሆኑም፥ እነዚህ 144,000 አይሁዶች በመጨረሻው ዘመን ከእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው ምርጥ ሕዝቦች ሲሆኑ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በየትኛውም የታሪክ ወቅት ላይ የሚገኙትን ታማኝ ምርጦች ያመለክታሉ።

ቁጥር 144,000 ፍጹምነትንና ሙላትን ስለሚያመለክት፥ ጠቃሚ ቁጥር ነው (144 = 12 X 12)። አንዳንዶቹ በዚህ ቁጥር ውስጥ «መላውን» የእግዚአብሔርን ምልዓትነት ይመለከቱበታል - አሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች (የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን) እና አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት (የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን)። ይህ የዚህ ምንባብ ጥሩ ማዛመጃ ሊሆን ቢችልም፥ ዳሩ ግን እነዚህ 144,000ዎቹ ሁሉ አይሁዶች እንደሆኑና ነገዳቸውም ስለተጠቀሰ፥ መሠረታዊው ትርጓሜ መሆን ግን አይችልም።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው ከ144,000ዎቹ አንዱ እንደሆነ ሲነግረኝ፥ «የየትኛው ነገድ አባል ነህ? ይኼን ልታረጋግጥ ትችላለህ?» ብዬ ጠየቅሁት። በመሠረቱ፥ ይኼን ሊያረጋግጥ አይችልም ነበር፤ ከአይሁድ ውጭ ማንም ሰው ራሱን እንደ አንዱ የዚህ ነገድ አባል አድርጎ ሊቆጥር የሚችል የለም። የዘር ሐረጎቹ ዘገባዎች በሙሉ ተቆጥሮ ለመድረስ

የመወሰዳቸውና «የመጥፋታቸው» ጉዳይ እንኳ ለእግዚአብሔር ችግር አይሆንበትም። እርሱ ሕዝቡንና ምንጫቸውን ያውቃል (ማቴ. 19:28፤ የሐዋ. 26:7፤ ያዕ. 1:1 ተመልከት)።

ይህም ሆኖ፥ ምንባቡን ቃል በቃል ለመተርጎም የምናደርገው ሙከራ እንከን የለውም ለማለት አይደለም። ከሌሎች ነገዶች ጋር ርስት ሳይኖረው ሌዊ በዚህ የዘር ሐረግ ውስጥ የተጠቃለለው ለምን ይሆን? (ዘኁ. 18:20-24፤ ኢያሱ 13:14)። ብዙውን ጊዜ ከወንድሙ ምናሴ ጋር ተለይቶ የማይጠቀሰው ኤፍሬም ተዘንግቶ ዮሴፍ የተመዘገበው ለምንድነው? በመጨረሻም፥ ዳን በዚህ ስፍራ ባይጠቀስም ቅሉ፥ ዳሩ ግን በሕዝቅኤል ስለ መሬት ክፍፍል በሚናገረው ክፍል ውስጥ የተጠቀሰው ለምንድነው? (ሕዝ. 48:1)። ለእነዚህ ጥያቄዎች በርካታ የ«ይመስላል» አሳቦች ቢቀርቡም፥ ዳሩ ግን ትክክለኞቹን መልሶች አናውቃቸውም። እስራኤል የሚለውን በቤተ ክርስቲያን በመተካት በመንፈሳዊ መንገድ ብንተረጉመው እንኳ፥ ከዚህ የተሻለ እርግጠኛነት አይኖረንም። «ምሥጢራቱን» ለእግዚአብሔር ልንተወው ሲገባ፥ ሆኖም እነዚህንም ነገሮች አለማወቃችን ለምናውቀው ከመታዘዝ እንዳያቅበን ልንጠነቀቅ ይገባል (ዘዳ. 29:29)።

የዳኑ አሕዛቦች (7:9-17) - የራእይ መጽሐፍ አትኩሮት በዓለም ሁሉ ለሚኖሩ ሰዎች እግዚአብሔር በሚያደርጋቸው ነገሮች ላይ ስለሆነ፥ መጽሐፉን ስታነብ ዓለም-አቀፋዊ አመለካከት ማዳበርህ የማይቀር ይሆናል። በጉ የታረደው፥ «ከነገድ ሁሉ፥ ከቋንቋም ሁሉ፥ ከወገንም ሁሉ፥ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን» ለማዳን ነበር (ራእይ 5:9)። በዚህ ሥፍራ የተገለጹት እጅግ ብዙ ሰዎች «ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም» የመጡ ነበሩ (7:9)። የጌታችን የሥልጣን ቃል፥ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» የሚል ነበር (ማር. 16:15)።

የእነዚህ እጅግ በርካታ ሕዝቦች ማንነት አጠያያቂ አይሆንም። ከሽማግሌዎች አንዱ ለዮሐንስ ገልጾለታልና (ቁ. 14) - በመከራው ጊዜ ውስጥ በክርስቶስ በማመን የዳኑ አሕዛቦች ናቸው። (ይህንኑ የሰዎች ቡድን በራእይ 14 ደግሞ እንመለከታለን)። ዛሬ በብዙ የዓለም ክፍሎች በአንጻራዊ መልኩም ቢሆን ለክርስቶስ መመስከሩ ቀላል ሲሆን፥ በመከራው ወቅት፥ በተለይም በመጨረሻው አጋማሽ ላይ ሁኔታው

እንዲህ አይሆንም። በዚያን ጊዜ፥ ሰዎች «የአውሬውን ምልክት» እስካልተቀበሉ የመግዛትና የመሸጥ ዓቅም ስለማይኖራቸው መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን እንኳ ለማሟላት ይሳናቸዋል። ቁጥር 16 እንደሚያመለክተው፥ ረሃብ (13፡17 ተመልከት)፥ ጥማት (16፡4 ተመልከት)፥ ብሎም የመጠለያ እጦት ይፈታተናቸዋል። (በ16፡8-9 ስለፀሐይ ቃጠሎ የሚለውን ተመልከት)።

በዙፋኑ ፊት ቆመው ሳሉ በዚያ አካባቢ ያለመቀመጣቸው እውነታ፥ እነዚህ ወገኖች ከሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ጋር እንዳልተቀላቀሉ ያሳያል። ዮሐንስም ራሱ እነማን እንደሆኑ አያውቅም ነበር! የብሉይ ኪዳን አማኞች ወይም ቤተ ክርስቲያን ቢሆኑ ኖሮ፥ ዮሐንስ ባወቃቸውም ነበር። የሽማግሌው ማንነታቸውን ለዮሐንስ የመናገር አስፈላጊነት ልዩ ሕዝብ እንደሆኑ ያሳያል፤ በእርግጥም ናቸው።

በመሠረቱ፥ በሰማያዊቱ ከተማ (ራእይ 21-22)፥ ልዩነቶች ሁሉ ይወገዱና ሁላችንም በክብር የእግዚአብሔር ሕዝብ እንሆናለን። ሆኖም እግዚአብሔር መርሐ ግብሩን በሰብአዊ ታሪክ ውስጥ በመፈጸም ላይ እስካለ፥ በአይሁዶች፥ በአሕዛብ፥ በቤተ ክርስቲያንና በታላቁ መከራ ቅዱሳን መካከል ልዩነቶች ይኖራሉ።

ዮሐንስ ስለእነዚህ ሰዎች ግሩም ገለጻ አቅርቧል።

በመጀመሪያ፥ በእግዚአብሔርና በበጉ ዙፋን ፊት ስለቆሙ፥ «ተቀባይነት አግኝተዋል»። ውሸታሞች በሚወደዱበትና ሰይጣን በሚሠለጥንበት ጊዜ ለእውነት በመቆማቸው ምክንያት በምድር ላይ ተቀባይነትን ስለማጣታቸው ጥርጥር የለውም። ነጫጭ ልብሶቻቸውና የዘንባባ ዝንጣፊዎቹ ድልን ያውጃሉ - እውነተኛ ድል አድራጊዎች ነበሩ። አይሁዶች ልዩ ብሔራዊ የደስታ ጊዜ በሆነው የድል በዓላቸው ዕለት በዘንባባ ዝንጣፊዎች ይጠቀማሉ (ዘሌ. 23፡40-43)።

ከዚያም፥ እጅግ ደስተኞች ስለመሆናቸው እንመለከታለን። ለእግዚአብሔርና ለበጉ የምስጋና መዝሙሮችን ሲያቀርቡ፥ ዙፋኑን የከበቡትም ሁሉ በአምልኮአቸው ውስጥ ተሳታፊዎች ይሆናሉ።

ሦስተኛ፥ ሽልማት ተቀብለዋል። በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት የመቅረብና እርሱን የማገልገል ዕድል ተሰጥቷቸዋል። የእግዚአብሔር

ሰዎች ወደ መንግሥተ ሰማያት ሲደርሱ፥ በዚያ የሚሠሩት ሥራ ይጠብቃቸዋል! እርሱን በፍጹምነት ለማገልገል መቻል አለብን። በጕ እረኛችን ይሆንና በመልካም ነገሮች ሁሉ ያረካናል (ኢሳ. 49፡10፤ ራእይ 21፡4 አንብብ)።

የሰባተኛው ማኅተም መከፈት «የሰባት መለከቶችን ፍርዶች» የሚያስከትል ሲሆን (ራእይ 8 - 11)፥ በዚህም ጊዜ የእግዚአብሔር ፍርድ በጥልቀትም ሆነ በደረጃ ይጨምራል። ይሁንና ይህ ከመሆኑ በፊት፥ እግዚአብሔር በቁጣው ጊዜ ምሕረቱን እንደሚያስብ የሚያረጋግጥልን ቃል ይገኛል (ዕንባ. 3፡2)። ከእግዚአብሔር ቁጣና በሰይጣንና በጭፍሮቹ ከሚነሣው ሽብር ባሻገር፥ እጅግ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይድናሉ።

ዘመኑ ወይም የአገዛዝ ሥርዓቱ ምንም ዓይነት ቢሆን፥ የእግዚአብሔር የማዳን መንገድ ሁልጊዜም አንድ ነው - የእግዚአብሔር በግ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን።

ይሁንና፥ በዚያን ጊዜ እጅግ ብዙ ሰዎች አዳኙን ትተው «በአውሬው» የሚታመኑበትም አሳዛኝ ሁኔታ ይኖራል። ዛሬስ ቢሆን ከክርስቶስ ይልቅ ሰይጣንን፥ ከሚመጣው ይልቅ አሁን ያለውን ዓለም የሚመርጡ ሰዎች አሉ አይደለም? እነዚህም ሰዎች «የአውሬውን ምልክት» እንደሚቀበሉት የታላቁ መከራ ዘመን ሰዎች ሁሉ የተኮነኑ ይሆናሉ።

አንተም እስከዛሬ በአዳኙ ካላመንህ፥ ዛሬውኑ እመንበት። በእርሱ ካመንህ ደግሞ፥ ሌሎችም ከሚመጣው ቁጣ ይድኑ ዘንድ የማዳኑን የምሥራች አካፍላቸው።

- 6 -

መለከቶቹን ንፉ!

ራእይ 8 - 9

አሁን የማኅተም ፍርዶች የተፈጸሙ ሲሆን፥ የመለከት ፍርዶች ይጀምራሉ። እነዚህም የመለከት ፍርዶች በባቢሎን ውድመትና በክርስቶስ ወደ ምድር መመለስ በሚያበቁ፥ የጽዋ ፍርዶች ይተካሉ። ከማኅተሞች ወደ መለከቶች ከዚያም ወደ ጽዋዎቹ በምንሄድበት ጊዜ፥ ፍርዶቹ እየከፉ እንደሚሄዱ ልብ በል። እንዲሁም፥ ቀጥሎ የተመለከተው አጭር ማጠቃለያ እንደሚያሳየው የመለከትና የጽዋ ፍርዶች በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ፡-

መለከቶች	የፍርዱ ተጠቂ	ጽዋዎች
1. 8፡1-7	ምድር	16፡1-2
2. 8፡8-9	ባሕር	16፡3
3. 8፡10-11	ወንዞች	16፡4-7
4. 8፡12-13	ሰማያት	16፡8-9
5. 9፡1-2	የሰዎች መሠቃየት	16፡10-11
6. 9፡13-21	ሠራዊት (የጦር)	16፡12-16
7. 11፡15-19	የተቆጡ ሕዝቦች	16፡17-21

የመለከት ፍርዶች በመጀመሪያው የመከራ አጋማሽ የሚደርሱ ሲሆን፥ የጽዋ ፍርዶች ደግሞ በመጨረሻው አጋማሽ ላይ ይታያሉ፤ እነዚህም «የእግዚአብሔር ቁጣ» በመባል ይታወቃሉ (ራእይ 14፡10፤ 15፡7)። የመለከት ፍርዶች እግዚአብሔር በግብፅ ምድር ላይ ካወረዳቸው መቅሰፍቶች ጋር ይመሳሰላሉ። ታዲያ እንደ ፈርዖን ሁሉ «አገለግለው ዘንድ እግዚአብሔር ማነው?» ለሚል የዓለም ሕዝብ፥ ይህ መቅሰፍት ይበዛበት ይሆን!

የሰባተኛው ማኅተም መከፈትና የስድስተኛው መለከት መነፋት፥ ሦስት ከፍተኛ ውጤቶችን አስከትለዋል።

ዝግጅት (ራእይ 8፡1-6)

ይህ ዝግጅት ሁለት ነገሮችን ያካተተ ነው- ዝምታ (8፡1) እና ልመናን (8፡2-6)።

የሰማይ ሠራዊት ጥቂት ቀደም ብለው በከፍተኛ የምስጋና ድምፅ እግዚአብሔርንና በጉን አምልከው ነበር (7፡10-12)። ይሁንና በጉ ሰባተኛውን ማኅተም በከፈተ ጊዜ፥ በሰማይ ለግማሽ ሰዓት ያህል ጸጥታ ሰፈነ። ዮሐንስ የጸጥታውን ምክንያት ባይነግረንም፥ ለምክንያቱ በርካታ አማራጮች ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ መጽሐፉ ሙሉ ለሙሉ ስለተከፈተና ምናልባትም ገጾቹ ስለተገለጡ፥ የሰማይ አካላት ሁሉ የከበረው የእግዚአብሔር ዕቅድ ሲገለጥ ለማየት ይችሉ ነበር። ምናልባትም የሰማዩ ሠራዊት በተመለከቱት ነገር በመገረም ተውጠው ይሆናል።

የእግዚአብሔር ብርቱ ፍርዶች በምድር ላይ ሊወርዱ ስለተቃረቡ፥ በመሠረቱ ይህ ጸጥታ «ከማዕበሉ በፊት የሚሰፍነው ጸጥታ» መሆን አለበት። «የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና ... በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ዝም በሉ» (ሶፎ. 1፡7፤ ከቁጥር 14 - 18፥ በተለይም በቁጥር 16 ላይ «የመለከት ... ጩኸት ቀን» የሚለውን ልብ ብለህ ተመልከት)። «እግዚአብሔር ከተቀደሰ ማደሪያው ነቅቶአልና ሥጋ ለባሽ ሁሉ ሆይ፥ በፊቱ ዝም በል» (ዘካ. 2፡13)። «እግዚአብሔር ግን በተቀደሰ መቅደሱ አለ ምድርም ሁሉ በፊቱ ዝም ትበል» (ዕንባ. 2፡20)።

በዚህ የዝምታ ወቅት፥ ሰባት መላእክት ለዮሐንስ ጠቃሚ መልእክት የሚያስተላልፉትን መለከቶች ተቀበሉ። ዮሐንስ አይሁዳዊ እንደ መሆኑ፥ በእስራኤል ብሔራዊ ሕይወት ውስጥ የመለከቶችን ጠቀሜታ ያውቅ ነበር። በዘኍልቍ 10 መሠረት፥ መለከቶች ሦስት አስፈላጊ አገልግሎቶች ነበሯቸው - ሰዎችን ማሰባሰብ (ቁ. 1-8)፥ ጦርነት እንደተነሣ ማወጅ (ቁ. 9)፥ ልዩ ቀናትን ማስታወቅ (ቁ. 10)። መለከት በሲና ተራራ ላይ ሕግ ሲሰጥ (ዘጸ. 19፡16-19) እና እንደዚሁም አንድ ንጉሥ በተቀባና ዙፋን ላይ በወጣ ጊዜ ሁሉ ተነፍቷል (1ኛ ነገሥት 1፡34፥ 39)። በመሠረቱ፥ ከብሉይ ኪዳን ጋር ቅርበት ያለው ማንኛውም ሰው በኢያሪኮ መፈራረስ ወቅት መለከቶች እንደተነፉ ያውቃል (ኢያሱ 6፡13-16)።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ ለዮሐንስ እንደ መለከት አስተጋባ (ራእይ 1፡10)። የመለከት ድምፅ ዮሐንስን ወደ ሰማይ የመራው ሲሆን (4፡1)፥ አንዳንዶች ይህንን በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-18 ለቤተ ክርስቲያን ከተሰጠው የንጥቀት የተስፋ ቃል ጋር ያዛምዱታል። ሰባቱ የመለከት ድምፆች ጦርነት መታወጁን ከማብሰራቸውም በላይ፥ የተቀባው የእግዚአብሔር ንጉሥ በክብር ዙፋን ላይ እንደተቀመጠና በጠላቶቹ ላይ ሊፈርድ እንደደረሰ የሚገልጹ ናቸው (መዝ. 2፡1-5)። የመለከት ድምፆች ኢያሪኮን እንዳፈራረሱ ሁሉ፥ በመጨረሻውም ቀን ባቢሎንን ድል ያደርጓታል።

ከአስገራሚው ዝምታ በመቀጠል፥ በሰማይ ከሚገኘው ወርቃማ መሠዊያ አጠገብ ቆሞ የነበረው መልአክ አንዳንድ ተግባራትን ሲያከናውን እናያለን (ራእይ 9፡13፤ 14፡18፤ 16፡7 አንብብ)። በመገናኛው ድንኳንና በመቅደሱ ውስጥ፥ ወርቃማው መሠዊያ ከመጋረጃው የሚቆምና ዕጣንን ለመሠዋት የሚያገለግል ነበር (ዘጸ. 30፡1-10)። መልአኩ እርሱና ባለቤቱ ኤልሳቤጥ ልጅ እንደሚወልዱ በተናገረበት ወቅት ዘካርያስ የሚፈጽመው ተግባር ይህንኑ ነበር (ሉቃ. 1 ከቁጥር 5 ጀምሮ)። በዚህ መሠዊያ ላይ የሚታጠነው ዕጣን ወደ እግዚአብሔር ዘንድ የሚያርግ ጸሎት መግለጫ ነበር [መዝ. (141)፡2]።

በ8፡4 ላይ የምናነበው «የቅዱሳን ጸሎት» ወደ «ቅድስና» የደረሱና በሰማይ የሚገኙ ልዩ ቡድኖች የሚያቀርቡት ጸሎት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ፥ የእግዚአብሔር ልጆች «ሁሉ» በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ለእግዚአብሔር የተለዩ ቅዱሳን ናቸው (2ኛ ቆሮ. 1፡1፤ 9፡1፥ 12፤ 13፡13)። እንዲሁም፥ በሰማይ የሚገኙ ሰዎች በምድር ላይ ለሚኖሩ አማኞች እንደሚጸልዩ፥ ወይም ጸሎታችንን በእነርሱ አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ እንደምንችል የሚያሳይ ግልጽ አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኝም። ይህ ተግባር በተለይ የሚገባው ለበጉ ስለሆነ፥ በወልድ አማካኝነት ጸሎታችንን ለአብ እናቀርባለን (ራእይ 5፡3)። ለዘመናት የእግዚአብሔር ሕዝቦች፥ «መንግሥትህ ትምጣ፥ ፈቃድህ ይፈጸም» በማለት ሲጸልዩ ነበርና አሁን እነዚያ ጸሎቶች ሊፈጸሙ ተቃርበዋል። እንደዚሁም፥ በታላቁ መከራ ወቅት በሰማዕትነት ያለፉት ሰዎች እግዚአብሔር ጉዳያቸውን እንዲዳኝላቸው ይጸልዩ ነበር

(6፡9-11)። በተጨማሪም ዳዊት በመዝሙሩ ውስጥ የሚያቀርበው የተለመደ ልመና ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነበር [ለምሳሌ ያህል መዝሙር 7፥ (26)፥ (35)፥ (52)፥ (55)፥ (58) አንብብ]። እነዚህ «እርግማን የተንጸባረቀባቸው መዝሙሮች» እግዚአብሔር ቅዱስ ሕጉን በማስከበር ሕዝቡን እንዲታደጋቸው የሚያሳስቡ ጩኸቶች እንጂ፥ ራስ-ወዳድነት የነገሠባቸው የግላዊ ቂም በቀል መግለጫዎች አይደሉም።

በታላቁ የስርየት ቀን፥ ሊቀ-ካህኑ ዕጣን ከማጠኛው ጥና ውስጥ ይጨምርና ከደም መሥዋዕቱ ጋር ይዞ ወደ ቅድስተ-ቅዱሳን ይገባል (ዘሌ. 16፡11-14)። ይሁንና በዚህ ትዕይንት ላይ ግን፥ መልአኩ ዕጣኑን ከመሠዊያው ላይ ይጨመርና (ጸሎቶችን በእግዚአብሔር ፊት አቀረበ) ጥናዎቹን ከመሠዊያው ወደ ምድር ይወረውራቸዋል። በሕዝቅኤል 10 ውስጥ የሚገኘው ተመሳሳይ አሳብ ይህ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንደሚያመለክት ያሳያል፤ በራእይ 8፡5 ላይ የተገለጹ ነገሮችም ይህንኑ አሳብ ያጠናክራሉ። ማዕበሉ ሊጀምር ነው! (4፡5፤ 11፡19፤ 16፡18 ተመልከት)።

ብንወድም ብንጠላም፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጸሎቶች በእግዚአብሔር ፍርዶች ውስጥ የተካተቱ ናቸው። መሠዊያውና ዙፋኑ ዝምድና አላቸው። ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እንደ ተገለጸው፥ የጸሎት ዓላማ የሰውን ፈቃድ በሰማይ መፈጸም ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ላይ መፈጸም ነው - ፍርድ ቢኖርበትም እንኳ። እውነተኛ ጸሎት ብርቱ ተግባር ነውና፥ መሠዊያውን ከዙፋኑ ብዙም ባናርቀው መልካም ነው።

ጥፋት (ራእይ 8፡7-13)

የመጀመሪያዎቹ አራት የመለከት ፍርዶች «ተፈጥሮአዊ» ሲሆኑ፥ ምድርን፥ ባሕርን፥ ወንዞችንና ሰማያዊ አካላትን ጎድተዋል። አምስተኛውና ስድስተኛው ግን በቅድሚያ እጅግ ካሠቃዩ በኋላ ወደ ሞት የሚያደርሱትን የአጋንንት ኃይሎች መፈታት ይጨምራሉ። የመጨረሻው የመለከት ፍርድ በዓለም ሕዝቦች ሁሉ መካከል ቀውጢ ሁኔታ ይፈጥራል (11፡15-19)።

ጥፋት በምድር ላይ (8፡7) - «ደም የተቀላቀለበት በረዶና እሳት» የሚለው፥ እግዚአብሔር በግብፅ ላይ ያወረደውን ሰባተኛ መቅሰፍት

ያስታውሰናል (ዘጸ. 9፡18-26)። ነቢዩ ኢዩኤልም በመጨረሻው ዘመን «ደምና እሳት» እንደሚመጣ ተናግሯል (ኢዩ. 2፡30)። ይህ መለኮታዊ ፍርድ ስለሆነ፥ እንዴት በረዶ፥ እሳትና ደም እንደሚቀላቀሉ ለማብራራት መጣሩ አላስፈላጊ ድካም ነው። «እሳት» በኃይለኛ የኤሌክትሪክ ሞገድ የሚፈጠረውን መብረቅ ሊያመለክት ይችላል።

የዚህ ፍርድ ማነጣጠሪያዎች አረንጓዴ ተክሎች ማለትም ዛፎችና ሣሮች ሲሆኑ፥ ከእነዚህም ውስጥ አንድ ሦስተኛው እጅ ይቃጠላል። ይህም የተፈጥሮን ሚዛን ብቻ ሳይሆን፥ የምግብ አቅርቦትንም ጭምር እንደሚጎዳ ለመረዳት አያዳግትም። ዛፎችን የሚያመለክተው የግሪክ ቃል «ፍሬ የሚሰጡ ዛፎች» የሚል ትርጉም ሲኖረው፥ የከብቶች የግጦሽ ስፍራ መውደሙም የሥጋና ወተት ምርቶችን በአመዛኙ ይጎዳል።

ጥፋት በባሕር ላይ (8፡8-9) - የውኃ ወደ ደምነት መለወጡ የመጀመሪያውን የግብፅ መቅሰፍት ያስታውሰናል (ዘጸ. 7፡19-21)። ዮሐንስ የሚቃጠለው ነገር ተራራን ያህል ግዙፍ እንደሆነ እንጂ፥ የሚቃጠለው ተራራ ከሰማይ የተጣለ ስለመሆኑ አለመናገሩን አስተውል። በዚህም በሦስተኛው ፍርድ ምክንያት፥ አንድ ሦስተኛው ውኃ ወደ ደምነት ተለወጠ፤ አንድ ሦስተኛው የውኃ ውስጥ ፍጥረት ሞተ፤ ከመርከቦችም አንድ ሦስተኛው እጅ ወደሙ። ይህም እጅግ ከፍተኛ የሆነ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ውድቀት የሚደርስበት ሁኔታ ይሆናል።

ውኃማ አካላት የየብስን ሦስት አራተኛ እጅ እንደሚሸፍኑ በመረዳት የዚህን ፍርድ መጠን ልትገነዘብ ትችላለህ። የውኃ ብክለትና የበርካታ ፍጥረታት መሞት በውኃማ አካላት ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሕይወትን መዛባት ያስከትላል፤ ይህም ፍች ወደ ማይገኝላቸው ተጨማሪ እንቆቅልሾች ያመራል። በጃኑዌሪ 1፥ 1981 ዓ.ም. 24,867 ውቂያኖስ አቋራጭ የንግድ መርከቦች ተመዝግበው ነበር። እንግዲህ ከእነዚህ ውስጥ 8, 289 ዋጋ ያላቸው መርከቦች ቢጠፉ፥ በመርከብ ሥራ እንዱስትሪ ላይ የሚያንዣብበውን የድንጋጤ ማዕበል እስኪ አስበው። ጭንቆቻቸውስ!

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች «ባሕር» የሚለውን «ሜድትራንያን ባሕር» ብለው ይፈቱታል። ሜድትራንያን ባሕር የሚሸፍነው 96, 9100 ካሬ ማይሎችን ብቻ ስለሆነና በማዕከላዊ መጠን

የ5,000 ጫማዎች ጥልቀት ብቻ ስላለው፥ ይህ በዓለም ላይ ብዙም ጉዳት አያደርስም። በመሆኑም፥ ታላላቅ ውኃማ አካላት ሁሉ በዚህ ፍርድ ውስጥ ተጠቃለው እንደቀረቡ አድርጎ መውሰዱ የተሻለ ነው።

ጥፋት በወንዞች ላይ (8፡10-11) - የእግዚአብሔር ፍርድ ወደ ምድር ውስጣዊ ክፍል በመዝለቅ፥ ወንዞችንና ምንጮችንም ይነካል፤ በዚህም ምክንያት ንጹሑ ውኃ እንደ እሬት ወደሚመር ነገር ይለወጣል። ብሔራዊ የመልከዓ ምድር ማኅበር፥ ከአማዞን ወንዝ (4, 000 ማይል ርዝመት) እስከ ሪኦ ዲ ላፕላታ (150 ማይል ርዝመት) በሚራራቁ መጠኖች ውስጥ የሚገኙ 100 ዋና ዋና ወንዞች በዓለም ዙሪያ እንዳሉ ይዘረዝራል። የዩ.ኤስ.ኤ የአካባቢ አሰሳ ቡድን በበኩሉ፥ ከታላቁ የሚሲሲፒ ወንዝ (3,710 ማይል ርዝመት) ጀምሮ በዩናይትድ እስቴትስ ሠላሳ ታላላቅ ወንዞች እንደሚገኙ ይዘግባል። እንግዲህ እንደትንቢቱ የእነዚህም ወንዞችና የምንጮቻቸው አንድ ሦስተኛው መራራ ይሆንና፥ ለሚጠጣው ሰው ሞትን ያስከትላል ማለት ነው።

እግዚአብሔር የተቆጠሩና ስም የተሰጣቸው ከዋክብት አሉት (ኢዮብ 9፡9-10)። ይህ የወደቀው ኮከብ በሙቀት ከቀለጠ በኋላ ወደ ምድር ሲቀርብ በመፈረካከስ ወደ ተለያዩ ውኃማ አካላት ላይ መውደቅ የጀመረ ይመስላል። ይህ ኮከብ ምድርን ቢመታት፥ ዓለማችን ትደመሰስ ነበር፤ ስለዚህ ይህ ኮከብ ወደ ምድር ከባቢ አየር ሲገባ «መበታተን» ነበረበት። በመሠረቱ፥ ይህ ክስተት መለኮታዊ ቁጥጥር ያለበት ስለሆነ፥ በታወቁ የሳይንስ ሕግጋት ልንወስነው መሞከር አይገባንም።

«እሬት» (ወይም «እሬቶች») በመባል የተተረጎመው ቃል፥ በአንዳንድ አገሮች የታወቀው የ«አብሲንት» መጠጥ ስም ነው። የቃሉም ትርጉም፥ «ሊጠጣ የማይችል» የሚል ሲሆን፥ በብሉይ ኪዳን ከኃዘንና ከታላቅ አደጋ ጋር የሚመሳሰል ነው። «አልቃሻው ነቢይ» ኤርምያስ ብዙውን ጊዜ በዚህ ቃል ተጠቅሟል (ኤር. 9፡15፤ 23፡15፤ ሰቆ. ኤር. 3፡15፥19)፤ አሞጽም እንዲሁ (አሞጽ 5፡7 «ወደ እሬት የምትለውጡ»)። ሙሴ እሬት እንደሚያፈራ ሥር ሁሉ፥ ጣዖትን ማምለክ ለእስራኤል ኃዘንን እንደሚያስከትል በማስገንዘብ አስጠንቅቋል (ዘዳግ. 29፡18)። ሰለሞንም ማመንዘር የሚያስደስት ቢመስልም፥ ዳሩ ግን በመጨረሻው፥ እንደ እሬት ምሬትን እንደሚያፈራ በመግለጽ አስጠንቅቋል (ምሳ. 5፡4)።

ከእነዚህ ውኆች የሚጠጡ ሰዎች በሞት አደጋ ላይ ከሆኑ፥ በእነዚህ ውኆች ውስጥ የሚኖሩ ዓሦችና ሌሎችም ፍጥረታት እንዴት ይሆናሉ? በእነዚህ ወንዞች ዳርቻ የሚገኙ ተክሎችስ? የአካባቢ ሁኔታ ጠበብት ዛሬ የውኃ ብክለት በሚያስከትላቸው አስከፊ ውጤቶች የሚጨነቁ ከሆነ፥ ሦስተኛው መለከት ሲነፋ ምን ይሉ ይሆን?

በዚህ ሥፍራ በግብፅ ላይ ከደረሰው መቅሰፍት ጋር ቀጥተኛ ተመሳሳይነት አናገኝም። ይሁንና፥ እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ በማራ መራራ ውኃ ያጋጠማቸው ሲሆን፥ ሙሴ ውኃውን ማንጻት ያስፈልገው ነበር (ዘጸ. 15፡23-27)። ይሁንና በታላቁ መከራ ጊዜ መለኮታዊው ኃይል በምንም ዓይነት ውኃውን የማንጻት ተግባር አይኖረውም።

ጥፋት በሰማያት (8፡12-13) - የመጀመሪያዎቹ ሦስት መለከቶች ፍርዶች አንድ ሦስተኛውን የውኃና የመሬት ክፍል ብቻ የጎዱ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ይህ አራተኛው ፍርድ ዓለሙን በሙሉ ይተናኮለዋል። ለምን? ምክንያቱም የመሬት ዓይነተኛ የኃይልና የጉልበት ምንጭ በሆነችው ፀሐይ ላይ ስለሚደርስ ነው። ከምድር ላይ አንድ ሦስተኛው የፀሐይ ብርሃን ስለሚቀነስ፥ የሰውና የተፈጥሮን የአኗኗር ዘይቤዎች ከሚደግፍ ኃይል አንድ ሦስተኛው ይጎድላል ማለት ነው።

ይህ ፍርድ በግብፅ ለሦስት ቀናት ከቆየው ከዘጠነኛው መቅሰፍት ጋር ይመሳሰላል (ዘጸ. 10፡21-23)። «የእግዚአብሔር ቀን . . . ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም» (አሞጽ 5፡18)። የሚመጣውን ታላቅ የሙቀት ልዩነትና ይህም የሰውን ጤንነትና የምግብ ዕድገት እንዴት እንደሚጎዳ አስብ።

የአራተኛው ጽዋ ፍርድ ሁኔታውን ስለሚቀለብስና የፀሐይ ኃይል እጅግ ስለሚያይል (ራእይ 16፡8-9)፥ ይኼኛው ፍርድ ጊዜያዊ ክስተት እንደሚሆን መገመት ይቻላል። ከዚያም፥ በመከራው መፈጸሚያ አካባቢ፥ የአዳኙን መመለስ ለማወጅ ፀሐይና ጨረቃ ዳግም ይጨልማሉ (ማቴ. 24፡29-30፤ ሉቃ. 21፡25-28 አንብብ)። ነቢዩ ኢዩኤል «የእግዚአብሔር ቀን መጥቶአልና . . . በጽዮን መለከትን ንፉ . . . የጨለማና የጭጋግ ቀን» ብሏል (ኢዩ. 2፡1-2)። እውነትም ጨለማ! ፍጥረት በማጣት መሠቃየቱ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የሰው ተፈጥሮ

ጨለማን ተገን በማድረግ በወንጀልና በኃጢአት ተግባራት ላይ እንደሚሰማራም አያጠራጥርም። «ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና» (ዮሐ. 3፡20)።

በዚህ ነጥብ ላይ፥ አንድ አስደናቂ መልእክተኛ በሰማይ ይታይና ለምድር ዜጎች ሁሉ ዋይታን ያስተጋባል። በዚህ ሥፍራ በብዙዎቹ መዛግብት ላይ የተጠቀሰው በ«መልአክ» ፈንታ «ንስር» ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ሁለቱም የሰዎችን አትኩሮት መሳባቸው የማይቀር ነው። ይህ ዮሐንስ በዙፋኑ ፊት እግዚአብሔርን ሲያመልክ ያየው ንስር-መሳይ እንስሳ ይሆን? (4፡7-8)። እግዚአብሔር ለዚህ ልዩ ተልዕኮ ልኮት ይሆን? ይህ ሊሆን የሚችል ቢሆንም፥ በእርግጠኛነት ልንናገር ግን አንችልም።

በቁጥር 13 ላይ የተጠቀሱት ሦስቱ «ዋይታዎች» የተቀሩት ሦስት መላእክት መለከታቸውን እንደነፉ የሚከተሉትን ፍርዶች ያመለክታሉ። መልአኩ፥ «ይህ የከፋ ጥፋት ከመሰላችሁ እስኪ ትንሽ ቆዩ! የባሰው ገና ይመጣል!» በማለት የጮኸ ይመስላል።

«በምድር ላይ የሚኖሩ» የሚለው ሐረግ በራእይ ውስጥ 12 ጊዜ ያህል ተጠቅሶአል (3፡10፤ 6፡10፤ 8፡13፤ 11፡10፤ 12፡12፤ 13፡8፥ 12፥ 14፤ 14፡6፤ 17፡2፥8)። ይህም ሕያዋን ሰዎች ሁሉ የሚኖሩበት በመሆኑ፥ «በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች» ከሚለው የላቀ ትርጉም አለው። ይልቁንም፥ የሰዎቹን ዓይነት ያመለክታል - ለምድርና ለምድራዊ ነገር የሚኖሩ ሰዎች ማለት ነው። እነዚህ ሰማያዊ ዜግነት ካላቸው ሰዎች በተቃራኒው ጎራ የሚመደቡ ናቸው (ፊልጵ. 3፡18-21)። ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ ስለእነዚህ ዓለማዊ ሰዎች ጥሩ አድርጎ የገለጸ ሲሆን (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)፥ በኋላም በዚህ ትንቢት «የምድር ነዋሪዎች» ዳግም እንዳልተወለዱ ያብራራል (13፡18)።

የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን እግዚአብሔርን ያከብሩና ለፈቃዱም ይታዘዙ ስለነበር፥ በሰው ታሪክ መጀመሪያ አካባቢ ሰማይና ምድር ኅብረት ነበራቸው። በኋላ ግን በምድር ላይ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ ሰይጣን ስለፈተናቸው፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፉ፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሰማይና በምድር መካከል ትልቅ የመለያያ ሸለቆ ተጋረጠ።

ሆኖም ይህ ሽለቆ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ዓለም በመምጣት ለዓለሙ ኃጢአት በሞተ ጊዜ ተደላደለ።

መፈታት (ራእይ 9፡ 1-21)

የራእይን መጽሐፍ ልዩ ጥናታቸው ያደረጉት የቀድሞው ዶክተር ዊልበር ኤም. ስሚዝ አንድ ጊዜ እንዲህ በማለት ጽፈው ነበር፡- «በምዕራፍ 17 እና 18 ውስጥ ባቢሎን በግልጽ ተለይታ ከመጠቀሷ በስተቀር፥ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙት የሁለቱ ፍርዶች ትርጉም፥ በራእይ ውስጥ ከሚገኙት ትንቢቶች ሁሉ ለመረዳት የሚከብድ ነው» (ዊክሊፍ ባይብል ኮመንቴሪ፥ ገጽ 1509)። ራእይ 9 በትክክለኛው ጊዜ ስለ ተለቀቁና በሰው ልጅ ላይ እንዲፈርዱ ስለተፈቀደላቸው ሁለት አስፈሪ ሠራዊቶች ይገልጻል።

ከጥልቁ የወጣ ሠራዊት (9፡ 1-12) «መጨረሻ የሌለው ጥልቀት» ትክክለኛ ትርጓሜው «ከልክ ያለፈ ጥልቀት»ማለት ሲሆን፡- ሉቃስ ይህ «ጥልቁ» የአጋንንት መኖሪያ እንደሆነ ሲገልጽ (ሉቃ. 8፡31)፥ ዮሐንስም ጌታችን በሚመለስበት ጊዜ ሰይጣን ለጊዜው በዚያ «እንደሚታሰር» ያመለክታል (ራእይ 20፡ 1-3)። ሐሳዊ-መሲሑም ማለትም «አውሬው» ከዚህ ከጥልቁ ይወጣል (11፡7፤ 17፡8)። የእሳት ባሕር ግን የሰይጣንና እርሱን የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ የመጨረሻ «እስር ቤት» ስለሆነ፥ ጥልቁ የተባለው የእሳት ባሕር አይደለም (20፡ 10)። ሆኖም በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር ያለ ስውር የሙታን መንደር አካል ነው። ዛሬ፥ በዚህ ሥፍራ የተጠቀሰው አስፈሪ ሠራዊት በእስራት ውስጥ ሆኖ የሚፈታበትን ሰዓት ይጠባበቃል።

ይህ የወደቀው ኮከብ በጥልቁ ለሚገኙ ፍጥረታት ንጉሥ የሆነ ሰው ነው (ቁ. 11)። ሠራዊቱን ለመፍታት ከመቻሉ በፊት የጥልቁ መክፈቻ ሊሰጠው ስለሚያስፈልግ፥ ሙሉ ሥልጣን አይኖረውም። ምናልባት ይህ «ኮከብ» ሰይጣንና ሠራዊቱ ማለትም አጋንንቶቹ ሊሆኑ ይችላል (ኤፌ. 6፡ ከቁጥር 10 ጀምሮ)። ከሰይጣን ስሞች አንዱ «ሉሲፈር» የሚል ሲሆን፥ ትርጉሙም «ድምቀት» ማለት ነው፤ እንዲሁም ደግሞ «ከአጥቢያ ኮከብ» ጋር ተወዳድሯል (ኢሳ. 14፡ 12-14)። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፥ «ሰይጣን እንደመብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ» ብሏል (ሉቃ. 10፡ 18)።

ጥልቁ ጉድጓድ ሲከፈት፥ የእቶን በር የተከፈተ ይመስል ጢስ ይቦልቅ ጀመር። ኢየሱስ ሲኦልን ከእሳት እቶን ጋር ያወዳደረ ሲሆን (ማቴ. 13፡42፥ 50)፥ ይህም ሰዎች በጉዳዩ ላይ ከመሳለቃቸው በፊት ቆም ብለው እንዲያስቡ የሚያደርግ መግለጫ ነው። ጢሱ አየርን ከመበከሉም በላይ፥ አራተኛው መለከት ከመነፋቱ በፊት በጽልመት የተዋጠችውንም ፀሐይ ይብሱኑ አጨለማት።

ይሁንና ከጢሱ የወጣውና ከአንበጣ መንጋ ጋር የተወዳደረው የአጋንንት ሠራዊት ነበር በሰው ልጅ ላይ ሽብር የፈጠረው። በግብፅ ስምንተኛው መቅሰፍት አጥፊ የአንበጣ መንጋ ነበር (ዘጸ. 10፡1-20)። እነዚህን ትናንሽ ነፍሳት አይተው የማያውቁ ሰዎች ስለሚያደርሱት አደጋ የሚያውቁት ነገር የላቸውም። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ ሲሻ፥ አንዳንድ ጊዜ ሰብሎችን ያወድሙ ዘንድ አንበጣዎችን ይልካል (ዘዳ. 28፡38፥ 42፤ ኢዩ. 2)።

በመሠረቱ አንበጣዎች በጅራታቸው የብረት ጥሩር የሚመስል መውጊያ ስለሌላቸው፥ እነዚህ የተጠቀሱት እውነተኛ አንበጦች አይደሉም። እነዚህ ፍጥረታት አረንጓዴ ተክሎችን አይጎዱም፤ እንዲያውም ይህንን ጥፋት እንዳይፈጽሙ ተነግሯቸዋል። ለዚህ አጋንንታዊ ሠራዊት በእግዚአብሔር ማኅተም ያልተጠበቁትን ሁሉ የማሠቃየት ተግባር ተሰጥቶታል። ስለሆነም ከእስራኤል ነገድ ውስጥ 144,000 ሰዎች ከዚህ አስጨናቂ ፍርድ ያመልጣሉ (ራእይ 7፡1-8)። እንዲያውም፥ በጌታ ያመኑ ሁሉ በአንድ በተለየ መንገድ ታትመው ከሥቃዩ ይተርፋሉ።

የአንበጣ ተለምዶአዊ የሕይወት ዘመን ቆይታ ለአምስት ወራት የሚደርስ (ከመጋቢት እስከ መስከረም) እንደመሆኑ፥ ይህም የፍርዱ ርዝማኔ መሆኑ ነው። እነዚህ አጋንንት ሰዎችን በመውጋት፥ የተወጉትን ሰዎች ሞትን እስኪመኙ ድረስ ያሠቃዩአቸዋል፤ ሞት ግን ከእነርሱ ይሸሻል (ኤር. 8፡3)።

የእነዚህ ፍጥረታት ዝርዝር መግለጫ ከምንባቡ እንደምንረዳው ከሆነ፥ ዮሐንስ የሚጽፈው ስለተራ አንበጦች አለመሆኑን ነው። ዳሩ ግን ከግልጽ ተምሳሌትነቱ ባሻገር፥ ለጦርነት የተዘጋጀውን ኃይለኛ ሠራዊት ወደማመልከቱ ያዘነብላል። አጋንንቱ ፈረስ የሚመስሉ አካላትና እንደሰው

የሚመስሉ ፊቶች ያሏቸው ከመሆኑም፥ ራሶቻቸውም በዘውድና በረዥም ጸጉር ተሸፍነው ነበር። እንደ አንበሣ የሚመስሉ ጥርሶችና በብረት ልብስ የተሸፈኑ ቆዳዎች አሏቸው። በሚበሩበት ጊዜ፥ በዚያ አካባቢ በሰረገላዎች ላይ የተቀመጠ ሠራዊት የሚያልፍ ይመስል ከፍተኛ ሁካታ ይፈጥራሉ። እነዚህን ነገሮች ወደ መንፈሳዊ እሳቤ መውሰድ ወይም ከዘመናዊ የጦርነት ስልት አኳያ ለመተርጎም መሞከሩ አስፈላጊ አይደለም። ዮሐንስ የዚህ ፍርድ አስቃቂነት እንዲሰማን ለማድረግ በምስል ላይ ምስል እየደራረበ አቅርቦልናል።

ትክክለኛ አንበጦች ንጉሥ የላቸውም (ምሳሌ 30፡27)፤ ይሁንና ይህ ሠራዊት የጥልቁ ጉድጓድ መልአክ የሆነውን የሰይጣንን አገዛዝ ይከተላል። ስሙ «አጥፊ» ነው። «ሌባው (ሰይጣን) ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለሌላ አይመጣም» (ዮሐ. 10፡10)። ትክክለኛ አንበጦች ማንንም ሳይለዩ ሲጎዱ ይህ ሠራዊት ግን የጌታ ያልሆኑትን ብቻ ለይቶ ያጠቃል።

የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደመሆናችን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የሲኦልንና የሞትን መክፈቻ ስለሚይዝና (ራእይ 1፡18) በሰይጣን ላይ ሳይቀር መለኮታዊ ሥልጣን ስላለው፥ በምስጋና ልንመላለስ እንችላለን። እግዚአብሔር ለእነዚህ ሁሉ ነገሮች የራሱ የጊዜ ሰሌዳ ስላለው፥ እጅግ ፈጥኖ ወይም እጅግ ዘግይቶ የሚፈጸም ነገር አይኖርም (2ኛ ተሰ. 2፡6፤ ራእይ 9፡15 አንብብ)።

ከምሥራቅ የተለቀቀ ሠራዊት (9፡13-21) መልአኩ የቅዱሳንን ጸሎት ያቀረበው በወርቅ የዕጣን መሠዊያ ላይ ሲሆን (8፡3-5)፥ አሁንም ከዚሁ መሠዊያ አራት መላእክት እንዲለቀቁ የሚያዝ ድምፅ ያስተጋባል። ማንኛውም ቅዱስ መልአክ ስለማይታሰር፥ እነዚህ መላእክት በደልን የፈጸሙ ይመስላል። እያንዳንዳቸውም በተፈቱ ጊዜ የሚከተሏቸውን እጅግ በርካታ፥ ማለትም 200 ሚሊዮን ፍጥረታት የሚገኙበትን ሠራዊት ተከፋፍለው በኃላፊነት ይመሩ ነበር። ሠራዊቱ በትክክለኛው ጊዜ፥ ለተለየ ዓላማ ነበር የተፈታው - የዓለምን አንድ ሦስተኛ ሕዝብ (ለማሠቃየት ብቻ ሳይሆን) ለመግደል። አንድ አራተኛ የሰው ልጅ ቀደም ብሎ ስለተገደለ (6፡8)፥ ስድስተኛው የመለከት ፍርድ በሚገባደድበት ወቅት ከዓለም ሕዝብ ግማሹ ይሞታል ማለት ነው።

ይህ በዓለም ዙርያ በወራሪነት የሚንቀሳቀስ እውነተኛ ሰዎች የሚገኙበት ሠራዊት ይሆን? ላይሆን ይችላል። አንደኛው ነገር፥ በዚህ አንቀጽ ውስጥ አጽንኦት የተሰጠው ለፈረስ ጋላቢዎቹ ሳይሆን፥ ለፈረሶቹ ነው። መግለጫው ከምናውቃቸው የጦርነት ፈረሶች፥ ወይም ታንክን ከመሳሰሉ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ጋር አይገጥምም። በመሆኑም ይህንን እውነተኛ ሠራዊት እንደሆነ አድርጐ መቁጠርም ሆነ 200 ሚሊዮን ወታደሮች እንዳሏቸው ከሚናገሩት አንዳንድ አገሮች (ለምሳሌ ቻይና) ጋር ማዛመዱ ዮሐንስ ለማስተላለፍ የሚፈልገውን መልእክት በትክክል አለመረዳት ነው።

የእነዚህ ፈረሶች ከፍተኛ ጉልበት የሚገኘው በአፋቸውና በጅራታቸው እንጂ፥ በእግራቸው ላይ አይደለም። እሳት፥ ጢስና ዲን ከአፋቸው የሚወጣ ሲሆን፥ ጅራታቸውም ተናዳፊ እባቦችን ይመስላል። ሰዎችን ከፊትም ሆነ ከኋላ ሊያጠቁ ይችላሉ።

እኔ እንደማምነው ግን፥ ይህ በአራት የወደቁ መላእክት የሚመራ ሠራዊት፥ እግዚአብሔር እስኪፈቅድለት ድረስ እንቅስቃሴ ለማድረግ የማይችልና በጌታ ታስሮ የሚገኝ ሌላው የአጋንንት ሠራዊት ነው። የታሰሩበት ሥፍራ የሥልጣኔ እምብርት በሆነው በኤፍራጥስ ወንዝ ዳርቻ ቢሆንም (ዘፍጥ. 2፡14)፥ የመታሰራቸው ምክንያት አልተገለጸም፤ ኤፍራጥስ ከእስራኤል አጎራባች አካባቢዎች አንዷ ነች (15፡18)።

ይህ የአምስት ወራት ሥቃይና ከዚያም በኋላ የብዙዎች ለእሳት፥ ለጢስና ለእቶን ሕልፈት መዳረግ፥ ምናልባትም ወንዶችንና ሴቶችን በጉልበታቸው ወድቀው ንስሐ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል ብለን እናስብ ይሆናል።

ዳሩ ግን እንዲህ አይሆንም። እነዚህ ፍርዶች ስኬታማ መፍትሔዎች ሳይሆኑ፥ አይቀሬ ተግባራት ናቸው - እግዚአብሔር ቅዱስ ሕጉን እያስከበረና በመከራ የሚሠቃዩትን ሕዝቦቹን በፍትሕ በመዳኘት ነፃ እያወጣቸው ነው (ራእይ 6፡9-11 አንብብ)። ከቁጥር 20-21 የሚገኘውን ክፍል በድንገት ብናነበው እንኳ፥ በእግዚአብሔር ፍርዶች መካከል እንኳ የሰውን ልጅ የከፋ ኃጢአት ልንመለከት እንችላለን። በራእይ 9 ውስጥ እጅግ የሚያስፈራው ነገር እግዚአብሔር የሚልከው

ፍርድ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር እየፈረደባቸው እያለ እንኳ ሰዎች እየፈጸሟቸው የሚገኙት ኃጢአቶች ናቸው።

ወንዶችና ሴቶች የሚፈጽሟቸውን ኃጢአቶች ተመልከት:-

የአጋንንት አምልኮ - ከጣኦት አምልኮ ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ኃጢአት ሲሆን (1ኛ ቆሮ. 10፡19-21)፥ በጊዜው መሪ ኃጢአት ይሆናል። ሰይጣን የሚሠራው ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር ቢሆንም፥ ዳሩ ግን፥ መቼም ቢሆን ለመመለክ ይፈልግ ነበር (ኢሳ. 14፡12-15፤ ማቴ. 4፡8-10)። በዚህ ጊዜ «ሃይማኖት» በአመዛኙ የሚዘወተር ይሁን እንጂ፥ ሃይማኖቱ የውሸት ሃይማኖት ይሆናል። ሰዎች የእጆቻቸውን ሥራዎች የሚያመልኩ ሲሆን፥ ከእነዚህም መካከል የሚያንጹዋቸው ሕንፃዎች፥ የሚሠሩዋቸው ማሽኖች፥ የሚቀረቁሩዋቸው ከተሞችና ጣዖቶቻቸው ሊገኙባቸው ይችላሉ።

እነዚህ የሞቱትን አማልክት የሚያመልኩ ሙት ኃጢአተኞች ናቸው! [መዝ. (115)]። አማልክቶቻቸው ሊጠብቋቸው ወይም ሊያድኗቸው ባይችሉም፥ ዳሩ ግን እነዚህ ሰዎች እውነተኛውን አምላክ ትተው ሰይጣንና ጣዖታትን ማምለካቸውን ይቀጥላሉ።

ግድያና ሌብነትም በዚያን ጊዜ የተለመደ ተግባር ይሆናል፤ የተለያዩ ዓይነት የወሲብ ግድፈቶችም በስፋት ይለመዳሉ። «አስማት» ተብሎ የተተረጎመው ቃል በግሪክ «ፈርማኪያ» የሚባል ሲሆን፥ «የመድኃኒቶች (ዕፆች) አጠቃቀም» ማለት ነው። ዕፆች ከጥቅም ላይ የሚውሉት በአመዛኙ በአረማዊ የሃይማኖት ሥርዓቶችና በአጋንንት አምልኮ ውስጥ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የዛሬውን «በመድኃኒት (ዕፅ) የታጠረ ማኅበረሰብ» ስንመለከት፥ ለእነዚህ አጋንንታዊ ልምምዶች መስጠቱን የመገምገም ችግር አይጋረጥብንም።

በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ ጣዖታትን በመሥራትና በማምለክ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን የሙሴ ትእዛዛት ይተላለፋል። በተጨማሪም በሚፈጽሟቸው ግድያዎች ስድስተኛውን ትእዛዝ ሲተላለፉ፥ በሌብነታቸው ስምንተኛውን ትእዛዝ ይተላለፋሉ። በዝሙታቸው፥ ሰባተኛውን ትእዛዝ ይተላለፋሉ። በመሆኑም፥ ጊዜው «ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን» የሚያደርግበት የሥርዓት-አልበኝነት ዘመን ይሆናል (መሳ. 21፡25)።

ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር ዕቅዱን የሚያከናውን ሲሆን፥ የሰዎች ኃጢአቶችም ሆነ የሰይጣንም ሤራ ፈቃዱን ከመፈጸም አያግደውም።

አሁን አንዳንድ ጉልህ ክስተቶች መፈጸም ወደሚገባቸው፥ ወደ መከራው ማዕከላዊ ዘመን ደርሰናል (10-14)። እስካሁን የሰባቱን ዓመታት አጋማሽ ያህል ተጉዘናል (ዳን. 9፡27)። በዚህም የመጀመሪያ አጋማሽ ጊዜያት፥ ሐሳዊው-መሲሕ እንደ ሰላም አድራጊና የእስራኤልም ልዩ ወዳጅ በመሆን ሥራውን የጀመረ ሲሆን፥ አሁን ግን እውነተኛ ማንነቱ ይገለጻል። ሰላም አደፍራሽና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያሳድድ ሆኖ ይለወጣል።

በዚህ የትንቢት ጉዞ መካከለኛ ደረጃ ላይ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ነገሮች ደማቅ ብርሃን የሚረጩ ሆነው አይገኙም - ይደበዝዛሉ፤ ይህም ሆኖ፥ በነገሥታት ንጉሥና በጌቶቹ ጌታ አማካኝነት አሁንም የአሸናፊነቱን ሚና ይጫወታሉ።

- 7 -

የምስክርነት ጊዜ

ራእይ 10-11

በራእይ 10-14 ውስጥ በሰባቱ ዓመታት መከራ አጋማሽ ላይ የሚፈጸሙትን ክስተቶች እንመለከታለን። ይህም ዮሐንስ የሦስት ዓመታት ተኩሉን ጊዜ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ በተደጋጋሚ የሚገልጽበትን ምክንያት ያስረዳናል (11፡2-3፤ 12፡6፥ 14፤ 13፡5)። በመከራው መጀመሪያ ላይ፥ ሐሳዊው-መሢሕ አይሁዶችን ለመጠበቅና በኢየሩሳሌም ዳግም ለሚገነቡት የመቅደስ ሕንፃ እገዛ እንደሚያደርግ ቃል በመግባት የግዛት ማስፋፋቱን በዘዴ ጀምሮ ነበር። ይሁንና ከሦስት ዓመታት ተኩል በኋላ፥ ቃል ኪዳኑን በማፍረስ፥ ቤተ መቅደሱን ከመውረሩም በላይ፥ አይሁዶችን ማሳደድ ይጀምራል።

ምንም እንኳ የዚህ የመከራው አጋማሽ ክስተቶች አስጨናቂ ሊሆኑ ቢችሉም፥ እግዚአብሔር ግን ለዓለም የሚመሰክሩለትን አያጣም። በራእይ 10-11 ሦስት አስፈላጊ ምስክርነቶች ይገኛሉ - የብርቱው መልአክ (10፡1-11)፥ የሁለቱ ልዩ ምስክሮች (11፡1-14) እና በሰማይ የሚገኙ ሽማግሌዎች ምስክርነቶች (11፡15-19)።

የብርቱው መልአክ ምስክርነት (ራእይ 10፡1-11)

በራእይ ውስጥ መላእክት ከስድሳ ጊዜያት በላይ ተጠቅሰዋል። መላእክት በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች ለመፈጸም የሚላኩ ሠራዊት ናቸው። ዛሬ አማኞች ስለእነዚህ አገልጋዮች አገልግሎት እምብዛም ባያስቡም (ዕብ. 1፡14)፥ ዳሩ ግን አንድ ቀን ወደ ሰማያት በምንገባበት ጊዜ፥ እነዚህ መላእክት በዚህ ምድር ለእኛ ያደረጉልንን ነገሮች እንረዳለን።

የመልአኩ ገለጻ (10፡1-4) - መልአኩ አንዳንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርያት ስላሉት፥ ገለጻው ያስደንቀናል። ዮሐንስ ከዚህ በፊት «ብርቱ መልአክ» ሲናገር የሰማና ያየ ሲሆን (ራእይ 5፡2)፥ በዚህ ሥፍራም «ብርቱ» የሚለውን ተመሳሳይ ቃል ይጠቀማል። መላእክት ሁሉ ብርቱዎች ሲሆኑ [መዝ. (103)፡20]፥ ዳሩ ግን አንዳንዶቹ ከሌሎች የበለጠ ኃይልና ሥልጣን ያላቸው ይመስላል።

በመጀመሪያ ቀስተ-ደመናውን የተመለከትነው በእግዚአብሔር ዙፋን አካባቢ ሲሆን (ራእይ 4፡3)፥ አሁን ግን በዚህ መልእክተኛ ራስ ላይ እንደ ዘውድ (አክሊል) ተቀምጦ እናየዋለን። ቀስተ-ደመናው እግዚአብሔር ዳግም ዓለምን በጥፋት ውኃ እንደማያጠፋ ቃል የገባበት ምልክት ነበር። በቁጣውም እንኳ፥ እግዚአብሔር ምሕረቱን ያስባል (ዕንባ. 3፡2)። ይህ መልአክ ማንም ይሁን ማን፥ የእግዚአብሔር ዙፋን ሥልጣን ተሰጥቶታል።

ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር የሚገለጸው በደመና ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በክብር ደመና ከመምራቱም በላይ (ዘጸ. 16፡10)፥ ሕግ በተሰጠ ጊዜ ጥቁር ደመናዎች የሲናን ተራራ ጋርደውት ነበር (19፡9)። እግዚአብሔር ለሙሴ የተገለጸው፥ በክብር ደመና ነበር (24 ከቁጥር 15 ጀምሮ፤ 34፡5)። «ሰረገላውን ደመና የሚያደርግ» [መዝ. (104)፡3]። ኢየሱስ ባረገ ጊዜ ደመና የተቀበለው ሲሆን (የሐዋ. 1፡9)፥ በሚመለስበትም ጊዜ በደመና ይገለጻል (ራእይ 1፡7)።

የመልአኩ ፊት «እንደ ፀሐይ» የሚያበራ መሆኑ በራእይ 1፡16 ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከተገለጸው ጋር የሚዛመድ ሲሆን፥ እግሩም በዚያው ሥፍራ በቁጥር 15 ስለጌታችን ከተገለጸው ጋር ይመሳሰላል። እንደ አንበሳ የሚያገሳው ድምፁም ራእይ 5፡5ን ያመለክታል። በመሆኑም ይህ እንደ ንጉሣዊ መልአክ ሆኖ ለዮሐንስ የቀረበው መልአክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ እንደ «እግዚአብሔር መልአክ» ሆኖ ይገለጽ ነበር (ዘጸ. 3፡2፤ መሳፍንት 2፡4፤ 6፡11-12፥ 21-22፤ 2ኛ ሳሙ. 24፡16)። ይህም ለአንድ ጊዜ የተለየ ዓላማ የተገለጸበት እንጂ፥ ለዘለቄታው ሥጋ የለበሰበት ሁኔታ አልነበረም።

ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች ሁለት ባሕርያት መልአኩ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ይገልጻሉ - በእጁ የነበረው መጽሐፍና አሰፋፈሩ አቋቋሙ። ትንቢተ መጽሐፍ ዮሐንስ የሚያስተላልፋቸውን ቀሪዎቹን ትንቢታዊ መልእክቶች ይዟለች። መጽሐፉን ለመውሰድና ማኅተሞቹን ለመፍታት የሚገባው ጌታችን ብቻ ስለሆነ (5 ከቁጥር 5 ጀምሮ)፥ ቀሪዎቹንም መልእክቶች ለባሪያው ለመስጠት የሚገባው እርሱ ብቻ ነው በማለት ልንደመድም እንችላለን።

እንደዚሁም የመልአኩ አቋቋም፥ ግዛቱን በባለንብረትነት የሚቆጣጠር የድል-አድራጊ ዓይነት ነው። ዓለሙ ሁሉ የራሱ እንደሆነ ይናገራል (ኢያሱ 1፡1-3 ተመልከት)። በእርግጥ፥ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ሊናገር የሚችለው ድል አድራጊው አዳኝ ብቻ ነው። ሐሳዊው-መሲሕ ወዲያው ወረራውን በመፈጸም ዓለሙ ሁሉ ለገዥነቱ እንዲንበረከክ ያስገድዳል። ሆኖም፥ ይህ ከመሆኑ በፊት ግን አዳኙ፥ አብ ተስፋ የገባለትን ውርስ፥ ማለትም የዓለም ባለቤትነቱን ያረጋግጣል (መዝ. 2፡6-9)። ሰይጣን ለማጥቃት የሚያደባባቸውን ሰዎች ለማስፈራራት እንደ አንበሳ የሚያገሣ ሲሆን (1ኛ ጴጥ. 5፡8)፥ የይሁዳ አንበሳ ግን ድልን ለማወጅ ያገሣል [መዝ. (95)፡3-5፤ ኢሳ. 40፡12-17 አንብብ]።

ዮሐንስ ሰባቱ ነጐድጓዶች የተናገሩትን ነገር እንዳይጽፍ ለምን እንደተከለከለ አናውቅም። በመሆኑም በዚህ «በተፈታው» መጽሐፍ ውስጥ የምናገኘው «የታተመ» ነገር ቢኖር ይኸው ብቻ ነው (ዳን. 12፡9፤ ራእይ 22፡10 ተመልከት)። ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ድምፅ ከነጐድጓድ ጋር ተወዳድሮ ቀርቧል [ዮሐ. 12፡28-29፤ መዝ. 29፤ ኢዮብ 26፡14፤ 37፡5]። እግዚአብሔር እውነቱን ለመሰወር እስከመረጠ፥ የእኛ መመራመር ዋጋ የለውም (ዘዳ. 29፡29)።

የመልአኩ እወጃ (10፡5-7) - በሚያውጀው ነገር ምክንያት ብቻ ሳይሆን፥ በሚያውጅበትም መንገድ ምክንያት፥ የመልአኩ እወጃ በአድናቆት እንድንሞላ ያደርገናል። ይኸውም መልአኩ መሐላ የሚፈጽም ይመስል እጆቹ ወደላይ ተዘርግተው የሚታዩበት ታላቅ ትዕይንት ነው።

እንግዲህ ይህ መልአክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሆነ፥ መሐላ መግባቱ ለምን ያስፈልገዋል? የተነገሩትን ነገሮች ጥብቅነትና እርግጠኛነት ለማጽናት! ቃል ኪዳኑን ከአብርሃም ጋር ባደረገና (ዕብ. 6፡13-20) ልጁ ሊቀ-ካህን እንዲሆን ባወጀ ጊዜ (7፡20-22)፥ እግዚአብሔር ራሱን «ከመሐላ በታች» አድርጓል። እንዲሁም ለዳዊት መሲሑ ከእርሱ ቤተሰብ እንደሚወጣ ቃል በገባበት ጊዜ መሐላ ፈጽሞአል (የሐዋ. 2፡29-30)።

በራእይ 10፡6 ላይ አጽንኦት የተደረገው በፈጣሪው በእግዚአብሔር ላይ ነው። የተለያዩ ፍርዶች በሰማይ፥ በምድርና በባሕር ላይ የወረዱ

ሲሆን፥ ገናም ብዙ ፍርዶች ይመጡ ነበር። «አይዘገይም» የሚለው ቃል እንደሚያስረዳው፥ እግዚአብሔር ከደኅንነት ርቀው የጠፉ ኃጢአተኞች የንስሐ ጊዜ ያገኙ ዘንድ ፍርዶቹን ሲያዘገይ ሰንብቷል (2ኛ ጴጥ. 3፡1-9)፤ አሁን ግን ፍርዶቹን በማውረድ፥ ዓላማዎቹን ይፈጽማል።

በሰማያት የነበሩ ቅዱሳን ሰማዕታት በገዳዮቻቸው ላይ እግዚአብሔር ሳይበቀል በመቆየቱ አሳብ እንደገባቸው አስታውስ (ራእይ 6፡10-11)። «እስከ መቼ? ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ?» የሚለው ከዘመን ዘመን በመከራ ውስጥ የሚያልፉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚያሰሙት ጩኸት ሆኖ ቆይቷል። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎቹን በመፈጸሙ ረገድ ለሰዎች የሚዘገይ የመምሰሉ ሁኔታ፥ ተሳላቂዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲክዱና እውነተኛነቱን እንዲጠራጠሩ አድርጓል (2ኛ ጴጥ. 3 ተመልከት)። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ሲሆን፥ የጊዜ ሰሌዳውም ፍጹም ነው። ይህም ለቅዱሳን ዕረፍት፥ ለኃጢአተኞች ደግሞ ፍርድ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ፥ «ምሥጢር» በውጭ ለሚገኙት የተሰወረና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ግን በቃሉ አማካኝነት የተገለጸ «ቅዱስ ምሥጢር» ነው (ማቴ. 13፡10-12)። «የእግዚአብሔር ምሥጢር» ዓለምን ለዘመናት ሲያምሳት ከቆየው ክፋት ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት። በዓለም ውስጥ የሥነ ምግባር ጉድለትና የተፈጥሮ ክፋት የሚታየው ለምንድን ነው? ለምን እግዚአብሔር አንዳች መፍትሔ አይፈልግም? በመሠረቱ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎልጎታ እንደ ኃጢአተኛ በተቆጠረና፥ በኃጢአተኛውም ዓለም ምትክ መለኮታዊ ቁጣ በተቀበለ ጊዜ፥ እግዚአብሔር «መፍትሔ እንደሰጠ» ማንኛውም ክርስቲያን በግልጽ የሚረዳው ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ክፉው እንዲኖር የሚፈቅደው ዓለም ለፍርድ እስከትጐመራ ድረስ እንደሆነ እናውቃለን (2ኛ ተሰ. 2 ከቁጥር 7 ጀምሮ፤ ራእይ 14፡14-20)። እግዚአብሔር ቀደም ብሎ የኃጢአትን ዋጋ ስለከፈለ፥ ፍርዱን ለማዘግየት ይችላል - ማንም ደግሞ ፍትሕ-አልባ ወይም ለሰዎች የማይገደው እንደሆነ አድርጐ ሊወቅሰው አይችልም።

ለዚህም ምሥጢር ማብቃት ምልክቱ የሰባተኛው መለከት መነፋት ነው (11፡14-19)። የመከራው ሁለተኛ አጋማሽ የሚጀምረው፥

መላእክት የእግዚአብሔር ቁጣ የሚፈጸምባቸውን ጽዋዎች ማፍሰስ ሲጀምሩ ነው (15፡1)።

መልአኩ ለዮሐንስ የሰጣቸው ትእዛዛት (10፡8-11)፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰራጨትና ቃሉንም የውስጣዊው ሰውነታችን አካል የማድረግ ኃላፊነት እንዳለብን ያስታውሱናል። ለዮሐንስ መጽሐፉን ማየት ወይም ይዘቶቹንና ዓላማውን ማወቅ ብቻ አይበቃውም ነበር - ወደ ውስጣዊ ሰውነቱ ማስገባት ያስፈልገው ነበር።

የእግዚአብሔር ቃል ከተለያዩ ምግቦች፥ ማለትም ከእንጀራ (ማቴ. 4፡4)፥ ወተት (1ኛ ጴጥ. 2፡2)፥ ሥጋ (1ኛ ቆሮ. 3፡1-2) እና ከማር [መዝ. (119)፡103] ጋር ተወዳድሯል። እንደ ኤርምያስ (ኤር. 15፡16) እና ሕዝቅኤል (ሕዝ. 2፡9-3፡4) ያሉ ነቢያት፥ ለሌሎች ከማካፈላቸው በፊት ቃሉን «መብላት» ምን ማለት እንደሆነ ያውቁ ነበር። ቃሉ ሁልጊዜም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ከመሰጠቱ በፊት «ሥጋ መሆን» አለበት (ዮሐ. 1፡14)። የእግዚአብሔርን ቃል የስብእናው አካል አድርጐ ከመቀበሉ በፊት እንደ ገደል ማሚቶ ለሚያስተጋባው ሰባኪ ወይም አስተማሪ ወዮለት!

እግዚአብሔር ቃሉን ወደ አፋችን በማስገባት፥ እንድንጐርሰው አያስገድደንም። በእጃችን ሲሰጠን መቀበል መቻል አለብን። እንዲሁም ደግሞ ቃሉ በሕይወታችን ውስጥ የሚያስከትለውን ለውጥ ለማስቀረት አንችልም - ኃዘንና ደስታ፥ መራርነትና ጣፋጭነት ሊከሰቱ ይችላሉ። የእግዚአብሔር ቃል ጣፋጭ የተስፋ ቃሎችንና ዋስትናዎችን፥ እንዲሁም መራራ ማስጠንቀቂያዎችንና የፍርድ ትንቢቶችን ያካትታል። ክርስቲያን፥ የሕይወትና የሞት ምስክርነትን ይሸከማል (2ኛ ቆሮ. 2፡14-17)። ታማኝ አገልጋይ የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ያውጃል (የሐዋ. 20፡27)። አድማጮቹን ለማስደሰት ብቻ የእግዚአብሔርን መልእክት አይቀይጥም (2ኛ ጢሞ. 4፡1-5)።

መልአኩ ዮሐንስን ዳግመኛ እንዲተነብይ ይልከዋል - ሥራው ገና አላለቀም ነበር። በርካታ ሰዎችንና ሕዝቦችን፥ ልሳናትንና ነገሥታትን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ትንቢታዊ እውነት ማወጅ ነበረበት (5፡9)። ብዙውን ጊዜ «ሕዝቦች» የሚለው ቃል አሕዛቦችን የሚያመለክት

ሲሆን፥ ዮሐንስ የዚህን ትንቢት ቀሪ ክፍሎች በሚያቀርብበት ጊዜ ስለ ዓለም ሕዝቦች ብዙ የሚለው ይኖረዋል።

የሁለቱ ምስክሮች ምስክርነት (ራእይ 11፡ 1-14)

የምስክሮቹ አገልግሎት (11፡1-6) በመጀመሪያ ተገልጾአል። ስፍራው ኢየሩሳሌም ሲሆን፥ ጊዜውም በመጀመሪያው የመከራ አጋማሽ ወቅት ነው። እስራኤል እውነተኛ ባሕርዩ ገና ባልተገለጸበት በሐሳዊ-መሲሕ ጥበቃ ሥር በመሆን፥ ዳግም በተገነባው ቤተ መቅደሷ ውስጥ አምልኮቷን ታካሂድ ነበር። እዚህ ላይ ልንረዳ የሚገባው፥ ከቁጥር 1-2 የሚገኘውን ክፍል መንፈሳዊ ለማድረግ መሞከርና ቤተ መቅደሱ ቤተ ክርስቲያንን እንደሚያመለክት መቁጠር፥ አንዳንድ አዳጋች ችግሮችን ማስከተሉን ነው። በመጀመሪያ ደረጃ፥ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ብትሆን እንኳ፥ ዮሐንስ የሕዝቦችን የማይታይ አካል እንዴት ሊለካ ይችላል? የሚለው ጥያቄ ሊያጋጥመን ይችላል። ደግሞ ቤተ መቅደሱ ቤተ ክርስቲያን ከሆነ፥ የሚያመልኩት ሰዎች እነማን ሊሆኑ ይችላሉ? መሠዊያውስ ምንድን ነው? ቤተ ክርስቲያን አይሁዶችንና አሕዛቦችን በአንድ አካል የምታስተባብር እስከሆነ ድረስ (ኤፌ. 2 ከቁጥር 11 ጀምሮ)፥ አሕዛቦች በቤተ መቅደስ ውስጥ ከአይሁዶች የተለዩት ለምንድን ነው? በመሆኑም፥ ይህንን ቤተ መቅደስ በቅድስቲቱ የኢየሩሳሌም ከተማ እንደሚገኝ እውነተኛ ሕንፃ ብቻ አድርጎ መተርጎሙ ከሁሉም የላቀ ጥበብ ይመስላል (ነህምያ 11፡1፥18፤ ዳን. 9፡24)።

ዮሐንስ መቅደሱን መለካቱ ተምሳሌታዊ ተግባር ነው። አንድን ነገር መለካት ማለት የራስህ እንደሆነ መናገር ማለት ነው። በሺካጎ ከተማ ቤታችንን በሸጥን ጊዜ፥ ቤቱን የገዙት ሰዎች የተለያዩ አካባቢዎችን እንዲለካና መለወጥ ያለባቸውን ነገሮች እንዲጠቁማቸው፥ አንድ የሕንፃ ንድፍ ሠራተኛ (አርክቴክት) አምጥተው ነበር። የንድፍ ሠራተኛው ገዢዎቹ ከእኛ ጋር ሳይስማሙ በፊት መጥቶ ቢሆን ኖሮ፥ አናስገባውም ነበር። ጌታ በዮሐንስ አማካኝነት «ይህ ከተማና መቅደስ የእኔ ስለሆኑ፥ ሁለቱም የእኔ ንብረት መሆናቸውን አስታውቃለሁ» እያለ ነበር። ለዚህም ከሕዝቅኤል 40-41 እና ዘካርያስ 2፡1-3 ውስጥ ተስማሚ የሆነ የብሉይ ኪዳን የድሮ ታሪክ እናገኛለን።

በተለይ አሕዛቦች ኢየሩሳሌምን ተቆጣጥረው ስለነበር፥ ዮሐንስ ያደረገው ነገር ጠቃሚ ነበር። ሐሳዊው-መሢሕ ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያፈረሰ ሲሆን (ዳን. 9፡27)፥ በዚህ ጊዜ ቤተ መቅደሱን ለራሱ ሰይጣናዊ ዓላማዎች ሊጠቀምበት በዝግጅት ላይ ነበር (2ኛ ተሰ. 2፡3-4)። ይህ ሁሉ በራእይ 13 ይብራራል። ኢየሱስ፥ «የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች» ብሏል (ሉቃ. 21፡24)። «የአሕዛብ ዘመን» የተጀመረው ባቢሎን ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን ማፈራረስ በጀመረችበት በ606 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድስቲቱን ከተማ ነፃ ለማውጣትና እስራኤልን ለማዳን እስኪመለስ ድረስ ይቀጥላል (ዘካ. 14)።

ሁለቱ ምስክሮች የሚያገለግሉት በመከራው የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ እንደሆነ ልብ በል (ራእይ 11፡3፤ 1,260 ቀናት)። ከዚያም ኢየሩሳሌም ለአርባ ሁለት ወራት በአሕዛቦች የምትረገጥ ሲሆን፥ ይህም የመከራው የመጨረሻ አጋማሽ ነው።

ምስክርነታቸው ከእስራኤልና ከመቅደሱ ጋር የተያያዘ ነው። የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ቃል እንደቀደሙት ዘመናት በውስጥ ሳይሆን ከመቅደሱ ውጭ መሆኑ ምንኛ አሳዛኝ ነገር ነው! ኢየሱስ ትቶት እንደሄደው መቅደስ ሁሉ፥ ይህም አዲስ ቤት የረከሰ ይሆናል (ማቴ. 23፡38 ተመልከት)። እነዚህ ሁለት ሰዎች በግልጽ ነቢያት ተብለው የተጠሩ ሲሆን (ራእይ 11፡3፥ 6)፥ እኔም ብሆን አባባሉን በብሉይ ኪዳን እንደነበረው የትንቢት አገልግሎት አድርጌ እወስደዋለሁ። ሰዎችን ወደ ንስሐና እውነተኛ ወደሆነው የእስራኤል አምላክ የመመለስ ጥሪ እንደሆነ አምንበታለሁ።

እነዚህ ምስክሮች የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን እንደ ሙሴና ኤልያስ የእግዚአብሔርን ሥራና የፍርድ ተአምራት ይፈጽማሉ (ዘጸ. 7፡14-18፤ 1ኛ ነገሥ. 17 ከቁ. 1 ጀምሮ፤ 2ኛ ነገሥ. 1፡1-12)። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ሚልክያስ 4፡5-6ን በመጥቀስ፥ ከሁለቱ ምስክሮች አንደኛው ኤልያስ ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ፤ ይሁንና ኢየሱስ ያ ትንቢት በመጥምቁ ዮሐንስ እንደተፈጸመ ተናግሯል (ማቴ. 17፡10-13)። ይህም ሆኖ፥ መጥምቁ ዮሐንስ ወደ ምድር ተመልሶ የመጣው ኤልያስ እንዳልሆነ ስለራሱ ተናግሯል (ዮሐ. 1፡21፥ 25፤ ሉቃ. 1፡16-17 ተመልከት)። ሆኖም

በእስራኤል ታሪክ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን በንስሐ ለመመለስ ልዩ መልእክተኞችን - «ኤልያሶችን» ይልክ እንደነበር በመረዳት፥ ይህንን ውዝግብ በከፊል ለማብራራትና ለመረዳት ይችላል። በዚህም መሠረት፥ የሚልክያስ ትንቢት በምስክሮቹ ይፈጸማል።

ለዮሐንስ የተናገረው መልአክ የሁለቱን ምስክሮች አገልግሎት ከሙሴና ኤልያስ ጋር በማዛመድ ፈንታ፥ ከዘሩባቤልና ከሊቀ-ካህኑ ኢያሱ ጋር አያይዞታል (ዘካ. 4)። እነዚህ ሁለት ሰዎች እስራኤልን ዳግም በፍልስጥኤም ለመመሥረትና ቤተ መቅደሱን ዳግም ለመገንባት እገዛ አድርገዋል። ሥራው ተስፋ የሚያስቆርጥ ሲሆን፥ አሕዛቦቹ ይበልጥ አዳጋች አደረጉት፤ ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር ለሥራው መገባደድ የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ኃይል ሰጣቸው። የእግዚአብሔር ሥራ ከቶውንም በቀላል የሚወጡት ስላልሆነ፥ ይህ እውነት በዘመናት ሁሉ ለእግዚአብሔር ባሪያዎች ማበረታቻ ነው።

ሁለቱም ምስክሮች በመስዋዕትነት የሚያልፉት (11፡7-10) ምስክርነታቸውን ከፈጸሙ በኋላ ብቻ ነው። ታዛዥ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሥራቸው እስኪፈጸም ድረስ ሕያዋን ናቸው። «አውሬው» (ሐሳዊው-መሲሕ) በዚህ ጊዜ በሥልጣን ላይ ሲሆን፥ ቤተ መቅደሱን ለመቆጣጠር ይፈልጋል፤ ይሁንና ሁለቱ ምስክሮች ከመንገድ እስኪወገዱ ድረስ አይሆንለትም። ማንም «አውሬው»ን ሊዋጋና ሊያሸንፍ ስለማይችል (ራእይ 13፡4)፥ እግዚአብሔር ምስክሮቹን እንዲያርድ ይፈቅድለታል።

ምስክሮቹ በተገቢው ሥርዓት እንዲቀበሩ እንኳ አይፈቅድላቸውም [መዝ. (79)፡1-3]። ይሁንና ይህ በሥርዓት ለመቀበር ያለመታደል (በድናቸው በመንገድ ላይ መጣሉ) እንኳ ለሰው ልጆች ምስክርነትን ያስተላልፋል። ትዕይንቱን የቴሌቭዥን ካሜራዎች በቀጥታ ከኢየሩሳሌም ለዓለም ሕዝብ እንደሚያስተላልፉትና የዜና ዘጋቢዎችም በጉዳዩ ጠቀሜታ ላይ እንደሚወያዩበት አያጠያይቅም። የምድር ላይ ነዋሪዎች በጠላቶቻቸው መወገድ ይደሰቱና ስጦታዎችን በመለዋወጥ «ሰይጣናዊ ገናን» ያከብራሉ። በመሆኑም ሁለቱ ምስክሮች በኢየሩሳሌም ብቻ ሳይወሰኑ፥ ዳሩ ግን በሌሎች የዓለም ክፍሎች ላይ ክስተቶችን የሚያስከትሉ ይመስላል።

እነዚህ ሁለቱ ነቢያት ያለጥርጥር ከእስራኤል ጋር ግንኙነት የሚኖራቸው ሲሆን፥ ዓለም በአመዛኙ የእስራኤልን ሕዝብ አትደግፍም።

በመከራው አጋማሽ ላይ፥ «አውሬው» በእስራኤል ላይ ይነግና አይሁዶችን ማሳደድ ይጀምራል። ሁለቱ ምስክሮች ሕዝቡን ለመጠበቅ በዚያ ስለማይኖሩ፥ አስፈሪ ፀረ-ሴማዊ እንቅስቃሴ ይጀመራል።

ኢየሩሳሌም «ታላቂቱ ከተማ» በመባል የተጠራች ሲሆን (ራእይ 11፡8)፥ ይህም ከሰብዓዊ ዕይታ አንጻር እውነተኛ አገላለጽ ነው። ይሁንና እግዚአብሔር ሰዎችንና ሕዝቦችን የሚመለከተው በመንፈሳዊ ገጽታቸው ነው። ለእርሱ ኢየሩሳሌም እንደ ሰዶም የተበከለችና ዓለማዊት፥ እንደ ግብፅም ዓመፀኛና ትዕቢተኛ ሆና ትቆጠራለች።

የምስክሮቹ መነሣት (11፡11-14) ሁለቱ ምስክሮች በተአምራዊ ሁኔታ ከሞት መነሣት ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ወደ ሰማይም ያርጋሉ። እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው በመታደግ፥ ሁኔታቸውን በቅርብ ለሚከታተለው ዓለም የጠበቀ ምስክርነት እንዲያስተላልፉ ያደርጋል። በዚህም ታላቁ የዓለም ደስታ በታላቅ ፍርሃት ይተካል። (በምዕራፍ 11 ውስጥ «ታላቅ» የሚለው ቃል 8 ጊዜ እንደተደጋገመ አስተውል።)

ለመሆኑ ሦስት ተኩል ቀናት የተባሉትን በቀጥታ ቃል በቃል ልንተረጉማቸው ይገባል? ወይስ «ከጥቂት ጊዜ በኋላ» ለማለት የተጠቀሱ ይሆን? እንዲህ ለማለት መሞከሩ ክንዋኔውን በጣም ውስን ማድረግ ይመስላል። ይህ ካልሆነ ደግሞ ረዘም ያለ ጊዜ፥ ለምሳሌ ሦስት ዓመት ተኩል ያመለክት ይሆን? ሁለት የሙታን አስከሬኖች በከተማዪቱ መንገድ ላይ ከሦስት ዓመታት በላይ ይጠበቃሉ ማለቱ የማይመስል ይሆናል። ምናልባት ይህ በመከራው መካከል ቅዱሳን ሁሉ እንደሚነጠቁ የሚያመለክት ሲሆን፥ ሦስት ተኩል ዓመታቱ ግን የመከራውን የመጀመሪያ አጋማሽ የሚሸፍን ነው። ይህ ከሆነ፥ በሁለቱ ምስክሮች ሞት የተመለከተው ምንድን ነው? ይህ አተረጓጐም አንደኛውን ችግር ቢያቀልልም፥ ሌላ ጥያቄ ያስነሣል።

በራእይ 11፡2 ላይ የሚገኙ አርባ ሁለት ወራት ቀጥተኛ ትርጓሜ እንዳላቸው ሁሉ፥ እነዚህም ቀናት ቃል በቃል የሚፈጸሙ ይመስላሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህ የጊዜ ርዝመት ለምን እንደተመረጠ ስለማይናገር፥ በዚህ ጉዳይ ላይ መመራመሩ ፋይዳ አይኖረውም።

የጌታችን «ወዳጆች» ወደ ሰማይ ሲያርግ የተመለከቱት ሲሆን (የሐዋ. 1፡9-12)፥ ዳሩ ግን የምስክሮቹ ጠላቶች ከሞት ሲነሡ

ለመመልከት በፍርሃት ይዋጣሉ። በተጨማሪም፥ ታላቅ የምድር መናወጥ በተነሣና 7,000 ሰዎችን በገደለ ጊዜ እና የኢየሩሳሌም አንድ አሥረኛው ክፍል ሲወድም፤ ፍርሃታቸው ገደብ የለሽ ይሆናል። ስድስተኛው ማኅተም በተከፈተ ጊዜ ታላቅ የምድር መናወጥ የተከሰተ ሲሆን (ራእይ 6፡12)፥ ሰባተኛው ጽዋ በፈሰሰ ጊዜ ከዚያ የበለጠ ርዕደ-ምድር ይከሰታል (16፡18-20)።

የሽማግሌዎች ምስክርነት (ራእይ 11፡15-19)

ከራእይ 8፡13 ጀምሮ የሦስተኛውን «ወዮ» መምጣት እንጠባበቅ ነበርና ከዚህ በመቀጠል ቀርቧል። ሰባተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ፥ ሦስት አስገራሚ ክስተቶች ተፈጽመዋል።

የድል አወጃ (11፡15) - እነዚህ «ታላላቅ ድምፆች» ምናልባት የሰማይ መዘምራን ይሆናሉ። ታላቁ አወጃ የዚህ ዓለም መንግሥት (በዚህ ጊዜ «አውሬው» ዓለምን ስለተቆጣጠረ፥ ዮሐንስ በነጠላ ስያሜ ይጠቀማል) ለኢየሱስ ክርስቶስ መሰጠቷን መግለጽ ነው። ክርስቶስ እስኪመለስ ድረስ የንጉሣዊ መብቶቹን ባለቤትነት የማይቆጣጠር ሲሆን፥ ድሉን ግን ቀደም ብሎ ተቀዳጅቷል። ምንም እንኳን ሰይጣን እርሱን ለመፈታተን የዓለምን መንግሥታት እንደሚሰጠው ሊያግባባው ቢሞክርም፥ ጻሩ ግን እርሱ ስጦታውን አልተቀበለም ነበር (ማቴ. 4፡8-9)። ይልቁንም፥ በመስቀል ላይ በመሞት፥ በመነሣትና ወደ ሰማይ በድል በማረግ፥ከአብ ውርስ አግኝቷል (መዝ. 2፡4-9)።

ይሁንና፥ ጌታችን ዛሬም ቢሆን በመግዛት ላይ እንዳልሆነ በመገመት ልንሳሳት አይገባም - እየገዛ ነው። በዕብራውያን 7፡1-2 መሠረት፥ ኢየሱስ ክርስቶስ «የጽድቅ ንጉሥ» እና «የሰላም ንጉሥ» ነው። ከአብ ጋር በዙፋን ላይ የተቀመጠ ሲሆን (ራእይ 3፡21)፥ ጠላቶቹን ሁሉ ድል እስከሚያደርግ ድረስ ይነግሣል (1ኛ ቆሮ. 15፡25)። ዛሬ በመንፈሳዊ መንግሥት ላይ የሚገዛ ሲሆን፥ ወደፊት ግን በዓለም ሕዝቦች ሁሉ ላይ በመንገሥ በብረት በትር ይገዛቸዋል።

ሁኔታዎች ምንም ያህል አስቸጋሪዎች ቢሆኑም፥ ወይም የእግዚአብሔር ሰዎች ምንም ያህል እንደተሸነፉ ቢያስቡም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ አሁንም የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ሆኖ ሁሉንም በመቆጣጠር ላይ ይገኛል። እኛም አንድ ቀን የድል ባለቤቶች እንሆናለን!

የምስጋና ሆታ (11፡16-18) - ሽማግሌዎቹ የራሳቸውን ዙፋናት በመልቀቅ፥ በእግዚአብሔር ፊት በአምልኮ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ይሰግዳሉ። ስለሦስት ልዩ በረከቶችም ምስጋና ያቀርባሉ - ክርስቶስ በበላይነት ስለሚገዛ (ቁ. 17)፥ በጽድቅ ስለሚፈርድ (ቁ. 18)፥ እና በቸርነት ለቅዱሳኑ ስለሚሸልም (ቁ. 18)።

በራእይ 4፡10-11፥ ሽማግሌዎቹ ፈጣሪን ያመሰገኑት ሲሆን፥ በ5፡9-14 ላይ አዳኙን ያመልኩታል። በዚህ ስፍራ ትኩረት የተሰጠው ለአሸናፊው ንጉሥ ነው። በጊዜው ሮም አሸናፊና ንጉሥ ስለነበረች፥ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የተሸነፈች ትመስል ነበር። ዮሐንስ ለቅዱሳኑ ከአዳኙ ጋር የሚነግሡ «የካህናት መንግሥት» መሆናቸውን እያስታወሰ ነበር (1፡5-6)። አንዳንድ ጊዜ የሰማዩ ዙፋን ባዶና ተቀማጭ የሌለበት ቢመስልም፥ እውነቱ ግን እንዲህ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይልም ሥልጣንም አለው - እንዲያውም ማናቸውም ሥልጣን ሁሉ (ማቴ. 28፡18)። «ስለ ነገሥህ . . .» የሚለው ጥሩ ትርጉም ነው።

ክርስቶስ በበላይነት መግዛት ብቻ ሳይሆን፥ ዳኑ ግን በጽድቅም ይፈርዳል (11፡18)። በጉ አንበሳም ነው! በቁጥር 18 ውስጥ፥ ለተቀረው የራእይ መጽሐፍ ማውጫ የሚሆን ነገር ይገኛል። እነዚህ ክስተቶች መልአኩ መለከቱን በነፋበት ጊዜ አልተፈጸሙም። መለከቱ የሂደቱን መጀመር ብቻ ያመለከተ ሲሆን፥ ክስተቶቹ ግን በታቀደላቸው መሠረት ይፈጸማሉ።

«ሕዝቦቹ ተቆጥተው ነበር»፥ ግን ምን ያስቆጣቸዋል? ያለጥርጥር ጌታ ለእነርሱ መልካምና ቸር ነበር። ጉድለታቸውን ሞልቶላቸዋል (የሐዋ. 14፡15-17፤ 17፡24-31)፤ ዳርቻቸውን ወስኖላቸዋል፤ እንዲሁም ለሰዎች የመዳን ዕድል ለመስጠት ፍርዱን አዘግይቷል። ከዚህም በላይ፥ ዓለሙን ሁሉ ያድን ዘንድ ልጁን ልኳል። ዛሬ እግዚአብሔር ለሕዝቦች ይቅርታን ይሰጣል። ከዚህ የበለጠ ምን ሊያደርግላቸው ይችል ኖሯል?

እንግዲህ፥ ሕዝቦች ለምን ይቆጣሉ? ለዚህ ምክንያቱ በራሳቸው መንገድ ለመሄድ ስለሚፈልጉ ነው። «አሕዛብ ለምን ያጉረመርማሉ? ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ? የምድር ነገሥታት ተነሡ፥ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ እንዲህ ሲሉ ተማከሩ፡- ማሰርያቸውን እንበጥስ፥ ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል» (መዝ. 2፡1-3)። በፈጣሪ ፈንታ ፍጥረትን ለማምለክና ለማገልገል ይሻሉ (ሮሜ 1፡25)። እንደ

ኍረምሳ ልጅ፥ ሕዝቦች ማንኛውንም መከላከያ በማስወገድ ራሳቸውን ልቅ ለማድረግ የሚጥሩ ሲሆን፥ እግዚአብሔርም እንደመሻታቸውና ፍላጎታቸው እንዲሆኑ ይፈቅድላቸዋል። ውጤቱም ሌላ «ባቢሎን» - ወይንም ሰው «ገነትን በምድር ላይ» ለመገንባት የሚጥርበት የመጨረሻ ሙከራ ይሆናል (ራእይ 17-18)።

የዓለም ሕዝቦች የሚያሳዩትን የአመላከከት ለውጥ ልብ በል። በራእይ 11፡2፥ ሕዝቦች (አሕዛቦች) በጭካኔ ኢየሩሳሌምን ይቆጣጠሯታል። በ11፡9፥ በሁለቱ ምስክሮች መገደል ደስ ይሰኛሉ። አሁን ግን፥ ትዕቢታቸውና ደስታቸው የፀሐይ ሙቀት እንዳረፈበት ጤዛ በኖ በመጥፋቱ፥ ተቆጥተዋል። ይህ የቁጣና የጥላቻ አመለካከት እያደገ ይሄድና በመጨረሻው ሰዎች እግዚአብሔርን በአርማጌዶን ጦርነት እንዲዋጉት ያስተባብራቸዋል።

«ቁጣህም መጣ።» በቁጥር 18፥ «ቁጣ» የሚለው ቃል ለማንኛውም ዓይነት ቁጣ የሚያገለግል ቢሆንም፥ ዳሩ ግን የሰው ቁጣ ከቶውንም ከበጉ ቁጣ ጋር ሊስተካከል አይችልም (6፡16-17)። የከፋው የሰይጣን ቁጣ እንኳ ቢሆን፥ ከእግዚአብሔር ቁጣ ጋር ሊዛመድ አይችልም (12፡17)። በመጀመሪያው የመከራ አጋማሽ ከባድ ሥቃይ ቢኖርም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ቁጣ የሚገለጸው በሁለተኛው አጋማሽ ውስጥ ብቻ ነው (11፡18፤ 14፡10፤ 16፡19፤ 19፡15)። ቁጣን የሚገልጹ ሁለት የግሪክ ቃላት ሲኖሩ፥ አንደኛው «ቱምስ» ማለትም «ከውስጥ ፈንቅሎ የሚወጣ የስሜታዊነት ቁጣ» ነው፤ ሁለተኛውና በዚህ ሥፍራ ያገለገለው «ኦርጅ» የሚለው ሲሆን፥ «የእግዚአብሔር ቁጣ፥ የተረጋጋ የቁጣ ዝንባሌ» የሚል ትርጉም ይይዛል። የእግዚአብሔር ቁጣ በደም ፍላት የሚካሄድ ስሜታዊ ድንፋታ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በኃጢአት ላይ የሚገለጽ የተቀደሰ ቁጣ ነው። እነዚህ ሁለቱም የግሪክ ቃላት በራእይ ውስጥ የእግዚአብሔርን ቁጣ ለመግለጽ አገልግለዋል - ኦርጅ አራት ጊዜ የተጠቀሰ ሲሆን፥ ቱምስ ሰባት ጊዜ (14፡10፥ 19፤ 15፡1፥7፤ 16፡1፥19፤ 19፡15) ተጠቅሷል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ስለሚጠላና ጽድቅንና ፍርድን ስለሚወድ፥ ቁጣው ሙሉ በሙሉ ስሜት-አልባ አይደለም፤ ይሁንና ትዕግሥት የሌለበትና የማይገመትም አይደለም።

«በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ» የሚለው ወደ እግዚአብሔር ትንቢታዊ መርሐ-ግብር ፍጻሜ ይወስደናል። በአንድ

በኩል፥ እግዚአብሔር ሁልጊዜም በጽድቅ እየፈረደ ስላለ፥ ሁሉም ቀን «የጌታ ቀን» ነው። እግዚአብሔር ከደኅንነት ርቀው ለጠፉ ሰዎች ስለሚታገሥ፥ ብዙውን ጊዜ ፍርድን ያዘገያል። ይህም ሆኖ፥ በኃጢአተኞች ሁሉ ላይ ፍርድ የሚበየንበት የመጨረሻ ቀን ስላለ፥ አንዳቸውም አያመልጡም። ይህም ፍርድ በራእይ 20፡11-15 ተገልጾአል።

በተጨማሪም፥ «የክርስቶስ የፍርድ ወንበር» የሚባል የእግዚአብሔር ልጆች ፍርድ ይኖራል (ሮሜ 14፡10-13፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡9-15፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡9-11)። እግዚአብሔር ለታማኝ አገልጋዮቹ ሽልማት ይሰጥና (ማቴ. 25፡21)፥ በምድር ላይ የተሠቃዩባቸው መከራዎች በህልውናው ክብር በመደምሰስ ይረሳሉ። የእግዚአብሔር ልጆች ለኃጢአታቸው ባይፈረድባቸውም (ይኼኛው ፍርድ በመስቀል ላይ ስለተፈጸመ) በሥራቸው ላይ ፍርድ ይሰጥና ከጌታቸው እጅ የከበረ ሽልማት ያገኛሉ።

የክርስቶስ የፍርድ ወንበር ሕዝቡን ወደ ቤቱ ከወሰዳቸው በኋላ በሰማይ የሚፈጸም ነው። መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ፥ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ነቀፋ ተወግዶ ቅዱሳን ከእርሱ ጋር ለመግዛት ይዘጋጃሉ (ኤፌ. 5፡25-27፤ ራእይ 19፡7-8)። ዛሬ፥ ስንኩልነታችንንና ነቀፋችንን ብቻ ደህና አድርገን ስለምናውቅ፥ እግዚአብሔርን በምናገለግልበት ጊዜ ከመጠን በላይ እንቃትታለን፤ ይሁንና አንድ ቀን፥ «በፍጹምነት» እናገለግለዋለን።

«ምድርን የሚያጠፉ» የሚለው ለእግዚአብሔር የማይገዙትን የምድር ላይ ነዋሪዎች ያመለክታል። እነዚህ ሰዎች ለምድርና ለምቾቷ እየኖሩ፥ ዳሩ ግን ያችኑ የሚያመልኳትን ምድር የማጥፋታቸው ጉዳይ ምንኛ አሳዛኝና ቅኔያዊ ገለጻ ነው! ሰው እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደሆነና እርሱም ፍጡር እንደሆነ ሲዘነጋ፥ ከእግዚአብሔር የተቀበላቸውን ሀብቶች መበዝበዝ ይጀምርና ይህም በበኩሉ ወደ ጥፋት ያመራል። ሰው የፍጥረት አስተዳዳሪ እንጂ፥ ባለቤት አይደለም።

ከዚህ በፊት እንደተጠቀሰው፥ ቁጥር 18 ገና ስለሚመጡ ነገሮች የሚናገር የማጠቃለያ ዓረፍተ ነገር ነው። እግዚአብሔር በዓለም ዓላማዎቹን ለመፈጸም ታማኝ በመሆኑ የቀረበለት ሰማያዊ የምስጋና መዝሙር ነው። አሁንም፥ ሰማያዊ አካላት ስለፍርድ የመዘመራቸው

ጉዳይ እንግዳ ነገር ይሆንብናል። ምናልባት የበለጠ የዞሩት ዕይታ (ግንዛቤ) ቢኖረን ኖሮ፥ በምስጋናቸው ለመካፈል እንችል ነበር።

የእግዚአብሔር ታማኝነት ዋስትና (11፡19) - ይህ ምዕራፍ የተከፈተው በምድር ላይ የሚገኘውን ቤተ መቅደስ በማመልከት ሲሆን፥ አሁን ግን በሰማይ ቤተ መቅደስን እናያለን። የዚህም አትኩሮት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር እንዳለ በሚያመለክተው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ላይ ነው።

በብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳንና ቤተ መቅደስ ውስጥ፥ ታቦቱ ከመጋረጃው አልፎ በቅድስተ-ቅዱሳን ውስጥ ይቀመጣል። የእግዚአብሔር ክብር በታቦቱ ላይ የሚያርፍ ሲሆን፥ ሕጉም በታቦቱ ውስጥ ይገኝ ነበረና፥ ይህ ሁለቱ በምንም ዓይነት መንገድ መለያየት እንደሌለባቸው በግሩም ሁኔታ ያብራራልናል። እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና፥ በኃጢአት ላይ በጽድቅ መፍረድ አለበት። ይሁንና፥ ለሕዝቡ የተስፋ ቃሎቹን የሚጠብቅ ታማኝ አምላክ ነው። እስራኤላውያንን በዮርዳኖስ ባሕር አሻግሮ ወደ ርስታቸው የመራቸው የእግዚአብሔር ታቦት ነበር (ኢያሱ 3፡11-17)። ይህ የታቦት ራእይ ዮሐንስ ይህንን መጽሐፍ ለላከላቸው ለእነዚህ በመከራ ውስጥ ለሚገኙ የእግዚአብሔር ሰዎች ታላቅ ማበረታቻ ነበር። ዮሐንስ፥ «እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎቹን ይፈጽማል! ክብሩንም ይገልጻልና ተማምናችሁ ጠብቁት!» እያላቸው ነበር።

ዮሐንስ አሁንም፥ የማዕበልን ምልክቶች ይመለከታል - ያያልም (ራእይ 4፡5፤ 8፡5 ተመልከት)። በምድር ላይ በሚኖሩ ዓመፀኛ ሰዎች ላይ ታላቅ ፍርድ የሚተላለፍበት ጊዜ የቀረበ ሲሆን፥ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ላይ ስለሚገኝ፥ የእግዚአብሔር ሰዎች መፍራት አያስፈልጋቸውም ነበር። ታቦቱ የእርሱን ህልውናና የተስፋ ቃሎቹን ታማኝነት ያስታውሳቸዋል። በእያንዳንዱ የስርየት ቀን ደም የሚረጭበት የምሕረት መክደኛ የሚቀመጠው በዚያው ታቦት ላይ ነበር (ዘሌ. 16፡15-17)። በቁጣውም እንኳ፥ እግዚአብሔር ምሕረቱን ያስባል (ዕንባ. 3፡2)።

አሁን ዓለምን ለሚቆጣጠረው ሐሰተኛ ክርስቶስና የሰይጣን ቁንጮ ለሆነው «አውሬ» ትንግርታዊ መገለጽ መድረኩ ተዘጋጅቷል።

- 8 -

ሦስቱ አስከፊ ባሕርያት

ራእይ 12-13

ራእይ 12-13 በመጨረሻው የመከራው ዘመን ውስጥ ስለሚከሰተው ትርዒት ሦስት ቁልፍ ባሕርያትን ያስተዋውቀናል - ዘንዶው ሰይጣን፥ ሐሰተኛው ክርስቶስና ሐሰተኛው ነቢይ። እነዚህ ሦስቱ እውነተኛውን አምላክና በምድር ላይ የሚገኘውን ሕዝቡን የሚቃወሙ የክፋው ሥላሴ አምሳሎች ናቸው። ምንም እንኳን እነዚህ ክስተቶች በዚያን ወቅት ለሚኖረው የእግዚአብሔር ሕዝብ ልዩ ጠቀሜታ ቢኖራቸውም፥ ሆኖም ግን የእነዚህ ሁለት ምዕራፎች መልእክት በማንኛውም ዘመን ውስጥ ሆነው መከራ የሚቀበሉትን ቅዱሳን ሁሉ ሊያበረታታ ይችላል።

ሰይጣን ትልቅ የቤተ ክርስቲያን ባላንጣ ሲሆን፥ በሰማይ የሚገኙትን ቅዱሳን በመክሰስና በምድር ያሉትንም በማጥቃት፥ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ይዋጋል። ይሁንና ክርስቶስ አሮጌውን እባብ ስላሸነፈ፥ ለሕዝቡ ድልን ያጐናጽፋል።

ከሳሹ ሁልጊዜም ሰዎችን እንደ መሣሪያ ተጠቅሞ ሥራውን የሚያከናውን ሲሆን፥ በዚህም ጊዜ በ«አውሬው» (ሐሰተኛ ክርስቶስ ወይም ሐሳዊ-መሢሕ) እና በሐሰተኛው ነቢይ ይጠቀማል። ሰይጣን አስመስሎ ለመሥራት የሚጣጣር ሲሆን፥ ሰዎችን በማታለል ከቁጥጥሩ ሥር ሊያደርጋቸው ይሻል። «አውሬው» የሕዝቦችን ቀውጢ ችግሮች ለማስወገድ የተስፋ ቃል የሚሰጥ የወደፊቱ የዓለም አምባገነን ሲሆን፥ ሐሰተኛው ነቢይ «የቅስቀሳው አገልጋይ» ነው። ለጊዜው፥ የሰይጣን ሥላሴ ከስኬታማ ውጤት የሚደርስ ቢመስልም፥ ከዚያ በኋላ ግን የእነርሱ የዓለም መንግሥትነት መፍረስ ሲጀምርና የዓለም ሕዝቦች ለአንድ የመጨረሻ ጦርነት ሲሰባሰቡ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ይገለጽና ጦርነቱ ያበቃል።

ለመሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ለብዙ መቶ ዓመታት ከክፉ ጋር ሲታገሉ የነበሩት በዚህ ዓይነቱ መልክ አልነበረምን? በጊዜው የነበረው ገዥ ቄሣር፥ ወይም ሒትለር፥ እስታሊን ወይም፥ መለኮታዊ መረዳትን በመካድ ሰብአዊነትን የሚያከር መሪ ቢሆን፥ ሰይጣን በኃይሉ

እንዳስታጠቀውና እንዳነቃቃው ግልጽ ነው። ገዥው ለሕዝቡ የሚያስፈልጋቸውንና የሚመኙትን ሁሉ ለማድረግ የተስፋ ቃል ይገባላቸዋል - ሆኖም ወደ ባርነት ይመራቸዋል! ብዙውን ጊዜ መርሐ-ግብሩን ለሕዝቡ ለማድረስና በግድም ባይሆን በማታለል እንዲታዘዙት ለማድረግ፥ በተባባሪው ይጠቀማል። በአመዛኙም የመገዛታቸው ጉዳይ ከሞላ-ጎደል የአምልኮት ያህል የሚቆጠር ነበር።

ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሕዝቡን በእነዚህ ገዢዎች ፍትሕ-አልባ የጭካኔ ተግባር እንዲሠቃዩ ቢፈቅድም፥ ዳሩ ግን በሰማዕትነት ታላቅ ድል እንዲቀዳጁ አስችሏቸዋል። እውነተኛ ድል-ነሺዎች እነርሱው ነበሩ! ከዚያም ነፃነትን አስገኝቶላቸዋል። ያም ሆኖ ግን ዐደቱ ራሱን እንዲደግም ለማድረግ ያህል እያንዳንዱ አምባገነን ከበፊቱ በከፋ ጭካኔ ያስተዳድራል። ይህም ሁኔታ ሐሳዊው መሢሑ በጊዜው ሲገለጽ እጅግ ወደ ላቀው ደረጃ ይደርሳል (2ኛ ተሰ. 2)።

ዘንዶው (ራእይ 12)

በዚህ ምዕራፍ የዮሐንስ ራእይ የሚጀምረው በሰማይ በሚታዩ ሁለት ድንቆች ነው (12፡1-6)። የመጀመሪያው ልጅ የምትወልደውን ሴት የሚያመለክት ነው። ይህ ልጅ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ ስለቀረበ (ቁ. 5ን ከራእይ 19፡15 እና መዝ. 2፡9 ጋር አወዳድር)፥ ይህቺ ተምሳሌታዊት ሴት እስራኤል እንጂ ሌላ ልትሆን አትችልም። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣው በእስራኤል በኩል ነበር (ሮሜ 1፡3፤ 9፡4-5)። በተጨማሪም፥ በራእይ 12፡1 የቀረበውን ገለጻ ከዘፍጥረት 37፡9-10 ጋር ስናወዳድር፥ አተረጓጐሙ ትክክል ይመስላል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ፥ እስራኤል ብዙውን ጊዜ ከሴት፥ በተለይም ምጥ ከያዛት ሴት ጋር ተወዳድራ ቀርባለች (ኢሳ. 54፡5፤ 66፡7፤ ኤር. 3፡6-10፤ ሚክ. 4፡10፤ 5፡2-3)። ከሃዲው የዓለም ዘይቤ ከጋለሞታ (17፡ ከቁጥር 1 ጀምሮ)፥ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ከንጽሕት ሙሽራ ጋር ተወዳድራለች (19 ከቁጥር 7 ጀምሮ)።

ልጁ ተወለደና ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ተነጠቀ (12፡5)። በዚህ ምዕራፍ የክርስቶስን መወለድና በድል ያሸበረቀ ዕርገቱን የተመለከትን ሲሆን፥ ዳሩ ግን ስለሞቱም ሆነ ሕይወቱ የተገለጸ ነገር የለም። በጥቅሱ

(12፡5) መካከል የሚገኘው ድርብ-ሠረዝ (፤) የሠላሳ ሦስት ዓመታትን ታሪክ ያመለክታል።

በሰማይ የታየው የመጀመሪያው አስደናቂ ምልክት ልጅ የወለደችው ሴት ስትሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ትልቁ ቀይ ዘንዶ ነው። ቁጥር 9 ግልጽ እንደሚያደርገው፥ ዘንዶው ሰይጣን ነው። ቀይ ቀለም ከሞት ጋር የተያያዘ ሲሆን (6፡4)፥ ሰይጣን ነፍሰ-ገዳይ ነው (ዮሐ. 8፡44)። ራሶች፥ ቀንዶችና ዘውዶች በራእይ 13፡1 እና በ 17፡3 በድጋሚ ይከሰታሉ። ራሶች ተራሮችን (17፡9)፥ ቀንዶች ደግሞ ነገሥታትን የሚወክሉ ሲሆን (17፡12)፥ የእነዚህን ምልክቶች ትርጉሞች ወደ በኋላ በዝርዝር እንመለከታለን።

ዘንዶው ከሰማይ በመጣሉ (12፡9)፥ የመላእክትን ሢሶ ይዞ ወረደ (ቁ. 7፥ 9)። እነዚህም መላእክት በቁጥር 4 ላይ «ከዋክብት» ተብለዋል (ዳን. 8፡10 ተመልከት)። ይህም ሰይጣን ከጭፍሮቹ ጋር በእግዚአብሔር ላይ ባመፀ ጊዜ፥ ከሰማይ ለመውደቁ ግልጽ ማጣቀሻ ነው (ኢሳ. 14፡12-15)። ይሁንና፥ በራእይ 12፡7-10 የተጠቀሰው መጣል ገና ወደፊት የሚፈጸም ነው።

ሕፃኑ እንደተወለደ፥ ወዲያው ሰይጣን ሊያጠፋው ጣረ። ይህ በ«ሴቲቱ» እና በሰይጣን መካከል የሚካሄደው ግጭት ሰው በኃጢአት ከመውደቁ አንሥቶ ባለማቋረጥ ከመቀጠሉም፥ (ዘፍጥ. 3፡15)፥ በብሉይ ኪዳን ታሪክ ሁሉ ሰይጣን የአዳኙን መወለድ ለማስቀረት እንደተጣጣረ እናያለን። እስራኤልን ወይም የመሢሑን የዘር ግንድ ለማጥፋት፥ ሁልጊዜም «ዘንዶው» ቆሞ በመጠባበቅ ላይ ነበር። የግብፁ ፈርዖን «ዘንዶ» ተብሎ የተጠራ ሲሆን (ሕዝ. 29፡3)፥ ናቡከደነፆርም እንዲሁ ተብሎ (ኤር. 51፡34) ተጠርቷል። በአንድ ወሳኝ ወቅት ላይ፥ ንጉሣዊ የዘር ሐረግ በአንድ ሕፃን ልጅ ተወስኖ ነበር! (2ኛ ነገሥት 11፡1-3)። ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ፥ ሰይጣን ያጠፋው ዘንድ ንጉሥ ሄሮድስን በመሣሪያነት ተጠቀመ (ማቴ. 2)። ሰይጣን ይሁዳን ጌታችንን አሳልፎ ይሰጠውና ይሰቀል ዘንድ በተጠቀመበት ጊዜ፥ የተሳካለት መስሎት ነበር። መስቀሉ ግን የሰይጣን ሽንፈት ነበር! «እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ (ሰይጣንን) . . . ድል ነሡት» (ራእይ 12፡11)።

ዛሬም ሳይቀር ሰይጣን ወደ ሰማይ ደርሶ የእግዚአብሔርን ሰዎች የመክሰስ ዕድል አለው፤ ይሁንና ከፍ ብሎ የነገሠውን አዳኝ ከዙፋኑ ላይ የማውረድ ዓቅም ግን አይኖረውም። ዘዴው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማሳደድና ከተሳካለትም መዋጥ ነው (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። ለአይሁዶች ልዩ ጥላቻ ስላለው፥ ከፈረዖንና ከሐማ ዘመን ጀምሮ (መጽሐፈ አስቴርን ተመልከት) እስከ ሒትለርና እስታሊን ድረስ ከፀረ-ሴማዊነት እንቅስቃሴ በስተጀርባ የነበረው ኃይል እርሱ ነው። በመጨረሻም፥ በመከራው አጋማሽ ላይ በዓለም ታይቶ የማያውቅ ፀረ-ሴማዊ ማዕበል ይነግሣል (12፡6)። ጌታ ግን በእነዚህ ሦስት ተኩል ዓመታት ሕዝቡን ይታደጋል (1,260 ቀናት፤ ራእይ 11፡2፤ 13፡5 ተመልከት)።

በማኅተም ታትመው ከተጠበቁት 144,000 ሰዎች ባሻገር፥ የሚያምኑ የአይሁድ ቅሪቶች በዚህ የመከራ ጊዜ ውስጥ ያልፋሉ። እግዚአብሔር በየት ስፍራ እንደሚጠብቃቸው ወይም ማን እንደሚንከባከባቸው የተገለጸ ነገር የለም። ማቴዎስ 24፡15-21 በመጨረሻው ዘመን ለሚኖሩ አይሁዳውያን አማኞች የተለየ ትርጉም ይኖረዋል። በተለይ በቁጥር 15 ውስጥ የሚገኘውን አሳብ ልብ በል።

እኔና አንተም ዛሬ በተመሳሳይ ግጭት ውስጥ እንኖራለን (ኤፌ. 6 ከቁጥር 10 ጀምሮ)። ሰይጣን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት በመጣጣር ላይ የሚገኝ ሲሆን፥ ድላችንም የሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ብቻ ነው።

በዚህ አጽናፍ-አቀፍ ትርዒት ውስጥ ቀጣዩ ትዕይንት በሰማይ የሚደረገው ጦርነት ነው (ራእይ 12፡7-12)። ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚገልጹልን፥ ሰይጣን ዛሬም እንኳ ወደ ሰማይ የመዝለቅ ዕድል አለው (ኢዮብ 1-2)። በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ በላይ የነበረ ሲሆን፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ወደ ምድር ተጣለ (ኢሳ 14፡12-15)። ደስ የሚያሰኝ ነገር ቢኖር፥ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በታማኝነት ክርስቶስን በማገልገል ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ስትመልስ፥ ሰይጣንም እንደዚሁ ተሸንፎ መጣሉ ነው - (ሉቃ. 10፡1-2፤ 17-20፤ ማቴ. 16፡18፤ 12፡29)።

ያለምንም ጥርጥር የክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ መሞት ለሰይጣን የላቀ ሽንፈት ነበር (ዮሐ. 12፡31-33)። አንድ ቀን ሰይጣን

ከሰማይ ይጣላል (ራእይ 12፡7-10)፤ በመጨረሻውም ወደ ሲዖል ይወርዳል (20፡10)።

ይህ የሰማያዊ አካላት ግጭት ምንድን ነው? ሚካኤል የእስራኤል ሕዝብ አጋዥ ከመሆኑም (ዳን. 10፡10-21፤ 12፡1፤ ይሁዳ ቁ. 9)፥ የእግዚአብሔርን መላእክት ወደ ድል የመራው እርሱ የመሆኑ እውነታ፥ በተለየ ሊጤን ይገባዋል። ሚካኤል ማለት «እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው?» ማለት ነው ይህም በተለይ ሰይጣን በያህዌ ላይ የሚሰነዝረውን የራስ-ወዳድነት ጥቃት ያሳያል - «በልዑልም እመሰላለሁ» (ኢሳ. 14፡14)። ሰይጣን በእስራኤል ላይ ያለው ጥላቻ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ አንድ የመጨረሻ ጥቃት እንዲፈጽም ቢገፋፋውም፥ ዳሩ ግን ሚካኤልና የሰማይ ሠራዊት ያሸንፉታል።

ይሁንና በዚህ ጦርነት ውስጥ የተካተተ ምናልባትም አንድ ሌላ ነገር ሊኖር ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ወደ ሰማይ ከተወሰደች በኋላ፥ አማኞች በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይቆሙና ሥራቸው ይመረመራል። በዚህም ፍርድ መሠረት፥ ሽልማት ይሰጣል (ሮሜ 14፡10-12፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡10-15፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡10-11)። በዚህ ክስተት ላይ ሰይጣን ተገኝቶ የቤተ ክርስቲያንን «እድፈትና የፊት መጨማደድ» ሁሉ እያመለከተ፥ ቅዱሳንን የሚከስ ይመስላል (ኤፌ. 5፡24-27)።

«ዲያብሎስ» ማለት «ከሳሽ» ማለት ሲሆን፥ «ሰይጣን» ደግሞ «ተቃዋሚ» ማለት ነው። ሰይጣን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እየቀረበ ቅዱሳንን በመክሰስ ሲዋጋ (ኢዮብ 1-2፤ ዘካ. 3)፥ ሰማያዊ ጠበቃ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ቤተ ክርስቲያንን በእግዚአብሔር ቅዱስ ዙፋን ፊት ይወክላል (1ኛ ዮሐ. 2፡1-2)። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ብሎ ስለሞተ፥ «በበጉ ደም» የሰይጣንን ክሶች ልናሸንፍ እንችላለን። ደኅንነታችን የተረጋገጠው በሥራችን ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በጎልጎታ ላይ ከተፈጸመው የእርሱ ሥራ የተነሣ ነው።

ቤተ ክርስቲያን «እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይደርስባት» በክብር ወደፊት ስትራመድ፥ ሰይጣን ምንኛ በቁጣ ይታወክ ይሆን! ከሳሹ ዘዴዎቹ ሁሉ እንዳልሠመሩለት ሲያውቅ፥ በቁጣ ተሞልቶ የሰማዩን ሰላም ለማናጋት መዛት ይጀምራል። ይህ ወደፊት የሚከሰተው ጦርነት ከቤተ ክርስቲያን ጋር የሚዛመደው እንዴት

ነው? ቅዱሳንን በሰማይ የሚከሰው ይኸው አባብ በምድር የሚገኙትንም ሕዝቦች ያታልላል (12፡9)፤ ከዘዴዎቹም መካከል አንዱ ስለ ቤተ ክርስቲያን የውሸት ዘገባ ማቅረብ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች አደገኞች፥ ተንኰለኞችና ብሎም አጥፊዎች እንደሆኑ በማስመሰል በሕዝቦች መሀል መርዘኛ ወሬ በመንዛት ያታልላል። የሕዝቦች መሪዎች በክርስቶስና በሕዝቡ ላይ ውጊያ ለመክፈት የሚሰባሰቡት በሰይጣን ተታለው ነው (መዝ. 2፤ የሐዋ 4፡23-30)። በየትኛውም ዘመን የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሰዎች የዓለምን ተቃውሞ እንደተለመደ ነገር አድርገው መጠባበቅ አለባቸው። ብሎም ግን ለኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ በመሆን ሁልጊዜም ጠላትን ለማሸነፍ ይችላሉ።

የፈሰሰው የክርስቶስ ደም በእግዚአብሔር ፊት በፍጹም ብቃት እንድንቆም ያስችለናል (1ኛ ዮሐ. 1፡5-2፡2)። ይሁንና ለእግዚአብሔር ቃል የሚኖረን ምስክርነትና ሕይወታችንን ለክርስቶስ ለመስጠት ያለን ፈቃደኛነት ሰይጣንን ያሸንፈዋል። ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ሊስተካከል አይችልም - ሁሉን የሚችል፥ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ፥ ሁሉንም የሚያውቅ አይደለም። ኃይሉ የተወሰነ ከመሆኑም፥ የእግዚአብሔር ሰዎች በደሙና በቃሉ ኃይል በሚተማመኑበት ጊዜ፥ ዘዴዎቹ ፋርሽ ይሆናሉ። ለጌታ የተሰጠን ከሆን፥ ሰይጣን የሚያደርገው ማንኛውም ነገር ከ«አምላካችን ማዳንና ኃይል፥ መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን» ሊያስቀረን አይችልም (12፡10)፤ ታላቁ የእግዚአብሔር ዓላማም ግቡን ይመታል።

ልምምዳቸው ምንም አስቸጋሪ ቢሆን፥ በየትኛውም ዘመን ወይም ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ አማኞች በዚህ ድል ሊደሰቱ ይችላሉ። ውጊያችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ከክፉ መንፈሳዊያን ኃይሎች ጋር ነው፤ እነዚህም በአዳኛችን ድል ተመተዋል (ኤፌ. 6 ከቁጥር 10 ጀምሮ፤ እንዲሁም 1፡15-23)።

ሰይጣን በሚጣልበት ጊዜ ሰማይ ደስ ይሰኛል፤ ዳሩ ግን የመከራው ሁለተኛው አጋማሽ በዓለም የከፋ ሥቃይ ስለሚያስከትል፥ ምድር «ዋይ» ትላለች። በራእይ 12፤12 ላይ የሚገኘው «ወዮ» በ8፡13 ላይ የተጠቀሱትን ሦስት «ወዮዎች» ያስታውሰናል። የመጀመሪያው «ወዮ» በ9፡1-12 የተጠቀሰ ሲሆን፥ ሁለተኛው በ9፡13-21 ተጠቅሷል። ሦስተኛው «ወዮ» በ11 ከቁጥር 14 ጀምሮ የተገለጸ ሲሆን፥ ዳሩ ግን

ይህም ምንባብ እግዚአብሔር ለምድር ያለውን ዕቅድ ወደ ፍጻሜ የሚያደርስበትን ክስተቶች አጠቃሎ ያቀርባል። ሰይጣንን ወደ ምድር በመጣል አስከፊ ቁጣውን በምድር ላይ እንዲያፈስ መፍቀዱ የዚህ የሦስተኛ «ወዮ» አካል ሳይሆን አይቀርም።

በመሆኑም ይህ ሰይጣን በምድር ላይ የሚያወርደው ቁጣ በቲያትሩ ውስጥ ሦስተኛው ትዕይንት መሆኑ ነው (12፡13-16)። ጊዜው አጭር እንደሆነና ዳግም ወደ ሰማይ የመመለስ ዕድል እንደማይኖረው በመረዳት፥ ተቃዋሚው ቁጣውን ሁሉ ወደ ምድር ማውረድ አለበት። ከእስራኤል (ከሴቲቱ) ይጀምርና የፀረ-ሴማዊነትን ማዕበል በዓለም ዙሪያ ያጧጡፋል። አይሁዶች የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች ስለሆኑና ደኅንነት ወደ ዓለም የመጣባቸው አማካዮች ስለሆኑ፥ ሰይጣን ሁልጊዜም አይሁዶችን ይጠላል። ሰይጣን፥ በተለይ መሢሑ የተስፋ ቃል የገባውን መንግሥት ለመመሥረት ወደ ምድር የሚመለስበት ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ፥ የአይሁድን ሕዝብ ለማውደም ታጥቆ ይነሣል። የአይሁድ ቅሬቶች (አማኞች) ጌታን ለመቀበልና ለመንግሥቱ መሠረት ለመጣል መዘጋጀት አለባቸው (ራእይ 1፡7፤ ዘካ. 12፡9-14፡21)።

እግዚአብሔር ለአይሁድ ቅሬቶቹ ጥበቃና እንክብካቤ የሚደረግበትን ስፍራ ያዘጋጃል። የቅሬቶቹ ከሰይጣን ማምለጥ፥ በበራሪ ንስር ተምሳሌት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ቀደም ሲል ከእስራኤል ጋር በተያያዘ መልኩ ተደጋግሞ መጠቀሱ፥ ደስ የሚያሰኝ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ «በንስር ክንፍ» ከማውጣቱም (ዘጸ. 19፡4)፥ ንስር ልጅዋን እንደምትንከባከብ በምድረ በዳ ተንከባከባቸው (ዘጸ. 32፡11-12)። ከባቢሎን ምርኮ መመለሳቸው፥ እንደ ንስር በክንፍ የመብረር ያህል ነበር (ኢሳ. 40፡31)።

ቅሬቶቹ በመጨረሻው የመከራ አጋማሽ መጠለያ እንደሚያገኙ አስታውስ። ይሁንና ይህ የመጠለያ ስፍራ የት እንደሚሆን አናውቅም፤ ማወቃችንም ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም። ዳሩ ግን ትምህርቱ ለሁላችንም ግልጽ ነው - እግዚአብሔር በምድር ላይ ዓላማዎቹን ለመፈጸም ሊጠቀምባቸው የሚፈልጋቸውን ሰዎች ይንከባከባቸዋል። እርግጥ ነው፥ አንዳንዶች ሕይወታቸውን ሲሰጡ (ራእይ 12፡11)፥ ሌሎች ግን ይተርፋሉ (ለዚህ መመሪያ እውነትነት የሐዋርያት ሥራ 12ን በምሳሌነት ተመልከት)።

«ወንዝ የሚያህል ውኃ» የሚለው ሐረግ በዚህ ስፍራ ባይብራራም፥ ዳሩ ግን በመዝሙር (124) ውስጥ የዚህ ተመሳሳይ አሳብ ይገኛል። (በዚሁ በመዝሙር (124) በቁጥር 7 «እንደ ወፍ . . . አመለጠች» የሚለውን ልብ ብለህ ተመልከት።) ይህ «የወንዝ ውኃ» አንድም የጥላቻን ገንፍሎ መውጣትና የፀረ-ሴማዊን እንቅስቃሴ መጠናከር ሲያመለክት፥ በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤልን የሚወሩና ቅሪቶቹን ለመርታት የሚጥሩትን ሠራዊት ያሳያል። ትርጉሙም እንደዚህ ከሆነ፥ የመሬት መከፈት እግዚአብሔር ወራሪዎቹን ለማጥፋት የሚልከው ርዕደ-ምድር ይሆናል። ሰይጣን ለመግደል የሚፈልጋቸው ሰዎች በአስተማማኝ ሁኔታ እንደተጠበቁ ሲረዳ፥ ወደ ተሸሸገው የደኅንነት ስፍራ ወዳልተወሰዱ ሰዎች ይመለሳል። ጦርነት ይከፍትና ለጊዜውም ቢሆን ድልን እንዲቀዳጅ እግዚአብሔር ይፈቅዳል (13፥7)፤ ይሁንና የቀደመው እባብ በመጨረሻ ድል ይሆናል።

ከባሕር የወጣ አውሬ (ራእይ 13፥1-10)

በአንዳንድ ጥቅሶች ላይ «እንዲሁም እርሱ [ሰይጣን] በባሕር አሸዋ ላይ ቆመ» የሚል እናነባለን። ባሕር አሕዛብን የሚያመለክት ሲሆን (17፥15)፥ ከመካከላቸውም ሰይጣን «ሐሳዊ-መሢሕ» የምንለውን «የላቀ መሪ» ያስነሣል። እስካሁን ድረስ ሐሳዊ-መሢሕ አሥሩን የአውሮፓ መንግሥታት በመምራት ላይ የሚገኝ ሲሆን፥ አሁን ግን የዓለም አምባገነን መሪ ለመሆን በሚያስችለው የሥልጣን ወንበር ላይ በሰይጣን ረዳትነት ይቆናጠጣል።

ሐሳዊ-መሢሕ ሰላምን በማስፈን ሥራውን እንደሚጀምርና (6፥2) ለሰባት ዓመታት አይሁዶችን ለመጠበቅ በሚገባው ቃል ኪዳን፥ የዓረብ-እስራኤልን ችግር «እንደሚያቃልል» ቀደም ሲል መግለጻችን ይታወሳል (ዳን. 9፥27)። ይህም ጥበቃ፥ ሕዝቡ ዳግም ቤተ መቅደሱን እንዲገነባና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን እንዲያዋቅር ቢያስችልም (11፥1፤ ዳን. 9፥27)፥ ዳሩ ግን በሰባት ዓመቱ አጋማሽ ላይ (አሁን ከራእይ 10-14 በምናጠናው የጊዜ ገደብ) ቃል ኪዳኑን በማፍረስና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶቹን በማገድ፥ ራሱን አምላክ አድርጎ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያቆማል (ዳን. 9፥27፤ 2ኛ ተሰ. 2፥1-12)።

የ«አውሬው» ተምሳሌታዊ ገለጻ ስለመሠረቱና ስለባሕርዩ አንዳንድ ነገሮችን እንድንግር ያስችለናል። ሐሳዊውን መሢሕ እግዚአብሔር በመለኮታዊ አምሳል እንደተፈጠረ ሰው አያየውም - በሰይጣን አገዛዝ ሥር እንደሚገኝ የጱር አውሬ እንጂ! ሰው ቢሆንም (13፡18)፥ ከጥልቁ ስለሚወጣ (11፡7፤ 17፡8)፥ ኃይሉን የታጠቀው ከሲኦል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጸ አምላክ እንደሆነ ሁሉ፥ «አውሬው»ም የሰውን ሥጋ የለበሰ ሰይጣን ይሆናል (ዮሐ. 13፡2፥ 27 ተመልከት)።

ሰባቱ ራሶች ሰባት ተራሮችን ይወክላሉ (17፡9)፤ ሮም በሰባት ተራሮች ላይ የተመሠረተች ከተማ በመሆኗ፥ ይህ ለዚያች ኃያል ከተማ የተሰጠ ሽፍን ማጣቀሻ መሆን አለበት (17፡18)። በተለይም ይህ ማጣቀሻ ለዮሐንስ ዘመን በቅርብ የተዛመደ ማብራሪያ ይሆናል!

አሥሩ ቀንዶች አሥር መንግሥታትን ያመለክታሉ (ዳን. 7፡24፤ ራእይ 17፡12)። «አውሬው» የዓለም አምባገነን ከመሆኑ በፊት፥ የታደሰው የሮም መንግሥት ማለትም «የተባበሩት የአውሮፓ መንግሥታት» መሪ ይሆናል። ሕዝቦች ወደ በኋላ የሚያስከትለውን ኃዘንና ውድመት ሳይገነዘቡ፥ ለጊዜው በሚያስገኝላቸው «ሰላም» ማመስገናቸውና አድናቆታቸውን መግለጻቸው አይጠረጠርም።

በራእይ 13፡2 ላይ የተጠቀሱት ሦስት አራዊት፥ ዳንኤል በሕልሙ ያያቸውን አራት አራዊት - አንበሳ (ባቢሎን)፥ ድብ (ሜዶንና ፋርስ)፥ ነብር (ግሪክ) እና «አስፈሪ አውሬ» (ሐሳዊ - መሢሕ) ያስታውሱናል (ዳን. 7)። ዮሐንስ እነዚህን አራዊት ወይም መንግሥታት ወደ ኋላ ዞር ብሎ ስለሚመለከት፥ ቅደም-ተከተሉ የተገላቢጦሽ ሆነ - ዳንኤል ግን ወደፊት ይመለከት ነበር። የመጨረሻዎቹ የዓለም መንግሥታት መሠረታቸውን የሚያገኙት ከቀድሞዎቹ መንግሥታት እንደመሆኑ፥ ክፋታቸውንና ኃይላቸውን በአንድ ያስተባብራሉ። በእነዚህም አራዊት ጭካኔ ላይ የሰይጣን የራሱ ኃይል፥ ዙፋንና ሥልጣን ይታከልበታል!

ሰይጣን ታላቅ «ቁንጮው» የሆነውን ሐሳዊ-መሢሕ ወደ ዓለም ካመጣ በኋላ ቀጣዩ ተግባር ምን ይሆን?

በመጀመሪያ፥ አድናቆት ይኖራል (13፡3) - የተሸበረው ዓለም በሐሳዊው - መሢሕ ኃይልና በቅጽበት ወደ ዓለም-አቀፍ ዝናና ሥልጣን በመሸጋገሩ፥ መደነቁ አያጠራጥርም። በተጨማሪም፥ የሰው ልጅ

በ«ቁስሉ» መፈወስም ይደነቃል። ይህ ቁስል ምንድንነው? ዮሐንስ ይህንን «ቁስል» ባያብራራውም፥ ምናልባት ወደ በኋላ (17፡9-13) የጻፈው ነገር ተምሳሌትነቱን ለመተርጐም ያስችለን ይሆናል። ዮሐንስ በሰይፍ መቁሰሉን ጨምሮ ሦስት ጊዜ ደጋግሞ ስለጠቀሰው (ቁ. 3፥ 12፥ 14)፥ «ቁስሉ» አስፈላጊ መሆን አለበት።

ሰባቱ ራሶች ሰባት ተራሮችን ያመለክታሉ፤ ይሁንና ሰባት ነገሥታትን ወይም መንግሥታትንም ያመለክታሉ (17፡10)። ሐሳዊ-መሢሕ ወይም አውሬው ከእነዚህ ሰባት ነገሥታት አንዱ ሲሆን (17፡11)፥ ዳሩ ግን ስምንተኛውም ነው። ያም ሆኖ ሁለት ጊዜ እንደሚገዛ ተገልጿል - ግን እንዴት? «አውሬው» የአሥሩን መንግሥታት ፌዴሬሽን የሚመሠርት አውሮፓዊ መሪ በመሆን (17፡12) በሂደት ይገለጽና ኋላ ላይ ግን ይገደላል የሚል አሳብ አለ። ራእይ 11፡7 እና 17፡8 «አውሬው» ከጥልቁ ጉድጓድ እንደሚወጣ ይገልጻሉ። ታዲያ ሰይጣን (በእግዚአብሔር ፈቃድ) ሰውን ከሞት ሊያስነሣ ይችል ይሆን? ሰይጣን ለሞተ ጣዖት ሕይወት የመስጠት ኃይል ካለው (13፡15)፥ ለሞተ አካልስ ሕይወትን መስጠት ይሳነው ይሆን?

«አውሬው» ከሰባቱ ነገሥታት አንጻር አንዱ ሆኖ ከገዛ፥ ከሞተና ዳግም ከተነሣ፥ እንደ ስምንተኛ ንጉሥ ሆኖም ይገዛል ማለት ነው። በሌላ በኩል፥ ምስሉ ግለሰቦችን ሳይሆን መንግሥታትን የሚወክል ከሆነ፥ በዓለም ዕይታ ውስጥ ቀደም ሲል «ሞቶ የነበረ መንግሥት» ዳግመኛ ይከሰታል ማለት ነው። ይሁንና አንድ መንግሥት እንዴት በሰይፍ ሊሰየፍ እንደሚችል ለመረዳት ያዳግታል። ስለዚህ ይህንን ትንቢት ከግለሰቦች ጋር ማዛመዱ ይበልጥ ተስማሚ ይመስለኛል።

የአውሬው ሁኔታ ግን መደነቅን ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን አምልኮንም ያስከትላል። (13፡4)። አምልኮን ምንጊዜም ቢሆን ሰይጣን ሲቋምጥለት የኖረው ነገር ሲሆን (ማቴ. 4፡8-10)፥ በ«አውሬው» አማካኝነት ያገኘዋል። በዚህ ምዕራፍ ዘግየት ብሎ የተጠቀሰው ሁለተኛው «አውሬ» የሐሳዊ-መሢሑን ሃይማኖት ዓለም አቀፋዊ ሃይማኖት በማድረግ ያደራጀዋል - ያስፋፋዋልም።

ከዚህም በተጨማሪ የመደለያ ቃላት ይኖራሉ (13:5-6) - ሁሉም አምባገነን መሪዎች ከሥልጣን ለመቆናጠጥ የበቁት ሰዎችን በንግግራቸው በመደለል ነው ለማለት ይቻላል።

አዶልፍ ሒትለር ወደ ሥልጣን ኮርቻ በሚወጣበት ጊዜ፥ እጅግ በርካታ ሕዝቦችን እንዴት በንግግሩ እንደማረከና እንዳሳመናቸው አንዳንዶቹን የምናስታውሰው ነው። ሰይጣን «አውሬውን» ታላቅና እንደበተ-ርቱዕ ተናጋሪ አድርጐ የሚያስታጥቀው ሲሆን፥ በንግግሮቹም እግዚአብሔርን፥ ስሙን፥ ማደሪያውን (ሰማይን)፥ ብሎም በሰማይ የሚኖሩትን ቅዱሳን ይሳደባል። ሰይጣን በቅርቡ ከሰማይ ወደ ምድር ስለሚጣል፥ ይህ ስድብ ወደፊት እንደሚከሰት ይጠበቃል።

ሰይጣን እግዚአብሔር ፈቃድ ካልሰጠው በቀር ምንም ሊያደርግ ስለማይችል (ኢዮብ 1-2፤ ሉቃ. 22:31-32 ተመልከት)፥ «የአውሬው» ሥልጣን የውክልና እንጂ የራሱ የሆነ ነገር አይደለም። ሥልጣኑም ለሦስት ዓመት ተኩል፥ ማለትም ለመጨረሻው የመከራ አጋማሽ ጊዜ ያህል በእጁ ይቆያል።

በምሽት ራእዩ፥ ዳንኤል «አውሬውን» አራተኛውና የመጨረሻው መንግሥት ሆኖ ያየዋል (ዳን. 7:19-28)። እንደ ዮሐንስ ራእይ ሁሉ፥ በዚያም ስፍራ «አውሬው» ሥልጣኑን ለመጨበጥ ከነገሥታቱ ሦስቱን ማሸነፍ እንዳለበት ከሚያመለክት መገለጥ በተጨማሪ፥ የአሥር ቀንዶችም ተመሳሳይ አምሳል ተጠቅሶ ይገኛል። ዳንኤል «የአውሬን» የስድብ ቃላትም ሰምቷል (7:25)።

በመጨረሻም፥ ጦርነት ይኖራል (ራእይ 13:7-10) እግዚአብሔር ሐሳዊ-መሢሕ በሕዝቡ ላይ ጦርነት እንዲከፍትና («የልዑልንም ቅዱሳን ይሰብራል» ዳን. 7:25) አንዳንዶቹንም ድል እንዲነሣቸው ይፈቅድለታል። ዮሐንስ አንዳንዶቹ ቅዱሳን በምርኮ እንደሚወሰዱና አንዳንዶቹም በሰማዕትነት እንደሚያልፉ ተንብዮአል። ይሁንና ከእምነታቸው የተነሣ፥ ትዕግሥት ወይም ጽናት ስለሚኖራቸው (ዕብ. 6:12፤ ራእይ 1:9 ተመልከት)፥ ከስደቱና ከሞቱ ባሻገር ጌታን አይክዱም።

በዚያን ጊዜ የዓለም ሕዝብ በሁለት ምድብ ይከፈላል - የዳኑና ስማቸውም በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈላቸው ሰዎች

«ለአውሬው» አይገዙም። ከደኅንነት ርቀው የጠፉት የምድር ነዋሪዎች ግን «አውሬውን» በማምለክ ፈቃዱን ይፈጽማሉ። ይህንን እውነት ራእይ 13፡9 በየትኛውም ዘመን ከሚኖር ከ«ማንኛውም» ሰው ጋር እንደሚያዛምደው አስተውል። በዮሐንስ ዘመን፥ ማንኛውም ሰው የ«ቄሣርን ጌትነት» መቀበል ስለነበረበት፥ ይህ ትርጉም የሚሰጥ ነበር። እንደዚሁም፥ በማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ዘመን፥ እውነተኛ አማኞች ምንም ቢመጣ ለክርስቶስ ያላቸውን አቋም ማጽናት ያስፈልጋቸዋል።

እንደዚሁም «አውሬው» ክርስቶስን መስሎ ለመቅረብ የሚጥር ሐሳዊ-መሢሕ መሆኑን ልብ በል። ዓለም ክርስቶስን ሳይሆን ፀረ-ክርስቶስን (ዮሐ. 5፡43)፥ እውነትን ሳይሆን ውሸትን ትቀበላለች (2ኛ ተሰ. 2፡8-12)። ኢየሱስ መልካም የደኅንነት ቃላት ሲናገር፥ ሰዎች ለመስማት አልፈለጉም ነበር፤ ወደፊት ግን «የአውሬውን» የስድብ ቃላት እንደ ጥዑም ዝማሬ ያህል ያዳምጣሉ። ዓለም ክርስቶስን አታመልከውም - ዳሩ ግን ለፀረ-ክርስቶስ ወድቀው ይሰግዳሉ።

በራእይ 17 ውስጥ፥ የከሃዲዋ ዓለም ዋና ቤተ ክርስቲያን ተምሳሌት በሆነችው «ጋለሞታ» አማካኝነት «አውሬው» ወደ ሥልጣን ሲሸጋገር እንመለከታለን። ይህም በአንድ የእምነት ክፍል ላይ ወይም በአንድ እምነት ዘርፍ ላይ ያተኰረ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በመላው ዓለም የእግዚአብሔርን ልጅና የእግዚአብሔርን እውነት የማግለል ዘይቤ የሚያመለክት ነው። ይህም ሆኖ፥ «አውሬው» ዓለም-አቀፋዊ የሥልጣን ወንበር ላይ ሲቀመጥ፥ «ጋለሞታዩቱን» ዳግም ስለማይፈልጋት ወዲያውኑ ያጠፋትና የራሱን ሰይጣናዊ ሃይማኖት ይመሠርታል።

ከምድር የወጣው አውሬ (ራእይ 13፡11-18)

በራእይ 16፡13፤ 19፡20፤ እና 20፡10 ላይ ከምድር የወጣው አውሬ «ሐሰተኛው ነቢይ» በመባል ተጠርቷል። ዘንዶው ወይም ሰይጣን አብን መስሎ የሚቀርብ ሲሆን («በልዑልም እመስላለሁ»)፥ «አውሬው» ሐሰተኛው ክርስቶስን፥ ሐሰተኛው ነቢይ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን መስሎ ለመቅረብ ይጥራል። ይህም ሰይጣናዊውን ሥላሴ የተሟላ ያደርገዋል።

ከመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች አንዱ ክርስቶስን ማስከበርና ሰዎች እርሱን እንዲያምኑና እንዲያመልኩ መምራት ነው (ዮሐ. 16፡7-15)።

ሐሰተኛው ነቢይ ወደ ሐሳዊ-መሢሑና ወደ ምስሉ በማመልከት፥ ሰዎች በ«አውሬው» አማካኝነት ሰይጣንን እንዲያመልኩ ያደርጋል።

የቀንዶች ምስል (ራእይ 13፡11) ሐሰተኛው ነቢይ ሥልጣን እንዳለው ያመለክታል፤ ይሁንና የዘውድ አለመኖር ሥልጣኑ ፖለቲካዊ እንዳልሆነ ያመለክታል። ጌታችን ሐሰተኛ ነቢያት እንደሚነሡ በመግለጽ ያስጠነቀቀ ሲሆን (ማቴ. 24፡11፥24)፥ ይኼኛው ከሁሉም የላቀ ይሆናል። የበግ ባሕርይ ይኖረውና የዘንዶን ድምፅ ያሰማል። ምንኛ አታላይ ይሆን ይሆን! ዓለምም ሆ! ብላ ትከተለዋለች፥ በሚናገረው ታምንበታለች!

ጌታችን በምድር ላይ ያገለግል በነበረበት ጊዜ፥ በአብዛኛው የአይሁድ መሪዎች በእርግጥ መሢሐቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሆነ ምልክት እንዲያሳያቸው ይጠይቁት ነበር - ኢየሱስ ግን ለጥያቄያቸው አዎንታዊ ምላሽ አልሰጠም። ሐሰተኛው ነቢይ ግን ዓለምን ወደ ሰይጣናዊ አምልኮ የሚመሩ አታላይ ምልክቶችን ያሳያል (2ኛ ተሰ. 2፡9)። ከሁሉም የሚልቀው ምልክቱ በዳንኤል (ዳን. 9፡27፤ 11፡36) ኢየሱስ (ማቴ. 24፡15) እና ጳውሎስ (2ኛ ተሰ. 2፡4) የተጠቀሰው «የጥፋት ርኩሰት» ይሆናል።

«የጥፋት ርኩሰት» ምንድን ነው? በኢየሩሳሌም በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚቆም «የአውሬው» ምስል ነው። ጣዖት በራሱ አስጸያፊ ነገር ሲሆን፥ ዳሩ ግን በቤተ መቅደሱ ውስጥ ማቆሙ ከስድቦች ሁሉ የላቀ ነው። ሰይጣን በሰማይ አምልኮ እንዲደረግለት ለማዘዝ ስለማይችል፥ ከሰማይ ቀጥሎ ሁለተኛውን የክብር ደረጃ ወደ ያዘችው ስፍራ ያመራል - በቅድስቲቱ ከተማ ወደሚገኝ የአይሁድ ቤተ መቅደስ (ዳን. 8፡9-14)።

በሰይጣን ኃይልን የለበሰው ሐሰተኛው ነቢይ «የውሸት ድንቆቹን» የሚሠራ ሲሆን፥ በሁለቱ ምስክሮች የተፈጸሙትን አንዳንድ ምልክቶች ሳይቀር እያስመሰለ ያራባል (ራእይ 13፡13፤ 11፡5 ተመልከት)። እስከዚህ ጊዜ ድረስ፥ ሁለቱ ምስክሮች በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉ ሲሆን፥ ዳሩ ግን «አውሬው» ያርዳቸውና ቤተ መቅደሱን ይወስዳል። እግዚአብሔር ሁለቱን ምስክሮች ከሙታን አስነሥቶ ወደ ሰማይ በሚወስድበት ጊዜ፥ ሐሰተኛው ነቢይ ለ«አውሬው» ምስል

ሕይወት በመስጠት ተግዳሮቱን ይወጣዋል። በዚህም ምስሉ መቆም ብቻ ሳይሆን መናገርም ይችላል!

በሃይማኖታዊ የማታለል ተግባር ሰዎችን ለመቆጣጠር በመቻሉ ሳይረካ፥ ሐሰተኛው ነቢይ ጠንካራ የምጣኔ ሀብት ተቋሞችንም ይመሠርታል። (ከክርስቲያኖች በቀር - 20፡4) ሰዎች ሁሉ ለመሸጥ ወይም ለመግዛት ልዩውን ምልክት ይቀበላሉ፤ ይሁንና ያንን ምልክት ለመቀበል የሚቻለው ለ«አውሬው» በመገዛትና በማምለክ ብቻ ነው። በእውነቱ ይህ በሮም ግዛት ውስጥ ለነበረው የቄሣር አምልኮ ጠንካራ ማጣቀሻ ሲሆን፥ ዳሩ ግን ይኸው ተመሳሳይ ደንብ በታሪክ እንደታየው ሌሎችም የፖለቲካ መሪዎች የተጠቀሙበት ነው።

ይህ ልዩ ምልክት የ«አውሬው» ስም ወይም መለያ የሆነው ምሥጢራዊው ቁጥር 666 ነው። በጥንቱ ዓለም፥ ማለትም በግሪክም ሆነ በዕብራይስጥ በቁጥሮች ምትክ የፊደል ሆሄያት የሚያገለግሉ ሲሆን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎችም የዚህን ስምና ቁጥር ምሥጢር ለመግለጽ ሲጣጣሩ ኖረዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ጥብቅ ጥናት እስከተካሄደ፥ ተስማሚ የሚሆነው ስም የማግኘቱ ጉዳይ ከሞላ-ጐደል የማይከብድ ነው!

ሰው በስድስተኛ ቀን ስለተፈጠረ፥ ስድስት የሰው ቁጥር ነው። ፍጥረት የተፈጠረው ለሰው ሲሆን፥ በተመሳሳይ መልኩ የስድስት ቁጥር ማኅተም አርፎበታል - በቀን ሃያ አራት ሰዓታት (4X6)፥ በዓመት አሥራ ሁለት ወራት (2X6) ይገኛሉ። ሰባት የፍጹምነትና የሙላት ቁጥር ሲሆን፥ ስድስት ግን ፍጹምነት የጐደለው «የሰው ቁጥር» ነው።

ከማናቸውም የሰው ግምታዊ የአስተሳሰብ ቀመሮች ባሻገር፥ የዚህን ስምና ቁጥር ትርጉም የሚያውቅ እንደሌለ ለመናዘዝ እንገደዳለን። በዚያን ጊዜ በምድር ላይ የሚኖሩ አማኞች ግን ትርጉሙን በግልጽ እንደሚረዱት አያጠራጥርም። «ሰይጣናዊው ሥላሴ» 7 ቁጥርን ሊጠቀም አይችልም - በዚያው በ666 ይርጋ እንጂ!

የተረጋገጠው እውነት ይህን ያህል ነው - በቅርብ ዓመታት ውስጥ፥ ቁጥሮችን ለመታወቂያነት የመጠቀሙ ዓለም-አቀፋዊ እንቅስቃሴ እያደገ ሲሄድ ተመልክተናል። በዩናይትድ ስቴትስ፥ የአንድ ሰው ማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር አይቀሬ ነው። እንዲያውም፥ ለኮምፒውተር ቁጥሮች ከስሞች የበለጠ ጠቀሜታ አላቸው! ምናልባት ይኼ «አውሬው»

በሚገዛበት ጊዜ በምድር ላይ ስለሚሆነው ነገር የተሰጠ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ይሆናል።

እስከ አሁን በተከታታልነው ጥናት፥ በመከራው አጋማሽ ዘመን ላይ ደርሰናል። ዳሩ ግን ለጌታ መመለስ ገና አልተዘጋጀንም። ዮሐንስ ታላቁ ትርዒት እንዴት እንደሚፈጸም ከመግለጹ በፊት፥ ቀጥለው የሚመጡትን ታላላቅ ክስተቶች ለማመልከት ቆም ይላል - እኛም ይህንኑ እንመለከታለን።

ፀረ-ክርስቲያናዊ ዘይቤ በዓለማችን ውስጥ ጎልቶ ስለሚታይ፥ እውነተኛ አማኞች የዓለም አካል መሆን የለባቸውም (1ኛ ዮሐ. 2፡15-17)። በዚህ የመጨረሻ ዘመን ለጌታችን ታማኞች ሆነን እንድንገኝ (2ኛ ጢሞ. 3)፥ ሐሰተኛ አምልኮን ማስወገድ አለብን (1ኛ ቆሮ. 10፡14-22)።

- 9 -

የድል ድምፆች

ራእይ 14-16

ከራእይ 14-16 ውስጥ ያለውን ክፍል ወደ ጥምረት ከሚያመጡት ዓበይት አሳቦች አንዱ አሥራ አንድ ጊዜ የተጠቀሰው «ድምፅ» የሚለው ቃል ነው። በመጽሐፉ ውስጥ በተዘገቡት ክስተቶች፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ወይም ከደኅንነት ርቆ ለጠፋው ዓለም ይናገራል፤ ወይም ፍጥረታቱ ጌታን በማመስገን ወይም ዓለምን በማስጠንቀቅ ይናገራሉ። ዓለም ወደመከራው የመጨረሻው አጋማሽ ስትሻገር፥ ሰማይ ዝም አይልም።

የ144, 000ዎቹ ድምፅ (ራእይ 14፡1-5)

ይህ የአይሁድ ሰዎች የሚገኙበት ልዩ ቡድን ሰባተኛው ማኅተም ከመከፈቱ በፊት በእግዚአብሔር የታተመ ሲሆን (ራእይ 7)፥ አሁን ግን በጽዮን ተራራ ላይ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ይታያሉ። ይህንን ሥዕል በራእይ 13 ላይ በግንባሮቻቸው ምልክት ከተደረገላቸው የ«አውሬው» ተከታዮች ጋር አነጻጽር (ቁ. 16)። ዓለም የቱንም ያህል በኃጢአት የተበላሸ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ታማኝ ሰዎች አሉት።

144,000ዎቹ በጽዮን ተራራ ላይ ከክርስቶስ ጋር ቆመዋል፤ ግን የትኛው ጽዮን? ሰማያዊው (ዕብ. 12፡22-24)፥ ወይስ ምድራዊው? በግሌ እንደማምነው ይህ ሰማያዊ የጽዮን ተራራ ሲሆን፥ ትዕይንቱም የክርስቶስን ዘውድ መጫንና ወደ ምድር በሚመለስበት ጊዜ መንግሥት የመመሥረቱን እውነት ያጠናክረዋል (ዘካ. 14 ከቁጥር 4 ጀምሮ)። ዛሬ ክርስቶስ በሰማያዊው ጽዮን ላይ በዙፋኑ የተቀመጠ ሲሆን (መዝ. 2፡6)፥ እኛም ከእርሱ ጋር ተቀምጠናል (ኤፌ. 2፡6)። በራእይ 14 ውስጥ የሚገኘው ትዕይንት እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደሚጠነቀቅና በመጨረሻም ወደ ክብር ስፍራ እንደሚወስዳቸው የሚያረጋግጥ ነው።

144,000ዎቹ ከክርስቶስ ጋር መቆም ብቻ ሳይሆን ይዘምሩም ነበር (ራእይ 14፡2-3)። በመከራው ጊዜ ከነበራቸው ልዩ ልምምድ የተነሣ፥ ሌሎች የማይሳተፉበትን መዝሙር የመዘመር ዕድል ነበራቸው [መዝ. (33)፡3፤ (40)፡3፤ (96)፡1፤ (98)፡1፤ (144)፡9፤ (149)፡1

ተመልከት]። እነርሱም በሰማያዊ በገናዎችና ሌሎች ሰማያዊ ድምፆች በመታገዝ ይዘምራሉ። አንድ ቀን ኃዘናችን ወደ ዝማሬ እንደሚለወጥ ማወቁ ምንኛ የሚያጽናና ነው!

በተጨማሪም ዮሐንስ መለየታቸውን ገልጾአል (ራእይ 14፡4-5)። 144,000ዎቹ ከምድር ስለተዋጁ፥ ምድራውያን አልነበሩም። የሰማይ ዜጎች እንጂ፥ የምድር ላይ ነዋሪዎች አልነበሩም። አማኞች ዛሬ የዚህ የተለየ ቡድን አካላት ባይሆኑም፥ ዳሩ ግን እንደእነርሱ ከምድር በመዋጀታቸው የዚህም ዓለም አካላት አይደሉም (ዮሐ. 17፡14-19፤ ፊልጵ. 3፡17-21)።

«በሴቶች ያልረከሱ» የሚለው ሐረግ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም የወሲብ ግንኙነት ክፉ እንደሆነ አያመለክትም - ክፉም አይደለም (ዕብ. 13፡4)። ይህ የተጠቀሰው እነዚህ 144,000 የአይሁድ ሰዎች ያላገቡ መሆናቸውን ለማመልከት ያህል ብቻ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ሴሰኝነትና ዝሙት ጣዖትን የማምለክ መግለጫዎች ናቸው (ዘጸ. 34፡15፤ ያዕ. 4፡4)። አብዛኛው ዓለም ለ«አውሬው» ምስል ሲሰግድ፥ 144,000ዎቹ ግን ለእውነተኛው አምላክ ታማኞች ነበሩ። ሌሎች የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ሲዋሹ፥ 144,000ዎቹ፥ ያለነውርና ያለነቀፋ ነበሩ።

«በኩራት» የሚለው «ከሁሉም የላቁ ምርጦች» ማለት ሲሆን፥ ዳሩ ግን የተጠበቀውንም መከር የሚያመለክት አሳብ ያዘለ ነው። በበኩራት በዓል ወቅት፥ ጠቅላላው መከር የጌታ እንደሆነ በምልክትነት ለማሳየት ካህኑ ነዶውን በእግዚአብሔር ፊት ይወዘውዘዋል (ዘሌ. 23፡9-14)። 144,000ዎቹ ገና የሚመጣው መከር በኩራት ሊሆኑ ይችላሉ፤ ምናልባትም ወደፊት የሚመጣው መንግሥት ማዕከላት ይሆናሉ። ይሁንና፥ እንዲህ ላለው ሰማያዊ ቡድን ምድራዊ መንግሥት መመሥረቱ አጻጋች ይመስላል።

የመላእክት ድምፆች (ራእይ 14፡6-20)

በዚህ ትዕይንት ቢያንስ ስድስት የተለያዩ መላእክት ተካተዋል፤ እያንዳንዳቸውም የሚያውጁአቸው የተለዩ መልእክቶች ነበሯቸው።

«የፍርዱ ሰዓት ደርሶአል!» (14፡6-7) በአሁኑ ጊዜ መላእክት ወንጌሉን የመስበክ ዕድል የላቸውም። የወንጌሉ አደራ የተሰጠው ለእግዚአብሔር ሰዎች ነው። ሰዎች «አውሬው»ን በመፍራት አክብሮትን

በሚሰጡበት በዚህ ወቅት፥ ይህ ሰማያዊ መልእክተኛ እግዚአብሔርን ብቻ እንዲፈሩትና እንዲያከብሩት ያስጠነቅቃቸዋል። ይህም እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደሆነና አምልኮም የሚገባው ለእርሱ ብቻ እንደሆነ የሚያሳስብ ነው። ይህ እኛ የምናውቀው ዓይነት የወንጌል መልእክት ሳይሆን (1ኛ ቆሮ. 15፡1-4)፥ ዳሩ ግን የሥነ-መለኮት ምሁራን «ተፈጥሮአዊ ሥነ-መለኮት» የሚሉትንና በሮሜ 1 ከቁጥር 18 ጀምሮ የተጠቀሰውን አሳብ የሚያስታውሰን ነው።

ፍጥረት ሁሉ ለእግዚአብሔር ህልውና፥ ለኃይሉና ጥበቡ ምስክርነቱን ይሰጣል። ይህም ሆኖ፥ «አውሬው» ሰዎችን፥ በዓለም ላይ ኃላፊነት እንዳለውና ፍጻሜአቸውም በእጆቹ ውስጥ እንደሚገኝ አድርጐ ያሳምናቸዋል። የመልአኩ መልእክት ግን ሰዎችን ወደ መሠረታዊ እውነት፥ ማለትም እግዚአብሔር ፈጣሪ ነውና አምልኮት፥ አገልግሎትም ለእርሱ ብቻ ይገባል ወደሚለው አሳብ ይጣራል። የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት እንጂ፥ «አውሬውን»ን መፍራት አይደለም (ምሳ. 9፡10)።

«ባቢሎን ወደቀች!» (14፡8) ይህ እወጃ የራእይ 18ን ክስተቶች (16፡18-19ም አንብብ) ስለሚያመለክት፥ በዝርዝር እናየዋለን። «ባቢሎን» የሚለው ስም «አውሬው» ዓለምን ለሚያስተዳድርበት ሥርዓት ከእግዚአብሔር የተሰጠ የአምልኮ ስም ሲሆን፥ ይኸውም ማናቸውንም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። «ጋለሞታ» (ራእይ 17) የሚለው ቃል ደግሞ «አውሬው» ድርጅቱን ለመገንባት የሚጠቀምበትን ሃይማኖታዊ ዘይቤ የሚያመለክት ነው። ሐሳዊ-መሢሕ የራሱን ሃይማኖት መሥርቶ ሲያበቃ (13፡11-15)፥ «ጋለሞታዪቱ»ን ያጠፋታል፤ ባቢሎንን የሚያጠፋት ግን እግዚአብሔር ነው።

«ከእግዚአብሔር ቁጣ አምልጡ!» (14፡9-13)። ሦስተኛው መልእክት የተላለፈው በተለይ «አውሬው»ን በመከተሉ ውሳኔ ላይ ለሚገኙ ሰዎች ነው። ይህም «ቀላሉ መንገድ» በእርግጥ ከባድ እንደሆነ፥ ማለትም «ዓለምን መከተል» ከእግዚአብሔር ዘንድ መኮብለል እንደሆነ በመግለጽ የሚያስጠነቅቅ ነው! የግሪኩ ምንባብ፥ «ማንም ሰው አውሬውን በማምለኩ ቢቀጥል» በማለት፥ አሁንም ንስሐ ገብቶ ወደ ደኅንነት ለመምጣት ዕድል ያለው መሆኑን ያመለክታል።

«ጽዋ መጠጣት»፥ አንዳንድ ጊዜ የፍርድ መግለጫ በመሆን አገልግሏል (ኤር. 25 ከቁጥር 15 ጀምሮ፤ 51 ከቁጥር 7 ጀምሮ፥ እንዲሁም ራእይ 14፡8)። እግዚአብሔር በሰው ልጅ ላይ የሚያወርደው ፍርድ ከሰማይ የሚፈሱ የ«ቁጣ ጽዋዎች» ናቸው (ራእይ 16)። እግዚአብሔር በዚህ ቁጣ ውስጥ ምሕረትን አይቀላቅልም [መዝ. (75)፡8፤ ዕንባ. 3፡2) - በዓመፀኛው ዓለም ላይ ያልተበረዘ ቁጣውን ያወርዳል እንጂ።

እንደ «እሳትና ዲን» (ራእይ 14፡10) ብሎም እንደ «ጢስ» (14፡11) የመሳሰለው አገላለጽ አንዳንዶችን ያሳዝናቸዋል። «የፍቅር አምላክ የሆነው እግዚአብሔር እንዴት ፍጥረታቱ በዘላለማዊ ሥቃይ እንዲማቅቁ ሊፈቅድ ይችላል?» ሲሉ ይጠይቃሉ። ይሁንና የእግዚአብሔር ፍቅር በስሜት ላይ ያልተመሠረተ ቅዱስ ፍቅር እንደሆነና ኃጢአትን በፍትሕ ፈርዶ ማስወገድ እንዳለበት ልንገነዘብ ይገባል። «መሠቃየት» የሚለውን ቃል ላንወደው ብንችልም፥ ዳሩ ግን በዚህ ስፍራ የምንመለከተው ይህንኑ ነው (ቁ. 10፤ 9፡5፤ 11፡10፤ 20፡10 ተመልከት)።

በተጨማሪም እግዚአብሔር በተደጋጋሚ ኃጢአተኞችን እንዳስጠነቀቀና ንስሐ ገብተው የሚመለሱበትን ዕድል እንደሰጠ ልንገነዘብ ይገባል። በእነዚህ ተከታታይ ድርጊቶች ውስጥ፥ የመጀመሪያው መልአክ ኃጢአተኞች ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ የጋበዘ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ጠቅላላው «የባቢሎናውያን» ዘይቤ እንደሚወድም አስጠንቅቋል። እግዚአብሔር ፍርዶችንና ማስጠንቀቂያዎችን ከሰጠ በኋላ እንኳን ሰዎች በኃጢአታቸው ከቀጠሉ ከራሳቸው በቀር የሚወቅሱት ሰው አይኖርም።

ዮሐንስ አንባቢዎቹን በቁጥር 11 እና 13 መካከል ያለውን ልዩነት ከልብ እንዲያጤኑት ፈልጐአል - ለኃጥአን ዕረፍት የላቸውም - ቅዱሳን ግን ዘላለማዊ ዕረፍት አላቸው (2ኛ ተሰ. 1፡3-12 ተመልከት)። ከሐሳዊ መሢሕ ጋር ለአጭር ጊዜ ከመግዛት ይልቅ፥ ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም መንገሡ ይመረጣል። ለጥቂት ጊዜ ከመከራ ከመሸሽግና ለዘላለም ከመሠቃየት ይልቅ፥ አሁኑኑ መከራን በትዕግሥት መቀበሉ ይመረጣል።

«የማጨጃው ሰዓት ስለደረሰ» (14፡14-20) - በዚህ ስፍራ በነጭ ደመና ላይ እንደተቀመጠ ሆኖ የተገለጸው ያለጥርጥር ጌታችን ኢየሱስ

ክርስቶስ ነው (ዳን. 7፡13-14 ፤ ራእይ 1፡13 ተመልከት)። አስቀድመን የጽዋ ምስል የተመለከትን ሲሆን፥ አሁን ደግሞ የመከርን መግለጫ እናያለን፤ ሁለቱም የሰብል (ቁ. 14-16) እና የወይንን (ቁ. 17-20) መከር የሚያመለክቱ ናቸው። ይህም የዓለምን የመጨረሻ ፍርድ መቃረብ ያመለክታል።

አንዳንድ ጊዜ ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ነፍሳት ወደ ክርስቶስ መመለስ እንደ መከር ተግባር የተገለጸ ቢሆንም (ዮሐ. 4፡34-38)፥ ይህ ምስል ስለ እግዚአብሔር ፍርድ የቀረበ ተምሳሌት ነው (ሉቃ. 3፡8-17፤ ማቴ. 13፡24-30፤ 36-43)። እግዚአብሔር የበደል ዘሮች እስከሚበስሉበት ደረጃ ድረስ እንዲያድጉ ይፈቅዳል - ከዚያም ይፈርዳል (ዘፍጥ. 15፡16)።

የወይን መከር ብዙውን ጊዜ የፍርድ መግለጫ ነው (የጌታ ቀን እንደቀረበ የሚያመለክተውን ኢዩኤል 3 ከቁጥር 13 ጀምሮ ተመልከት)። በመሠረቱ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሦስት የተለያዩ «ወይኖች» ይናገራል። እስራኤል ለእግዚአብሔር ክብር ፍሬ እንድታፈራ የተተከለች የእግዚአብሔር ወይን ስትሆን፥ ዳሩ ግን ሕዝቡ ከእርሱ ስለተመለሰ መቆረጥ ነበረባት [መዝ. (80)፡8-16፤ ኢሳ. 5፡1-7፤ ማቴ. 21፡33-46 ተመልከት)። ዛሬ ክርስቶስ ወይን ሲሆን፥ አማኞችም በእርሱ ውስጥ የሚገኙ ቅርንጫፎች ናቸው (ዮሐ. 15)። ዳሩ ግን ሰማያዊ ወይን ከሆነው ከክርስቶስ በተፃራሪ፥ ዓለማዊ የሆነው ‹ምድራዊ ወይን› ጉምርቶ፥ ለፍርድ በመቃረብ ላይ ይገኛል። ሰዎችን የሚያሰክረውና በቁጥጥሩ ሥር የሚያውለው ኃጢአታዊ ዘይቤ - ባቢሎን፥ አንድ ቀን ይቆረጥና «ወደ እግዚአብሔር ቁጣ መጥመቂያ» ውስጥ ይጣላል።

አንዳንዶች በዚህ ውስጥ የዓለም ሠራዊት ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ የሚነሣበትን «የአርማጌዶን ጦርነት» መቃረብ የሚያመለክቱ ፍንጮች እንደሚገኙ ይናገራሉ (ዘካ. 14፡1-4፤ ራእይ 16፡16)። በእርግጥ ዮሐንስ 4 ጫማ ጥልቀትና 200 ማይሎች ርዝመት ስላለው የደም ወንዝ ሲናገር በተምሳሌት እየተጠቀመ መሆኑ አያጠራጥርም (ኢሳ. 63፡1-6 ተመልከት)። ዛሬ እግዚአብሔር ለሰዎች በጸጋ ቢናገርም፥ አይሰሙትም። ስለሆነም አንድ ቀን፥ በቁጣ መናገር አለበት። በዚህም ጊዜ ሰዎች

መራራውን ጽዋ ይጠጣሉ - የኃጢአት መከር ይሰበሰባል - የምድሪቱም ወይን ይቆረጥና በወይን መጥመቂያ ውስጥ ይጨመራል።

የድል-ነሺዎች ድምፅ (ራእይ 15፡ 1-4)

በዚህ ነጥብ ላይ፥ ዮሐንስ ሰባት መላእክት የእግዚአብሔር ቁጣ የተሞላባቸውን ሰባት ጽዋዎች ይዘው አንድ ተግባር ለማከናወን ሲዘጋጁ ይመለከታል። ኃጢአተኛው ዓለም «ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ» ሊጠጣ ተቃርቦ ነበር (ራእይ 14፡ 10)። ይሁንና ከዚያ በፊት፥ የበረከት መልእክት «ጣልቃ ገብቶ» እንመለከታለን። እግዚአብሔር «ሦስተኛውን ወዮ» ከመላኩ በፊት (11፡ 14)፥ አሁንም ለታማኝ ሕዝቡ በድጋሚ ዋስትና ይሰጣል።

ዮሐንስ በታላቁ መከራ ዘመን ውስጥ «አውሬው»ንና ዘይቤውን ያሸነፉትን አማኞች ይመለከታል። እነዚህ «ነፍሳቸውን እስከሞት ያልወደዱ» ሰዎች ናቸው (12፡ 11)። ከሰይጣናዊ ዘይቤ ጋር ስለማይተባበሩና የ«አውሬው»ን ምልክት ስለማይቀበሉ፥ ለመግዛትም ሆነ ለመሸጥ አይችሉም ነበር (13፡ 17)። ለዕለታዊ እንጀራቸው ሙሉ ለሙሉ በጌታ ላይ ጥገኞች ሆነው ተደግፈው ነበር። አንዳንዶቻቸው ወደ ወኅኒ ቢወርዱና ሌሎችም ቢታረዱ እንኳ (13፡ 10)፥ ሁላቸውም በእምነትና በትዕግሥት ይመላለሱ ነበር።

ይህ ትዕይንት ሁሉ እስራኤላውያን ከግብፅ ከወጡ በኋላ ካጋጠማቸው ሁኔታ ጋር የሚዛመድ ነው። ሕዝቡ ከግብፅ የወጣው በበጉ ደም ከመሆኑም፥ አሳዳጁ የግብፅ ሠራዊት በቀይ ባሕር ውስጥ ሰጥሞ ቀርቶ ነበር። እስራኤላውያን ግን እግዚአብሔርን በማመስገን፥ ከባሕሩ ባሻገር ቆመው «የሙሴን መዝሙር» ዘመሩ።

ዮሐንስ የተመለከታቸውና የሰማቸው የታላቁ መከራ ቅዱሳን፥ ልክ በቀይ ባሕር ዳርቻ እንደቆሙት እስራኤላውያን ሁሉ፥ በሰማይ በ«ብርጭቆ ባሕር» አጠገብ ቆመው ነበር (4፡6)። የሙሴን መዝሙርና የበጉን መዝሙር ይዘምሩ ነበር። የሙሴ መዝሙር በዘጸአት 15 ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን፥ አዝማቹ «ጉልበቴ ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፤ መድኃኒቴም ሆነልኝ» የሚል ነው (ቁ. 2)። 144,000 ዎቹም ማንም ሊዘምረው የማይችለውን መዝሙር ዘምረዋል፤ ሆኖም ግን ቅዱሳን ሁሉ ሊዘምሩት የሚችሉት ነው።

እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮ በተመለሱና መንግሥታቸውንና የቤተ መቅደስ አምልኮአቸውን ዳግም ማከናወን በጀመሩ ጊዜ፥ በምረቃ በዓላት ላይ ይህንኑ አዝማች ይዘምሩ ነበር [መዝ. (118) በተለይም ቁ. 14 ተመልከት]።

እንደዚሁም እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ምድራቸው ወደፊት በሚመልስበት ጊዜ፥ ይህንኑ መዝሙር ደግመው እንደሚዘምሩ ኢሳይያስ ተንብዮአል (ኢሳ. 11፡15-12፡6)። በመሠረቱ፥ የሙሴ መዝሙር በአይሁድ ሕዝብ ዝማሬ ውስጥ ከሌሎችም እጅግ ተቀዳሚው መዝሙር ነው።

ይህ ትዕይንት በቤተ ክርስቲያን ዘመን ለሚሠቃዩ ቅዱሳን ታላቅ ዋስትናና ጽናትን ይሰጣል። የዓለምን ዘይቤ ድል መንሣት ይቻላል! «ለአውሬው ምልክት» መገዛት አያስፈልግም። በበጉ ደም አማካኝነት ነፃ ወጥተናል። ጌታችን በመስቀል ላይ የፈጸመው ተግባር በደሙ የተከናወነ «መንፈሳዊ ነፃ መውጣት» ነው (ይህንኑ ነፃ የ«መውጣት» አሳብ የሚያቀርበውን ክፍል ከሉቃስ 9፡31 ተመልከት)።

በመዝሙራቸው፥ የታላቁ መከራ ቅዱሳን የእግዚአብሔርን ሥራዎችና መንገዶች ያመሰግናሉ። የምድር ነዋሪዎች እግዚአብሔርን ለሥራዎቹ ሊያመሰግኑት፥ ፍለጋውንም በፍጹም ሊረዱ አይችሉም! የእግዚአብሔር ሥራዎች ታላቅና ድንቅ ሲሆኑ፥ መንገዱም ፍትሐዊና ቅን ነው። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች እንዲሠቃዩ በመፍቀዱ፥ በዚህ ሳቢያ የተፈጠረ ማጉረምረም የለም። ዛሬ በዚሁ ዓይነት የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት ብንቀበል፥ ከብዙ ኃዘን እንድናለን! «እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው፤ በሥራውም ሁሉ ቸር ነው» [መዝ. (145)፡ 17]።

«የቅዱሳን ንጉሥ» የሚለው ሐረግ «የዘመናት ንጉሥ» ተብሎም ሊነበብ ይችላል። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ንጉሥ ከመሆኑም ባሻገር፥ ታሪክንም ይቆጣጠራል። በመሆኑም፥ በአጋጣሚ የሚፈጸም ነገር የለም። ዘማሪዎቹ እግዚአብሔርን ለማመስገንና ለማክበር ይሻሉ፤ ይህም የመጀመሪያው መልአኩ ያወጀው ምስጋና ነው (14፡7)። ከዚህ መዝሙር ጋር ተዛማጅነት ያለው አሳብ በመዝሙር (86)፡9፤ (90)፡1-2፤ (92)፡5፤ (98)፡2፤ (111)፡9 እና (145)፡17 ውስጥ ሊገኝ ይችላል።

ራእይ 15፡4 ሕዝቦች ሁሉ መቼ በጉን እንደሚያመልኩትና እንደሚታዘዙለት በመተንበይ የመንግሥቱን መቃረብ የሚያመለክት ሌላው ክፍል ነው። ቁጥሩ የእግዚአብሔር ፍርዶች ሊገለጹ እንደተቃረቡም ያውጃል።

የፍጻሜ ድምፅ (ራእይ 15፡5-16፡21)

ከመቅደሱ ውስጥ የወጣ አንድ «ታላቅ ድምፅ» ሰባቱ መላእክት የያዙዋቸውን ጽዋዎች እንዲያፈሱ ያዛል (16፡1)፤ ከዚያም በኋላ «ተፈጽሞአል!» በማለት ያውጃል (16፡17)። «የእግዚአብሔር ምሥጢር» ተፈጽሞአል (10፡7)። በክብር ስፍራ የነበሩ ቅዱሳን፥ «እስከ መቼ?» ሲሉ የጠየቁ ሲሆን (6፡9-11)፥ አሁን ጩኸታቸው ምላሽ ያገኛል።

እንደሚያመጡዋቸው ፍርዶች ሁሉ እንደ ሥራዎቻቸው ሁሉ ቅዱስ በመሆናቸው፥ ሰባቱ መላእክት ከሰማያዊው ቤተ መቅደስ ይወጣሉ (11፡19 ተመልከት)። የመላእክቱ አለባበስ የካህናትን አልባሳት ያስታውሰናል - አገልግሎታቸው ቅዱስ አገልግሎት ነውና። የብሉይ ኪዳን የመገናኛ ድንኳንና ቤተ መቅደስ በተመረቁ ጊዜ፥ እነዚህ ምድራዊ ሕንፃዎች በእግዚአብሔር ክብር ተሞልተው ነበር (ዘጸ. 40፡34-35፤ 2ኛ ዜና 7፡1-4)፤ ዳሩ ግን አሁን ሰማያዊው መቅደስ በጢስ ይሞላል (ኢሳ. 6፡4፤ ሕዝ. 10፡4 ተመልከት)። ይህም ጢስ የእግዚአብሔርን ክብርና ኃይል የሚያመለክት ነው።

እያንዳንዱ መልአክ ጽዋውን የሚያፈስበት የተወሰነ ስፍራ አለው። የምድር ነዋሪዎች አስቀድመው በማኅተምና በመለከት ፍርዶች የተሠቃዩ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ይህ ተከታታይ ፍርዶች የሚቀርቡበት የመጨረሻው ጽዋ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ይቋጨዋል። ይህም ወደ ባቢሎን ውድቀትና ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ወደሚመለስበት ክስተት በማምራት የሚከናወን ነው።

የሚነዘንዝ ቁስል (16፡2) - ይህ የጽዋ ፍርድ በግብፅ የደረሰውን ስድስተኛ መቅሰፍት ያስታውሰናል (ዘጸ. 9፡8-12፤ ዘዳግ. 28፡27፥ 35 ተመልከት)። በዚህ ፍርድ «ለአውሬው» የተገዙና የመጀመሪያውን መልአክ ማስጠንቀቂያ ችላ ያሉት ብቻ ይሠቃያሉ (ራእይ 14፡6-7)።

በአምስተኛው ጽዋ ጊዜ ሰዎች በመጀመሪያው ፍርድ ሕመም የተነሣ አሁንም ስለሚሠቃዩ፥ እነዚህ ቁስሎች እንደማይድኑ ከቁጥር 10-11 እንረዳለን። ይህም ሆኖ ሥቃዩ ወደ ንስሐ አይመራቸውም (ራእይ 9፡20-21 ተመልከት)። ዊልያም አር. ኒዌል፥ «ሰዎች በጸጋ ካልዳኑ፥ ጭራሹንም አይድኑም» ይሉ ነበር።

ጠቅላላው የዓለም ሕዝብ ለማለት ይቻላል፥ ምንም መድኃኒት በማይፈውሰው ሕመም ሲሠቃይ መመልከቱ አስፈሪ ነገር ነው። የማያቋርጥ ሕመም የሰውን ተፈጥሮ ስለሚፈታተን፥ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተስማምቶ መኖር ይሳነዋል። በመሆኑም፥ በዚያን ጊዜ ሰብአዊ ግንኙነቶች ከመቼውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።

ውኃ ወደ ደም ይለወጣል (16፡3-6) - ሁለተኛውና ሦስተኛው ጽዋዎች ከግብፁ የመጀመሪያ መቅሰፍት ጋር ይመሳሰላሉ (ዘጸ. 7፡14-25)። ሁለተኛው ጽዋ በባሕር ላይ የሚያተኩር ሲሆን፥ ሦስተኛው ደግሞ ወንዞችንና ምንጮችን ወደ ደም ይለውጣቸዋል። የሁለተኛው መለከት ፍርድ በሚፈጸምበት ጊዜ፥ አንድ ሦስተኛው የባሕር ክፍል ወደ ደም ተለውጧል፤ ዳሩ ግን በዚህ ፍርድ ጠቅላላው ባሕርና ውቂያኖስ ይበከላል። ሦስተኛው መለከት አንድ-ሦስተኛውን የወንዞችና የምንጮች ክፍል እንደ እሬት መራራ የሚያደርገው ሲሆን፥ ሦስተኛው ጽዋ ግን እነዚያን መራራ ውኆች ሁሉ ወደ ደም ይለውጣቸዋል።

ሰማይ የዚህን አስጨናቂ ፍርድ ፍትሐዊነት ያረጋግጣል - የምድር ነዋሪዎች የእግዚአብሔርን ሰዎች ደም ስላፈሰሱ፥ ደም መጠጣታቸው ተገቢ ነው። በእግዚአብሔር አገዛዝ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ ነው። ፈረዖን የአይሁዶችን ሕፃናት ወንዶች በውኃ አስጥሞ ለማጥፋት ቢሞክርም፥ ዳሩ ግን በመጨረሻ በቀይ ባሕር ውስጥ የሰጠመው የራሱ ሠራዊት ነበር። ሐማ መርዶክዮስን በግንድ ላይ ለማሰቀልና አይሁዶችን ለማጥፋት ቢያቅድም፥ ዳሩ ግን በግንድ ላይ የተሰቀለው እርሱ ራሱና ለጥፋት የተዳረገውም ቤተሰቡ ነበር (አስቴር 7፡10፤ 9፡10)። ንጉሥ ሳያል እግዚአብሔርን በመታዘዝ አማሌቃውያንን ለማጥፋት ባለመፈለጉ፥ በምትኩ እራሱ በአማሌቃዊ ሰው ተገደለ (2ኛ ሳሙ. 1፡1-16)።

ከፍተኛ የፀሐይ ትኩሳት (16፡8-9) - ምድራዊ ሕይወት በሙሉ በፀሐይ ብርሃን ላይ ይወሰናል። በቀደሙት ፍርዶች፥ የተወሰነው የፀሐይ ክፍል የሚጨልም ሲሆን (8፡12)፥ አሁን ግን የፀሐይ ትኩሳት ይጨምራል። በምድረ በዳ የቆየ ሰው የፀሐይ ሙቀት ምንኛ የከፋ ሊሆን እንደሚችል ያውቃል። በዚህ ጊዜ ውኃ ወደ ደም መለወጡን ስናስታውስ፥ ሰዎች እንዴት በፀሐይ ቃጠሎና በጥም እንደሚሠቃዩ መገመት ይቻላል። የሚያሳዝነው፥ ይህም ፍርድ እንኳ ሰዎችን ለፈጣሪ ወደ መንበርከክ አለማምጣቱ ነው! (ሚልክ. 4፡1 ተመልከት)።

ጽልመት (16፡10-11) - ይህ ጨለማ ዓለም-አቀፋዊ ሳይሆን፥ «በአውሬው፥» በዙፋኑ እና በመንግሥቱ ላይ ብቻ የሚደርስ ነው። ይህም አምስተኛውን መለከትና (ራእይ 9፡2) ዘጠነኛውን መቅሰፍት ያስታውሰናል (ዘጸ. 10፡21-23)። «የአውሬው» ዙፋን ወዴት ነው? ምስሉ የሚገኘው በኢየሩሳሌም መቅደስ ውስጥ ስለሆነ፥ ይህም የሥራው ማዕከል ይሆናል። አለበለዚያም ዋና ጽሕፈት ቤቷ በሮም ከተማ ከሚገኝባት ከሃዲ ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር ከዚያው ከሮም ሆኖ ይገዛ ይሆናል።

እግዚአብሔር ዘጠነኛውን መቅሰፍት በግብፅ ላይ ባወረደበት ጊዜ፥ እስራኤላውያን ከሚገኙባት የጌሴም አካባቢ በቀር ምድሪቱ በሙሉ በጨለማ ተውጣ ነበር። አምስተኛው የጽዋ ፍርድ የዚህ ተገላቢጦሽ ሲሆን፥ በዓለም ብርሃን እያበራ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን «በአውሬው» መናገሻ ጽልመት ይነግሣል! ይህም ለ«ምስሉ» በምድር ሁሉ መሰራጨት ትልቅ እንቅፋት ይሆናል።

የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅ (16፡12-16)- ይህ ገናና ወንዝ ቀደም ሲል ስድስተኛው መለከት በተነፋ (ራእይ 9 ከቁጥር 13 ጀምሮ) እና በዚያ ታስረው የነበሩ መላእክት በተፈቱ ጊዜ ተጠቅሶ ነበር። በዚያን ጊዜ፥ የአጋንንታዊ ፈረሰኛ ሠራዊት ይፈታል። በመሆኑም፥ ከዓለም ሕዝቦች የተውጣጣው ሠራዊት ለታላቁ የአርማጌዶን ጦርነት ይሰበሰባል። የኤፍራጥስ ወንዝ መድረቅም «የምሥራቅ ነገሥታት» ወደ ፍልስጥኤም ምድር ተሻግረው ቅድስቲቱን ከተማ የሚወሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

ብዙውን ጊዜ ስለ «አርማጌዶን ጦርነት» ብንናገርም፥ ዳሩ ግን ይህ ሐረግ በተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ተጠቅሶ አናገኝም።

ጀኔራል ዶግላስ ማክአርዘር፥ መስከረም 2፥ 1945 ዓ.ም. ከጃፓን ጋር የተደረገውን የሰላም ውል ሲያስፈጽሙ እንዲህ ብለው ነበር:- «ይህ የመጨረሻው ዕድላችን ነበር። [ከጦርነት በላይ] የላቀና ፍትሐዊነትን የጠበቀ ነገር ካላዘጋጀን፥ አርማጌዶን ከበራችን ደጃፍ ቆሞ ያንኳኳል።»

«አርማጌዶን» የሚለው ቃል፥ «ሐር መጊዶ» ማለትም «የመጊዶ ኮረብታ» ከሚሉ ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት የተገኘ ነው። ትርጉሙም «የወታደሮች ሰፍራ» ወይም «የእርድ ሰፍራ» ማለት ነው። በተጨማሪም፥ የኤስድራሎን ሜዳ ወይም የኢይዝራኤል ሸለቆ ተብሎ ተጠርቷል። የሰፍራው ወርድ 14 ማይሎች፥ ርዝመቱ ደግሞ 20 ማይሎች ሲሆን፥ ናፖሊዮን፥ «ከማናቸውም የምድር ገፅታ ይልቅ፥ ለጦርነት ያመቸ ሥፍራ» በማለት የጠራው ነው። ከቄርሜሎስ ተራራ ላይ ቆመህ ለጥ ያለውን ሜዳማ ሰፍራ ስትመለከት፥ ከዓለም ሕዝቦች የተውጣጣውን ሠራዊት ለማሰባሰብ ለምን እንደተመረጠ ልትገነዘብ ትችላለህ።

ባላቅ የከነዓንን ሠራዊት ያሸነፈው በዚህ ሰፍራ ነበር (መሳ. 5፡19)። ጌዴዎንም ምድያማውያንን ጦርነት የገጠመው በዚህ ሰፍራ ሲሆን (መሳ. 7)፥ ንጉሥ ሳዖል የሞተው በመጊዶ ነበር (1ኛ ሳሙ. 31)። ቲቶና የሮም ሠራዊት በዚህ የተፈጥሮ መተላለፊያ የተጓዙበት ሲሆን፥ የመካከለኛው ዘመን የመስቀል ዘማቾችም እንዲሁ ተጠቅመውበታል። የብሪታንያ ጄኔራል አሌንቢ በ1917 የቱርክን ሠራዊት ባሸነፈ ጊዜ በዚሁ ጐዳና ተጠቅሟል።

በሰው አስተሳሰብ፥ ከዓለም ሕዝብ የሚውጣጣው ሠራዊት በራሱ አሳብ የሚሰባሰብ ቢመስልም፥ ዳሩ ግን የወታደሮቹ እንቅስቃሴ በእግዚአብሔር ዕቅድ የሚከናወን መሆኑን ዮሐንስ ይገልጽልናል። ሰይጣናዊው ሥላሴ በአጋንንታዊ ኃይሎች አማካኝነት ሕዝቦችን በማንቀሳቀስ፥ ገዢዎች ሠራዊታቸውን እንዲያሰባስቡ ያደርጋል። እንዲያውም ገዢዎችን የሚያስደንቁና ለመተባበር የሚያነሣሷቸውን ተአምራት ይፈጽማል። ይህ ሁሉ ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዓላማዎች ከመፈጸም አይዘልም (ራእይ 17፡17 ተመልከት)። አሕዛብ አርማጌዶንን እንደ ጦርነት ቢመለከቱትም፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን፥ ለሰማይ ወፎች እንደተሰናዳ የ«እራት» ግብዣ የሚቆጠር ነው (19፡17-21)።

ዘካርያስ 12 እና 14 ይህንን ክስተት ከእስራኤል አመለካከት አንጻር ያብራሩታል። «አውሬው» በኢየሩሳሌም በሚገኘው መቅደስ ውስጥ ምስሉን ስላቆመና ብዙዎቹም አይሁዶች ስለማይሰግዱለት፥ ቅድስቲቱ ከተማ የጥቃቱ ማነጣጠሪያ ትሆናለች። እንደዚሁም እግዚአብሔር ለአሕዛብም ዓላማ ስላለው፥ በዚህ ጦርነት ውስጥ የሚሳተፉት አይሁዶች ብቻ አይደሉም። ኢዩኤል 3፡9-21 የዘካርያስን ማጣቀሻዎች በማዛመድ፥ እግዚአብሔር አይሁዶችን አሕዛቦች በማጉላላታቸው እንደሚፈርድባቸው ቁጥር 19 ይናገራል (ሶፎ. 3 ከቁጥር 8 ጀምሮ፤ ኢሳ. 24 ተመልከት)።

የጦርነቱ ውጤት በራእይ 19 ተጠቅሶ እናገኘዋለን - ጌታ ይመለስና ጠላቶቹን ድል ይነሣል። በመሠረቱ፥ የሠራዊቱ መሰባሰብና ወደጦሩ ሜዳ መገስገስ ሁሉን ቻይ ለሆነው አምላክ ምኑም አይደለም! ሰዎች ሲቆጡበትና ሕጉን ሲተላለፉ፥ «በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፥ ጌታም ይሣለቅባቸዋል። በዚያን ጊዜ በቍጣው ይናገራቸዋል፥ በመዓቱም ያውካቸዋል» (መዝ. 2፡4-5)።

«ተፈጽሞአል!» (16፡17-21) - ዲያብሎስ «በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ» በመሆኑ፥ ምናልባት ይህ ሰባተኛው ጽዋ በግዛቱ ላይ የተለየ ጉዳት ሳያደርስ አይቀርም (ኤፌ. 2፡2)። ይሁንና ፈጥኖ የተከሰተው ለውጥ የሕዝቦችን ከተሞች ያጠቃው አውዳሚ ርዕደ-ምድር ነው። በሰይጣን ዘይቤ ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚገለጽበት ጊዜ ደረሰ - በሃይማኖታዊ ዘይቤው (ጋለሞታዪቱ - ራእይ 17)፥ በፖለቲካዊና በኢኮኖሚያዊ ዘይቤው (ባቢሎን ራእይ 18)፥ እንዲሁም በወታደራዊ ዘይቤው ላይ (ሠራዊት - ራእይ 19) ፍርድ ይሰጣል።

«ታላቂቱ ከተማ» (16፡19) ምናልባትም ኢየሩሳሌም ትሆናለች (11፡8 ተመልከት)። ቀደም ሲል ነቢዩ ዘካርያስ የኢየሩሳሌምን የመሬት አቀማመጥ ስለሚለውጠው ርዕደ-ምድር የተነበየ ሲሆን (ዘካ. 14፡4)፥ በዚህ ስፍራ ግን ቁልፉ አሳብ ባቢሎን እንደምትወድቅ ነው (ኤር. 50-51 ተመልከት)። የዓለምን ሕዝቦች የተቆጣጠረው «የአውሬው» ታላቅ የኢኮኖሚ ሥርዓት፥ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ይወድማል።

በርዕደ-ምድሩ ላይ ታክሎ የሚመጣው ከፍተኛ ክብደት ያላቸው በረዶዎች የሚገኙበት ነጐድጓድ ነው። (አንድ ታላንት ሦስት ፈረሱላ ያህል ነው!) ይህ ፍርድ በግብፅ ከተፈጸመው ሰባተኛው መቅሠፍት ጋር

ይመሳሰላል (ዘጸ. 9፡22-26)። ይሁንና ፈረዖንና የግብፅ መሪዎች እንዳደረጉት ሁሉ፥ የምድር ነዋሪዎችም ንስሐ አይገቡም፤ እንዲያውም፥ እግዚአብሔርን ይሰድቡታል! ሆኖም ተሳዳቢዎች በድንጋይ ተወግረው እንዲገደሉ የተወሰነባቸው በመሆኑ፥ የበረዶው መውረድ የሚያስደንቅ አይሆንም (ዘሌ. 24፡16)።

እነዚህን ሦስት ምዕራፎች በመከለስ፥ በመከራ ውስጥ ለሚገኙ ክርስቲያኖች የሚሰጡትን ማበረታቻ እንመለከታለን። የታተሙት 144, 000 ሰዎች ከጽዮን ተራራ ላይ ደርሰው እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል (ራእይ 14፡1-5)። ሰማዕታቱም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ፥ በክብር ይመላለሳሉ (15፡1-4)። የዮሐንስ መልእክት ግልጽ ነው - በ«አውሬው» ላይ ድል መንሣትና አሸናፊ መሆን ይቻላል!

የሠራዊቱ እንቅስቃሴዎች፥ የሕዝቦች በኮንፌዴሬሽን መተባበር፥ ብሎም በእግዚአብሔር ላይ የሚደረገው ዓለም - አቀፍ ተቃውሞ፥ ጌታን ቃሉን ከመፈጸምና ዓላማዎቹን ከማከናወን ሊያቅበው አይችልም። ሰዎች እንዳሻቸው የማድረግ ኃይልና ሥልጣን እንዳላቸው ያስባሉ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፥ ሳይታወቃቸው የእግዚአብሔርን ዕቅዶችና ዓላማዎች በመፈጸም ላይ ናቸው!

በሁሉም ዘመን የሚገኙ ክርስቲያኖች ከራእይ 14-16 በተጠቀሱ ክስተቶች ውስጥ ሲያልፉ ኖረዋል። ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመጨቆን የሚነሣ «አውሬ» እና ወደጥፋት ለመምራት የሚጣጣር ሐሰተኛ ነቢይ ነበር። ሕዝቦች ጦርነት በከፈቱ ቁጥር በ«አርማጌዶን» ሜዳ ላይ ነበርን።

በመጨረሻው ዘመን ግን፥ እነዚህ ክስተቶች ወደፊት ይፋጠኑና የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች በከፍተኛ ደረጃ ፍጻሜያቸውን ያገኛሉ። በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የትዕይንቱ ተካፋይ እንደማትሆን አምናለሁ፤ የሐሳዊ-መሢሕን አገዛዝ መታገሥ የሚኖርባቸው የአይሁድና አሕዛብ አማኞች ይኖራሉ።

በራእይ 16፡15 ላይ የሚገኘው ምክር ለሁላችንም የሚጠቅም ነው፡- «እነሆ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።» ኢየሱስ ክርስቶስ በማንኛውም ጊዜ ሊመለስ ስለሚችል፥ ሕይወታችንን በንጽሕና መጠበቁ፥ መንቃቱና በታማኝነት መኖሩ ጠቃሚ ነው።

- 10 -

ጥፋትና ውድመት

ራእይ 17-18

ከራእይ 17 ጀምሮ፥ ዮሐንስ በጉ በ«አውሬው» እና በመንግሥቱ ላይ የሚቀዳጀውን ድል ደረጃ በደረጃ ይዘረዝራል። በምዕራፍ 17፥ በሃይማኖታዊ ዘይቤ ላይ ፍርድ ሲሰጥ፥ በምዕራፍ 18፥ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዘይቤው ይወድቃል። በመጨረሻም፥ ጌታ ራሱ ወደ ምድር ተመልሶ፥ በሰይጣን፥ በ«አውሬው» እና በሐሰተኛው ነቢይ ላይ ፍርዱን ይገልጻል (19፡19-20) - ከዚያም፥ መንግሥቱን ይመሠርታል።

ዮሐንስ ተምሳሌትን ከተጠቀመባቸው ምክንያቶች አንዱ በማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የሚኖሩ አማኞች ሁሉ በመልእክቱ ይበረታቱ ዘንድ ነው። እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ንጽሕት ድንግል ስትሆን (ራእይ 19፡7-8፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡2 ተመልከት)፥ ሐሰተኛ ሃይማኖታዊ ዘይቤ የምትከተለዋ ግን እውነትን በመጣል ራስዋን ለግል ጥቅሞች አሳልፋ የሰጠች ጋለሞታ ነች። በዘመናት ሁሉ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ያሳደደች «ጋለሞታ» መኖሯ ሲታወቅ፥ ይህም ከፍጻሜ የሚደርሰው በመጨረሻው ዘመን በሚነግሠው ዓለም አቀፋዊ ከሃዲ የሃይማኖት ዘይቤ ነው።

እንደዚሁም፥ የሰዎችን አስተሳሰቦችና ፍጻሜዎች ለመቆጣጠር የሚሻው «ባቢሎን»፥ ማለትም ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት በሁሉም ዘመን ውስጥ ተንጸባርቋል። ንጽሕት ሙሽራ የ«ጋለሞታዪቱ» ተቃራኒ እንደሆነች ሁሉ፥ ለበጉ ሚስት የተዘጋጀችው ዘላለማዊቷ ቤተ ክርስቲያን ማለትም የእግዚአብሔር ከተማ የሆነችው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ የ«ባቢሎን» ተቃራኒ ነች (ራእይ 21፡ ከቁጥር 9 ጀምሮ)። የእያንዳንዱ ዘመን አማኞች ራሳቸውን ከ«ጋለሞታዪቱ» እና ከ«ባቢሎን» መጠበቅ አለባቸው።

በሚከተሉት ሁለት ምዕራፎች፥ ዮሐንስ ሁለት መለኮታዊ ፍርዶች እንደሚገለጹ ይተነብያል።

የጋለሞታዪቱ መውደቅ (ራእይ 17)

ትዕይንቱ የሚጀምረው በግብዣ ነው (17፡1-2)። ከመላእክት አንዱ ዮሐንስን እግዚአብሔር በ«አውሬው» ዓለም-አቀፋዊ የሃይማኖት ዘይቤ ላይ የሚያደርገውን ነገር እንዲመለከት ይጋብዘዋል። በዚህ ምዕራፍ፥ ሴቲቱ አራት ጊዜ «ጋለሞታ» ተብላ የተጠራች ስትሆን (ቁ. 1፥ 5፥ 15-16)፥ ኃጢአቷም «ዝሙት» ተብሏል (ቁ. 2፥ 4)። ክፉ ተጽዕኖዋ ወደ ዓለም ሁሉ ከመሰራጨቱም በላይ፥ ወደ ከፍተኛ ስፍራዎች («የምድር ነገሥታት»ም) ዘንድ ደርሶ ነበር።

ከግብዣው ቀጥሎ፥ ዮሐንስ «በመንፈስ» ወደ ምድረ በዳ ተወሰደ። በዚያም «ጋለሞታዪቱ»ን ከመመልከቱም፥ ያየውን ሁሉ በዘገባ መልክ ይዘረዝራል (ቁ. 3-6)። ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ባማረ የአትክልት ስፍራ ስለምትገኘው ንጽሕት ሙሽራ ሲናገር፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ፍጻሜ ግን፥ የዘመኑ ሥልጣኔ ውጤት የሆነችውንና በምድረ በዳ ውስጥ የምትገኘውን የረከሰች ጋለሞታ ያሳየናል። ኃጢአት ለዓለም የሚያስገኘው ፋይዳ ይኸው ነው!

ገለጻው በሙሉ በግሩም ሁኔታ ቀርቧል። ሴቲቱ በውድ ልብሶች ያሸበረቀች ከመሆኗም፥ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች አጊጣለች። በእጇ የወርቅ ጽዋ የያዘች ሲሆን፥ በቅዱሳንም ደም ሰክራለች። በግንባሯም የተለየ ስም ተጽፏል (13፡16፤ 14፡1 ተመልከት)።

የአቀማመጧን ሁኔታ መረዳት በጣም ጠቃሚ ነው። «በብዙ ውኆች፥» (17፡1)፥ እንዲሁም ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች በነበሩት ቀይ አውሬ ላይ ተቀምጣ ነበር። ዮሐንስ ሴቲቱንና «አውሬው»ን በተመለከተ ጊዜ «በእጅጉ መደነቁ» አያስገርምም።

ይሁንና ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው? እዚህ ላይ የሚያስደስተው ነገር፥ መልአኩ ለዮሐንስ (እና ለአማኞች ሁሉ) የእነዚህን ምልክቶች ማብራሪያ መስጠቱ ነው (ቁ. 7-18)።

ከሴቲቱ እንጀምር። ቁጥር 18 እንደሚያመለክተው፥ ሴቲቱ በዮሐንስ ዘመን ከነበረች ከተማ ጋር ትዛመድ ነበር («የምትነግሥ» የሚለው የአሁኑን ጊዜ ያመለክታል)። ይህች ከተማ ባለጸጋና ኃያል ስትሆን፥ ጣዖት አምላኪ («ተሳዳቢ») እና አደገኛም ነበረች። በአንድ

በኩል፥ ሕዝቦችን (በወርቅ የወይን ጽዋ በተገለጸው) በቆሻሻና በእርኩሰት ትበክላለች፤ በሌላ በኩል፥ የጌታ የሆኑትን ታሳድዳለች (ቁ. 6)። የ«ታላቂቱን ጋለሞታ» ማንነትና ዓለም-አቀፋዊ ተሳትፎ፥ ኃያል፥ ባለጸግነት፥ ብክለት፥ ስደት የሚሉ ቃላት ይገልጹልናል።

በሴቲቱ መጠሪያ ስሟም ውስጥ «ምሥጢር» አለ (ቁ. 5)። በአዲስ ኪዳን፥ «ምሥጢር» በመንፈሳዊ ማስተዋል የሚነሣሡ ሰዎች ብቻ የሚረዱት ድብቅ እውነት ነው። ከእግዚአብሔር ምሥጢራት አንዱን ለመረዳት መንፈሳዊ እውቀትንና ምርመራን ይጠይቃል። በዚህ ስፍራ፥ ምሥጢሩ ከባቢሎን ጋር የሚዛመድ ነው።

የባቢሎን ከተማ የተቆረቆረችው በናምሩድ ሲሆን (ዘፍጥ. 10፡8-11)፥ «ባብ-ኤል» ማለት ደግሞ «የእግዚአብሔር ደጅ» ማለት ነበር። በቅኔያዊ አነጋገር፥ ዝነኛው የባቢሎን ግንብ፥ ሰው እግዚአብሔርን ላለመታዘዝ ያደረገው አምልኮተ ጣዖታዊ ሙከራ ነበር (11፡1-9)። እግዚአብሔር የሰዎችን አንድ ቋንቋ ወደ ብዙ በመቀየር በግንበኞቹ ላይ ፍርድን ሲያመጣ፥ «ባብ-ኤል» «ድብልቅ» የሚለውን ትርጉም ያዘ። ቆይቶም ከኋለኛው ዘመን ታሪክ ውስጥ እንደምንረዳው፥ ባቢሎን በመጨረሻው ወደ ፋርስ እና ሜዶን ከመከፋፈሏ በፊት ታላቅ መንግሥት ሆና ነበር። ይሁንና በዘፍጥረት 10 ከተጠቀሰችው የናምሩድ ከተማ ጅማሬ አንሥቶ የባቢሎናውያን የከፋ ፀረ-እግዚአብሔራዊ አቋም በታሪክ ሁሉ ተስተውሏል።

ሴቲቱ «ታላቅ ጋለሞታ» ስትሆን፥ «የጋለሞቶች»ም እናት ናት። የባቢሎናውያን ዘይቤ፥ በአንድም ይሁን በሌላ በኩል ለሐሰት ሃይማኖቶች ሁሉ መፈልፈል አስተዋጽኦ አድርጓል። እንዲሁም ባቢሎን ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲቃወሙና አገልጋዮቹን እንዲያሳድዱም ግፊት አድርጋለች።

ሰባቱ ተራራዎች (ራእይ 17፡9) ምናልባት በሰባት ኮረብታዎች ላይ የተመሠረተችውን የሮም ከተማ ያመለክቱ ይሆናል። በመሠረቱ በዮሐንስ ዘመን፥ የሮም መንግሥት የሐሰት ሃይማኖት እያስፋፋ፥ ሕዝቦችን በጣዖት አምልኮውና በኃጢአቱ እየበከለና ቤተ ክርስቲያንን እያሳደደ በምቾት ይኖር ነበር።

በመሆኑም ዮሐንስ ኃጢአተኛዪቱን የሮም ከተማ ወይም ፖለቲካዊ ዘይቤዋን በክፉዋ ጋለሞታ ተምሳሌትነት ወክሎ በመጠቀሙ አንባቢዎቹ አይደነቁም። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን እንኳ ጋለሞታ ብሎ ጠርቶአታል! (ኢሳ. 1፡21)። ኢሳይያስ ጢሮስ ጋለሞታ እንደሆነች የተናገረ ሲሆን (ኢሳ. 23፡16-17)፥ ናሆምም ነነዌን ለመግለጽ በተመሳሳይ ቃላት ተጠቅሟል (ናሆም 3፡4)። (ከዮሐንስ ትንቢታዊ መልእክት ጋር የሚዛመድ ተጨማሪ ታሪካዊ ጉዳዮችን ለመመልከት ኤርምያስ 50-51 አንብብ)።

አስቀድሞ እንደተገለጸው፥ ቀይ ቀለም፥ የሰይጣን (ራእይ 12፡3) እና የኃጢአት (ኢሳ. 1፡18) ቀለም ነው። ይህ ቀለም ከሌሎችም ይበልጥ በሮም አገር የተወደደ ከመሆኑም፥ በተለይም ቀይና ሐምራዊ ቀለሞች ከማዕረግና ከብልጽግና ጋር ይዛመዱ ነበር።

ይህም ቢሆን ቅሉ፥ ሴቲቱ ግን ከሚሸከማት ከ«አውሬው» ተለይታ ለብቻ መታየት የለባትም። አውሬው ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች አሉት። ሰባቱ ራሶች ሰባት ተራሮችን (ራእይ 17፡9)፥ እንዲሁም ሰባት ነገሥታትን ወይም መንግሥታትን ያመለክታሉ (17፡10)፤ ይህም ከብሉይ ኪዳን ተምሳሌት ጋር ይዛመዳል [መዝ. (30)፡7፤ ዳን. 2፡35]። ሰባቱ ተራሮች በመልከዓ ምድራዊ ግንዛቤ ሰባቱ የሮም ተራሮች ተደርገው ሊተረጐሙ እንደሚችሉ ቀደም ሲል ተመልክተናል፤ ዳሩ ግን ከታሪካዊ ግንዛቤ አኳያ እንደ ሰባት መንግሥታትም ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ።

በራእይ 17፡10 ገለጻ መሠረት፥ ከእነዚህ ነገሥታት (ወይም መንግሥታት) አምስቱ ያለፉ፥ አንዱ በዮሐንስ ዘመን የነበረና አንዱ ገና ወደፊት የሚመጣ ነበር። ይህም ከሆነ፥ አምስቱ ያለፉት መንግሥታት ግብፅ፥ አሦር፥ ባቢሎን፥ ፋርስና ግሪክ ይሆናሉ። በዮሐንስ ዘመን የነበረው መንግሥት ስድስተኛው የሮም መንግሥት ሲሆን፥ ወደፊት የሚመጣው ደግሞ የ«አውሬው» መንግሥት ሰባተኛው ይሆናል። ቁጥር 10-11ን ለመረዳት፥ ቁጥር 12ን መመልከት ይኖርብናል።

«አውሬው» ሰባት ራሶች ብቻ ሳይሆን፥ አሥር ነገሥታትን የሚወክሉ አሥር ቀንዶችም አሉት። እነዚህ ግን የተለዩ ነገሥታት ናቸው - «አውሬው»ን ለሥልጣን ከማብቃታቸውም በላይ፥ ሥልጣናቸውን

እንኳ ለእርሱ ለመልቀቅ ፈቃደኞች ናቸው። የመጀመሪያው ማኅተም በተከፈተበት ወቅት (6፡1-2)፥ ሐሳዊ-መሢሕ በሰላማዊ መንገድ ሕዝቦችን ድል ሊነሣ እንደጀመረ አስታውስ። «የተባበሩት የአውሮፓ መንግሥታት»ን በማደራጀትና ለመካከለኛው ምሥራቅ ሰላም በማምጣት በጭንቀት ለተወጠረው ዓለም ታላቅ መሪ ለመሆን በቅቷል።

ይሁንና በሰባቱ ዓመት አጋማሽ ላይ፥ ይህ ገዥ ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በማፍረስ (ዳን. 9፡27)፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብና እስራኤልን ማሳደድ ይጀምራል። በሰይጣን ኃይል በመታጠቅና በሐሰተኛው ነቢይ በመታገዝ፥ «አውሬው» የዓለም አምባገነንና አምላክ ይሆናል። በዚህም ዓይነት፥ «አውሬው» «ከሰባቱ [ነገሥታት፥ መንግሥታት] አንዱ» ሲሆን፥ ደግሞም «ስምንተኛው» ነው። መንግሥቱ በቀድሞው የሮም መንግሥት ላይ የተመሠረተ («ከሰባቱ አንደኛው») ቢሆንም፥ በተጨማሪም እንደ አዲስ መንግሥት («ስምንተኛው») የሚቆጠር ነው።

ታዲያ ይህ ሁሉ ከባቢሎን ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? ናምሩድ ግዛቱን ከመሠረተበት ጊዜ አንሥቶ፥ «የባቢሎናውያን» የሐሰት ሃይማኖት «ዘይቤ» የታሪክ አካል ሆኖ ቆይቷል። የሚገርመው ግን ሊቃውንት ይህን ሃይማኖት ከእውነተኛው የክርስትና እምነት ተመሳሳይ ነው ሲሉ መግለጻቸው ነው። ሆኖም ይህ አባባል፥ ሰይጣን የእግዚአብሔርን እውነት አስመስሎ ለማቅረብ ያደረገው ጥረት አካል መሆኑን መገንዘብ ያሻል! ባቢሎናውያን የእናትንና ልጅን አምልኮ የሚለማመዱ ሲሆን፥ በልጁም ሞትና ትንሣኤ ያምናሉ።

በዮሐንስ ዘመን የነበሩ አንባብያን «ጋለሞታዪቱ» የሮምን መንግሥት እንደምትወክል አድርገው ሲረዱ፥ በመካከለኛው ዘመን የነበሩ አንባብያን ደግሞ ከሮም ሃይማኖታዊ ዘይቤ ጋር ሊያዛምዱት ይችላሉ። በዛሬውም ጊዜ ቢሆን ጥቂት አማኞች፥ «ጋለሞታዪቱ»ንና የባቢሎናውያንን ዘይቤ የሚያዛምዱት፥ መሠረታዊውን የሥነ መለኮት እውነት ዝቅ በማድረግ፥ የቃሉን ሥልጣን እያገለለችና አማኞች ነን የሚሉትን ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ባለው እምነት ሳይሆን፥ በሌሎች አንዳንድ መሥፈርቶች መሠረት ለማስተባበር ከምትጥረው ከሃዲዋ «ዓለማዊት ቤተ ክርስቲያን» ጋር ነው።

ይሁንና፥ የዮሐንስ ትንቢት በሚፈጸምበት ዘመን፥ አንድ አስደናቂ ነገር ይፈጸማል - «ጋለሞታዪቱ» በዚያው በተሸከማት ሥርዓት ትደመሰሳለች! «አውሬው» «ጋለሞታዪቱን» እንደሚሸከም መረዳቱ ጠቃሚ ነው። ሰይጣን (እና ሐሳዊ-መሢሕ) የራሱን ዓላማዎች ከፍጻሜ ለማድረስ (የዓለምን ሥልጣን ለመጨበጥ) ከሃዲ የሆነ ሃይማኖታዊ ዘይቤን መሣሪያ አድርጎ ይጠቀማል፤ ዳሩ ግን ሥልጣኑን ከያዘ በኋላ «ጋለሞታዪቱን» ወዲያ አሽቀንጥሮ ይጥልና የራሱን ሃይማኖታዊ መዋቅር ይዘረጋል። ይህም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ቃል ፍጻሜ የሚያመራ ይሆናል! (ራእይ 17፡17)።

«አውሬው» ምስሉን በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያቆመው በመከራው አጋማሽ አካባቢ ስለሆነ፥ «ጋለሞታዪቱ» እና «አውሬው» በመጀመሪያው ሦስት ተኩል ዓመታት ውስጥ አብረው እንደሚሠሩ አድርገን ልንወስድ እንችላለን። ለዚህም አሥሩ ነገሥታት «ጋለሞታዪቱን» በማጥፋቱ ዘመቻ እንደሚተባበሩት የተረጋገጠ ነው (17፡16)። እነዚህም በመጀመሪያው የመከራ አጋማሽ «የተባበሩት የአውሮፓ መንግሥታ»ን በሚያቋቁምበት ጊዜ ከአውሬው ጋር አባላት የሚሆኑት አሥሩ ነገሥታት ናቸው።

በታሪክ እንደተዘገበው ሁሉ፥ የፖለቲካ መዋቅሮች ሃይማኖታዊ ድርጅቶችን ለፖለቲካዊ ዓላማቸው ማስፋፊያ በማድረግ «ሲጠቀሙባቸው» ቆይተዋል። እንደዚሁም፥ ሃይማኖታዊ ቡድኖች ዓላማዎቻቸውን ከግብ ለማድረስ በፖለቲካዊ መዋቅሮች እንደተገለገሉ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረናል። የቤተ ክርስቲያን እና የመንግሥት ጋብቻ የሚያስደስት አይደለም፤ በመሆኑም፥ ከዚህ ጥምረት ውስጥ የሚወጡ ልጆች በአብዛኛው የከፉ ችግሮችን አስከትለዋል። አምባገነን መሪዎች ከሃይማኖት ጋር ወዳጅነት በሚመሠርቱበት ጊዜ፥ በአመዛኙ በሃይማኖቱ ተጽዕኖ ዓላማቸውን ካሳኩ በኋላ፥ በመጨረሻው ሃይማኖትን ለማጥፋት መፈለጋቸውን እንመለከታለን። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት በተለየ አቋም በምትሠራበት ጊዜ ግን፥ በዓለም ከፍተኛ ሚና ስትጫወት ቆይታለች።

በዚህ አጋጣሚ የ«ጋለሞታዪቱ»ን ጥፋት የሚያመለክተውን ገለጻ፥ ከኤልዛቤል አሟሟት ጋር አወዳድር (2ኛ ነገሥት 9፡30-37)።

በመጨረሻም፥ በጌታ የሚታመኑ ሰዎች በ«ጋለሞታዪቱ» እንዳልተሳቡና በነገሥታትም እንዳልተረቱ ልብ በል (ራእይ 17፡14)። እውነተኛ አማኞች «አሸናፊዎች» መሆናቸውን ዮሐንስ በድጋሚ ያመለክታል።

የሰይጣንን የማስመሰል ሃይማኖት ለመገንዘብ መንፈሳዊ ምርመራን የሚጠይቅ ከባድና ረቂቅ ጥናት ማካሄድ ያሻዋል። ጳውሎስ፥ መሠረታዊ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሐሰተኞች ተታልለው ለክርስቶስ ከነበራቸው እምነትና መሰጠት እንዳይወሰዱ ከፍተኛ ሸክም ይሰማው ነበር (2ኛ ቆሮ. 11፡1-4)። በማንኛውም ዘመን ቢሆን፥ ብዙኃኑ ከሚቀበለው «ታዋቂ ሃይማኖት» ጋር የመወገንና የእምነትን መሠረታዊ ነገሮች ችላ የማለት ከፍተኛ ውጥረት ተመስክሯል። ስለዚህ በዚህም በመጨረሻው ዘመን፥ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4 እና 2ኛ ጢሞቴዎስ 3 ውስጥ የተሰጡትን ምክሮች ከልባችን በመቀበል፥ ለጌታችን በእውነተኛነት ልንኖር ይገባል።

የባቢሎን ውድመት (ራእይ 18)

ባቢሎን ጥንታዊት ከተማና ኃያል መንግሥት ብቻ ሳትሆን፥ ዳሩ ግን ሰው በእግዚአብሔር ላይ ላካሄደው ዓመፅ በአርአያነቷ የምትጠቀስ ነች። በራእይ 18፥ ባቢሎን የ«አውሬው»ን የዓለም ዘይቤ፥ በተለይም ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገጽታዎቹን ትወክላለች። እንደዚሁም፥ ዮሐንስ ቢያንስ 8 ጊዜ ያህል ባቢሎንን «ከተማ» ብሎ ይጠራታል (14፡8፤ 17፡18፤ 18፡10፥ 16፥ 18-21)። የብሉይ ኪዳን ትንቢት ከተማዪቱ ራሷ ዳግም እንደማትሠራ የሚናገር ይመስላል (ኢሳ. 13፡19-22፤ ኤር. 51፡24-26፥ 61-64)። አንዳንዶች፥ በተለይም «ጋለሞታዪቱ» እና «አውሬው» በመከራው የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ መተባበር ስለሚጀምሩ፥ ባቢሎንን ከሮም ጋር ያቆራኛሉ። ምናልባት ጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክቱን በሚጽፍበት ጊዜ «ባቢሎን»ን ለሮም «የምሥጢር ስም» አድርጎ ተጠቅሞበት ሊሆን ይችላል (1ኛ ጴጥ. 5፡13)። በመሠረቱ፥ የዮሐንስ አንባቢዎች እነዚህን ስለባቢሎን የተጻፉትን ነገሮች ሲያነቡ፥ ስለ ሮም መንግሥት ማሰባቸው የማይቀር ነው።

ዮሐንስ አራት ድምፆች አራት አስፈላጊ መልእክቶችን ሲያስተላልፍ ይሰማል።

የኩነኔ ድምፅ (18፡1-3) - ይህ አዋጅ በራእይ 14፡8 ውስጥ (አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ጸሐፊዎች 16፡19ንም ይጨምራሉ - እኔ ግን በዚያ ስፍራ የተጠቀሰችውን «ታላቂቱን ከተማ» ኢየሩሳሌምን በማለት ተርጉሜአለሁ) ተጠቁሟል። በዚህ ስፍራ ነቢዩ ኤርምያስ የታሪካዊቷን ባቢሎን መውደቅ ለተመለከተበት በኤርምያስ 51-52፥ ግልጽ ማጣቀሻ ይገኛል። አሁን ግን ዮሐንስ የተመለከተው በ«አውሬው» የተዋቀረችው የዓለም ዘይቤ፥ ማለትም መንፈሳዊቷ ባቢሎን ስትወድም ነው። ይህን አዋጅ የተናገረው መልአክ በምድር ሁሉ ላይ የሚያበራ ታላቅ ሥልጣንና ክብር ስለነበረው፥ ተራ መልአክ አልነበረም። ከሰይጣን የተንኰል መሣሪያዎችና ከክፉ ሰዎች ተቃውሞ ባሻገር፥ «ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለች» (ዕንባ. 2፡14)።

«ወደቀች! ወደቀች!» የሚለው ሐረግ የእወጃውን ክብደት አጉልቶ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ድርብ ፍርድንም ያመለክታል። በራእይ 17 ውስጥ የምትገኘው «ጋለሞታዪቱ»፥ ሃይማኖታዊቷን ባቢሎንና በዚህ በራእይ 18 የተጠቀሰችውን ፖለቲካዊቷን ባቢሎንን ያጣምራል። ይህ አሳብ እግዚአብሔር ባቢሎን ለብዙ ኃጢአቷ «ሁለት እጥፍ» ፍርድ እንደምትቀበል በሚያውጅበት በቁጥር 6 ላይ በጉልህ ተንጸባርቋል።

የበጉ ሙሽራ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መኖሪያ ስትሆን (ኤፌ. 2፡22)፥ በሌላ በኩል፥ ባቢሎን የሰይጣን መኖሪያ ነች (ራእይ 18፡2)። ይህም በጥንታዊቷ ባቢሎን ላይ ከደረሰው ፍርድ ጋር ይዛመዳል (ኢሳ. 13 ከቁጥር 21 ጀምሮ፤ ኤር. 51 ከቁጥር 37 ጀምሮ)። በተጨማሪም፥ ዮሐንስ ከተማዪቱን «የርኩሳንና የሚናቁሩም ወፎች ሁሉ መጠጊያ» በማለት ጠርቷታል (ራእይ 18፡2)። ክርስቶስም ስለዘሪው በተናገረው ምሳሌ፥ ወፎችን የሰይጣን መግለጫዎች አድርጐ አቅርቧል (ማቴ. 13፡31-32)።

ይህ ፍርድ የመጣው የባቢሎን «ዘይቤ» ዓለሙን ሁሉ ስለበከለ ነው። «ጋለሞታዪቱ»ን ለፍርድ እንዳበቃት ምክንያት ሁሉ፥ የእርሷም ኃጢአቷ የ«ዝሙት» ወይም የጣዖት አምልኮ ነው። ዘይቤው በሚሰጣቸው በማናቸውም ብልጽግናዎችና ምቾቶች የዓለም ሕዝቦች ተመርዘዋል። ሥርዓቱም ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን ለሚወዱ ሰዎች (2ኛ ጢሞ. 3፡4) የሚፈልጉትን ሁሉ ያሟላላቸዋል።

በየትኛውም ዘመን የሚኖሩ ክርስቲያኖች የ1ኛ ዮሐንስ 2፡15-17ን ማስጠንቀቂያ ልብ ማለት ያስፈልጋቸዋል። ዓለም በምትሰጣቸው ነገሮች መማረክ ምንኛ ቀላል ነው። መጠነኛ ወይን ጠጅ እንደሚጐነጭ ሰው፥ ቀስ በቀስ ከባድ የመጠጥ ቁራኛ በመሆን፥ ባለማቋረጥ ለመጠጣት የምንፈልግ ሰዎች ሆነን ልንገኝ እንችላለን። ክርስቶስን የሚቃወም የዓለም ዘይቤ ዙሪያችንን ከቦ ስለሚፈታተነን፥ ከእጅ አዙር ተጽዕኖው ልንጠበቅ ይገባል።

የዓለም ዘይቤ «አውሬው»ን እየተከተሉ በጉን የሚጠሉትን የምድር ነዋሪዎች ፍላጐት ያሟላል። ይህም ሆኖ፥ ዓለማዊው ሥርዓት ዘለቄታዊ እርካታ ሊሰጠንም ሆነ ሊያስደስተን አይችልም። የምቾትና የሀብት ፍቅር በመሠረቱ አጋንንታዊ፥ በውጤቱም አጥፊ የሆነ ተዘዋዋሪ የጣዖት አምልኮ ልምምድ ነው።

የመለየት ድምፅ (18፡4-8) - ይህ ምክር ከኤርምያስ 50፡8 እና 51፡6፥ 45 ጋር ይዛምዳል። በዘመናት ሁሉ፥ እውነተኞቹ የእግዚአብሔር ሰዎች ከዓለማዊና ፀረ-እግዚአብሔር ከሆኑት ነገሮች ራሳቸውን መለየት ያስፈልጋቸው ነበር። እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራው፥ ከአገሩ ተለይቶ እንዲወጣ አዘዘው (ዘፍጥ. 12፡1)። እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ ከግብፅ ካወጣ በኋላ፥ ዳግም ተመልሰው እንዳይሄዱ አዘዛቸው። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ፈሪሃ-እግዚአብሔር ካላደረበት ከማናቸውም ነገር ራሷን እንድትለይ ታዛለች (ሮሜ 16፡17-18፤ 2ኛ ቆሮ. 6፡14-7፡1)።

ዮሐንስ የእግዚአብሔር ሰዎች ከክፉው ዘይቤ መለየት ለምን እንደሚያስፈልጋቸው ሁለት ምክንያቶች ሰጥቷል። የመጀመሪያው ብክለትን በማስወገድ፥ በኃጢአቷ እንዳይተባበሩ ነው (ራእይ 18፡4)። «በሌሎችም ኃጢአት አትተባበር» (1ኛ ጢሞ. 5፡22)። የቃሉ ትርጉም «የጋራ ኅብረት ወይም ሽርክና» ማለት ነው። በጌታ መልካም ኅብረት እንዳለ ሁሉ (ፊልጵ. 4፡14)፥ ልናስወግደው የሚገባን ክፉ ኅብረትም አለ (ኤፌ. 5፡11)። እውነተኛ የመንፈስ ኅብረት በአማኞች መካከል የሚገኝ ሲሆን፥ ዳሩ ግን የክርስቶስ ተቃዋሚ ከሆኑ ኃይላት ጋር በመተባበር አቋማችንን ልናላላ አይገባም።

ሁለተኛው ምክንያት የእግዚአብሔር ሰዎች በባቢሎን ላይ ከሚወርዱት አስከፊ መቅሠፍቶች እንዲተርፉ ነው። እግዚአብሔር እያደገ የመጣውን የክፉውን ዘይቤ ኃጢአት ታግሦ ቢቆይም፥ አሁን ቁጣው የሚፈስበት ጊዜ ደርሶ ነበር። ባቢሎን በእርሱ ሕዝብ ላይ በፈጸመችው ግፍ መጠን እግዚአብሔር ብድሯን ይከፍላታል።

እግዚአብሔር የሚፈርድባቸው ግልጽ ኃጢአቶች የትኞቹ ናቸው? ባቢሎን የዓለምን ሕዝቦች ወደ ጣዖት አምልኮ በመሳብ የምትፈጽመውን ክፉ ተጽዕኖ አስቀድመን አይተናል። ሌላው ለፍርድ የሚቀርበው የትዕቢት ኃጢአቷ ነው - «ራስዋን እንዳከበረች . . . » (ራእይ 18፡7)። ራስዋን ከቶውንም ልትወድቅ እንደማትችል ንግሥት አድርጋ ቆጠረች፤ ይህም የውሸት ድፍረትና ትዕቢት በጌታ ዘንድ ምንም ዓይነት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም (ለተዛማጅ አሳብ ኢሳይያስ 47፥ በተለይም ከቁጥር 7-9 ተመልከት)።

ሦስተኛው ኃጢአት የባቢሎን የምቾትና ድሎት አምልኮ ነው። «መቀማጠል» ማለት (18፡7) ሌሎች ሲጐሳቆሉ ሳሉ በምቾትና በቅንጦት ተንደላቆ መኖር ማለት ነው። ይህም ሀብትንና ምቾትን የሕይወት ዋንኛ ዓላማ አድርጐ በመውሰድ፥ ለሌሎች ሰዎች ችግሮች ግድየለሽ መሆን ማለት ነው። ዮሐንስ ይህንን አመለካከት፥ «የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት፥ ስለ ገንዘብም መመካት» በማለት አጠቃሎታል (1ኛ ዮሐ. 2፡16)

የእግዚአብሔር ፍርድ በድንገት ስለሚመጣና ባቢሎን በአንዲት ቀን ስለምትጠፋ፥ የእግዚአብሔር ሰዎች ራሳቸውን ከዚህ ክፉ ዘይቤ ለመለየት መዘግየት የለባቸውም። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ፍርድ የሚፈጸመው «እንደ ብል» ውስጥ ውስጡን በመብላት ሲሆን (ሆሴዕ 5፡12)፥ በሌላ ጊዜ ግን «እንደ አንበሳ» (ሆሴዕ 5፡14) በማግሳት ከመቅጽበት ይደርሳል - መድረሻም ያሳጣል። በአንዲት ቀን፥ ጠቅላላው ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ይንኰታኰታል! ይሁንና፥ ሰማያዊ ዜግነት ያላቸው ሰዎች በዚህ ፍርድ ይደሰታሉ።

የሰቆቃ ድምፅ (18፡9-19) - ይህ ረዥም አንቀጽ፥ ባቢሎን በጢስ ስትዋጥና ሀብታቸው ሁሉ ሲወድም አይተው ነጋዴዎች የሚያሰሙትን የለቅሶ ድምፅ ይገልጻል። በዚህ ስፍራ የቀረበው መግለጫ በበርካታ

መርከቦች የተጐበኙትን ጥንታዊት ሀብታም ከተማ የሚያመለክት ነው። የከተማዪቱ ሀብት ለበርካታ አገሮች የተረፈና ብዙዎችንም በቅጥረኛነት የሚያስተዳድር ነበር። እዚህ ላይ ለባቢሎን ውድቀት ያለቀሱት ነጋዴዎች ብቻ ሳይሆኑ (ቁ. 11)፥ የምድር ነገሥታትም ጭምር እንደሆኑ መረዳቱ አስፈላጊ ነው (ቁ. 9)። ንግድና መንግሥትም በጥቅም ስለተሳሰሩ፥ አንዱን የሚጐዳው ሌላኛውንም ይጐዳዋል።

በዮሐንስ ዘመን የሮም ከተማ ያለጥርጥር የዓለም ንግድና መንግሥት ማዕከል ስትሆን፥ በሀብቷ መትረፍረፍና በምቾቷ ትታወቅ ነበር። በፖለቲካዊም ሆነ በኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፥ በግዛቷ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ በሮም ላይ ጥገኞች ነበሩ። በዛሬው ጊዜ ደግሞ በመንግሥትና በንግድ ዘርፎች መካከል የተወሳሰቡ ግንኙነቶች ከመገኘታቸውም፥ ሥርዓቱ በተዛማጅ የኮምፒውተር ቀልጣፋ አሠራሮች ስለሚታገዝ፥ ለ«ባቢሎን» ውድቀትና ለዓለም የኢኮኖሚ ዘይቤ ውድመት የሚደረገው እንቅስቃሴ ብዙም ጊዜ የሚፈጅ አይሆንም።

በቁጥር 9 ላይ «ዋይ፥ ዋይ እያሉ ያለቅሳሉ» የሚለው በዝምታ እንባ የማዝነብ ተግባር ሳይሆን፥ «ድምፅን ከፍ አድርጐ በመጮህ የሚከናወን ለቅሶ» ነው። በቁጥር 11 ላይ ይኸው ቃል «ማልቀስ» ተብሎ ተተርጉሞአል። ነጋዴዎቹ የሚያለቅሱት ለከተማዪቱ ሳይሆን፥ ጠቃሚ ደንበኞቻቸውን በማጣታቸው ለራሳቸው ሲሉ ነው። እግዚአብሔር ለተቀማጠለውና በሀብት ለተንበሸበሸው ሕይወታቸው ዳርቻ ገድቧልና ሠራተኞቻቸውም ሳይቀሩ ያለቅሳሉ (ቁ. 17-18)።

ዮሐንስ ለእነዚህ ነገሥታት፥ ነጋዴዎችና የመርከብ ባለቤቶች ብልጽግና ካስገኙት ሸቀጣሸቀጦች ጥቂቶቹን ይዘረዝራል። ወርቅ፥ ብር፥ የከበሩ ድንጋዮች ከዝርዝሩ መጀመሪያ ላይ ይገኛሉ። ከዚያም ውድ ልብሶችን (ቁ. 16) እና ከተለያዩ ነገሮች የተሠሩትን ዕቃዎች ይገልጻል። በቁጥር 12 ላይ የተጠቀሰው «መልካም መዓዛ ያለው እንጨት» በሮማውያን ዘንድ ለጌጣጌጥ ማስቀመጫዎችና ለሌሎችም የምቾት ዕቃዎች አገልግሎት ላይ ይውል ነበረና ከፍተኛ ተወዳጅነት ነበረው።

በዚያን ጊዜ፥ ከውጭ አገር የሚገቡ ቅመማ ቅመሞች ለምግብነትና ለሽቶ ማንጠሪያነት ስለሚያገለግሉ፥ በእጅጉ ተፈላጊነት ነበራቸው። ዛሬ ብዙ አገሮች እንደሚያደርጉት ሁሉ፥ የሮም ከተማ ከውጭ አገር በሚገቡ

ምግቦች ላይ ጥገኛ ለመሆን ተገድዳ ነበር። እንዲያውም፥ ትኩስ አትክልቶችንና ሥጋን በየዕለቱ የሚያመጡ ከባድ ተሽከርካሪዎችና ባቡሮች ባይኖሩ ኖሮ፥ በዛሬዎቹ ታላላቅ ከተሞቻችን ረሃብ በነገሠም ነበር።

በዝርዝሩ ላይ በስተመጨረሻው የተጠቀሰውና ፍርሃት የሚያሳድረው፥ «ባሪያዎችም የሰዎችም ነፍሳት» የሚለው አባባል ነው (ቁ. 13)። ከሮም ነዋሪ ሕዝብ አንድ-ሦስተኛ እጅ የሚሆነው በባርነት ሥር እንደነበረ ሲገመት፥ በግዛቷ ውስጥ በሚገኙ ታላላቅ የባሪያ መሸጫ ገበያዎች በየቀኑ 10,000 ሰዎች ያህል በጨረታ የመሸጣቸው ጉዳይ እንግዳ ነገር አልነበረም። በሮም ግዛት፥ እንደ ዕቃ እየተቆጠሩ፥ የተገዙና የተሸጡ፥ ግልጋሎት ያበረከቱና አግባብነት የጐደለው ማንገላታት የደረሰባቸው ምናልባትም ከሃምሳ ሚሊዮን የሚልቁ ሰዎች ነበሩ።

ሆኖም ዮሐንስ በዚህ ራእዩ በመጨረሻው ዘመን የባርነት ንግድም እንደሚኖር እያመለከተ ይሆን? ምናልባትም እንደ ጥንቱ ዓይነት የባርነት ንግድ ላይከናወን ቢችልም፥ ዳሩ ግን ዛሬም ቢሆን በማኅብረሰባችን ውስጥ እያደገ የሚሄድ የነፃነት መገፈፍ እንመለከታለን። ሰዎች በአትሌቲክስ ቡድኖች አማካይነት «የሚገዙና የሚሸጡ» (የሚነገድባቸውም) ሲሆን፥ ታላላቅ ኮርፖሬሽኖቻችንም የባለሥልጣኖቻቸውንና የሠራተኞቻቸውን ሕይወት በይበልጥ ለመቆጣጠር ይፈልጋሉ። ሰዎች በይበልጥ የምቾት ባሪያዎች ሲሆኑና በብዙ ዕዳ ውስጥ ሲዘፈቁ፥ ከእንደዚህ ዓይነቱ «ዘይቤ» መላቀቂያው ያጥራቸዋል።

በ«አውሬው» አገዛዝ ሥር የሚከናወነውን ዓለም-አቀፋዊ ባርነት ለመገንዘብም ብዙ ማሰብ አያሻንም። ለመግዛት ወይም ለመሸጥ በሚፈልግ ሰው ሁሉ ላይ የአውሬው ምልክት እንዲደረግ ግዴታ ከመኖሩም (13፡16-17) ሰውም ሁሉ ለምስሉ እንዲሰግድ እንደሚጠይቅ አስቀድመን ተመልክተናል። የ«ነፃነት» ተስፋ ቢሰጥም፥ ወንዶችንና ሴቶችን በባርነት ይገዛቸዋል (2ኛ ጴጥ. 2፡19)። የሰዎችን የልብ ትርታ በማዳመጥ (ራእይ 18፡14) በዚያው አንጻር በባርነት ሥር ያውላቸዋል።

ምናልባትም በዮሐንስ አእምሮ ውስጥ ሕዝቅኤል በጢሮስ ውድቀት ላይ የተቀኘው ሙሾ ሳይቀረፅ አልቀረም ይሆን ይሆናል (ሕዝ. 27)። አንተም ያንን ክፍል ስታነብ፥ አንዳንድ ተዛምዶዎች ታገኛለህ።

የደስታ ድምፅ (18፡20-24)፥ ከነገሥታቱና ከነጋዴዎቹ ለቅሶና ኃዘን በተቃራኒ፥ በባቢሎን ውድቀት ምክንያት የሰማይ ነዋሪዎች የሚያሰሙት የደስታ ድምፅ ይደመጣል። የእግዚአብሔር ሰዎች ነገሮችን ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር መመልከታቸው ምንኛ አስፈላጊ ነው! እንዲያውም፥ እግዚአብሔር በሰማዕትነት ላለፉት ባሪያዎቹ ብያኔ ስለሚሰጥ፥ በባቢሎን መደምሰስ እንድንደሰት ታዘናል (ራእይ 6፡9-11 ተመልከት)።

«ከእንግዲህ» የሚለውን ተደጋጋሚ ቃል ከልብ በማጤን አስተውል። ኤርምያስ በባቢሎናውያን በኩል በሕዝቡ ላይ ስለሚደርሰው ፍርድ ይሁዳን ሲያስጠነቅቅ በዚሁ ዓይነት አቀራረብ ተጠቅሞ ነበር (ኤር. 25፡8-10)። እንደተባለውም የዚሁ ተመሳሳይ ፍርድ በራስዋ በባቢሎን ላይ ደረሰ! ይህ የባቢሎንን መና መቅረት የሚያመለክተው ገለጻ፥ ማናቸውም ድሎትና ምቾት ሁሉ እንደሚጠፉ ነው። ሙዚቃውም ሆነ ምርቱ፥ ሥራውም ሆነ ሠርጉ፥ ሁሉም ከከፉ ፍጻሜ ላይ ይደርሳል።

ራእይ 18፡24 ከ17፡6 እና ከማቴዎስ 23፡35 ጋር መወዳደር አለበት። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማረድና ለማሳደድ፥ ሃይማኖትንና ንግድን ማሳበቢያ አድርጐ ሲጠቀም ቆይቷል። «አውሬው» ወደ ሥልጣን በሚወጣበት በመጀመሪያው የመከራው አጋማሽ፥ ሃይማኖታዊቱ ባቢሎንና ፖለቲካ - ኢኮኖሚያዊቷ ባቢሎን ጌታንና ሕዝቦቹን በመቃወም ተባብረው ይሠራሉ። በዚህም እግዚአብሔር በግድየለሽነት የሚመለከት ይመስላል፤ በተገቢው ሰዓት ግን፥ ጌታ ለሕዝቡ በመፍረድ «ጋለሞታዪቱ»ንና ታላቂቱን ከተማ ያጠፋቸዋል። እግዚአብሔር ሁልጊዜም ጠላቶቹን ይታገሣል፤ ይህም ሆኖ፥ ሥራውን ከጀመረ ግን በፍጥነትና ሙሉ በሙሉ ከፍጻሜ ያደርሰዋል።

በኃጢአተኞች ላይ ፍርድ መሰጠቱን የሚያበሥረውን ድምፅ መስማታችን እንድንደሰት ይጋብዘናል ብለን ማሰብ የለብንም። ከደኅንነት ርቀው የጠፉት ኃጢአተኞች ለዘላለም ቅጣት የተዳረጉ መሆናቸውን ስለምናውቅ፥ ይህ መለኮታዊ የፍርድ ብያኔ ሁልጊዜም ልባችንን በኃዘን ሊሰብረው ይገባል። በዚህ ክፍል ደስታው የተመሠረተው፥ ፍትሕ በመደረጉና በእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ ላይ ነው። ለመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በቤታቸው ውስጥ ተመቻችተው በመቀመጥ፥ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ መወያየቱ ቀላል ነው። ዳሩ ግን እኔና አንተ ከዮሐንስ ጋር በፍጥሞ

ደሴት ተቀምጠን ቢሆን ኖሮ፥ ወይም ከሚጽፍላቸው የመከራ ማዕበል ቅዱሳን ጋር ብንገኝ፥ ምናልባትም ከዚህ የተለየ አመለካከት ሊኖረን ይችላል። በእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ ትፍስሕት ቢሰማንም፥ ሆኖም ግን በምንም ዓይነት ግላዊ በቀልን ለመወጣት መመኘት አይገባንም (ሮሜ 12፡17-21)።

በዚህ በጥናታችን ነጥብ ላይ፥ የ«አውሬው» ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዘይቤ በመጨረሻው መውደሙን ተመልክተናል። የሚቀረው ነገር ቢኖር፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ መምጣትና «አውሬው»ን እና ሠራዊቱን ፊት ለፊት ተጋፍጦ መርታት ብቻ ነው። ይህንንም ካደረገ በኋላ፥ በምድር ላይ የጽድቅ መንግሥቱን ይመሠርታል።

ይሁንና እኔና አንተ መጠየቅና መመለስ የሚገባን ዋናው ጥያቄ፥ «እኛስ የባቢሎን ዜጎች ነን? ወይስ የመንግሥተ ሰማይ?» የሚለውን ነው።

ለመሆኑ ስምህ በሰማይ የተጻፈ በመሆኑ ልትደሰት ትችላለህ ወይ? ይህ የማይሰማህ ከሆነ፥ አሁኑኑ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን «ከባቢሎን ወጥተህ» ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብነት መቀላቀል አለብህ።

- 11 -

ንጉሡና መንግሥቱ

ራእይ 19-20

«ይህ ሁሉ ከፍጻሜ የሚደርሰው እንዴት ነው?» የሚለው ጥያቄ፥ የሰውን ልጅ ለዘመናት ሲያስጨንቀው የቆየ ጥያቄ ነው። የታሪክ ጠበብት የወደፊቱን ሁኔታ የሚጠቁም አሳብ እንደሚያገኙ ተስፋ በማድረግ፥ ያለፈውን ዘመን ሲያጠኑ ቆይተዋል። ፈላስፋዎች የነገሮችን ትርጉም ለመተንተን ቢጥሩም፥ ዳሩ ግን ቁልፉን ገና ከእጃቸው አላስገቡም። በመሆኑም፥ ነገር-ዓለሙ የተደበላለቀባቸው ሰዎች ወደ ኮከብ ቆጠራና ምትሐታዊ አሠራር ፊታቸውን ቢመልሱ የሚያስደንቅ አይሆንም።

የእግዚአብሔር የትንቢት ቃል «በጨለማ ስፍራ የሚበራን ብርሃን» ይመስል በልባችን ያበራልና (2ኛ ጴጥ. 1፡19)፥ በዚያ ላይ ልንደገፍ እንችላለን። በዚህ በራእይ 19-20፥ ዮሐንስ እግዚአብሔር የሰውን ታሪክ «እስከሚጠቀልል» ድረስ እና አዲሱን ሰማይና ምድር እስከሚዘረጋበት ወቅት፥ የሚፈጸሙትን አምስት ቁልፍ ክስተቶች መዝግቧል።

ሰማይ ሐሤት ያደርጋል (ራእይ 19፡ 1-10)

ባቢሎን በምድር ላይ በወደቀችበት ጊዜ፥ በሰማይ «በእርስዋ ላይ ደስ ይበላችሁ!» (18፡20) የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶ ነበር። በዚህ ክፍል የምናነበው፥ ለዚሁ ትእዛዝ በመንግሥተ ሰማይ የተሰጠውን ምላሽ ነው። «ሃሌሉያ» የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን (በግሪኩ «አሌሉያ»)፥ «ጌታ ይመስገን» ማለት ነው። ይህ የሰማይ «ሃሌሉያ አዝማች» ሲሆን፥ የሚዘመረውም ለሦስት ምክንያቶች ነው። በመጀመሪያ . . .

እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ ፍርድ ሰጥቷል (19፡ 1-4) - የራእይ 17ቷ «ታላቂቱ ጋለሞታ» በመከራው አጋማሽ ላይ በ«አውሬው» እና በተባባሪ ገዢዎቹ ስለተደመሰሰች (17፡ 16)፥ በዚህ ስፍራ የተጠቀሰችው «ታላቂቱ ጋለሞታ» ታላቋ ባቢሎን መሆን አለባት። ራእይ 17፡2ን ከ18፡3 እና 9 ጋር ስናስተያይ፥ ተያያዥነቱ ግልጽ ይሆንልናል። ከሃዲው ሃይማኖታዊ ዘይቤና ሰይጣናዊው ኢኮኖሚያዊ - ፖለቲካዊ ዘይቤ ማለት ሁለቱም፥ ዓለምን ወደ ጥፋት በመምራት የሰውን ልጅ ይበክላሉ።

ሁለቱም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማሳደድና ብዙዎቹን በመግደል በደል ፈጽመዋል።

መዝሙሩ በእግዚአብሔር ባሕርያት ላይ ያተኩራል፤ ይህም እርሱን ለማክበር ትክክለኛው መንገድ ነው። እኛም ልንዘምር የሚገባው እግዚአብሔር «እውነተኛና ጻድቅ» (15፡3፤ 16፡7፤ 17፡6) እንዲሁም በቅዱስ ፍርዶቹ የከበረ በመሆኑ እንጂ፥ በባቢሎን ኃጢአተኛነት ወይም በአወዳደቋ ታላቅነት በመደሰታችን አይደለም። ከራእይ 8፡1-6 እንደተረዳነው፥ የእግዚአብሔር ዙፋንና መሠዊያ ከፍርዶቹ ጋር የተያያዙ ናቸው። ቁጥር 3 ከራእይ 14፡10-11፥ ቁጥር 4 ደግሞ ከራእይ 5፡6-10 ጋር መወዳደር አለበት። ሁለተኛ . . .

እግዚአብሔር በንጉሥነት እየገዛ ነው (19፡5-6) - ቀጥተኛው ትርጉሙ፥ «ሁሉን የሚችል ጌታ አምላካችን መንገሥ ጀምሮአል» የሚል ነው። ይህም ማለት የሰማዩ ዙፋን ባዶ ሆኗል ወይም አይሠራም ማለት አይደለም፤ ጉዳዩ እንዲህ አይደለም። የራእይ መጽሐፍ «የዙፋኑ መጽሐፍ» ሲሆን፥ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር በምድር ላይ ዓላማዎቹን በመፈጸም ላይ ይገኛል። ይህ የምስጋና ድምፅ መዝሙር (97)፡1ን የሚያስተጋባ ማሚቶ ነው - «እግዚአብሔር ነገሠ፤ ምድር ሐሤትን ታድርግ።»

እግዚአብሔር በሰማይ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ሲገዛ ነበር፤ አሁን ግን የሰይጣንንና የ«አውሬው»ን መንግሥት ጨምሮ፥ የምድርን ዙፋናት የሚቆጣጠርበት ጊዜ ደረሰ። በሉዓላዊነቱ፥ ክፉ ሰዎችና መላእክት ከሁሉም የከፉ ተግባራቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ ታግሷል፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደሆነ ሁሉ በምድርም ላይ የሚፈጸምበት ጊዜ ደረሰ። ዮሐንስ በፍጥሞ በነበረ ጊዜ ዶሚቲያን የሮም ንጉሥ ሲሆን፥ ከተሰጡት ማዕረጎች አንዱ «ጌታና አምላክ» የሚል ነበር። እንግዲህ፥ ዮሐንስ በዚህ ምዕራፍ ስድስት የመጀመሪያ ቁጥሮች ውስጥ «ሃሌሉያ» የሚለውን ቃል አራት ጊዜ መጠቀሙ፥ ለአንባቢዎቹ ምንኛ የሰመረ ትርጉም ይሰጣቸው ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ አምልኮና ምስጋና የሚገባው ለያሄዌ አምላክ ብቻ ነው። ሦስተኛ . . .

ሙሽራዪቱ ተዘጋጅታለች (19፡7-10)- በመሠረቱ፥ ሙሽራዪቱ ቤተ ክርስቲያን ነች (ኤፌ. 5፡22-33፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡2)፤ በጉ

ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ሙሽራው ነው (ዮሐ. 3፡29)። በሰርግ ወቅት፥ በሙሽራዪቱ ላይ ማተኮር የተለመደ ነው፤ ሆኖም በዚህ ጊዜ ግን፥ ክብሩን የሚቀበለው ሙሽራው ነው! «ደስ ይበለን፤ ሐሤትም እናድርግ፤ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።»

«ሙሽራዪቱ የለበሰችው ልብስ ምን ነበር?» የሚለው ከሰርግ በኋላ የሚነሣ የተለመደ ጥያቄ ነው። የበጉ ሙሽራ «የቅዱሳንን የጽድቅ ሥራ» ትለብሳለች (ቀጥተኛ ትርጉም)። ሙሽራዪቱ በሰማይ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ስትቀርብ ከቶውንም ውብ አልነበረችም (እንዲያውም፥ ጳውሎስ በኤፌሶን 5፡27 ላይ እንደሚለው፥ በእድፍ፥ በጉድፍና በነቀፋ የተሳበሰች ነች)፤ ዳሩ ግን አሁን በክብር ታበራለች። ለይፋዊ ሥነ-ሥርዓት ራስዋን አዘጋጅታለች።

በዚያን ዘመን የአይሁድ ሰርጎች ከምዕራባውያኑ የጋብቻ ሥርዓቶች የተለዩ ነበሩ። በመጀመሪያ፥ በአብዛኛው ሙሽራውና ሙሽራዪቱ ገና ትናንሽ ልጆች ሳሉ በቤተሰብ የሚከናወን ትጭጭት ነበር። ይህም ትጭጭት መተሳሰር ስለሆነ፥ እንደ ፍች ባለ ሁኔታ ብቻ ሊፈርስ ይችል ነበር። በተጨማሪም በትጭጭት ወቅት የሚፈጸም ማንኛውም ዓይነት የወሲብ ግንኙነት እንደ ዝሙት ይቆጠር ነበር።

ይፋዊ ሥነ-ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ፥ ሙሽራው ወደ ሙሽራዪቱ ቤት በመሄድ የራሱ ያደርጋታል። በመሆኑም ለሰርጉ እራት ወደ ቤት የሚወስዳት ሲሆን፥ እንግዶችም ሁሉ ከደስተኞቹ ሙሽሮች ጋር አብረው ይደሰታሉ። ይህም በዓል ለሳምንት ያህል ጊዜ ሊከበር ይችላል።

ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ለኢየሱስ ክርስቶስ «የታጨች» እንደመሆኗ፥ እኛም እርሱን ባናየውም እንኳን እንወደዋለን (1ኛ ጴጥ. 1፡8)። አንድ ቀን፥ ወደ ምድር ይመለስና ሙሽራዪቱን ወደ ሰማይ ይወስዳታል (ዮሐ. 14፡1-6፤ 1ኛ ተሰ. 4፡13-18)። በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት፥ በሥራዎችዋ ሁሉ ላይ ፍርድ ይሰጥና እድፎችዋና ጉድፎችዋ ሁሉ ይወገዳሉ። ይህ እየተፈጸመ ሳለ፥ በመከራው ዘመን ፍጻሜ ላይ ቤተ ክርስቲያን ከሙሽራዋ ጋር ወደ ምድር ለመመለስ ትዘጋጃለች - ከእርሱ ጋር በክብር ለመግዛት (ሉቃ. 13፡29፤ ማቴ. 8፡11 ተመልከት)። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፥ ጠቅላላው የመንግሥት ዘመን «የጋብቻው እራት ጊዜን» ያህል እንደሚሆን ያምናሉ።

ራእይ 19፡9 በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ሰባት ብፅዕናዎች ውስጥ አራተኛውን ይይዛል (1፡3 ተመልከት) እርግጥ፥ ሙሽራዪቱ ወደዚህ ወደ እራሷ ሰርግ አልተጋበዘችም። ይህ ግብዣ የተደረገው ለእንግዶች፥ ማለትም በብሉይ ኪዳን ዘመን ለነበሩና በመከራው ዘመን ውስጥ ላለፉ አማኞች ነው። በዘላለሙ መንግሥት፥ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ልዩነት አይኖርም። ዳሩ ግን ልዩነት የሚኖረው ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በምትገዛበትና እስራኤል ተስፋ በተገባላት መሢሐዊ በረከቶች በምትደሰትበት በመንግሥቱ ዘመን ወቅት ይሆናል።

ዮሐንስ በዚህ ሁሉ ከመደናገጡም፥ በፍርሃት ስለራደ የሚመራውን መልአክ ለማምለክ ከእግሩ ሥር ይወድቃል (በኋላም ይህንኑ ተግባር ይፈጽማል - 22፡8-9)። በመሠረቱ፥ መላእክትን ማምለክ ስህተት ሲሆን (ቈላ. 2፡18)፥ ዮሐንስም ይህንን ያውቅ ነበር። ስለዚህ በዚህ ልምምዱ ዮሐንስ በስሜት ማዕበል መዋዡቁን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለብን። እንደ ዮሐንስ ሁሉ ይህም መልአክ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና (ዕብ. 1፡14) እኛም አገልጋዮችን ማምለክ አይገባንም (የሐዋ. 10፡25-26 ተመልከት)።

ክርስቶስ ይመለሳል (ራእይ 19፡11-20፡3)

በመጀመሪያ፥ ዮሐንስ ድል-ነሺውን ይገልጽና (ራእይ 19፡11-16) በመቀጠልም ስለድሉቹ ያስነብበናል (19፡17-20፡3)። በነጭ ፈረስ ላይ የተቀመጠው ሐሰተኛው ክርስቶስ ሲሆን (6፡2)፥ ይኼኛው ግን እውነተኛው ክርስቶስ ነው። አመጣጡም በአየር ላይ ሕዝቡን ወደ ቤቱ ለመውሰድ ሳይሆን (1ኛ ተሰ. 4፡13-18)፥ ዳሩ ግን ከሕዝቡ ጋር ጠላቶቹን ለማሸነፍና መንግሥቱን ለመመሥረት ወደ ምድር መመለሱ ነው።

በኢየሱስ ስም ላይ የተደረገውን አጽንኦት ተመልከት (ራእይ 19፡11-13፥ 16)። ታማኝነትን ካጕደለው (ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በማፍረስ) እና ሐሰተኛ ከሆነው (በማታለልና በጣዖት አምልኮ አማካኝነት በመግዛት) ከ«አውሬው» በተቃራኒ፥ እርሱ «ታማኝና እውነተኛ» ነው (3፡14 ተመልከት)። መከራ ለሚቀበሉ ቅዱሳን፥ የተስፋ ቃሎቹ እውነት ስለሆኑ እግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነና እንደማይተላቸው ማስታወስ ይኖርባቸዋል።

ምናልባትም «የምሥጢሩ ስም» (ቁ. 12 ተመልከት) ከ«አዲሱ ስም» ጋር አንድ ዓይነት ሊሆን ይችላል (3፡12)። ይህ ስም ምን እንደሆነ ስለማናውቅ፥ የምንጨምርበት ማብራርያ አይኖርም፤ ዳሩ ግን በሰማይ እንኳ ስለጌታችን አዳዲስ ነገሮችን እንደምንማር ማወቃችን አስደሳች ነው!

«የእግዚአብሔር ቃል» የሚለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለጌታችን ከተሰጡት የተለመዱ ስሞች አንዱ ነው (ዮሐ. 1፡1-14)። አሳባችንንና መሻታችንን በቃላችን አማካኝነት ለሌሎች እንደምናስተላልፍ ሁሉ፥ አብም በልጁ ማለትም ሥጋን ባለበሰው ቃል አማካኝነት ራሱን ለኛ ይገልጻል (14፡7-11)። ቃል ከሆሄያት የተገነባ ሲሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስም «አልፋና ዖሜጋ» ነው (ራእይ 21፡6፤ 22፡13)። እርሱ ለእኛ ለተገለጸው የእግዚአብሔር ራእይ «መለኮታዊ የፊደል ገበታ» ነው።

የእግዚአብሔር ቃል «ሕያውና ኃያል» ሲሆን (ዕብ. 4፡12)፥ የሚልቀው ደግሞ ዓላማዎቹን በምድር ላይ መፈጸሙ ነው (ራእይ 17፡17፤ 6፡11፤ 10፡7፤ 15፡1)። ያህዌ ራሱ፥ «እፈጽመው ዘንድ በቃሌ እተጋለሁ» ይላል (ኤር. 1፡12)። አብ ዓለምን የፈጠረው በቃሉ አማካኝነት ሲሆን (ዮሐ. 1፡1-3)፥ ለፍርድና ለማጠቃለያም በቃሉ ይጠቀማል።

የክርስቶስ እጅግ የላቀው ስም «የነገሥታት ንጉሥ እና የጌቶች ጌታ» የሚለው ነው (ራእይ 19፡16)። ይህም ድል አድራጊ ስሙ ሲሆን (17፡14)፥ እንደ ዳንኤል 2፡47 እና ዘዳግም 10፡17 የመሳሰሉትን ማጣቀሻዎች ያስታውሰናል። ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡15 ላይ፥ ይህንኑ ማዕረግ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስጠት ተጠቅሞበታል። ነገሥታትና ጌቶች ሁሉ ለእርሱ መገዛት ስላለባቸው፥ ማዕረጉ የክርስቶስን ሉዓላዊነት ያመለክታል። በሮም መንግሥት ዙፋን ላይ የተቀመጠው ማንም ይሁን ማን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የዚያ ሰው ንጉሥና ጌታ ነበር።

የክርስቶስ ታላቅነት የታየው በስሞቹ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን ዮሐንስ ስለሚነግረው ስለዚሁ ንጉሥ በሰጠው መግለጫም ጭምር ነው (ራእይ 19፡12-16)። «እንደ እሳት ነበልባል» ያሉት ዓይኖቹ ሁሉንም የሚመለከት መርማሪ ፍርዱን ያሳያል (1፡14)። በርካታ አክሊሎቹ

(ዲያዴሞስ) ከፍተኛ አገዛዙንና ሉዓላዊነቱን ያመለክታሉ። በደም የተረጨው ልብስ ፍርድን የሚያመለክት ሲሆን፥ ምናልባትም ከኢሳይያስ 63፡1-6 እና ራእይ 14፡20 ጋር በመገናዘብ የጠላቶቹን ድል መሆን ያሳያል። ልብሱ ላይ የሚረጨው የጌታችን ደም ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የጠላቶቹ ነው።

ስለታሙ ሰይፍ የእግዚአብሔርን ቃል ያመለክታል (ራእይ 19፡21፤ ዕብ. 4፡12፤ ኤፌ. 6፡17፤ ራእይ 1፡16 ተመልከት)። ይህም ክርስቶስ ጠላቱን «በአፉ መንፈስ» ከሚያጠፋበት ሁኔታ ጋር የሚስማማ ነው (2ኛ ተሰ. 2፡8፤ ኢሳ. 11፡4)። አስቀድመን በምድር ላይ በሚገዛበት ጊዜ በፍትሕ እንደሚያስተዳድር የሚያመለክተውን «የብረት በትር» አይተናል (ራእይ 2፡27፤ 12፡5)። የወይን መጥመቂ ተምሳሌት በአርማጌዶን ከሚፈጸመው ፍርድ ጋር መያያዝ አለበት (14፡14-20)፤ ኢሳ. 63፡1-6 ተመልከት)።

የሰማይ ሠራዊት ከእርሱ ጋር ስለሚሆኑ፥ ኢየሱስ የሚመጣው ብቻውን አይደለም። እነዚህ የሰማይ ሠራዊት እነማናቸው? ያለጥርጥር መላእክት የዚህ ሠራዊት አካል ናቸው (ማቴ. 25፡31፤ 2ኛ ተሰ. 1፡7) - ቅዱሳንም እንዲሁ (1ኛ ተሰ. 3፡13፤ 2ኛ ተሰ. 1፡10)። ይሁዳም ከዚህ ተመሳሳይ የሆነ ትዕይንት ይገልጻል (ይሁዳ 14-15)። ቅዱሳን የሚለው ቃል «የተቀደሱ» ማለት ስለሆነ፥ አማኞችንም ሆነ መላእክትን ሊያመለክት ይችላል።

ክርስቶስ ራሱ ጠላቱን በሦስት ታላላቅ ድሎች ስለሚረታ፥ ሠራዊቱ መዋጋት አያስፈልገውም።

የምድር ነገሥታትን ሠራዊት ድል ያደርጋል (19፡17-19፥ 21)። እነዚህ ተዋጊዎች «በጌታና እርሱ በቀባው ላይ» ለመዋጋት ቢሰባሰቡም (መዝ. 2፡1-3)፥ ዳሩ ግን የጦር መሣሪያዎቻቸው ከንቱ ሆነዋል። ጦርነቱ ወደ እርድ ይለወጥና ለአሞራዎቹ «እራት» ይተርፋል። የራእይ 19 የመጀመሪያው አጋማሽ የበጉን የጋብቻ እራት ሲያቀርብ፥ የመጨረሻ አጋማሽ ስለ «ታላቁ የእግዚአብሔር እራት» ይገልጻል (ሉቃ. 17፡37 ማቴ. 24፡28)።

በዚህ አንቀጽ ውስጥ «ሥጋ» የሚለው ቃል ስድስት ጊዜ ያህል ተጠቅሷል። ዮሐንስ በይበልጥ የሚጠቅሰው በወፎች ስለተበላው የሰዎች

አካል ሲሆን፥ በዚህ ስፍራ የጠለቀ ትርጉም እናገኛለን። ሰው ሥጋ በመሆኑና ብሉም በሥጋ ላይ በመደገፉ ይወድቃል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለወደቀው የሰው ተፈጥሮ የሚናገረው ምንም መልካም ነገር የለውም። ከጥፋት ውኃ በፊት ጌታ የተናገረውን አስታውስ - «መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፥ እርሱ ሥጋ ነውና» (ዘፍጥ. 6፡3)። (እንደዚሁም ዮሐ. 3፡6፤ 6፡63፤ ፊልጵ. 3፡3፤ ሮሜ 7፡18 ተመልከት።) «ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር» ነውና ሊፈረድበት ይገባል (1ኛ ጴጥ. 1፡24)።

ይህ አስቀድሞ እንደተገለጸው (ራእይ 14፡14-20፤ 16፡13-16) በጣም የታወቀው «የአርማጌዶን ጦርነት» ዘገባ ነው። ጌታችን ማድረግ የሚገባው ነገር ቢኖር ቃሉን መናገር ሲሆን፥ «የአፉ ሰይፍ» ጠላቶቹን ይበላቸዋል።

«አውሬው»ን እና ሐሰተኛውን ነቢይ ያሸንፋል (19፡20)። የዓመፁ መሪዎች የሰይጣን «ጀሌዎች» ስለሆኑ፥ እነዚህን ይዞ ማሰሩ ተገቢ ነው። እነዚህም ወደ እሳት ባሕር የሚጣሉ ሲሆን (20፡10፥ 14-15 ተመልከት)፥ ይህም ለኢየሱስ ክርስቶስ ለመገዛት ለማይፈልጉ ሁሉ ዘለቄታዊ የቅጣት ስፍራ ነው። በቀዳሚነት ወደ ገሃነም የሚወርዱት «አውሬው» እና ሐሰተኛው ነቢይ ናቸው። ሰይጣንም ከ1000 ዓመታት በኋላ (20፡10)፥ ስሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ካልተጻፈላቸው ሰዎች ጋር ለመሆን ወደዚያው ያመራል (20፡15)።

ዛሬ አማኝ ያልሆነ ሰው ሲሞት፥ መንፈሱ፥ «የማይታይ ዓለም» የሚል ትርጉም ወዳለው ሲኦል ይሄዳል - ይህም የሙታን መንደር ነው። አማኞች ሲሞቱ ግን ወዲያውኑ ጌታ ወዳለበት ስፍራ ይሄዳሉ (ፊልጵ. 1፡19-23፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡6-8)። በሲኦል ውስጥ የሚገኙ ሙታን ከሰይጣን፥ ከ«አውሬው፥» እና ከሐሰተኛው ነቢይ ጋር ለመሆን ወደ ገሃነም ይወርዱና፥ አንድ ቀን ሲኦል ወናዋን ትቀራለች (ራእይ 20፡13)።

ሰይጣን ድል ይሆናል (20፡1-3) - በቁጥር 1 ላይ የተመለከተው «ጥልቁ» ከሲኦል ጋር አንድ ዓይነት አይደለም፤ ቀደም ብለን የተመለከትነው «ጥልቁ ጉድጓድ» ነው (9፡1-2፥ 11፤ 11፡7፤ 17፡8)። እግዚአብሔር ገና የሚፈጽመው አንድ ተጨማሪ ነገር ስለነበር፥ ሰይጣን ወዲያውኑ ወደ ገሃነም አልገባም። በመሆኑም፥ ሰይጣን ለ1000

ዓመታት በጥልቁ ጉድጓድ ውስጥ ታሰረ። በመጀመሪያ ሰይጣን ከሰማይ ወደ ምድር የተጣለ ሲሆን (12፡9)፥ አሁን ደግሞ ከምድር ወደ ጥልቁ ይጣላል!

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ሰይጣን «የታሰረው» ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በሞተና ወደ ሰማይ ለማረግ ከሞት በተነሣ ጊዜ እንደሆነ ያስባሉ። ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ዋንኛውን ድል የተቀዳጀው በመስቀል ላይ መሆኑ ቢታወቅም፥ በሰይጣን ላይ የተላለፈው የፍርድ ውሳኔ ግን ገና ተግባራዊ አልሆነም ነበር። የተሸነፈ ጠላት ቢሆንም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርን ሰዎች ለማጥቃትና የእግዚአብሔርን ሥራ ለመቃወም አሁንም ነፃነት አለው (1ኛ ጴጥ. 5፡8)። ዶክተር ጄምስ ኤም. ግሬይ እንደሚሉት፥ ዛሬ ሰይጣን እስረኛ ከሆነ የታሰረው ያለጥርጥር በረዥም ሰንሰለት መሆን አለበት። ጳውሎስ በሰይጣን አለመታሰር እርግጠኛ ሲሆን (ኤፌ. 6 ከቁጥር 10 ጀምሮ)፥ ዮሐንስም ከእርሱ ጋር ይስማማል (ራእይ 2፡13፤ 3፡9)።

ጌታ ጠላቶቹን ካስወገደ በኋላ፥ አሁን የጽድቅ መንግሥቱን በምድር ላይ ለመመሥረት በነጻነት ይሠራል።

የቅዱሳን መንገሥ (ራእይ 20፡4-6)

ከቁጥር 1-7 ባለው ውስጥ «ሺህ ዓመት» የሚለው ሐረግ ስድስት ጊዜ ተጠቅሷል። ይህ የጊዜ ገደብ በታሪክ «ሚሌኒየም» ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን፥ በላቲን «ሚል» («ሺህ») እና «አኑም» («ዓመት») ማለት ነው። ይህም ክርስቶስ ለሺህ ዓመታት በምድር የሚነግሥበት መንግሥት ነው። በመጨረሻ፥ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያኑ በምድር ሕዝቦች ላይ ይነግሡና እስራኤልም በነቢያት ተስፋ በተሰጧት በረከቶች ሐሤት ታደርጋለች (ኢሳ. 2፡1-5፤ 4፡1-6፤ 11፡1-9፤ 12፡1-6፤ 30፡18-26፤ 35፡10 ተመልከት)።

ይህ በምድር ላይ የሚመሠረት እውነተኛ መንግሥት ነው ወይስ እነዚህ ቁጥሮች በመንፈሳዊ መልኩ ከዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚዛመዱ ናቸው? አንዳንድ ተርጓሚዎች «ሺህ ዓመታት» የሚለው ሐረግ «የመጠቀ ፍጹምነት»ን ለማሳየት ሲባል (10X10X10 = 1000) ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ ነው ብለው ያምናሉ። እነዚህ ወገኖች፥ አሁን ሰይጣን በመታሰሩና በመሸነፉ ቤተ ክርስቲያን የምትለማመዳቸውን

ድንቅ በረከቶችና የክርስቶስን ድል የሚያመለክት እንደሆነ በአጽንኦት ያሰምሩበታል። የዚህ አመለካከት አራማጆች በ«አሚሌኒያሊዝም» ማለትም በምድር ላይ እውነተኛ መንግሥት አይመሠረትም በሚለው ድምዳሚያቸው ይታወቃሉ።

የዚህ አመለካከት ችግር፥ ዮሐንስ ለምን ይህንኑ ክፍለ-ጊዜ ከሙታን ትንሣኤ ጋር እንዳቀናጀው አለማብራራቱ ነው። እነዚህ ሰዎች እንዴት እንደሞቱም እንኳ ስለሚናገር፥ ያለጥርጥር ስለ «መንፈሳዊ» ትንሣኤ እየተናገረ አልነበረም። እንዲሁም፥ በራእይ 20፡5 ዮሐንስ ስለሌላ ቀጥተኛ ትንሣኤ ጽፏል። ዛሬ የምንኖረው በሺህ ዓመታቱ የድል መንግሥት ውስጥ ከሆነ፥ ይህ ትንሣኤ የተፈጸመው መቼ ነው? ዮሐንስ ስለ ሙታን ሥጋዊ ትንሣኤና በምድር ላይ ስለሚመሠረት መንግሥት የጻፈውን በቀጥታ እንደሚፈጸም አድርጎ መውሰዱ ትክክል ይመስላል።

የሺህ ዓመታቱ መንግሥት ዓላማ ምንድን ነው? በአንድ በኩል፥ እግዚአብሔር ለእስራኤልና ለክርስቶስ የገባቸው የተስፋ ቃሎች የሚፈጸሙበት ነው (መዝ. 2፤ ሉቃ. 1፡30-33)። ጌታችን እነዚህን ለገዛ ሐዋርያቱ በአጽንኦት ነግሯቸዋል (ሉቃ. 22፡29-30)። ይህ መንግሥት ፍጥረት ሁሉ ከኃጢአት ባርነት ነፃ የሚወጣበትና የክርስቶስ ክብር በዓለም-አቀፍ ደረጃ የሚያበራበት ነው (ሮሜ 8፡19-22)። «መንግሥትህ ትምጣ!» ለሚለው የቅዱሳን ጸሎት ምላሽ ይሆናል። በተጨማሪም፥ እግዚአብሔር የኃጢአትን ኃጢአተኛነትና ከእግዚአብሔር ጸጋ በስቲያ የሰውን ልብ ክፋት ለመጨረሻ ጊዜ የሚያሳይበት ነው። በዚህ ላይ ወደ በኋላ ተጨማሪ አሳቦችን እናቀርባለን።

የመከራው ዘመን ሰማዕታት ከሞት ይነሡና ዙፋናትና ሽልማቶች ይሰጧቸዋል። በሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ተምሳሌትነት እንደተመለከተው፥ ቤተ ክርስቲያን የዚህ አገዛዝ ተካፋይ ትሆናለች (ራእይ 5፡10፤ 2፡26-28፤ 3፡12፥ 21፤ 1ኛ ተሰ. 4፡13-18፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡12 ተመልከት)። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የብሉይ ኪዳን አማኞችም የዚህ «የመጀመሪያው ትንሣኤ» አካል እንደሚሆኑ ያምናሉ (ዳን. 12፡1-4)።

«አጠቃላይ ትንሣኤ» የሚል ሐረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም። በአንጻሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ትንሣኤዎች እንዳሉ

ያስተምራል - የመጀመሪያው ወደ በረከት የሚመራው የዳኑት ሰዎች ትንሣኤ ሲሆን፥ ሁለተኛው ወደ ፍርድ የሚመራውና ከደኅንነት ርቀው የጠፉት የሚዳኙበት ነው (በተለይ ዮሐንስ 5፡28-29፤ ዳን. 12፡2 ተመልከት)። እነዚህ ሁለቱ ትንሣኤዎች በ1000 ዓመታት ርዝመት ይለያያሉ።

ራእይ 20፡6 በመጀመሪያው ትንሣኤ የሚነሡ ቅዱሳን የሚጋሩአቸውን በረከቶች ይገልጻል። እነዚህም በረከቶች፥ አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያገኙት ርስት አካል እንጂ፥ በጥረታቸው የሚያገኙአቸው አይደሉም። ይህ በራእይ ውስጥ ከሚገኙ ሰባት «ብፅዕናዎች» ስድስተኛው ሲሆን፥ የመጨረሻው በ22፡7 ላይ ተጠቅሶአል። እነዚህ ከሞት የተነሡት አማኞች እንደ ነገሥታትና ካህናት ከእርሱ ጋር በመንገሥ፥ የክርስቶስን ክቡር ሕይወት ከመጋራታቸውም፥ በ«ሁለተኛው ሞት» የማይጐዱና ከእሳት ባሕር ጋር የማይጋፈጡ ናቸው (20፡14)።

በሺህ ዓመቱ መንግሥት፥ የምድር ነዋሪዎች የከበሩት ቅዱሳን ብቻ ሳይሆኑ፥ ዳሩ ግን ለኢየሱስ ክርስቶስ በመገዛት የሚሰግዱ የዓለም ሕዝቦችም ጭምር ናቸው (ማቴ. 25፡31-40፤ 8፡11 ተመልከት)። በምድር ላይ ከሚታየው ፍጹም ሁኔታ የተነሣ፥ ሰዎች ረዥም ዘመን ይኖራሉ (ኢሳ. 65፡17-25፥ በተለይም ቁጥር 20)። ጋብቻ በመፈጸም በውጫዊ ሁኔታቸው ለጌታችን የጽድቅ አገዛዝ የሚገዙትን ልጆች ይወልዳሉ። ይሁንና የሺህ ዓመቱ ዘመን እየገፋ ሲሄድ ሁላቸውም እውነተኛ የዳግም ልደት ሕይወት ሳይታይባቸው ይቀራል፤ ይህም በሺህ ዓመቱ መንግሥት መጨረሻ ላይ እንደምን ሰይጣን ታላቅ የዓመፅ ሠራዊት ለማሰባሰብ እንደሚችል ያስረዳል (ራእይ 20፡8)።

ለብዙ መቶ ዓመታት ያህል ፈላስፋዎች፥ የሰው ዘር ከጦርነት፥ ከበሽታ፥ ብሎም ከሞት ነፃ ሆኖ ስለሚኖርበት «ወርቃማ ዘመን፥» «ዩቶጵያ» ሲያልሙ ኖረዋል። ሰዎች ይህን ግብ ለመጨበጥ ጥረው አልተሳካላቸውም። ይሁንና ይህ ዓይነቱ መንግሥት የሚመሠረተውና ምድር ከሰይጣንና ከኃጢአት ጭቆና የምትጸዳው፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በዳዊት ዙፋን ላይ ተቀምጦ ሲገዛ ብቻ ነው።

የሰይጣን ዓመፅ (ራእይ 20፡7-10)

በሺህ ዓመቱ መንግሥት መገባደጃ ላይ ሰይጣን ከጥልቁ ይፈታና በጌታ ላይ አንድ የመጨረሻ ዓመፅ እንዲፈጽም ይፈቀድለታል። ሆኖም ግን ለምን? ምክንያቱም የሰው ልብ እጅግ ክፉ እንደሆነና በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ሊለወጥ እንደሚችል ለመጨረሻ ጊዜ ለማረጋገጥ ነው። እስቲ የዚህን ዓመፅ አሳዛኝ ሁኔታ ከልብ በማስተዋል አስብበት። በእግዚአብሔር ልጅ ፍጹም መንግሥት፥ ፍጹም ተስማሚ በሆነ የአገዛዝ ጥላ ሥር የሚኖሩ ሰዎች፥ በመጨረሻ ላይ እውነትን ይቀበሉና በንጉሡ ላይ ያምፃሉ! ታዛዥነታቸውም ለማስመሰል ያህል እንጂ፥ ከቶውንም በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ከሚኖር እውነተኛ እምነት የመነጨ አልነበረም።

የ«ጎግና ማጎግ» መጠቀስ (ቁ. 8) ይህንን ጦርነት በሕዝቅኤል 38-39 ከተጠቀሰው ጋር አንድ አያደርገውም - በሕዝቅኤል የተጠቀሰው ሠራዊት ወረራውን የሚያካሂደው ከሰሜን ሲሆን፥ ይኼኛው ግን ከአራቱም የምድር ማዕዘናት ስለሆነ ነው። ይህም ሆኖ፥ በሁለቱም ጦርነቶች እምብርቷ እስራኤል ስለሆነች፥ እነዚህ ሁለቱም ክስተቶች ተዛማጅነት አላቸው። በዚህ ጦርነት፥ ኢየሩሳሌም [«የተወደደችው ከተማ» መዝ. (78)፡68፤ 87፡2] የማንጣጠርያ ስፍራ ትሆናለች። እግዚአብሔር በዚህ ዓመፅ ላይ በጣም ፈጣንና አጥጋቢ እርምጃ በመውሰድ፥ ሰይጣንን ወደ ገሃነም ይጥለዋል። ከዚህ በተጨማሪም ከሺህ ዓመቱ መንግሥት በኋላ እንኳን «አውሬው» እና ሐሰተኛው ነቢይ በእሳት ባሕር መሰቃየታቸው እንደሚቀጥል ልብ በል! (ማቴ. 25፡41 ተመልከት)።

በሌላም በኩል ይህ የሺህ ዓመቱ መንግሥት፥ እግዚአብሔር ስለ ሰው ልብ በተለያዩ የታሪክ ክፍለ-ጊዜያት የተናገረው ነገር ሁሉ «የሚጠቃለልበት» ነው። ዘመኑ የሕግ አገዛዝ ዘመን ቢሆንም፥ ዳሩ ግን ሕግ የሰውን በኃጢአት የተበከለ ልብ አይለውጥም። በመሆኑም፥ አሁንም ሰው በእግዚአብሔር ላይ ማመፁን ይቀጥላል። የሺህ ዓመቱ መንግሥት አለመታዘዝ በአግባቡ በፍትሕ የሚዳኝበት የሰላምና የፍጹም ድባብ ክፍለ-ጊዜ ነው፤ ይህም ሆኖ በመጨረሻው የንጉሡ ተገዢዎች ሰይጣንን በመከተል በጌታ ላይ ያምፃሉ። የአካባቢው ሰላም መሆን ለልብ መረጋጋት ዋስትና አይሰጥም።

እግዚአብሔርም የሰውን ታሪክ ሊጠቀልል ተቃርቧል። ይሁንና፥ አንድ ታላቅ ክስተት ይቀራል።

ኃጢአተኞች የእጃቸውን ያገኛሉ (ራእይ 20፡11-15)

በሁለተኛው ትንሣኤ፥ ደኅንነትን ያላገኙ ሰዎች ከሞት ተነሥተው በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት ይቆማሉ። ይህ የነጭ ዙፋን ፍርድ፥ የአማኞች ሥራዎች ከሚፈረዱበትና ሽልማቶች ከሚሰጡበት የክርስቶስ የፍርድ ወንበር ጋር ሊምታታብህ አይገባም። በዚህ የፍርድ ዙፋን ፊት የሚቀርቡት ያላመኑ ሰዎች ብቻ ሲሆኑ፥ ሽልማትም አይኖርም። ዮሐንስ በዚህ ስፍራ በፍርሃት የሚያርድ ትዕይንት ያቀርባል። ሰማይና ምድር ከፈራጁ ፊት ስለሚሸሹ፥ ኃጢአተኞች የሚሸሸጉበትን ስፍራ አያገኙም። ሁሉም ፈራጁን ፊት ለፊት መጋፈጥ አለበት።

አብ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ስለሰጠው፥ ፈራጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ዮሐ. 5፡22-30፤ ማቴ. 19፡28፤ የሐዋ. 17፡31)። እነዚህ ከደኅንነት ርቀው የጠፉት ኃጢአተኞች በሕይወት ሳሉ ክርስቶስን ስላልተቀበሉ፥ አሁን በዚህ በጠሉት ጌታ ተፈርዶባቸው ለዘላለማዊ ሞት መዳረግ ይኖርባቸዋል።

እነዚህ «ሙታን» የሚመጡት ከየት ነው? ሞት ሰውነታቸውን የሚሰጥ ሲሆን፥ (የሙታን መናፍስት መኖሪያ የሆነው) ሲኦል መንፈሳቸውን ይሰጣል። ከባሕርም ውስጥ ቢሆን ሙታን ይነሣሉ። ማንም ኃጢአተኛ ከፍርዱ አያመልጥም።

ኢየሱስ ክርስቶስ በእነዚህ ባልዳኑት ሰዎች ላይ የሚፈርደው «በመጻሕፍቱ ውስጥ» በተጻፈው መሠረት ነው። የምን መጻሕፍት? ለሁሉም መጻሕፍት ምንጭ የሆነው አንዱ የእግዚአብሔር ቃል ራሱ በፍርዱ ወቅት ለመመስከር መገኘቱ ነው። «እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል» (ዮሐ. 12፡48)። ማንኛውም ኃጢአተኛ በሕይወቱ ሳለ ለሰማው እውነት ተጠያቂ ይሆናል።

ምንም እንኳ አንድ ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የሚያበቃ መልካም ሥራ ሊሠራ ባይችልም፥ የሚፈረድባቸውን ኃጢአተኞች ሥራዎች የያዘም መጽሐፍ ይቀርባል (ኤፌ. 2፡8-9፤ ቲቶ 3፡5)። ታዲያ ይህ ከሆነ ዘንዳ፥ ኢየሱስ በነጩ ዙፋን ፊት የተከለከሉትን ሰዎች ሥራዎች መልካምነትና ክፋት የሚቆጣጠረው ለምንድን ነው? በገሃነም የሚሠቃዩበትን የቅጣት ልክ ለመወሰን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን በግል የመካዳቸው እውነታ አስቀድሞ ፍጻሜያቸውን በመወሰኑ፥ እነዚህ ሰዎች

ሁሉ ወደ ገሃነም ይጣላሉ። ይህም ሆኖ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ዳኛ በመሆኑ፥ ለእያንዳንዱ ኃጢአተኛ ተገቢውን ስፍራ ይመድብለታል።

በገሃነም የቅጣት ደረጃዎች ይኖራሉ (ማቴ. 11:20-24)። እያንዳንዱ ከደኅንነት ርቆ የጠፋ ኃጢአተኛ ተገቢውን ቅጣት የሚቀበል ሲሆን፥ ማንኛውም ቢሆን ከጌታ ጋር ሊከራከር ወይም በውሳኔው ላይ ይግባኝ ሊጠይቅ አይችልም። እግዚአብሔር የኃጢአተኞችን ሥራዎች ስለሚያውቅ፥ መጻሕፍቱ እውነቱን ይገልጻሉ።

ከዚህ በተጨማሪም በዚያ የዳኑትን የእግዚአብሔርን ሰዎች ስሞች የሚያካትት «የሕይወት መጽሐፍ» ይኖራል (ፊልጵ. 4:3፤ ራእይ 21:27፤ 13:8፤ 17:8)። ከእውነተኛ አማኞች በቀር የማንኛውም ያልዳነ ሰው ስም በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ አይመዘገብም (ሉቃ. 10:20)።

ፍርዱ በተፈጸመ ጊዜ፥ ከደኅንነት ርቀው የጠፉት ሁሉ ሁለተኛው ሞት ወደሆነው፥ የእሳት ባሕር፥ ወደ ገሃነም ይጣላሉ። ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የገሃነም ትምህርት «ክርስቲያናዊ አይደለም» በማለት ቢቃወሙም፥ ኢየሱስ ግን እውነትነቱን በግልጽ አስተምሮአል (ማቴ. 18:8፤ 23:15፥ 33፤ 25:46፤ ማር. 9:46)። ስሜታዊ የስብእና ሃይማኖት አምላክ ሁሉንም ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚያስገባና ማንንም ወደ ገሃነም እንደማይልክ ስለሚያስተምር፥ በዚህ የተሳሳተ አቋሙ የፍርድን እውነተኛነት የመጋፈጥ ዓቅም የለውም።

ገሃነም ለእግዚአብሔር የጽድቅ ባሕርይ ምስክር ነው። በኃጢአት ላይ መፍረድ አለበት። በተጨማሪም፥ ገሃነም ሰው «ሮቦት» ወይም ምንም ሊያደርግ የማይችል የግፍ ገፈት ቀማሽ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የወደደውን ለመምረጥ የሚችል ፍጥረት የመሆኑን እውነታ በማሳየት፥ ከዚህ አንጻር ለሰውም ኃላፊነት ምስክር ነው። እግዚአብሔር «ሰዎችን ወደ ገሃነም አይልካቸውም-» አዳኙን እምቢ በማለት ራሳቸው ራሳቸውን ይልካሉ እንጂ! (ዮሐ. 3:16-21፤ ማቴ. 25:41)። ገሃነም ለኃጢአትም አስከፊነት ምስክር ነው። እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚያይ ሁሉ፥ እኛም የኃጢአትን አስከፊነት ለአንድ ጊዜ እንኳን ተገንዝበነው ቢሆን ኖሮ፥ ለምን እንደ ገሃነም ያለ ስፍራ ሊኖር አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት በተረዳነው ነበር።

በጎልጎታ ከተሰጠው ዕድል አንጻር፥ ማንም ኃጢአተኛ እግዚአብሔርን ወደ ገሃነም አወረድከኝ ብሎ ሊኰንነው አይገባም። እግዚአብሔር ኃጢአተኞች በንስሐ እንዲመለሱ በትዕግሥት በመጠባበቅ፥ የማምለጫ መንገድ አዘጋጅቷል። በመሆኑም፥ እግዚአብሔር መመዘኛዎቹን ዝቅ አያደርጋቸውም - ወይም መስፈርቶቹን አይለውጣቸውም። ብቸኛው የደኅንነት መንገድ በልጁ ማመን ስለመሆኑ አንዴ ደንግጎአል።

የነጩ ዙፋን ፍርድ በምንም መልኩ የዘመናችንን ፍርድ ቤቶች አይመስልም። በነጩ ዙፋን ፍርድ ላይ ዳኛ እንጂ ጠበቃ አይኖርም፤ ከስ እንጂ መከላከያ አይቀርብም፤ ለፍርዱም ይግባኝ አይጠየቅም። ማንም ሰው ራሱን ለመከላከል ወይም እግዚአብሔርን በጽድቅ ጉድለት ሊከስ አይችልም። ምንኛ የሚያስፈራ ትዕይንት ይሆን ይሆን!

እግዚአብሔር አዲስ ምድርና ሰማይት ከማምጣቱ በፊት፥ በመጨረሻው ኃጢአትን ማስወገድ አለበት፤ ይህንንም በታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ያከናውነዋል።

በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከዚህ አስከፊ ፍርድ ልታመልጥ ትችላለህ። በዚህም፥ ከቶውንም የሁለተኛው ትንሣኤ አካል ከመሆን፥ ወይም ከዘግናኙና ወደ እሳት ባሕር በመጣል ከሚደመደመው የሁለተኛው ሞት ተሳታፊ ከመሆን ትተርፋለህ።

ኢየሱስ «ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም» ብሏል (ዮሐ. 5፡24)።

አንተስ በእርሱ በማመን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግረሃል?

- 12 -

ሁሉም ነገር ሲታደስ!

ራእይ 21-22

የሰው ልጅ ታሪክ በአትክልት ስፍራ ተጀምሮ የአትክልት ገነት በምትመስለው ከተማ ይፈጸማል። በሐዋርያው ዮሐንስ ዘመን፥ ሮም የተደነቀች ከተማ ነበረች፤ ይሁንና እግዚአብሔር ከጋለሞታ ጋር ያወዳድራታል። «በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነውና» (ሉቃ. 16፡15)። ዘላለማዊቷ የእግዚአብሔር ከተማ ግን፥ ለተወደዱ የእግዚአብሔር ልጆች ዘላለማዊ ስፍራ በመሆኗ፥ ከውብ ሙሽራ ጋር ተወዳድራለች (ራእይ 21፡9)።

በራእይ 21፡5-6 የተጠቀሱት የእግዚአብሔር አባባሎች እነዚህን ሁለት የመጨረሻ ምዕራፎች በተስማሚ ሁኔታ ያጠቃልሉታል። «እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ ... ተፈጽሞአል!»። ቀጣዩም ማጠቃለያ እንደሚያመለክተው፥ በዘፍጥረት የተጀመረው ነገር በራእይ ወደ ፍጻሜ ደርሷል፡-

ዘፍጥረት	ራእይ
ሰማያትና ምድር ተፈጠሩ ፥ 1፡1	አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፥ 21፡1
ፀሐይ ተፈጠረች ፥ 1፡16	ፀሐይ አታስፈልግም፥ 21፡23
ሌሊት ተፈጠረ ፥ 1፡5	ሌሊት አይኖርም፥ 22፡5
ባሕሮች ተፈጠሩ ፥ 1፡10	ባሕር አይኖርም፥ 21፡1
እርግማን ታወጀ ፥ 3፡14-17	እርግማን አይኖርም፥ 22፡3
ሞት በታሪክ ውስጥ ተከሰተ፥ 3፡19	ሞት አይኖርም፥ 21፡4
ሰው ከሕይወት ዛፍ ተባረረ ፥ 3፡24	ሰው ወደ ገነት ይመለሳል - 22፡14
ኃዘንና ሥቃይ ተጀመረ፥ 3፡17	ኃዘንም ሆነ እንባ አይኖርም 21፡4

የከተማዪቱ ዜጎች (ራእይ 21፡ 1-8)

ዮሐንስ የከተማዪቱን ዜጎች በተመለከተ፥ ሦስት ገለጻዎችን አስቀምጦልናል። በመጀመሪያ ...

የእግዚአብሔር ሕዝቦች ናቸው (21፡ 1-5) - የመጀመሪያዎቹ ሰማይና ምድር የተፈጠሩት ለመጀመሪያው ወንድና ለመጀመሪያዪቱ ሴት፥ ብሎም ለትውልዶቻቸው ነበር። እግዚአብሔር በዔድን ገነት ውስጥ ሲያስቀምጣቸው የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አሟልቶላቸው ነበር። የሚያሳዝነው፥ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ኃጢአት በመሥራት ሞትንና ውድመትን ወደ እግዚአብሔር ውብ ዓለም አስገቡ። ፍጥረት በእስራትና በጥፋት ውስጥ የሚገኘ በመሆኑ (ሮሜ 8፡ 18-23)፥ «ሰማያት እንኳ በፊቱ ንጹሐን አይደሉም» (ኢዮብ 15፡ 15)።

እግዚአብሔር ለሕዝብ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚሰጥ የተስፋ ቃል ገብቷል (ኢሳ. 65፡ 17፤ 66፡ 22)። እግዚአብሔር እንዲከብር ከተፈለገ አሮጌው ፍጥረት ለአዲሱ ፍጥረት ቦታ መልቀቅ አለበት። ኢየሱስ ይህንን ክስተት «ዳግመኛ ልደት» በማለት የጠራው ሲሆን (ማቴ. 19፡ 28)፥ ጴጥሮስም በእሳት ማንጻትና ማደስ እንደሆነ አድርጎ ይገልጸዋል (2ኛ ጴጥ. 3፡ 10-13)። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች አሮጌው ይታደስ እንደሆነ፥ ወይም አሮጌው ጠፍቶ ሙሉ በሙሉ በአዲስ ፍጥረት ይተካ እንደሆነ በሚኖራቸው አመለካከት አይስማሙም። «አዲስ» ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል «አዲስ ባሕርይ ያለው» የሚል በመሆኑ (ራእይ 21፡ 1፥ 5)፥ ለመጀመሪያው ገለጻ ድጋፍ ሳይሰጥ አይቀርም።

«ባሕርም ወደፊት የለም» የሚለው «ውኃ አይኖርም» ማለት አይደለም። ውኃን በተመለከተ፥ አዲስቱ ምድር የተለየ ይዘት ይኖራታል ማለት ነው። የዓለማችን ሦስት - አራተኛው እጅ ውኃ ሲሆን፥ በዘላለሙ መንግሥት ግን እንዲህ አይሆንም። በዮሐንስ ዘመን፥ ባሕር ማለት አደጋ፥ ማዕበልና መለየት (በጊዜው ዮሐንስ ራሱ በደሴት ውስጥ ነበር) ማለት ስለሆነ፥ ምናልባትም ገለጻው ከመልከዓ-ምድራዊ አባባል የጠለቀም ትርጉም ይኖረው ይሆናል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ ባሻገር፥ ዘላለማዊቱ ከተማ ምን ዓይነት እንደምትሆን መገመቱ አዳጋች ነው። ዮሐንስ የከተማዋን ውበት በማድነቅ

የተቀደሰች (21፡27)፥ የተዘጋጀች (ዮሐ. 14፡1-6)፥ እና ለሰርጓ አጊጣና ለብሳ እንዳሸበረቀች ያማረች ሙሽራ አድርጐ ይገልጻታል። በተጨማሪም በራእይ 21-22 እነዚህኑ ባሕርያት ይበልጥ ያጐላቸዋል።

ስለከተማዪቱ ከተሰጠው ገለጻ ሁሉ የሚልቀው ግን እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በዚያ መኖሩ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የመኖሪያ ስፍራ ግሩም ዘገባ ያቀርባል። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ከሰው ጋር በዔድን ገነት ይመላለስ ነበር። ከዚያም ከእስራኤል ጋር በመገናኛ ድንኳኑና በኋላም በቤተ መቅደስ ውስጥ ኖሯል። እስራኤል ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ከእነዚያ የመኖሪያ ስፍራዎች መለየት ያስፈልገው ነበር። በኋላም፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በመምጣት በመካከላችን «አደረ» (ዮሐ. 1፡14)። ዛሬ እግዚአብሔር በሕዝቡ አካል (1ኛ ቆሮ. 6፡10-20) እና በቤተ ክርስቲያን (ኤፌ. 2፡21-22) ውስጥ እንጂ፥ በሰው ሠራሽ መቅደሶች ውስጥ አይኖርም (የሐዋ. 7፡48-50)።

በመገናኛ ድንኳንም ሆነ በቤተ መቅደስ ውስጥ፥ መጋረጃው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ቆሞ ይጋርዳል። ያ መጋረጃ ኢየሱስ በሞተ ጊዜ ለሁለት በመቀደዱ፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ «አዲስና ሕያው መንገድ» አበጀ (ዕብ. 10 ከቁጥር 19 ጀምሮ)። ዛሬ እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካኝነት በአማኞች ውስጥ ቢያድርም እንኳ ገና የምንፈልገውን ያህል እግዚአብሔርን ልንረዳው ወይም ከእርሱ ጋር ኅብረት ልናደርግ አልጀመርንም። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር ባለበት ስፍራ ሆነን ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንደሰታለን።

ዘላለማዊቷ ከተማ እጅግ ግሩም ስለሆነች፥ ዮሐንስ እርሷን ለመግለጽ ከሁሉም በላይ ሆኖ ያገኘው በንጽጽር መጠቀሙን ነው - «ከዚህ የበለጠ አይኖርም።» ይህንን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያለበትን መጽሐፍ በመጀመሪያ ያነበቡ አማኞች፥ አብዛኛዎቻቸው ይሠቃዩና ይታረዱ ስለነበር፥ በሰማይ ሥቃይ፥ እንባ፥ ኃዘን፥ ወይም ሞት አለመኖሩን በማወቃቸው መደሰታቸው አያጠራጥርም። በዘመናት ሁሉ፥ የመንግሥት ሰማይ ተስፋ የእግዚአብሔርን ሰዎች ሲያበረታታ ኖሯል። ሁለተኛ . . .

የሰማይ ዜጐች የረኩ ሕዝቦች ናቸው (21፡6)- በዘመናዊ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ስለ ውኃ ብዙም አይጨነቁም፤ ዳሩ ግን በዮሐንስ ዘመን ይኼ ዋንኛ ችግር ነበር። ዮሐንስ ራሱ በሮም የማዕድን ማውጫ ስፍራዎች ውስጥ ሲሠራ የጥማትን ምንነት እንደተረዳ አይጠረጠርም። በዘመናት

ሁሉ የተሠቃዩ ቅዱሳን ከጌታ የተሰጣቸውን ይህንን ግሩም የተስፋ ቃል በመረዳት ይጠባበቁ ነበር። ደግሞም ለሁሉም የሚሆን፥ የነጻና የተትረፈረፈው ይህ ውኃ ሕያው ውኃ ነው! ሦስተኛ ...

እነዚህ ሰማያዊ ዜጎች አሸናፊ ሕዝብ ናቸው (21፡7-8)። «ድል የሚነሣ» የሚለው በዚህ መጽሐፍ ቁልፍ ሐረግ ነው (2፡7፥ 11፥ 17፥ 26፤ 3፡5፥ 12፥ 21፤ እንዲሁም 12፡11 ተመልከት)። ዮሐንስ በመጀመሪያ መልእክቱ እንዳመለከተው፥ እውነተኛ አማኞች ሁሉ አሸናፊዎች ስለሆኑ (1ኛ ዮሐ. 5፡4-5)፥ ይህ የተስፋ ቃል የተሰጠው «ለመንፈሳዊ ምርጦች» ብቻ አይደለም። ምክንያቱም እኛም የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን፥ ሁሉንም ነገር እንወርሳለን።

በ1871 ዓ.ም. በሺካጎ ከተነሣው ታላቅ እሳት በኋላ፥ ወንጌላዊ ድዋይት ኤል. ሙዲ የቤታቸውን ውድመት ለመመልከት ወደዚያው አምርተው ነበር። ታዲያ አንድ ወዳጃቸው ወደእርሳቸው ጠጋ በማለት፥ «ሁሉም ነገር በእሳት እንደወደመብህ ሰማሁኝ» አላቸው።

ሙዲም፥ «አይ! ነገሩን እንኳን በትክክል አልተረዳኸውም። በእሳት ከጠፋብኝ ይበልጥ የትትረፈረፈ ሀብት ቀርቶልኛል» አሉት።

ጠያቂውም፥ «ምን ማለትህ ነው? ይህን ያህል ሀብታም መሆንህን አላውቅም ነበር» አላቸው።

ሙዲም መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ገለጥ አድርገው ራእይ 21፡7ን አነበቡለት - «ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ።»

ከአሸናፊዎቹ በተቃራኒ፥ ቁጥር 8 በኃጢአት የተሸነፉትንና ጌታን የማያምኑትን ሰዎች ያቀርባል። ፍጻሜያቸው ምን ይሆን? የእሳት ባሕር! ዓለም ክርስቲያኖችን ሁሉንም እንዳጡ «ከሳሪዎች» አድርጐ ይመለከታል፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፥ ከሳሪዎቹ የማያምኑ ሰዎች ናቸው።

ፈሪዎች የተባሉት ለክርስቶስ የመቆም ድፍረት የሌላቸው ሰዎች ናቸው (ማቴ. 10፡32-33 ተመልከት)። «ርኩሳን» ማለት «የተበከለ» የሚል ፍች ሲኖረው፥ በኃጢአት ውስጥ በመዘፈቃቸው በአእምሮ፥ በመንፈስና በአካል የተበከሉትን ሰዎች ያመለክታል (2ኛ ቆሮ. 7፡1)። በራእይ 21፡8 ላይ የተጠቀሱት ሌሎች ባሕርያት ሁሉ ለ«አውሬው»

ተከታዮች እንደሚስማሙ ከመግለጽ በቀር፥ ልዩ ማብራርያ አያስፈልጋቸውም (17፡4፥ 6፤ 18፡3፥ 9፤ 19፡2 ተመልከት)።

የከተማዪቱ ባሕርይ (ራእይ 21፡9-22፡5)

ዘላለማዊቱ ከተማ የሙሽራዪቱ መኖሪያ ብቻ ሳትሆን፥ ራሷም ሙሽራ ነች። ከተማዪቱም የምትታወቀው በሕንፃዎችዋ ብዛትና ግዝፈት ሳይሆን፥ በሚኖሩባት ሕዝቦች ብቃት ነው። ዮሐንስ የተመለከታት ከተማ ቅድስትና ሰማያዊት ነበረች፤ እንዲያውም፥ ወደምድር የወረደችው ከተዘጋጀችበት ከሰማይ ነው። በርካታ ተምሳሌቶች እንደተካተቱባት ብንረዳም እንኳ፥ የዮሐንስ ገለጻ እንድንደነቅ ያደርገናል። ሰማይ እውነተኛ የውበትና የክብር ስፍራ ሲሆን፥ ለበጉ ሙሽራም ፍጹም የሆነ የመኖሪያ ቤት ነው።

«የእግዚአብሔር ክብር» በታሪክ ሁሉ በተለያዩ ስፍራዎች እንደታየ አስቀድመን አይተናል። የእግዚአብሔር ክብር በመገናኛ ድንኳንና በኋላም በቤተ መቅደስ ውስጥ ያደረ ሲሆን፥ ዛሬ ደግሞ በአማኞቹና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያድራል። ለዘላለሙ የእግዚአብሔር ክብር በቅድስት ከተማ ውስጥ የሚታይ ሲሆን፥ ከተማዪቱም የምትሻው ይህንኑ የክብር ብርሃን ብቻ ነው።

የከተማዪቱ ገለጻ የዮሐንስ አንባቢዎች የሚያውቋቸውን የከተሞች ግንባታ መንገድ - ማለትም መሠረቶች፥ ግድግዳዎችና በሮችን የተከተለ ነው። «መጻተኞችና እንግዶች» ከሚኖሩባቸው ድንኳኖች በተቃራኒ (ዕብ. 11፡8-10)፥ የዚህች ከተማ መሠረቶች ዘለቄታነት አላቸው። ግድግዳዎችና በሮቹ ሁሉ፥ ስለ አስተማማኝ ጥበቃ የሚናገሩ ናቸው። በበሮች አካባቢ የሚገኙ መላእክት እንደ ጠባቂ ወታደሮች ስለሚሠሩ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማንኛውንም ጠላት መፍራት አያስፈልገውም።

በዚህች ከተማ፥ የአሮጌና አዲስ ኪዳን ቅዱሳን ይሰባሰባሉ። አሥራ ሁለቱ በሮች የአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ስሞች የተጻፉባቸው ሲሆኑ፥ አሥራ ሁለቱ መሠረቶች የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስሞች የሚገኙባቸው ናቸው (ኤፌ. 2፡20 ተመልከት)። በመሠረቱ፥ የሌዊን ነገድ ጨምሮ አሥራ ሦስት ነገዶች ሲኖሩ፥ እንደዚሁም ጳውሎስን ጨምሮ አሥራ ሦስት ሐዋርያት ነበሩ። ዮሐንስ በራእይ 7 ነገዶችን ሲዘረዝር፥ የዳንና የኤፍሬም ነገዶች አልተጠቀሱም ነበር፤ ይህም ምናልባት ነገሮችን በጣም በቀጥታ እንዳንወስድ የሚያመለክት ይሆናል።

ዮሐንስ የሚያምኑ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ በከተማዪቱ ውስጥ እንደሚሰበሰቡ ያረጋግጥልናል (ዕብ. 11፡39-40)።

አስቀድሞ ዮሐንስ ምድራዊቱን ኢየሩሳሌም የለካ ሲሆን (ራእይ 11)፥ አሁን ግን ሰማያዊቱን ከተማ እንዲለካ ተጋብዟል። «አራት ማዕዘን» የሚለው «በሁሉም በኩል እኩል ጎኖች ያሏት» ማለት ስለሆነ፥ ከተማዪቱ በቅርጿ ምናልባት ኩብ ወይም ፒራሚድ ትሆናለች። ከዚህም በላይ፤ በሁሉም በኩል እኩል መሆኗ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ከተማ ፍጹምነት ያመለክታል - ከሥርዓት ወይም ከሚዛን ያለፈ ነገር አልነበረም።

መለኪያዎቹ አስገራሚዎች ናቸው! አንድ ክንድ አሥራ ስምንት ኢንች አካባቢ ይሆናል ብንል፥ የከተማዪቱ ቅጥሮች ከፍታ 216 ጫማዎች ያህል የረዘመ ይሆናል። እንደዚሁም የመለኪያ ዘንጉ 600 ጫማ ያህል ይረዝማል ብንል፥ ከተማዪቱ 1500 ካሬ ማይሎች ያህል ስፋት ይኖራታል ማለት ነው! ይህም የዩናይትድ ስቴትስን ሦስት-አራተኛ እጅ ይሆናል። ይህን በሚያህል ሰፊ ስፍራም፥ ያለጥርጥር ለሁሉም የሚበቃ ቦታ ይኖራል!

የከተማዪቱ ግንባታ በእጅጉ ያስደንቃል። ቅጥሮችዋ ከኢያስጲድ የታነፁ ሲሆኑ፥ ከተማዪቱም ከወርቅ ትሠራለች። እነዚህም (ኢያስጲድና ወርቅ) እንደ ከበረ ድንጋይ ንጹሕ ናቸው። የእግዚአብሔር የክብር ብርሃን እንደ ታላቅ ቅድስተ-ቅዱሳን በከተማዪቱ ሁሉ ያበራል።

ብዙውን ጊዜ የሕንፃ መሠረቶች ከመሬት በታች የሚደረጉ ሲሆን፥ ይኼኛው ግን ለታይታ መጋለጡ ብቻ ሳይሆን፥ በከበሩ ማዕድናት በግሩም ሁኔታ ይጌጣል። እያንዳንዱ መሠረት የራሱ ጌጥ የሚኖረው ሲሆን፥ የእግዚአብሔር ብርሃን በሚያበራበት ጊዜ የቀለሞቹ ውህደት ከፍተኛ ውበት ይኖረዋል።

ማንም ሰው በእነዚህ ቀለሞች ምንነት ላይ የጠበቀ አቋም ሊኖረው አይችልም - ጉዳዩም እምብዛም የሚያሳስብ አይደለም። ኢያስጲድ እንደተመለከትነው፥ ንጹሕ ብርጭቆ መሳይ ንጥረ-ነገር ነው። ሰንፔር ሰማያዊ ድንጋይ ሲሆን፥ ኬልቄዶን ምናልባትም አረንጓዴያማ ሰማያዊ ይሆናል። መረግድ አረንጓዴ ሲሆን፥ ሰርዶንክስ ምንም እንኳ አንዳንድ

ምሑራን እንደ ቀይና ነጭ አድርገው ቢገልጹትም፥ ቡኒ መስመር ያለበት ነጭ ድንጋይ ነው።

ሰርድዮን (አንዳንዴ እንደ «ደም የቀላ» ተብሎ የሚገለጽ) ቀይ ድንጋይ ሲሆን፥ ክርስቲሌቤ የዘመኑን «ቶፓዝ» (ወራውሬ) የሚመስል ቢጫ ድንጋይ ነው። ቢረሌ አረንጓዴ ሲሆን፥ ወራውሬ ቢጫ-አረንጓዴ ነው። ስለ ክርስጵራስስ እርግጠኞች አይደለንም፤ አንዳንዶች ወርቅ-ቅብ ቀለም እንዳለው ሲናገሩ፥ ሌሎች ግን አረንጓዴ ነው ይላሉ። ያክንት አንዳንዶች ቢጫ እንደሆነ ቢናገሩም፥ ሰማያዊ ሳይሆን አይቀርም፤ አሜቴስጢኖስ ደማቅ ሐምራዊ፥ ወይም ሰማያዊ-ቀይ ነው።

አምላካችን የውበት አምላክ ነውና ለሕዝቡ በሚያዘጋጃት ከተማ ላይ ውበቱን ያፈሰዋል። ጴጥሮስ ስለ «እግዚአብሔር ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች» በሚጽፍበት ጊዜ ምናልባት በአእምሮው ውስጥ የቅድስቷ ከተማ ምስል ሳይኖር አይቀርም (1ኛ ጴጥ. 4፡10) - «ደጋግ» ተብሎ የተተረጐመው ቃል በዚያው በግሪክ «በርካታ ቀለም ያለው፥ የሚያንጸባርቅ» ምላአት ነውና።

በጥንት ዘመን፥ ዕንቁ «ንጉሣዊ ጌጥ» ተደርጐ ይቆጠር ነበር፤ ይህም ከውስጡ ደቃቅ ድንጋዮች ከሚገኙበት ዛጐል የሚወጣ ነው። ዳሩ ግን ዜጐችዋን የሚረብሽ ወይም የሚያረክስ ምንም ዓይነት አደጋ ስለማይኖር፥ የሰማያዊቷ ከተማ የዕንቁ ደጆች ከቶውንም አይዘጉም (ራእይ 21፡25)።

ዮሐንስ አንዳንድ ነገሮች በከተማዪቱ ውስጥ እንደሌሉና አለመኖራቸውም ክብሯን ከማጉላት በቀር ያስከተለው ጉዳት እንደሌለ ገልጿል። ጠቅላላዋ ከተማ በእግዚአብሔር ህልውና ስለምትሞላ ቤተ መቅደስ አይኖርባትም። እንዲሁም፥ በመንግሥተ ሰማይ «ዓለማዊ» እና «የተቀደሰ» ብሎ ልዩነት አይኖርም። ጌታ የከተማዪቱ ብርሃን ስለሚሆንና ሌሊትም ስለማይኖር ፀሐይና ጨረቃ አይኖሩም (ኢሳ. 60፡19 ተመልከት)።

በራእይ 21፡24 እና 26 የሕዝቦች መጠቀስ እንደሚያስረዳው፥ በአዲስቱ ምድር ውስጥ ሰዎች ይኖራሉ። በዘላለሙ መንግሥት ውስጥ የሚኖሩት የከበረ አካል የለበሱ ፍጥረታት ብቻ ስለሆኑ፥ ምድሪቷ እንደዛሬዎቹ ከተሞች በሕዝብ ብዛት ሳቢያ ትበከላለች ብለን መስጋት የለብንም። ይልቁንም፥ ከእነዚህ ከተጠቀሱት ቁጥሮች ምንባብ የምንረዳው፥ ነገሥታትና ሕዝቦች የነገሥታት ንጉሥ ወደሚገኝባት ከተማ

ክብራቸውንና ሀብታቸውን የሚያመጡበትን ጥንታዊ ልማድ ማንጸባረቁን ነው። በሰማያዊቷ ከተማ፡ ሁሉም «የነገሥታቱን ንጉሥ» ያከብረዋል [መዝ. (68)፡29፤ (72)፡10-11፤ ኢሳ. 60]።

በራእይ 22፡1-5፥ ወደ ከተማዪቱ ውስጥ በመግባት እንደ ዔድን ገነት ውብ የአትክልት ስፍራ መሆንዋን እንመለከታለን። በዔድን ገነት አራት ወንዞች የነበሩ ሲሆን (ዘፍጥ. 2፡10-14)፥ በሰማያዊቱ ከተማ ግን አንድ ወንዝ ብቻ ይኖራል። ሕዝቅኤል የሚያነጻ ውኃ ከቤተ መቅደሱ ሲፈስ የተመለከተ ሲሆን፥ ይህም አለጥርጥር የሺህ ዓመቱ ትዕይንት ነው (ሕዝ. 47)፤ ዳሩ ግን ይህ ወንዝ የንጽሕና ሁሉ ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዙፋን በቀጥታ የሚፈስ ነው። ሰው መልካሙንና ክፉን ከምታሳውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበላ የተከለከለ ከመሆኑም በላይ፥ ከሕይወት ዛፍም እንዳይበላ ታዝዞ ነበር (ዘፍጥ. 2፡15-17፤ 3፡22-24)። በዘላለማዊው ቤት ግን፥ ሰው ወደ ሕይወት ዛፍ የመግባት ነፃነት ይኖረዋል። ወንዙና ዛፉ በከበረችው ከተማ ውስጥ የሚኖረውን የተትረፈረፈ ሕይወት ያመለክታሉ።

«ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም» የሚለው፥ እርግማን ወደ ተጀመረበት ወደ ዘፍጥረት 3፡14-19 ይወስደናል። የሚያስገርመው፥ ብሉይ ኪዳን እንኳ የሚጠቃለለው «መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ ...» በሚል ዓረፍተ ነገር ነው (ሚልክ. 3፡6)። አዲስ ኪዳን ግን «ከእንግዲህ ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም» እያለ ያውጃል። ሰይጣን ወደ ገሃነም ይወርዳል - ፍጥረት ሁሉ አዲስ ይሆናል - የኃጢአትም እርግማን ለዘላለም ይወገዳል።

በሰማይ ለዘላለም ምን እንሠራለን? ጌታን እያመሰገንንና እያገለገልን እንኖራለን። በሰማይ አገልግሎታችን ፍጹም ስለሚሆን፥ «ባሪያዎቹም ያመልኩታል [ያገለግሉታል]» የሚለው ታላቅ ማበረታቻ ይሆንልናል (22፡3)። በዚህ ምድር ላይ ጌታን ለማገልገል ስንሻ ባለማቋረጥ በኃጢአትና በድካም እንጠቃለን፤ ዳሩ ግን ወደ ክብር ስፍራ ስንገባ ማናቸውም መሰናክሎች ይወገዱና በፍጹም ድባብ ፍጹም አገልግሎት እያበረከትን እንኖራለን።

ይኼስ አገልግሎት ምን ይሆን? አገልግሎቱ ምን እንደሚሆን አልተነገረንም፤ አሁንም ማወቅ አያሻንም። «ዛሬ» እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልግብንን ነገር ማወቃችን ብቻውን በቂ ነው። በሕይወታችን ታማኝ መሆናችን በሰማይ ለሚኖረን የላቀ አገልግሎት

ያዘጋጀናል። እንዲያውም፥ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ወደተቀረው አጽናፈ-ዓለም እንደምንሄድና ምናልባትም ለተለዩ ተልዕኮዎች ወደ ሌሎች ስፍራዎች ልንላክ እንደምንችል ያስባሉ። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ይህን መሰሉን ዝርዝር ጉዳዮች ማሳወቁን አስፈላጊ ሆኖ አላገኘውምና ለእኛም አጓጉል ግምቶችን ማካሄዱ ጠቀሜታ አይኖረውም።

በተረፈ ግን በሰማይ አገልጋዮች ብቻ ሳንሆን፥ ነገሥታትም እንሆናለን። ከዘላለም እስከ ዘላለም እንነግሣለን! ይህም የክርስቶስን ሥልጣን በክብር እንደምንካፈል ያሳየናል። አማኞች እንደመሆናችን፥ ዛሬ ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠናል (ኤፌ. 2፡1-10)። በዘላለሙ መንግሥት ግን፥ በአዲስ ሰማያትና ምድር ላይ እንደ ነገሥታት እንገዛለን። ይህ እንዴት ያለ ክብር፥ እንዴትስ ያለ ጸጋ ነው!

ስለ ወደፊቱ የሰማይ ኑሮአችን በርካታ አስገራሚ ጥያቄዎች ሊነሡ ቢችሉም፥ ዳሩ ግን ብዙዎቹ ወደከበረው ቤታችን እስክንደርስ ድረስ ሳይመለሱ መቆየት አለባቸው። እንዲያውም፥ ዮሐንስ ወደ መንግሥተ ሰማይ መሄዳችንን እንደምክንያት አቅርቦ ዛሬ ያሉብንን ኃላፊነቶች በትክክል እንድንወጣ በማሳሰብ መጽሐፉን አጠቃሏል።

የከተማዪቱ መጠይቅ (ራእይ 22፡6-21)

መንግሥተ ሰማይ ወደ ፊት ልንደርስበት የምንጓጓለት ግብ ብቻ ሳይሆን አነሳሽ ምክንያትም ነው። አንድ ቀን በሰማያዊት ከተማ የምንኖር መሆናችንን ማወቁ፥ ዛሬውኑ በዚህ ባለንበት ስፍራና ሕይወት ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ሊያነሳሣን ይገባል። የሰማዪቱ ከተማ ራእይ፥ ለእምነት አባቶቻችን ከእግዚአብሔር ጋር ለመመላለስና እርሱንም ለማገልገል፥ አነሣሽ ምክንያት ሆኗቸዋል (ዕብ. 11፡10፥ 13-16)። ኢየሱስ ክርስቶስም መስቀሉን በተጋፈጠበት ወቅት፥ በሰማይ ወዳለው አባቱ እየተመለሰ የመሆኑን እውነታ አውቆ ተበረታቷል (ዕብ. 12፡2)። የሰማይ ተስፋ ዋስትና መንፈሳዊ ኃላፊነታችንን እንድንወጣ ሊያበረታታን እንጂ፥ በራስ ወደ መርካት ወይም ወደ ግዴለሽነት ሊመራን አይገባም። በመጀመሪያ . . .

የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ አለብን (22፡6-11፤ 18-19) - ዮሐንስ የጻፈው የእግዚአብሔርን ቃል ስለሆነ፥ ቃሉቹ ታማኝና እውነተኛ

ናቸው (ራእይ 19፡11 ተመልከት)። ይኸው በነቢያት በኩል የተናገረው አምላክ፥ በሐዋርያው ዮሐንስ በኩልም ተናግሯል። ለእግዚአብሔር መገለጽ «የመደምደሚያ ድንጋይ» የሆነው የዮሐንስ መጽሐፍ ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ሊገለል አይችልም። ዮሐንስ እውነትን እንደጻፈ ካልተቀበልን፥ የነቢያትንም እውነትነት ክደናል ማለት ነው።

«የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል» መጠበቅ ማለት ምን ማለት ነው? (22፡7)። በመሠረቱ፥ ይህ ማለት በጥንቃቄ መያዝ፥ መንከባከብና ምንም ሳይዛነፍ እንዳለ ማቆየት ማለት ነው። በመሆኑም፥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ መጨመርም ሆነ መቀነስ የለብንም (ዘዳ. 4፡2፤ ምሳሌ. 30፡5-6 ተመልከት)። ይህ ኃላፊነት በተለይ በክርስቶስ መመለስ ብርሃን ስንመለከተው ታላቅ ነው። በራእይ 22፡6 «በቶሎ› የሚለው ቃል «በፍጥነት የሚፈጸም» ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የክርስቶስን መመለስ ብትጠባበቅም፥ ገና አልተመለሰም። ይሁንና የዮሐንስ ትንቢቶች መፈጸም ሲጀምሩ፥ በፍጥነት ይከናወናሉ። አይዘገዩምም።

ከቁጥር 18-19 የሚገኙ ማስጠንቀቂያዎች፥ መጽሐፍ ቅዱስን የሚለውጡ ሰዎች የታላቁን መከራ መቅሠፍቶች ለመቀበል ወደ ምድር ተመልሰው ስለመምጣታቸው ወይም ደኅንነታቸውን ስለማጣታቸው የሚጠቁመን ነገር የለም። ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ ለሙሉ ሊረዳም ሆነ በውስጡ የተካተተውን እውነት ሁሉ ሊያብራራ ስለማይችል፥ ቃሉን የምናስተምር ሰዎች አንዳንዴ በእውቀት እያደግን በሄድን መጠን አተረጓጐማችንን እንለዋውጥ ይሆናል። እግዚአብሔር ልብን ስለሚያይ፥ አለማወቅን ከግዴለሽነት፥ አለመብሰልንም ከዓመፃ ለይቶ ሊመለከተው ይችላል።

መጻሕፍትን ለሕዝብ ለማሰራጨት የሚገለብጡ ሰዎች አሳቡን ለመለወጥ ሊፈተኑ ስለሚችሉ፥ በጥንት ዘመን ጸሐፍት በመጽሐፎቻቸው መደምደሚያ ላይ የዚህ ዓይነት ማስጠንቀቂያ ያስቀምጡ ነበር። ይሁንና፥ ዮሐንስ ማስጠንቀቂያውን ያሰፈረው ለሚገለብጠው ሰው ሳይሆን፥ ይህ መጽሐፍ በጉባዔ ውስጥ ከፍ ባለ ድምፅ ሲነበብ ለሚሰማው አማኝ ነበር። በንጽጽር ስንመለከተው ደግሞ፥ ይህ ዛሬ መጽሐፉን ለሚያነብና ለሚያጠና ሰው ሁሉ የሚዛመድ ይሆናል። የተሰጡትን ቅጣቶች ለማብራራት አንችል ይሆናል፥ ሆኖም የእግዚአብሔርን ቃል መለወጥ

አደገኛ መሆኑን ያለአንዳች ጥርጥር እናውቃለን። ቃሉን የሚጠብቅና ለቃሉም የሚታዘዝ ሰው ይባረካል። ቃሉን የሚለውጠውን ግን አንድ ቅጣት ይጠብቀዋል።

ዮሐንስ ለሁለተኛ ጊዜ፥ በሰማውና ባየው ነገር በፍርሃት ርዶ፥ ለሚናገረው መልአክ ሊሰግድ ወደቀ (19፡10 ተመልከት)። መልአኩም ሦስት የምክር ቃላት ሰጠው - መላእክትን አታምልክ፤ እግዚአብሔርን አምልክ፤ እንዲሁም፥ የራእዩን መጽሐፍ አታትመው። ጊዜው ገና ስላልደረሰ፥ ነቢዩ ዳንኤል መጽሐፉን እንዲያትም ተነግሮት ነበር (ዳን. 12፡4)። የዮሐንስ መጽሐፍ ግን ስለፍጻሜ፥ ገላጭ መጽሐፍ ስለነበር (ራእይ 1፡1)፥ መታተም አያስፈልገውም።

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ሕያው የሆነ አንድነት አሁንም በድጋሚ ያስታውሰናል። በጥናታችን፥ ዮሐንስ በመንፈስ ተመርቶ እንዴት ወደ ኋላ ወደ ብሉይ ኪዳን እንደተመለሰና፥ የዳንኤልን ትንቢት ጨምሮ፥ በዚያ በሚገኙት ተምሳሌቶች እንደተጠቀመ ተመልክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ ከሁሉም በላቀ ሁኔታ ራሱን ይተረጉመዋል።

ምናልባት ራእይ 22፡11 እግዚአብሔር ሰዎችን ንስሐ ገብተው መንገዳቸውን እንዳይቀይሩ መፈለጉን ለማመልከት ሲባል የሰፈረ ይሆን? አይደለም! - ይህን ማለት ከራእይ መልእክትና ከራሱ ከወንጌል ጋር ይቃረናል። የመልአኩ ቃላት፥ «እነሆም፥ በቶሎ እመጣለሁ» (ቁ. 7፥12)፥ እንዲሁም «ዘመኑ ቀርቦአልና» (ቁ. 10) በሚሉ ተደጋጋሚ ዓረፍተ ነገሮች አማካኝነት ሊተረጐም ይገባል። የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት በጣም ፈጣን ስለሚሆን፥ ሰዎች ባሕርያቸውን ለመቀየር የሚበቃ ጊዜ አያገኙም።

በመሆኑም፥ ቁጥር 11 በጥብቅ የሚያሳስበን፥ ውሳኔ ባሕርይን የሚቆጣጠረውን ያህል፥ ባሕርይም ፍጻሜን የሚቆጣጠረው መሆኑን እንድንረዳ ነው። በመከራ ውስጥ የሚንገላቱ አማኞች፥ «ፈሪሃ-እግዚአብሔራዊ ኑሮ ፋይዳ ይኖረው ይሆን?» ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ። ዮሐንስም፥ «አዎን!፥ ኢየሱስ እየተመለሰ ስለሆነ፥ ዋጋችሁን ይከፍላል» ብሎ ይመልሳል። ቀጥሎም የዮሐንስን ሁለተኛውን ምክር እንመለከታለን።

እኛ ጌታን የማገልገል ኃላፊነት አለብን (22፡12-15) - «ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ» የሚለው እግዚአብሔር መከራችንንና አገልግሎታችንን

እንደሚያውቅና ለእርሱ እስከተደረገ ድረስ ማንኛውም ነገር ከንቱ ሆኖ እንደማይቀር ያስገነዝበናል። በክርስቶስ የፍርድ ወንበር፥ ለአማኞች እንደየሥራቸው ፍርድ ይሰጥና በታማኝነት ላገለገሉ ቅዱሳን ሽልማቶች ይሰጣሉ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ፥ (ድዋይት ኤል ሙዲ እንደሚሉት) «እጅግ ሰማያዊ አስተሳሰብ ስላመዘነባቸው፥ በምድራዊው ሕይወታቸው እጅና እግራቸውን አጣጥፈው የተቀመጡ» ሰዎች አሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ሥራቸውን አቁመውና ንብረታቸውን ሸጠው በመቀመጥ የኢየሱስን መመለስ ብቻ ይጠባበቃሉ። በመሠረቱ፥ ለምጽአቱ ቀን ገድቦ መጠበቁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ አይደለምና ይህን መሰሎቹ ሰዎች በሙከራቸው አፍረውበታል። እንዲሁም፥ ኢየሱስ በቶሎ ይመለሳል ብለን ከማመናችን የተነሣ ግዴለሽና ሰነፍ መሆንን፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው አሳብ አይደለም። አንዳንድ የተሰሎንቄ አማኞች ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ በጳውሎስ ላይ ችግር ፈጥረው ነበር (2ኛ ተሰ. 3)።

ዮሐንስ «ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው» ማለቱ አስገራሚ አይሆንም (ራእይ 22፡14)። ኢየሱስ በቶሎ እንደሚመጣ ከልባችን ካመንን፥ ነቅተን በታማኝነት እንመላለሳለን (ሉቃ. 12 ከቁጥር 35 ጀምሮ)።

ራእይ 22፡13 ጌታን ለማገልገል ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ታላቅ ማበረታቻ ነው። እግዚአብሔር አልፋና ዖሜጋ፥ የመጀመሪያውና የመጨረሻው፥ ፊተኛውና ኋለኛው ስለሆነ፥ የሚጀምረውን ማንኛውንም ነገር ይፈጽመዋል (ፊልጵ. 1፡6፤ 2፡12-13 ተመልከት)። ሦስተኛው ኃላፊነታችን . . .

ሕይወታችንን በንጽሕና መጠበቅ አለብን (22፡14-16) - በዚህ ስፍራ ዮሐንስ የሚያነጻጽረው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በመጠበቅ ወደከተማዪቱ የሚገቡትንና ቃሉን በመተው ከከተማዪቱ የሚገለሉትን ሰዎች ነው (21፡8፥ 27 ተመልከት)። «ትእዛዛቱን የሚጠብቁት» የተለዩ ወይም የተመረጡ የቅዱሳን ቡድኖች ናቸው ማለቱ የሚያስኬድ አይመስልም። ሐረጉ «አሸናፊዎች» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሙሉ ያመለክታል። ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ የእውነተኛ ደኅንነት ምልክት ነው።

በቁጥር 16 ላይ የሚገኙ የጌታችን ማዕረጎች አስገራሚዎች ናቸው። «ሥር» በዓይን ሊታይ በማይቻልበት ሁኔታ በምድር ውስጥ ተቀብሮ የሚገኝ ሲሆን፥ «ኮከብ» ግን ማንም ሰው ሊያየው በሚችልበት ሰማይ ላይ ይኖራል። በ«ዳዊት ሥርና ዘር» ውስጥ የኢየሱስን አይሁዳዊ ብሔራዊ ስም እናገኛለን - በ«ሚያበራ የንጋት ኮከብ» ውስጥ ግን አጽናፋዊ ስሙን እናገኛለን። አንደኛው ስለውርደቱ ሲናገር፥ ሌላኛው ደግሞ ክብሩንና ግርማውን ያሳያል።

«የዳዊት ሥር ...» እንደመሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳዊትን ወደ መኖር አምጥቶታል። «የዳዊት ... ዘር» በመሆኑ፥ ኢየሱስ ከዳዊት ዘር አይሁዳዊ ሆኖ በመወለድ፥ ወደዚህ ዓለም መጥቷል። በዚህ ስፍራ የኢየሱስ አምላክነትና ሰብአዊነት ሁለቱም በግልጽ ይታያል። ለተመሳሳይ አሳብ ማቴዎስ 22፡41-46 ተመልከት።

«የንጋት ኮከብ» በፍጥነት የሚከተለውን ንጋት ያውጃል። ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያኑ እንደ «ንጋት ኮከብ» ይመጣል። ዳሩ ግን ለመፍረድ ሲመለስ፥ በሚያቃጥል ቁጣ እንደ «ጽድቅ ፀሐይ» ይሆናል (ሚልክ. 4፡1-3)። የእግዚአብሔር ሰዎች የጌታቸውን መመለስ ስለሚጠባበቁ፥ ሕይወታቸው ንጹሕና ለእርሱ የተሰጠ ሆኖ ይኖራል (1ኛ ዮሐ. 2፡28-3፡3)። ስለሆነም ...

የኢየሱስ ክርስቶስን መመለስ ልንጠባበቅ ይገባል (22፡17፥ 20-21)። ዮሐንስ በዚህ የመዝጊያ ምዕራፍ ሦስት ጊዜ፥ «እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ» ሲል ጽፏል (ቁ. 7፥ 12፥ 20)። ይሁንና ጌታ ምጽአቱን ለ2000 ዓመታት ያህል አራዝሟል። አዎን፥ ዘግይቶአል፤ ጴጥሮስም ምክንያቱን ይነግረናል - እግዚአብሔር ለዚህ ኃጢአተኛ ዓለም ንስሐ ገብቶ የሚድንበትን ዕድል ለመስጠት ይፈልጋል (2ኛ ጴጥ. 3 ከቁጥር 1 ጀምሮ)። ይህ በዚህ እንዳለ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ በቤተ ክርስቲያን (በሙሽራዪቱ) አማካኝነት ኢየሱስ እንዲመጣ ይጣራል - ሙሽራዪቱ ከሙሽራዋ ጋር ልትገናኝና ወደ ቤቷ ልትገባ ትናፍቃለችና። «አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና» (ራእይ 22፡20) ትላለች።

በተጨማሪም አማኞች ከደኅንነት ርቀው የጠፉትን ሰዎች፥ በክርስቶስ አምነው የሕይወትን ውኃ እንዲጠጡ መጋበዝ አለባቸው። እንደ እውነቱ፥ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን መመለስ እየተጠባበቀች የምትኖር ከሆነ፥ ይህ ዝንባሌዋ፥ አገልግሎቷን በማጠናከር ወንጌሉን ለማሰራጨትና ንጽሕናዋን ለመጠበቅ የሚገፋፋ ኃይል ይሆንላታል።

እኛም ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ለሌሎች ልንናገር እንሻለን። እውነተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት መረዳት፥ የእግዚአብሔርን ቃል እንድንታዘዝና ከደኅንነት ርቆ ለጠፋው ዓለም የእግዚአብሔርን ግብዣ እንድናጋራ ሊያነሣሣን ይገባል።

የራእይ መጽሐፍ ጥናታችን በእውነትም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የታገዘ ከሆነ፥ ከዮሐንስ ጋር በመሆን የመጽሐፍ ቅዱስን የመጨረሻ ጸሎት «አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና!» በማለት እናሰማለን።

አንተስ ይህንን አብረኸው ለማለት ዝግጁ ነህ???